# የ"ቶፕዳውን" (top-down) የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ተግባራዊነትና ውጤታማነት፦ በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ዘዴ (TEAM)
ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በ
እንግዳ ዘውዴ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ጥር 1992 ዓ.ም.

# የ"ቶፕዳውን" (Top down) የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ተግባራዊነትና ውጤታማነት፡- በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት


በ

እንግዳ ዘውዴ


ቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| | |
|---|---|
| ዶ/ር ኤርጋ ሀይለሚካኤል | |
| አማካሪ | ፊርማ |
| ዶ/ር ደጀኔ ሌታ | |
| ፈታኝ | ፊርማ |
| ዶ/ር ኤበበ ገ/ሄዎት | |
| ፈታኝ | ፊርማ |

# ምስጋና

ከመጀመሪያው ረቂቅ ጀምሮ ያለመሰልቸት ስህተቶችን በማረም፥ የአሰራር መንገዶችን በመጠቆምና በማበረታታት ክትትላቸው ያልተለየኝን አማካሪዬን ዶ/ር አረጋ ኀይለሚካኤል፥

የሙከራ ምርምሩ ባግባቡ እንዲከናወን ቀና ትብብር ያደረጉልኝን የኢትዮጵያ ትቅደም ቁጥር አንድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መምህርት ጸጋነሽ ማሞንና የ$9^{I}$ ተማሪዎችን፥

የጥናቴን ረቂቅ በጥንቃቄ በኮምፒውተር የቀረጸችውን ወ/ት ንግስት ግደይን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

# የአርእስት ማውጫ

**አርእስት** **ገጽ**


ምስጋና ........................................ i
የሰንጠረዥ ማውጫ........................................ iv
የአባሪ ማውጫ........................................ v
አጠቃሎ........................................ vi
1. መግቢያ........................................ 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ........................................ 1
1.2. የጥናቱ አላማ........................................ 6
1.3. የጥናቱ ወሰን........................................ 7
1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት........................................ 7
1.5. የቁልፍ ቃላት ብያኔ........................................ 7
2. የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት........................................ 11
2.1. ንባብን የማስተማር ስልተ-ትወራ (approaches)........................................ 11
2.1.1. ክሂል-ተኮር ስልተ-ትወራ........................................ 11
2.1.2. ስልተ-ተኮር ስልተ-ትወራ........................................ 13
2.2. የ "ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል መመሪያዎች........................................ 17
2.2.1. የሞዴሉ የሙከራ ጥናቶች........................................ 23
2.2.2. የተካሄዱት ቀደምት ደጋፊ ምርምሮች........................................ 34
2.2.2.1. በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተካሄዱ ምርምሮች........................................ 34
2.2.2.2. በሁለተኛ ቋንቋ የተካሄዱ ምርምሮች ........................................ 36
2.2.2.3. በልሳነ ክልኤዎች ላይ የተደረጉ ጥናቶች........................................ 40
2.2.3. ሞዴሉን አስመልክቶ የተሰነዘሩ አሉታዊ አስተያየቶችና ምላሾቻቸው..... 41
2.2.4. የትምህርት አውድ፥ የመምህሩና የተማሪዎች ሚና........................................ 45
2.2.4.1. የትምህርት አውድ........................................ 45
2.2.4.2. የመምህሩ ሚና........................................ 45
2.2.4.2.1. በቅድመ ንባብ........................................ 45
2.2.4.2.2. በንባብ ጊዜ........................................ 46
2.2.4.2.3. ከንባብ በኋላ........................................ 47
2.2.4.3. የተማሪዎች ሚና........................................ 47
2.2.5. የምንባቦች አመራረጥ፥ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች አይነትና ፈተና..... 47
2.2.5.1. የምንባቦች አመራረጥ........................................ 47
2.2.5.2. አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች (መልመጃዎች) አይነት.............. 49
2.2.5.3. አንብቦ የመረዳት ፈተና አይነቶች........................................ 50
2.2.5.3.1. የምርጫ ሰጭ ጥያቄዎች (ultiple-choice items).......... 51
2.2.5.3.2. የክፍት ጨራሽ (open-ended) ጥያቄዎች.................... 52
2.2.5.3.2.3. የእውነት/ሀሰት (true/false) ጥያቄዎች........... 52

3. የአጠናን ዘዴ........................................ 53
3.1. የትምህርት ቤትና የተማሪዎች አመራረጥ........................................ 54
3.1.1. የቅድመ ሙከራ ጥናት........................................ 54
3.1.2. የሙከራ ምርምር........................................ 55
3.1.3. የምንባቦች አመራረጥና የመልመጃ አዘገጃጀት........................................ 56
3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች........................................ 58
3.2.1. አንብቦ የመረዳት ፈተና አዘገጃጀትና አፈታተን........................................ 58
3.2.2. ለተማሪዎች የተሰራጨ የጽሁፍ መጠይቅ........................................ 59
3.2.3. የልምምድ ምልከታ ማስታወሻ........................................ 60
3.3. የትምህርት አቀራረብ ስርዓት ሂደት........................................ 61

3.4. የመረጃ አተናተን.................................................................................... 63
3.4.1. ከጽሁፍ መጠይቅና ከምልከታ የተገኘ ውጤት........................................................ 63
3.4.2. የፈተና ውጤቶች............................................................................................ 64
4. የጥናቱ ውጤት ትንተና.......................................................................................... 65
4.1. ከአንብቦ መረዳት ፈተና የተገኘ መረጃ ትንተና......................................................... 67
4.1.1. ከቅድመ ልምምድ ፈተና የተገኘ መረጃ ትንተና...................................................... 67
4.1.2. ከድህረ ልምምድ ፈተና የተገኘ መረጃ ትንተና...................................................... 70
4.1.3. የመላ ምት ፍተና (hypothesis testing)............................................................. 73
4.2. ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና.................................................................. 76
4.2.1. በክፍል አንድ ለቀረቡት ጥያቄዎች የተገኘ መረጃ ትንተና............................................ 76
4.2.2. በክፍል ሁለት ከ1-5 ለቀረቡት ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች........................................ 77
4.2.3. በክፍል ሁለት ከ6-21 ላሉት ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች........................................... 80
4.3. ከምልከታ ማስታወሻ የተገኘ መረጃ ትንተና............................................................. 86
5. የጥናቱ ግኝት ማጠቃለያ፥ መደምደሚያና አስተያየት................................................... 93
5.1. የጥናቱ ግኝት ማጠቃለያ.................................................................................. 93
5.1.1. የትምህርት አሰጣጡን ተግባራዊነትና ውጤታማነት በሚመለከት.................................... 94
5.1.2. ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ተግባራዊ ከማድረጋቸው አንጻር................................ 95
5.2. የመፍትሄ ሃሳቦች............................................................................................ 96
ዋቢዎች........................................................................................................ 99

## የሰንጠረዥ ማውጫ


| ሰንጠረዥ | | ገጽ |
|---|---|---|
| 1. | የቁጥጥርና የሙከራ ቡድን ቅድመ ልምምድ የፈተና ውጤት .......................... | 68 |
| 2. | የቅድመ ልምምድ የቡድኖች ውጤት t-ቴስት ማጠቃለያ................................ | 69 |
| 3. | የሙከራውና የቁጥጥር ቡድን የድህረ ልምምድ የፈተና ውጤት........................ | 71 |
| 4. | የሁለቱ ቡድኖች የድህረ ልምምድ ውጤት የt-ስሌት ማጠቃለያ........................ | 72 |
| 5. | የመላምት (hypothesis testing) ፍተና................................................ | 74 |
| 6. | የተጠኚ ተማሪዎችን ዳራ የሚያሳይ.................................................... | 76 |
| 7. | የተማሪዎች ቅድመ ልምምድ አስተያየት መግለጫ......................................... | 78 |
| 8. | ለልምምድ በቀረቡት መልመጃዎች አማካይነት የተማሩትን የንባብ ስልቶች ተግባራዊ ማድረጋቸውን የሚገልጹ............................................ | 81 |
| 9. | የመልጃዎችን አፈጻጸም የሚያሳይ የተማሪዎች መልሶች................................ | 82 |
| 10. | በጸጥታ ማንበብ ምን ያህል እንደረዳቸው የተማሪዎችን መልሶች የሚያሳይ.......... | 83 |
| 11. | የንባብ አላማን መወሰን፥ የምንባብ አይነትን መለየትና የመልዕክት ትንበያን ክንውን ውጤት የሚያሳይ.......................................................... | 84 |
| 12. | በትርጉም አዘል አሀድ ደረጃ በማንበብና የምንባቡን መልዕክት በድጋሚ በማንበብ ለመረዳት የሚደረገው ጥረት የሚያሳይ.............................. | 85 |
| 13. | ጠቅላላ ልምምዱን መውደድ አለመውደዳቸውን አስመልክቶ የቀረቡ የተማሪዎች መልሶች........................................................................ | 86 |

## የአባሪ ማውጫ


| አባሪ | | ገጽ |
| --- | --- | --- |
| ሀ. | የቅድመና የድህረ ልምምድ ፈተና | 110 |
| ለ. | የተማሪ መጠይቅ | 116 |
| ሐ. | የምልከታ ማስታወሻ | 119-128 |
| መ. | የማስተማሪያ ምንባቦችና መልመጃዎች | 129-152 |
| መ1. | ለቁጥጥር ቡድን የተዘጋጁ ምንባቦችና መልመጃዎች | 129-142 |
| መ2. | ለሙከራ ቡድን የተዘጋጁ ምንባቦችና መልመጃዎች | 141-151 |
| ሠ. | የተማሪዎች አስተያየት አስተማማኝነት ፍተና | 153-154 |

## አጠቃሎ


የዚህ ጥናት ዋና አላማ የ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴልን በአማርኛ ቋንቋ እንደ አንድ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማዳበሪያ ዘዴ መጠቀም የሚኖረውን ውጤታማነትና ተግባራዊነት መመርመር ነው፡፡ በመሆኑም በቅድሚያ በአሁኑ ወቅት በአማርኛ የንባብ ትምህርት ክፍለ-ጊዜ እያገለገለ ያለው የማስተማሪያ ዘዴ ምን እንደሚመስል የሚያመለክት ዳራዊ መረጃ በቅድመ ሙከራ ጥናት ማግኘት፥ ቀጥሎም የሙከራ ምርምር (experiemental research) ማካሄድና በሙከራ የተገኘውን ውጤት የሚያጠናክሩ አጋዥ መረጃዎችን ደግሞ በድህረ ሙከራ ጥናት ማሰባሰብ የጥናቱ የአሰራር ዘዴ ነው፡፡

ለቅድመ ሙከራው ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች የተጠናቀሩት በአራት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአስራ ስድስት የመማሪያ ምድቦች በተካሄዱ ምልከታዎች ነው፡፡ በዚህም በአሁኑ ወቅት የሚሰጠው የንባብ ትምህርት ልምምድ ተማሪዎችን እንደማያሳትፍ፥ አብዛኛዎቹ ትምህርታዊ ተግባራት በመምህራኑ እንደሚከናወኑና ተማሪዎች በቂ ልምምድ እንደማያደርጉ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የተጠቀሰው ዳራዊ መረጃ ከተገኘ በኋላ የጥናቱ ዋና አካል የሆነውን የሙከራ ምርምር ለማካሄድ 160 ተማሪዎች የሚገኙባቸው ሁለት የመማሪያ ምድቦችን በእጣ በመምረጥ የቁጥጥርና የሙከራ ምድቦችን (Control and experimental groups) አደራጅቶ የሙከራ ምድቡን የ"ቶፕዳውን" የንባብ ትምህርት አቀራረብ መመሪያ በሚያዘው መሰረት፥ የቁጥጥር ቡድኑን ደግሞ በተለመደው ዘዴ እንዲማሩ ተደረገ፡፡ ልምምዱ ከመጀመሩ በፊት ለሁለቱ ቡድኖች ተመሳሳይ ቅድመ ትምህርት ፈተና (Pre-test) ተሰጥቶ ውጤቱ በ t-ቴስት (t-test) ከተሰላ በኋላ በ0.05 የጉልህነት ደረጃ (Significance level) እና በ158 የነጻነት ደረጃ (degree of freedom) 0.260 ከt-ሰንጠረዥ ዋጋ 1.960 ያነሰ ሆኖ በመገኘቱ፥ ሁለቱ ቡድኖች የችሎታ መበላለጥ እንደማይታይባቸውና ተመጣጣኝ መሆናቸው ተረጋገጠ፡፡ ለሙከራው አላማ ስኬትም አጥኚው በድህረ ልምምድ የፈተና ውጤት መሰረት በቁጥጥሩና በሙከራው ቡድን መካከል የችሎታ መበላለጥ አይታይም የሚል ባዶ መላምት (Ho) እና በድህረ ልምምድ የፈተና ውጤት መሰረት በቁጥጥሩና በሙከራው ቡድን መካከል የችሎታ መበላለጥ ይኖራል የሚል አማራጭ መላምት (H1) ይዞ ተነሳ፡፡

ጥናቱ ለስድስት ሳምንታት የተካሄደ ሲሆን ሁለቱም ቡድኖች በቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት ተመሳሳይ ችሎታ ስለነበራቸው ተመሳሳይነት ያለውን የትምህርት ይዘት ተከታትለዋል፡፡ የሙከራው ጊዜ እንደተጠናቀቀም ለሁለቱም ቡድኖች ተመሳሳይ ድህረ ልምምድ ፈተና (Post-test) ተሰጥቶአቸው ውጤቱ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው የእስታትስቲክስ ስልት "two-tailed" ከተሰላ በኋላ በ0.05 የጉልህነት ደረጃና በ158 የነጻነት ደረጃ የተገኘው ውጤት 3.173 ከt-ሰንጠረዥ ዋጋ 1.960 የበለጠ በመሆኑ የሙከራው ቡድን የችሎታ ብልጫ እንዳመጣ የሚያረጋግጥ በመሆኑ አጥኚው ይዞት የተነሳው ባዶ መላ-ምት ተቀባይነት አላገኘም፡፡ እንደዚሁም የድህረ ሙከራ መረጃዎችን ለማግኘት

ሲባል ለሙከራ ቡድኑ አባላት የጽሁፍ መጠይቅ ተሰራጭቶ የተገኘው መረጃና የምልከታው ማስታወሻ ውጤት ሲገመገም የሙከራ ምርምሩን ውጤት የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል። ይህም የ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ እንደ አንድ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማዳበሪያ ዘዴ እስራ ላይ ቢውል የተሻለ ውጤት ሊያስገኝ እንደሚችል የሚያመለክት ነው። በመጨረሻም ከጥናቱ ግኝት በመነሳት የመፍትሄ ሃሳቦች ተጠቁመው ቀርበዋል።

# 1. መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ከቋንቋ ትምህርት አላማዎች አንዱ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማዳበር ነው:: አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማለት ደግሞ ያነበቡትን ጽሁፍ መልእክት ወይም ይዘት በሚፈለገው መጠን መገንዘብና ለሚፈለገው አላማ ለማዋል መቻል ማለት ነው:: ምንባቡ ወይም ጽሁፉ የት ተጻፈ? በማን ተጻፈ? ለምንስ ተጻፈ? የሚሉትን ጥያቄዎች በመመርመር መልእክቱን እንዳለ ከመቀበል አመዛዝኖ መረዳትን ያመለክታል:: Grellet (1981:3)፥ Williams (1984:3) Hyland (1995:104) እና Parrott (1993:174) የአንድን ምንባብ መልእክት መረዳት ምንባቡ የያዘውን አስፈላጊ መረጃ በተቻለ መንገድ ሁሉ መገንዘብ መሆኑን በመጠቆም ይህን ሃሳብ ያጠናክራሉ:: ከምንባቡ ውስጥ ተፈላጊውን መረጃ የመገንዘቡ ሂደትም የተለያየ ሊሆን እንደሚችል እነኚሁ ምሁራን ይገልጻሉ:: የሂደቱ መለያየት ምክንያትም ከሚነበበው ነገር፥ ከሚነበብበት አላማና ከማንበቢያው ዘዴ መለያየት ጋር የተያያዘ ነው:: ለምሳሌ Grellet (1981:3) እና Hyland (1995:104) እንደገለጹት፥ በአንድ ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ የተጻፈ ማስታወቂያና በመጽሔት ላይ የታተመ ሳይንሳዊ ጥናት በተመሳሳይ መንገድ አይነበብም:: የማስታወቂያው ፍሬ ሃሳብ በገረፍታ ንባብ ሊጨበጥ ሲችል የሳይንሳዊ ጥናቱን መልእክት ግን ለመረዳት ትኩረት የታከለበት ንባብ ያስፈልገዋል::

አንብቦ መረዳት ሲባልም የሚከተሉትን ችሎታዎች ሊያጠቃልል እንደሚችል Richards, Platt and Platt (1992:306-307)፥ McGary (1991:94)፥ Vance (1990:169-170)፥ Clarke & Silberstein (1977:144) እንዲሁም Stillie & Lynskey (1984:4-5) ይገልጻሉ:: እነዚህም፤

1. <u>የምንባቡን ግልጽ መልእክት መረዳት (Literal Comprehension)</u>:- በምንባቡ ውስጥ በቀጥታ የተገለጸውን መልእክት አንብቦ የሚነሱ ጥያቄዎችን መመለስን ያመለክታል:: በሌላ አገላለጽ የምንባቡን ግልጽ መልእክት መረዳት መልእክቱን ከሚጠየቁት ጥያቄዎች ጋር ማዛመድና ማብራራትን ይጠቁማል:: የጥያቄዎቹ አመላለስም በአንባቢው ግንዛቤ መሰረት ቃል በቃል ሊሆን ይችላል::
2. <u>ቅንብራዊ ግንዛቤ ወይም አንብቦ መረዳት (recognizational Comprehension)</u>:- በምንባቡ ውስጥ በግልጽ የተቀመጠውን መልእክት ከተለያዩ ፍንጮች በማገናዘብ ትንታኔ መስጠትና የተገኘውን መረጃ ማቀናበርን ያመለክታል:: የሚቀናበረው መረጃ ከምንባቡ ልዩ ልዩ ክፍሎች የሚገኝና በአንባቢው ግንዛቤ የሚዳብር ነው:: በመሆኑም የምንባቡን ዋናና ደጋፊ ሃሳቦች ለይቶ በዝርዝር መረዳትን ያካትታል:: Clarke & Silberstein (1977:144)፥ McGary (1991:94) እንደሚያብራሩት፥ አንባቢው የጸሀፊውን መልእክት ተረድቶ በራሱ አገላለጽ የሚያቀርብበትም መንገድ ነው:: አንባቢው ከምንባቡ የሚያገኘውን ትምህርት ከግል

ገጠመኙና እውቀቱ ጋር አያይዞ የሚያቀናብርበት በመሆኑም በአብዛኛው የንባብ ትምህርት ክፍል የሚተኮርበት ይሆናል::

3. አንድምታዊ/ምርምራዊ አንብቦ መረዳት (inferntial Comprehension):- በምንባቡ ግልጽና ቀጥተኛ መልእክት መነሻነት በግልጽ ያልተቀመጠውን መረጃ በጥልቀት መርምሮ መረዳትን የሚጠቁም ነው:: ይህም ማለት በምንባቡ ግልጽ መልእክት አማካይነት ይዘቱን አመዛዝኖ ሊሆን የሚችለውን ሃሳብ ማሰላሰልን እንደሚያጠቃልል ለማመልከት ነው /Stillie & Lynskey 1984:5፥ Lewin 1984:121):: በዚህ አንብቦ የመረዳት ዘርፍ አንባቢው የሚያነበውን ምንባብ ሃሳብ ደራሲው በውስጠ ታዋቂነት እንዴት እንዳስቀመጠው፥ ደራሲው ስለርእሱ ያለው አመለካከት ምን እንደሆነ ለመመርመር ብሎም ከግል እወቀቱ ጋር ለማዛመድ የሚችልበት ነው::
4. ግምገማዊ አንብቦ መረዳት /evaluative comprehension):- በተራ ቁጥር '3' ስር ከተጠቀሰው አንብቦ የመረዳት ዘርፍ ላቅ ያለ ነው:: ግምገማዊ አንብቦ መረዳት አብዛኛውን ጊዜ የጸሀፊውን ዳራዊ እውቀት፥ ስለርእሱ ያለውን አመለካከትና የጽሁፉን አላማ መገምገምን ይጠይቃል:: አንባቢው ምንባቡን ካነበበ በሁዋላ በተረዳው መሰረት መልእክቱን በማመዛዘን ያለውን ረብ፥ ተአማኒነት፥ ግልጽነት እንዲሁም በተገቢው መረጃና ተጨማሪ ማብራሪያዎች ተደግፎ መቅረቡን በመገምገም፥ በማዘዛዘንና በመጠየቅ የሚረዳበት ሲሆን ያገኘውን መልእክት መቀበልን ወይም ማጠናከርን ይይዛል:: ለምን? እንዴት? ውጤቱስ? የሚሉትን ጥያቄዎች አንስቶ ለመመለስ መሞከርን ይጠቀማል:: በተጨማሪም Aebersold & Field (1997:130)፥ Munby (1968:xii) እና መንዲዳ Ellis and Tomilson (1986)ን በመጥቀስ (1988:5-6) እንደሚገልጹት፥ የጸሀፊውን የቋንቋ አጠቃቀም፥ የቃላት አመራረጥ፥ የአረፍተ ነገር አወቃቀር እንዲሁም የጽሁፉን የአቀራረብ ስልት፥ ደራሲው ስለርእሱ ያለውን ስሜት፥ የጽሁፉ ስልት ለደራሲው አላማ ተገቢ የገለጻ መንገድ መሆን አለመሆኑን መሄስን ሁሉ ሊያጠቃልል ይችላል::
5. መቀበል፥ መርካትና ማድነቅ (appreciative comprehesion):- ምንባቡን በጥንቃቄ አንብቦ መልእክቱን ማድነቅን፥ በአቀራረቡ ጥራት መርካትን፥ የሚያመለክት ነው:: የቋንቋ አጠቃቀሙን፥ ስነጽሁፍ ከሆነ አተራረኩን፥ የስሜት-ነክ ጉዳዮች አገላለጹን የመሳሰሉትን መመርመርን የሚያቅፍ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዘርፍ ነው::

ከላይ የተዘረዘሩት ነጥቦች ለአጽንኦት ያህል በዚህ መልክ ቀረቡ እንጂ ፍጹም የሚለያዩ አይደሉም:: መገምገምን፥ መጠየቅንና ማመዛዘንን የሚያመለክቱት ደረጃቸው ላቅ ያለ ቢሆንም እነዚህን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ አንባቢው የግድ በምንባቡ ውስጥ የሚያገኘውን ግልጽ መልእክት መረዳትና የተረዳውንም በራሱ ግንዛቤ ማቀናበር ይጠበቅበታል:: በመሆኑም ዘርፎቹ የተወራረሱ፥ በተከታታይ ልምምድና ትምህርት የሚዳብሩ ናቸው:: ተወራራሽ በመሆናቸውም በሶስት ሊጠቃለሉ ይችላሉ:: የምንባቡን ግልጽ መልእክት በማንበብና በማብራራት ደረጃ፥

በምንባቡ ግልጽ መልእክት መነሻነት ያልተብራራውን መልእክት በመመርመር ደረጃና፥ የምንባቡን አጠቃላይ መልእክት ከአንባቢው ገጠመኝ፥ እውቀትና ችሎታ ጋር በማያያዝ ደረጃ መታየት አለባቸው /McGarry 1991፡94/፥ Grant 1987፡60)፡፡

ስለዚህ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማንኛውም የትምህርት መስክ አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም፡፡ ታዲያ በአሁኑ ወቅት ይህንን አስፈላጊና ጠቃሚ ችሎታ ለማዳበር ያለው አጠቃላይ ጥረት በአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ላይ ምን ይመስላል? ብለን ብንጠይቅ፥ ከሂሉ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን አንብቦ የመረዳት ችሎታን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የፈተሹ ጥናቶች (ጌታቸው አዱኛ 1986 ዓ.ም.፤ በድሉ ዋቅጅራ 1988 ዓ.ም.፥ ግርማ አውግቸው 1988 ዓ.ም.፥ ተስፋዬ ሸዋዬ 1986 ዓ.ም.፤ አጥናፍ ዋሴ 1989 ዓ.ም.፤ ማስተዋል ውበቱ 1989ዓ.ም.፤ ሰለሞን ሀለፎም 1990 ዓ.ም.‚ የኔሰው ደሴ 1990 ዓ.ም. ተፈራ በጋሻው 1990 ዓ.ም.) ያመለክታሉ፡፡ ለተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ መሆን አንዳንዶቹ በጥናቶቻቸው እንዳመለከቱት ምክንያቱ የንባብ ልምድ ማነስ ሲሆን ሌሎቹ በምክንያትነት የሚጠቅሱት የትምህርት አሰጣጡ ችግር መሆኑን ነው፡፡ ጥቂቶቹን ጥናቶች ቀጥለን እንመልከት፡፡

ተስፋዬ (1986፡9)፥ "ከመሰረቱም ቢሆን የብዙዎቻችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በተገቢው መንገድ ባለመዳበሩ" የማንበብ ልምዳችን ዝቀተኛ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ከዚህም የተነሳ የማንበብ አድማሳችን ጠባብ ነው፡፡ ከዚህ አልፎ ያነበብነውን የመገንዘብ ችሎታችንም የምንመኘውን ያህል ባለመዳበሩ አንብቦ የመገንዘብ ችሎታ (መጠየቅ፥ ማመዛዘን፥ መመራመር፥ ማመሳከር) የሚያጠቃልላቸውን ተግባራት የምንፈጽም ብዙዎች አለመሆናችንን ያመለክታሉ፡፡

አለማየሁ (1986) እና ጌታቸው (1986)፥ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መገኘቱን ይጠቁማሉ፡፡ እንደ መፍትሄ የሚያቀርቡትም ንባብን በተሻለ ዘዴ ማስተማርና ለንባብ ትምህርት ሰፊ ትኩረት ሰጥቶ ጥረት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡ በተለይም አለማየሁ (1986፡88፥91) የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር የተለያየ ይዘት ባላቸው ምንባቦች በመጠቀም ንባብን ከጽህፈት ክሂል በማዛመድ ማለማመድ የተሻለ ውጤት እንደሚያስገኝ ያመለክታሉ፡፡

ቀደም ሲል እንደተመለከተው፥ ጌታቸው (1986 ዓ.ም.)፥ ተስፋዬ (1986 ዓ.ም.)፥ አጥናፍ (1989 ዓ.ም.)፥ አለማየሁ (1986) እና በድሉ (1988)፥ ለንባብ ትምህርት ልዩ ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ቢያሳስቡም በቀጥታ በማስተማሪያ ዘዴው ላይ አላተኮሩም፡፡ በማስተማሪያ ዘዴው ውጤታማ አለመሆን ላይ በማተኮር አማራጭ ዘዴ መጠቀም እንደሚገባ ያመለከቱት ማስተዋል (1989 ዓ.ም.)፥ ሰለሞን (1990 ዓ.ም.)፥ ተፈራ (1990) እና የኔሰው (1990 ዓ.ም.) ናቸው፡፡

ማስተዋል (1989:49) የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ ለማወቅ ባካሄዱት ጥናት የተማሪዎቹ ችሎታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ገልጸው ችግሩ በአማርኛ አፋቸውን በፈቱትም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩት ተማሪዎች ውጤት ላይ በግልጽ መታየቱን ጠቁመዋል:: ማስተዋል፥ በአማርኛ የንባብ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ክፍል ተገኝተው ባካሄዱት ምልከታ የሚዘወተረው የማስተማሪያ ዘዴ የቃል ንባብ (oral reading) በመሆኑ ለሚታየው ችግር የጎላ ድርሻ እንዳለው ያመለክታሉ:: በማጠቃለያውም "ምንም እንኳን የተሻለ የማስተማሪያ መጻህፍት[1] ቢኖሩም የተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንዲዳብር የተሻለ የማስተማሪያ ዘዴ ካልተፈለገ ሁኔታውን ለመለወጥ አስቸጋሪ" መሆኑን በአጽንኦት ይገልጻሉ::

ስለሞን (1990:3) የተማሪዎቹን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማጠናከር የሚረዱ ወቅታዊ የማስተማሪያ ዘዴዎች በተግባር ያለመዋላቸውን፥ በዚህም የተነሳ የተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ እንደሆነና ባጠቃላይም የንባብ ባህልን ለማዳበር ልዩ ልዩ ስልቶች አለመቀየሳቸውን ይጠቁማሉ:: ስለሞን አስተያየታቸውን ሲያጠናክሩ "አማርኛን በመማር ማስተማር ሂደት ከሚታዩት ችግሮች አንዱ ለተሻለ ውጤት በማያበቁ ተለምዷዊ ዘዴዎች ማስተማር በመሆኑ ሁለ-ገብ ጠቀሜታ ያላቸውን ዘመነኛ ዘዴዎች በተግባር ማዋል ችግሩን ለማቃለል እንደሚረዳ" ይገልጻሉ:: ተፈራ (1990:1)ም ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ንባብ ትምህርት አቀራረብ በሚል ርዕስ ባካሄዱት ጥናት መግቢያ ላይ እንደሚያመለክቱት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው የሚጠበቀውን ያህል አይደለም:: ለዚህም ምክንያቱ ትምህርቱ በተገቢው መንገድ ተቀናብሮ ባለመተግበሩ እንደሆነ ተፈራ በአጽንኦት ገልጸዋል:: በጥናቱ ሂደት ባደረጉት የክፍል ክንውን ምልከታ ልምምዱ የሚካሄደው በቃል ንባብ (ተማሪዎችና መምህራን ተራ በተራ) መሆኑን ጠቁመው የሚያነቡትም ተማሪዎች የተወሰኑት እንደሆኑ ያስረዳሉ:: በስፋት የሚታየውን ችግር ለመቅረፍም የንባብ ትምህርት የተማሪዎችን ክሂል ለማዳበር በሚያስችል መልኩ ተቀናብሮ ተማሪዎቹ ተከታታይ ልምምድ እንዲያደርጉ ያሳስባሉ:: ስለዚህም ስለሞን (1990 ዓ.ም.)፥ ተፈራ (1990 ዓ.ም.) እና ማስተዋል (1989 ዓ.ም.) እንደሚያብራሩት፥ መምህራኑ ከነባሩ (traditional) "አንብቦ የማስነበብ ዘዴ " ተላቀው የተማሪዎቹን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማጎልበት ከሚረዱ መሰረታዊ ሃሳቦች ጋር ተዋውቀው ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል::

የኔሰው (1990 ዓ.ም.) በበኩላቸው በመስተጋብራዊ የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል አማካይነት አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩትን ማስተማር ችሎታቸውን ለማሻሻል የሚረዳ መሆኑን በጥናታቸው ማጠቃለያ አመልክተዋል::

---

[1] ማስተዋል የተሻለ የማስተማሪያ መጻሕፍት ሲሉ ከ1984 ወዲህ በስራ ላይ ያሉትን ነው::

ከላይ በተጠቀሱት ጥናቶች አስተያየት ላይ ተጨማሪ ፍንጭ ለማግኘት እንዲሁም የተማሪዎችንና የመምህራንን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ለመገምገም  በአማርኛ የንባብ ትምህርት ክፍል ምልከታ ተካሄዶ ነበር:: በምልከታውም ማስተዋል (1989)÷ ተፈራ (1990) እና ሰለሞን (1990) እንዳረጋገጡት÷ መምህራኑ የሚያዘወትሩት የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ በንበትና በመልመጃ ስራዎች ላይ የተመሰረተ መሆኑን÷ የልምምዱን አብዛኛውን ሰአት የሚሸፍነው የመምህራኑ ስራ በመሆኑ በልምምዱ ሂደት ተማሪዎች የሚኖራቸው ተሳትፎ አናሳ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል:: ይህም ለተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ እየተዳከመ መምጣት የማስተማሪያ ዘዴው የጎላ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው የሚያመለክት ነው::

በምልከታው ወቅት የተገኙትን ፍንጮች በሁለት ወገን በማስቀመጥ ከንድፈ ሃሳባዊ እሳቤዎች ጋር ማዛመድና ድክመታቸውን ለመጠቆም ይቻላል:: በስፋት የሚዘወተሩት የማስተማሪያ ዘዴዎች የቃል ንባብ እና የመልመጃ ስራዎች ናቸው:: የቃል ንባብን የማስተማሪያ ዘዴነት የሚጠራጠሩት ምሁራን እንደሚሉት ዘዴው ከመልዕክት ትርጎማ ወደ ክሂል ያዘነበለ ነው፤ ከጀማሪዎች ደረጃ ላለፉ ተማሪዎች ልምምድ የሚኖረው ጠቀሜታም ውሱን እንደሆነ (Williams 1984÷ Widdowson 1978÷ Greenwood 1992÷ Brown 1994 እና Aebersold and Field 1997)ያመለክታሉ:: ይህንን የትምህርት አቀራረብ መንገድ ከመስኩ ምሁራን አስተያየትና ከንድፈ ሃሳባዊ እሳቤዎች እንዲሁም ማስረጃዎች አያይዘን ብንገመግመው ንባብን ከማስተማር [ንባብን ከግንዛቤና ከመረዳት ጋር ተዛምዶ ማለት ነው] /Williams 1984:3÷ Widdowson 1978:63/ ንበትን (pronunciation) ወደ ማስተማሩ የሚያተኩር መሆኑን ለመረዳት ይቻላል:: ተግባራዊ አሰራሩንም ብንመለከት ትምህርታዊ ልምምዱ የሚካሄደው በመጀመሪያ ተማሪዎቹ ምንባቦቹን ጮክ ብለው እንዲያነቡ በመንገርና ሲሳሳቱ በማስተካከል እንዲሁም ተማሪዎች ካነበቡ በኋላ መምህሩ የእርማት ንባብ በማድረግ ነው:: የትምህርት አውዱም ተማሪ-መራሽ ከመሆን ይልቅ መምህር-መራሽ ነው::

በክፍል ክንውን ምልከታ ወቅት የዚህ ጥናት አቅራቢ ያነጋገራቸው መምህራን ስለመልመጃ አሰራራቸው እንደገለጹት ብዙውን ጊዜ መልስ በመንገር ላይ ያተኩራሉ:: ምክንያታቸውም ተማሪዎች የመልመጃ ጥያቄዎችን ከሞከሩ በኋላ ለሙከራቸው የእርማት መልስ መናገራቸው ምንባቡን መረዳታቸውን ያመለክታል የሚል ነው:: ይሁን እንጂ ከምንባቡ ቀጥለው የቀረቡትን መልመጃዎች ብቻ መስራትና ማሰራቱ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለው ድርሻ ውሱን ነው:: ምክንያቱም Zamel (1992:464) እነ Barnett (1989:134)ን÷ Belanoff (1987:102)ን እና Shannon (1989:96)ን ጠቅሰው እንደሚያስረዱት÷ ተማሪዎች የምንባብ መልዕክትን ለመረዳት ከመሞከርና ለምንባብ ትርጎማ የሚረዱ የንባብ ስልቶችን ከመለማመድ መልመጃዎችን ብቻ የሚሰሩ ከሆነ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማዳበር የጎላ ጠቀሜታ አይኖረውም:: ተማሪዎች በመልመጃዎች ላይ ብቻ ካተኮሩ አንብቦ መረዳት ሲባል መልመጃ መስራት መሆኑን አምነው መልዕክቱን ለመመርመር የሚያስችላቸውን የንባብ ሂደት

ችላ እንዲሉና የንባብን አላማ በተሳሳተ መልኩ እንዲገነዘቡት ያደርጋቸዋል:: የምንባቡን መልዕክትም ሳይጨብጡ መልመጃዎችን ለመመለስ ስለሚሞክሩ በሚገባ ላያነቡት ይችላሉ:: ይህም የንባብን ሂደት ከማጠናከር ውጤቱ ላይ እንዲነጣጠር ያደርጋል:: ውጤቱን ማስቀደም ደግሞ ማስተማር ሳይሆን መፈተን መሆኑን Alderson & Urquhart (1984)፥ Lewin (1984)፥ Williams (1984)፥ ያስረዳሉ:: ታዲያ በስፋት የሚያንጸባርቀውን ችግር ለመቅረፍ ወይም ለማስወገድ ምን ማድረግ ይበጃል? ለሚለው ጥያቄ በርካታ ምሁራን ማስተማር አስፈላጊ መሆኑን ሲያመለክቱ፥ የሀገርኛ ጠቋሚ ጥናቶችም ለንባብ ትምህርት ልምምዱ ልዩ ትኩረት እንደሚያስፈልግ ያስምሩበታል:: ለማስተማር ደግሞ በተሻለ የማስተማሪያ ዘዴና ወቅታዊ ስልት መጠቀም ተገቢ ነው::

## 1.2. የጥናቱ አላማ

በአገራችን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደካማ መሆኑን፥ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ችላ እየተባለ መምጣቱን ከተጠቀሱት ጠቋሚ ጥናቶች ለመረዳት ይቻላል:: የዚህ ጥናት አላማ ለችግሩ ማቃለያ ይሆን እንደሆን አማራጭ የማስተማሪያ ዘዴን ለመሞከርና ተግባራዊነቱን ለመመርመር የ"ቶፕዳውን" (top-down) አቀራረብን መርጦአል:: የተመረጠበት ምክንያትም ለተማሪዎች ገጠመኝ፥ ልምድና የመማር ጥረት ቅድሚያ የሚሰጥ በመሆኑና የትምህርቱ አውድ ተማሪን በማማከሉ በውጭ አገር በስፋት የተሰራበትና ውጤትም ያስገኘ፥ ወቅታዊ የስነልቡናዊ ስነልሳንን እንዲሁም የቋንቋ ትምህርትን ንድፈ ሀሳቦች ያቀናጀ መሆኑን በማመን (Walker 1998፥ Paran 1996፥ Parrott 1993) ነው:: የአጥኚውም ትኩረት የተለያዩ ተዛማጅ የንባብ ስልቶች (reading strategies) ማስተማሪያ የሆነውን የ"ቶፕዳውን" ሞዴል በኢትዮጵያ በአማርኛ የንባብ ትምህርት አውድ በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ተግባራዊነቱ ቢፈተሽ ችሎታቸውን ለማሻሻል ውጤት ይኖረዋል? የሚል መነሻ ሀሳብ ላይ የተመሰረተ ነው::

በጥናቱ ጻራ እንደተመለከተው የተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው:: ይህንን ደረጃ ለማሻሻል በ"ቶፕዳውን" የንባብ ትምህርት አቀራረብ በማስተማር የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ያስችላል፤

1.2.1. ሞዴሉ በአማርኛ ቋንቋ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል ይረዳልን?

1.2.2. ተማሪዎች የተለያዩ የንባብ ስልቶችን (የምንባብ መልስክት ትንበያን፡ አንድምታዊ ንባብን፥ አውዳዊ ቃላት አፈታትን፥ ንባብን ከቀዳሚ እውቀት

ማገናዘብን)፥ ንባብ የሚካሄድበትን አላማ (ለትምህርት፥ ለመረጃ ፍላጎት፥ ለመዝናናት፥ ወዘተ.) መሆኑን አውቀው ሊጠቀሙበት ይችላሉን?

1.2.3. ተማሪዎች ከ"ቶፕዳውን" የንባብ ትምህርት አቀራረብ ልምምድ በሁዋላ የሚቀርብላቸውን ትምህርትና ልምምድ ይወዱት ይሆን? ለምን?

ባጠቃላይ የሙከራ ምርምሩ አላማ የ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል እንደ አንድ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ (ንባብን) መጠቀም የሚኖረውን ፋይዳ ለመመርመር በመሆኑ ለጥናቱ አላማ መፈተሻያነት አጥኚው ከሙከራው በኋላ በቁጥጥሩም ሆነ በሙከራ ቡድኑ መካከል የችሎታ መበላለጥ አይታይም የሚል ባዶ መላምት (Ho) እና ከሙከራው በኋላ በቁጥጥሩና በሙከራው ቡድን መካከል የጎላ የችሎታ መበላለጥ ይኖራል የሚል አማራጭ መላምት (H1) ይዞ ተነሳ::

## 1.3. የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ የ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል ከልማዳዊው የማስተማሪያ ዘዴ የሚሻል መሆን አለመሆኑን በሙከራ ለማረጋገጥ ሞዴሉ የሚፈልገውን ስነ ትምህርታዊ መመሪያዎች በመከተል በክፍል ውስጥ ተግባራዊ በማድረግ የሚሻለውን መጠቆም ነው:: በመሆኑም መሰረታዊ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ከሚመለከቱ ጉዳዮች በስተቀር ወደ ዝርዝር የንባብ ትምህርት አሰጣጥ አያተኩርም:: መሰረታዊ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ሲባልም decode ማድረግ የሚችል ማንኛውም ሰው የሚኖረው የሚገባውን ችሎታ ለመጠቆም ነው:: ከዚህ በተጨማሪም Grant (1987) እና Ellis & Tom Linson (1988) እንደሚሉት፥ ለትምህርት የሚቀርበው ቋንቋ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ጽንሰ ሃሳቦች የዳበረና ሙያዊ አገልግሎት የሚሰጥ ካልሆነ የሚተኮርበት ጉዳይ መሰረታዊ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በመሆኑ ጥናቱ በዚሁ ላይ ተወስኗል:: ይህም ማለት አማርኛ ለሳይንስ፥ ለአካዳሚያዊ ጉዳዮች፥ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ፥ ለልዩ አገልግሎት፥ ወዘተ. ተብሎ በተለያዩ መስኮች ልዩ ግልጋሎት በመስጠት ደረጃ ላይ ስላልደረሰ የምናተኩርበት ዘርፍ መሰረታዊ የሆነውን ነው፤ አጠቃላይ የሆነውን ጽሁፍ አንብቦን ለመረዳት::

ጥናቱ በሞዴሉ የሚተኮርባቸውንና የሚጠቀሱትን ተላውጠዎች በቅንጅት ለተማሪዎች ችሎታ መሻሻል ያስገኛሉ የሚል በመሆኑ በአንዳቸውም ላይ የወሳኝነት ሚና አለው የሚል ሃሳብ የለውም::

## 1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት

1.4.1. በጥናቱ አላማ የተነሱትን ጥያቄዎች ለመመለስ ስለሚያስችል፥

1.4.2. በጥናቱ አላማ ለተነሱት ጥያቄዎች አዎንታዊ ምላሽ ከተገኘ የስርአተ ትምህርትና የመማሪያ መጻህፍት አዘጋጆች መመሪያዎቹን ከግንዛቤ አስገብተው በስራ ላይ እንዲያውሉዋቸው ስለሚጠቅምና አሉታዊ ከሆነ ደግሞ ችግሮቹ ታውቀው ለችግሮቹ መቅረፊያ መፍትሄ እንዲፈለግ ስለሚጠቅም፥

1.4.3. በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘውን የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል አማራጭ መንገድ ስለሚጠቅም፥

1.4.4. በመማር ማስተማሩ ሂደት ተሳታፊ የሆኑት መምህራን ስለትምህርት አሰጣጣቸው የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና ተማሪዎቻቸውን የበለጠ እንዲረዱ ስለሚጠቅም፥

ጥናቱ አስፈላጊነት አለው ተብሎ ይታመናል::

## 1.5. የቁልፍ ቃላት ብያኔ

የሚከተሉት ሙያዊ ቃላትና ስያሜዎች በዚህ ጥናት ውስጥ የያዙት ፍች እንደአገባባቸው ቀርቦአል፤

<u>መስተጋብራዊ</u> (interactive):- በGrabe (1988:56፥ 1991:381) ገለጻ መሰረት በሁለት መንገድ ሊፈታ የሚችል ነው:: አንደኛው፥ የንባብ ሂደትን የሚያመለክት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ማስተማሪያ ሞዴልን ይገልጻል:: በዚህ ጥናት ውስጥ የያዘው ፍች የመጀመሪያው ነው:: ይኸውም ንባብ ሲካሄድ የሚነበበው ምንባብ ብቻውን ለትርጉዋሜው የተሙዋላ ሳይሆን መነሻ በመሆኑ የምንባቡ መልእክት ከአንባቢው ዳራዊ እውቀት መዛመድ እንዳለበት ለማመልከት ነው:: ስለዚህ አንብቦ መረዳት ሲባል ውጤቱ የሚታየው በሁለቱ መካከል ባለው መጣጣም በመሆኑ የምንባቡ መልእክትም ሆነ የአንባቢው ዳራዊ እውቀት አስፈላጊነት ይኖራቸዋል:: ጥናቱ በዚሁ ግንዛቤ ላይ የተመሰረተ ስለሆነ አንብቦ መረዳት ስንልና ሞዴሎቹን በተናጠል ስናነሳ ንባብ መስተጋብራዊ መሆኑን እየገለጽን ነው /ለዝርዝሩ Nuttall 1982/1996፥ Wallace 1992፥ Smith 1985፥ Goodman 1986፥ Grabe 1988/1991፥ Wixson & Lipson 1986::/

<u>መስተጋብር</u> (interaction):- በንባብ ሂደት ውስጥ በአንባቢው የቋንቋ ችሎታ፥ የማስተማሪያ ዘዴ፥ የምንባቡ መልእክትና በክፍል ትምህርታዊ ክንውኖች እንዲሁም በአንባቢውና በምንባቡ መካከል የሚኖረውን ግንኙነት ያሳያል:: እነዚህ ዝርዝር ነገሮች ወይም ተላውጦዎች (variables) በሚኖራቸው መስተጋብር የሂደቱ ውጤት ሊሰምር ወይም ላይሰምር ይችላል /Williams 1984:16/::

"ቶፕዳውን" (top-down):- የአንባቢውን የቋንቋ ችሎታ፥ አእምሮታዊ ተግባርና ዳራዊ እውቀትን በመጠቀም የምንባቡን መልእክት መተንበይን፥ አውዳዊ የቃላት አፈታትንና አንድምታዊ የንባብ ስልትን በማስተማር ተማሪዎች ከምንባቡ ውስጥ ተፈላጊ መረጃ የሚቀስሙበትን ሂደት በማጠናከር ላይ የሚያተኩር የማስተማሪያ ሞዴል ነው:: ቀዳሚ እውቀትን በመጠቀም የሚገኘውን መረጃ መሰረት ለማስያዝና መልእክቱን ለመረዳት የተለያዩ የንባብ ስልቶችን በቅንጅት የማስተማርን እና በማራኪ ምንባቦች የመጠቀምን አስፈላጊነትም ያጸናል:: /Wallace 1992፥ Aebersold & Field 1997/::

ቦቶም አፕ (bottom-up):- በዚህ የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል ስነ ትምህርታዊ እሳቤዎች መሰረት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማዳበር ደረጃ በደረጃ እየዳበሩ የሚሄዱ ክሂሎችን መለማመድ አለባቸው:: የትምህርት አቀራረቡም ለልምምዱ የተመረጠውን ምንባብ በንኡሳን ክሂሎች በመከፋፈል ንበትን፥ የቃላት ፍችን፥ ከዚያም የዐረፍተነገሮችን ፍች ከተረጎሙ በኋላ ወደ አንቀጽ፥ ከአንቀጽ ወደ ሙሉ ምንባብ እንዲሄዱ የሚገፋፋ ነው:: የትምህርት አቀራረብ ሂደቱም መምህር-መራሽ ነው:: /Haverson 1991፥ Carrell 1998a/::

ዳራዊ እውቀት (background knowledge):- አንድ አንባቢ በትምህርት፥ በእለታዊ ገጠመኙ፥ በግል ንባቡና ከማህበረሰቡ ጋር በሚኖረው መስተጋብር የሚያዳብረውን እውቀት፥ የሚያመለክት ስያሜ ነው:: ይህ እውቀት አንባቢው የሚፈልገውን አዲስ መረጃ ለማመዛዘን፥ ለመገምገምና ለመመርመር የሚያስችለው ነው:: ከዚህ እውቀት ዋነኛው ክፍል የቋንቋ ችሎታና የአካባቢ ግንዛቤን ሊያጠቃልል ይችላል (Abersold & Field 1977፥ Eskey 1988/:: በአጠቃላይ የአንባቢው ዳራዊ እውቀት ከሚነበበው ምንባብ መልእክት ጋር ያለው ተዛምዶ ለፍች ፈጠራው ጥረት (reconstructing meaning) ቅለት ወይም ክብደት ቁልፍ ስፍራ ይኖረዋል::

አንብቦ የመረዳት ችሎታ (reading comprehension ability):- ተማሪዎች በራሳቸው ምርጫም ሆነ ለትምህርት የቀረበላቸውን ምንባብ መልእክት መርምረው፥ ገምግመውና አመዛዝነው ለመረዳት ያላቸውን ችሎታ ለማመልከት የገባ ስያሜ ነው:: /Williams 1984/::

አንድምታዊ ፍች (inferential meaning):- በምንባቡ ውስጥ ደራሲው ባስቀመጠው መልእክት አማካይነት ሊሆን የሚችለውን ሃሳብ በጥልቀት መርምሮ መረዳትን ያመለክታል:: አስፈላጊነቱም ተማሪዎች በግልጹ መልእክት ብቻ ሳይወሰኑ አውዳዊውንም አመዛዝነው እንዲረዱት ስለሚያስችላቸው ነው:: ምክንያቱም ጥሩ አንባቢዎች አጠያቂ ጸሀፍት (interrogative authors) በመሆናቸው የጸሀፊው አስተሳሰብ ወይም ገለጻ ወዴት እንደሚያመራ

መገመትና ማወቅ ይጠበቅባቸዋል:: የምንባቡ አተረጓጎም አረፍተ ነገሮቹና ቃሎቹ በምንባቡ ውስጥ በገቡበት አኳኋን ለየብቻቸው በተናጠል የያዙትን ሃሳብ ብቻ ማወቅ አይደለም፣ አይበቃምም:: Widdowson (1979:128-129) እንደሚሉት "አረፍተ ነገሮቹም ሆኑ ቃሎቹ የቀረቡበት የቋንቋና የሌሎች ኢ-ቋንቋዊ አውዶች በጋራ በአገልግሎት ላይ የዋለውን ቋንቋ ምሉእነት ያስገኛሉና::"

ምንባብ (text):- በአንድ በተወሰነ ርእስ ጉዳይ ዙሪያ መልእክትን ለማስተላለፍ የሚቀርብ ነው:: ጽሁፉ ወይም ምንባቡ የሚቀርብበት አውድ÷ የቋንቋ አጠቃቀምና የሚቀርብለት ታሳቢ ተደራሲ ይኖረዋል:: የአቀራረብ ቅርጹም ግጥም÷ ስድ ጽሁፍ÷ የፈጠራ ጽሁፍ ወይም የፈጠራ ያልሆነውን ቅርጽ (genre) ያጠቃልላል:: በጥናቱ ውስጥ ምንባብ (passage) ከሚለው ቃል ጋር በአቻነት የገባ ሆኖ ትርጉም-አዘል የተግባቦት መንገድ መሆኑን ይጠቁማል:: /Silberstein 1994÷ Wallace 1992/::

ማንበብ (reading):- ከሚነበበው ምንባብ ውስጥ የሚፈለገውን መልእክት ለመረዳት የሚደረገውን ጥረት ይገልጻል:: በዚህ አገባቡ ጽሁፍን ከዳር እስከ ዳር መውጣት ሳይሆን መልእክቱን ተረድቶ ለሚፈለገው አላማ ማዋልን ያመለክታል (Williams 1984:3÷ Grellet 1981:3)::

ትርጉም አዘል አሀዶች (Chunks, meaningful Units and/or sense groups):- በሚነበበው ምንባብ ውስጥ የሚገኙት ቃላትና ሀረጋት በቅንጅት የተሟላ መልዕክት የሚያስተላልፉበትን መንገድ ይጠቁማል:: ይህም ከዝርዝር ይልቅ ቅንጅት ላይ ማተኮርን የሚጠይቅ ነው:: ስለዚህ ለንባብ ትምህርት ልምምድ ውጤታማነትም አንባቢው በትርጉም-አዘል አሀዶች ደረጃ በማንበብ በአጠቃላይ የምንባቡ መልዕክት ላይ ማነጣጠር አለበት/:: Breznitz and Share 1992÷ Smith 1985/::

የአጭር ጊዜ ትውስታ (Short-Term Memory; STM):- በሚነበበው ምንባብ ውስጥ የሚገኙት ትርጉም-አዘል አሀዶች የሚያስተላልፉትን መልዕክት በአዕምሮ ይዞ ለማቆየትና ከቀዳሚው እውቀት ለማገናዘብ ጥረት ሲደረግ የሚፈጀውን የጊዜ ርዝመት መግለጫ ነው:: ይህ ትውስታ ለአጭር ጊዜ የሚቆይ በመሆኑ በንባብ ልምምድ ጊዜ በዝርዝር ነገሮች ላይ የሚተኮር ከሆነ የአገልግሎት ውሱንነት ይጎላበታል:: ስለዚህ ይህንን ችግር ለማስወገድ በትርጉም-አዘል አሀዶች ደረጃ ማንበብ ያስፈልጋል /Shafer 1978÷ Breznitz and Share 1992÷ Boiarsky 1993)::

# ምዕራፍ ሁለት

## የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

በዚህ ምዕራፍ በንባብ ትምህርት መስክ የተካሄዱ ጥናቶችና የባለሙያ አስተያየቶች ይቀርባሉ:: ቅኝቱ በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ/ውጭ ቋንቋዎች ትምህርት ላይ የተደረጉ ምርምሮችን የሚያካትት ሲሆን ለአቀራረብ እንዲያመች ምእራፉ በአምስት ንኡሳን ክፍሎች ተከፋፍሎአል::

በመጀመሪያው ንኡስ ክፍል በንባብ ትምህርት አቀራረቦች ላይ የተሰጡ አስተያየቶች የተካተቱ ሲሆን በሁለተኛው ክፍል የጥናቱ ማጠንጠኛ የሆነው የ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል ንድፈ ሃሳባዊ አሳቤዎች (assumptions)፥ የሞዴሉ መርሆዎችና የተካሄዱ የሙከራና ደጋፊ ጥናቶች ተቃኝተው ይቀርባሉ:: በሶስተኛው ክፍል ደግሞ በሞዴሉ ላይ የተሰነዘሩ አሉታዊ አስተያየቶችና ምላሾቻቸው እንዲሁም በሞዴሉ መሰረታዊ አሳቤዎች ላይ የተደረጉ መሻሻሎች ምንነትና የትኩረት አቅጣጫ ይቀርባል:: በአራተኛው ንኡስ ክፍል በሞዴሉ ትምህርታዊ መርሆዎች መሰረት ለመማር ማስተማሩ ሂደት ስኬታማነት የትምህርቱን አውድ፥ የመምህሩንና የተማሪዎችን ሚና የሚገልጹ የባለሙያ አስተያየቶች ተካተዋል:: በአምስተኛው ክፍል ስለማስተማሪያ ምንባቦች አመራረጥ፥ ስለአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አይነት፥ ስለአንብቦ መረዳት ፈተና አይነትና አዘገጃጀት እንዲሁም ስለፈተናዎች አጠቃላይ ጠንካራና ደካማ ጎኖች የባለሙያዎችን ሃሳብ አካቶአል::

## 2.1. ንባብን የማስተማር ስልተ ትወራዎች (Approaches)

እስከአሁን ድረስ በንባብ ትምህርት መስክ በስራ ላይ የዋሉትን የማስተማሪያ ስልተ ትወራዎች በሁለት ጠቅለሎ ማየት እንደሚቻል በርካታ ምሁራን (Atwell & Rhodes 1984: 702-703)፥ Haverson (1991:185)፥ Moran & Williams (1993:66) እና Wallace (1992:54) ይገልጻሉ:: እነዚህም ክሂል-ተኮር (skills-based) እና ስልት ተኮር (strategy-based) በመባል የሚታወቁት ናቸው:: እነዚህ ስልተ ትወራዎች በውስጣቸው የተለያዩ ቴክኒኮችንና የአፈጻጸም ቅደም ተከተሎችን ያካትታሉ:: እንደየተከሰቱበት ወቅት ከቦታ ቦታ ወይም ከተመራማሪ ተመራማሪ የሚለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ያቀርባሉ:: በዚህ ጥናት የሚጠቀሱት ነጥቦችም በስልተ ትወራዎቹ ከሞላ ጎደል የሚነኩ በመሆናቸው እያንዳንዳቸውን በተናጠል ቀጥለን እንመልከት::

ይህ ስልተ ትወራ ንባብን በማስተማር ረገድ በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ/ውጭ ቋንቋ አውድ በስፋት ሲያገለግል የኖረና አሁንም በአንዳንድ ሁኔታዎች በማገልገል ላይ የሚገኝ ስልተ ትውራ ነው (Nunan 1991፡63)፡፡ ስልተ ትውራው አንባቢዎች ከሚያነቡት ምንባቡ ውስጥ የሚፈልጉትን መረጃ ለመረዳት ካለፉበት ሂደት ይልቅ ተናጠላዊ ክሂሎችን ለማስጨበጥ ተማሪዎችን ያለማመዳል፡፡ ትኩረቱም በምንባቡ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት አስተካክሎ መጥራትና ምንባቡን ተከትለው ለሚቀርቡት የመልመጃ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ማግኘቱ ላይ ነው፡፡ ዋና ዋና መርሆዎችን እንደሚከተለው ማጠቃለል ይቻላል፡፡

- መስመራዊ የሆኑ ንኡሳን የንባብ ክሂሎችን የሚያስቀድሙ የንባብ ትምህርት ሞዴሎች እሳቤ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ መስመራዊ ሲባልም አንድ አንባቢ ጥሩ አንባቢ ለመሆን ቃላትን አስተካክሎ መጥራት ወይም ማንበብ፥ ከቃላት ወደ ሀረጋት ከዚያም ወደ ዐረፍተነገሮች በመራመድ እነዚህን በቅንጅት አንብቦ መልዕክቱን ለመረዳት መሞከር እንዳለበት ያመለክታል፡፡
- ተማሪዎችን በንኡሳን የንባብ ክሂሎች በስፋት ያለማምዳል፡፡
- አንብቦ መረዳት ሲባል ጸሀፊው ያቀረበውን መልእክት እንዳለ መቀበል መሆኑን ያመለክታል፡፡
- ውጤት ተኮር ነው፡፡ ግቡ ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ማግኘት ነው፡፡ በትክክለኛነት እሳቤ ስለሚመራ ፈርጀ ብዙ አስተያየትና የምንባብ አተረጓጎም አይቀበልም፡፡
- መምህር-መራሽ ነው፡፡ መምህሩ ተስማሚ የትምህርት አውድን ከመፍጠር ይልቅ የትምህርታዊ ክንውኑን አብዛኛውን ክፍል ያከናውናል፡፡

2.1.1. ክሂል-ተኮር ስልተ-ትወራን መነሻ በማድረግ ተሻሽሎ የቀረበው ሌላው የንባብ ትምህርት አቀራረብ ዘዴ በምንባቡ አማካይነት አራት ንባብ ነክ የክሂል ዘርፎችን የሚያስተምረው ነው፡፡ Atwell & Rhodes (1984፡703) እና Haverson (1991፡186) እንደሚያቀርቡት አራቱ ዘርፎች የቃላት ትምህርት፥ የቃል ንባብ፥ ሰዋሰውና አንብቦ መረዳት ናቸው፡፡ መሰረታዊ የትምህርት አቀራረቡም አራቱን ዘርፎች በተናጠል በመተንተን ተማሪዎች በተፈለገው ጊዜ አቀናጅተው እንዲጠቀሙ ለማስቻል ያለማምዳል፡፡ በመሆኑም የቃላት ትምህርቱ መልመጃዎች፥ ሰዋስው ነክ ጉዳዮችም ሆኑ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ተለያይተው ለየብቻቸው ይቀርባሉ፡፡ የመልመጃ ጥያቄዎቹ አዘገጃጀትም በምንባቡ ውስጥ የተገለጹትን ዝርዝርና ዋና ሃሳብ በመለየት ቃል በቃል እንዲመለሱ ታስቦ ነው፡፡

Atwell & Rhodes (1984)፥ Heaverson (1991)፥ Weaver (1990) እና Smith (1985) እንደሚጠቀሙት በንበትና በመልመጃዎች ላይ አነጣጥሮ ተናጠላዊ ክሂሎችን የሚያለማምደውም

ሆነ በምንባቡ አማካይነት አራቱን ንባብ ነክ ትምህርቶች የሚያቀርበው መንገድ የሚፈለገውን ውጤት አላስገኘም፡፡ በባህርያቸውም መስመራዊ (Linear) በመሆናቸው÷ መምህር-መራሽ÷ ምንባቡ የተሟላ ፍች አቅራቢ መሆኑንም በመቀበላቸው በክፍል ውስጥ ለሚነሱ ጥያቄዎችና ውይይቶች አንድ ወጥ የሆነ መልስ ይጠይቃሉ፤ ከሂደት ይልቅ ውጤት ላይ ስለሚያተኩሩ ለመሞከርና ለመሳሳት ብሎም ከስህተት ለመማር እድል አይሰጡም፡፡ የተማሪዎች ልምድና ገጠመኝ ተገቢ ቦታ የላቸውም፡፡

ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ክሂል-ተኮር የሆነው የአቀራረብ ስልተ-ትውራ መልእክቱን ችላ በማለቱ ትችቶች ተሰንዝረውበታል፡፡ በተለይም ከ1960ዎቹ መጨረሻ ገደማ ጀምሮ ተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርት ንድፈ ሃሳብ÷ የአእምሮታዊ ስነልቡና (cognitive psychology)÷ ስነልቡናዊ ስነልሳን (psycholinguistics) እና የመረጃ ትርጎማ ንድፈ ሃሳብ (information processing theory) የጥናት መስኮች መጠናከር የቋንቋ ትምህርት አላማዎችን÷ የማስተማሪያ መሳሪያዎችን አዘገጃጀት÷ እና እስትራቴጂዎችን በአጠቃላይ÷ የንባብ ትምህርትን በተለይ÷ በመቀየሩ ተማሪዎች በንባብ ትምህርት ዘርፍ የተለያዩ ንኡሳን ክሂሎችን ሜካኒካዊ በሆነ መንገድ መማር የሚጠበቅባቸው መሆኑ ቀርቶ÷ ቋንቋን ለተግባቦት አላማ እንዲማሩና በትምህርቱ ሂደትም ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ÷ ንቁ ተሳታፊ ሆነውም ከሚያነቡት ጽሑፍ ውስጥ ተፈላጊውን መልእክት ሊያስጨብጡ የሚያስችሉ ስልቶችን መማራቸው ቀዳሚ ትኩረት እያገኘ መጥቶአል፡፡

በአጠቃላይ÷ የንባብ ትምህርት ተግባቦታዊ መሆን እንዳለበት በተለያዩ የዘርፉ ምሁራን ተመልክቶአል፡፡ በመሆኑም የሚነበበው ምንባብ የተሙዋላ መልእክት ኖሮት በሚገባ እንዲተረጎም ተማሪዎች ከምንባቡ ጋር የተዛመደ ዳራዊ እውቀት አስፈላጊያቸው መሆኑ በጥናት ተረጋግጦአል፡፡ በንባብ ሂደት የተማሪዎች ዳራዊ እውቀት የጎላ ድረሻ እንዳለው በመረጋገጡ የንባብ ትምህርት አቀራረብም አዲሱን መስመር ተከትሎአል፡፡

### 2.1.2. ስልት-ተኮር ስልተ-ትወራ

ይህ ስልተ-ትወራ ህልውናውን ያገኘው ስነልቡናዊ ስነልሳንና አእምሮታዊ ስነልቡና እውን ከሆኑበት ከ1960ዎቹ መጨረሻ አንስቶ መሆኑ ቀደም ሲል ተገልጾአል፡፡ አዲሱ አመለካከትም በትምህርቱም ሆነ በምርምር ዘርፍ መሰረታዊ የአስተሳሰብ ለውጥ አስከትሎአል፡፡ ሜካኒካዊ የነበረው የንባብ ትምህርት አቀራረብ ተሻሽሎ ትኩረቱ ፍች ፈጠራ ላይ አነጣጥሮአል፡፡ የስልተ ትወራው ቀዳሚ አላማ ከሚነበበው ምንባብ ውስጥ የሚገኘውን መልእክት መረዳት እንጂ ቅርጽ አይደለም፡፡ የምንባቡን መልእክት ለመረዳት ደግሞ ተማሪዎችን የሚያለማምደው ተናጠላዊ ክሂሎችን ሳይሆን ጥሩ አንባቢዎች የምንባብ መልእክትን ለመረዳት ያለፉበትን ሂደት የሚያጠናክሩ የንባብ ስልቶችን ነው፡፡

የንባብን ሂደት ለማጠናከር ምንባቡን በወጥነቱ እንደተፈላጊው መረጃ ምንጭ መነሻነት መጠቀምን ይጠይቃል:: ምንባቡን በወጥነቱ የመጠቀሙ አስፈላጊነትም የጎላው ንባብ የበርካታ ተላውጦዎች ውስብስብ መስተጋብር በመሆኑ ነጣጥሎ ከማስተማር ይልቅ ተጣምረው ዘላቂነትና ተለጣጣቂነት ያላቸው ስልቶችን ማለማመዱ የተሻለ ውጤት የሚያስገኝ በመሆኑ ነው::

ከላይ እንደተጠቆመው የስነልቡናዊ ስነልሳን፥ የአእምሮታዊ ስነልቡናና የተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ንድፈ ሃሳብ መጠናከር ለቋንቋ መማር ስልቶች ልዩ ትኩረት አሰጥተዋል፤ ምክንያቱም ተማሪዎችን በሚያሳትፍ መንገድ ትምህርቱን ለማካሄድ አስፈላጊ የሆኑ ስልቶችን ማስተማር የተሻለ ነውና:: ተማሪዎችን ማሳተፍና የትምህርቱ አውድ ተማሪ-መራሽ መሆን በፍላጎት የመሳተፍ እድላቸውን ከማሳደጉም በተጨማሪ የመምህሩን የበላይነት ይቀንሳል:: ትምህርታዊ ክንውኖቹም በተማሪዎች መካከል እርስ በርስ፥ በመምህሩና በተማሪዎች የጋራ ውይይት ይዳብራሉ:: ለሚነሱትም ጥያቄዎች የተማሪዎቹ የየግል ተሳትፎ ስለሚታከልባቸው አንድና አንድ የሆነ መልስ የለም:: የምትህርቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የየግል ሃሳባቸውንና አስተያየታቸውን ይገልጻሉ፥ ጥያቄዎቹ ከተለያዩ አቅጣጫዎችና የመረጃ ፍንጮች አንጻር ተመዝነው ይመለሳሉ፥ ብዙዎቹን ያሳተፈ የክፍል ውስጥ ተራክቦ ስለሚኖር በራስ የመተማመንና በፍላጎት የመማር አጋጣሚዎች ከፍ ያሉ ይሆናሉ:: የስልተ ትውሩን ዋና ዋና መርሆዎች እንደሚከተለው ማጠቃለል ይቻላል::

- ስነልቡናዊ ስነልሳንን በተመረኮዙ የንባብ ማስተማሪያ ሞዴሎች እሳቤ ላይ የተመሰረተ ነው፥
- ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ የተለያዩ ውጤታማ የንባብ ስልቶችን እንዲጠቀሙና ራሳቸውን የቻሉ አንባቢዎች እንዲሆኑ፥ በተለያዩ ምንባቦች አማካይነት ማለማመድ አስፈላጊ መሆኑን ያመለክታል:: በዚህም ተማሪዎች፥
    - የየምንባቦቹን አርዕስቶች፥ ንኡሳን አርዕስቶችና ምንባብ ነክ ያልሆኑ አጋዥ ፍንጮች፤ ስዕሎች፥ ግራፎች፥ እና ዲያግራሞች ካሉ አስቀድመው በመቃኘት ከንባብ በፊት አጠቃላይ የሆነ የይዘት ግንዛቤ እንዲጨብጡ ማድረግ፥
    - ምንባቡን በመቃኘትና በገረፍታ በማንበብ ስለይዘቱ በማሰላሰል ምንባቡ ሊመልሳቸው የሚችለውን በርካታ ጥያቄዎች ማንሳትና በንባብ መልስ ለመፈለግ እንዲችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፥
    - የምንባቡን የጽሁፍ አይነት መለየት (ምንባቡ፥ ገላጭ፥ ተራኪ፥ ቀስቃሽ) መሆኑን ከአቀራረቡ ለመገመትና የሚያስተላልፈውን መልዕክት ለመመርመር የሚያስችለውን ሁኔታ ማመቻቸት፥
    - ከምንባቡ ውስጥ ዋናውንና ንኡሳን ጭብጦችን በመለየት ዝምድናቸውን ለመርመር የሚችሉበትን ስልት መጠቀምና ማለማመድ ተገቢ መሆኑን ያስገነዝባል፥

- አንብቦ መረዳት በአንባቢው ዳራዊ እውቀትና በምንባቡ መልእክት መካከል በሚኖረው መስተጋብር የሚወሰን መሆኑን ይገልጻል:: ተማሪዎች የጸሀፊውን ሃሳብ መርምረው እንዳለ መቀበል÷ ማሻሻል ወይም እስከ መንቀፍ ሊዘልቁ እንደሚችሉ ያስረዳል÷
- የተማሪዎቹ ዳራዊ እውቀት ስለሚለያይ የምንባብ አተረጓጎማቸውም የተለያየ በመሆኑ ለሚነሱ ጥያቄዎች አንድና አንድ የሆነ ትክክለኛ መልስ ልዩ ስፍራ የለውም::
- ትኩረቱ ሂደቱን ማጠናከር ነው:: ዋነኛው ግቡ ተማሪዎቹን ማሳተፍና እርስ በርስ በምንባቡ ይዘት ላይ እንዲወያዩ መንገድ ማሳየት ነው /Atwell & Rhodes 1984:703÷ Haverson 1991:185÷ Nunan 1993:82/::

ተማሪዎችን ጥሩ አንባቢዎች ለማድረግና ራሳቸውን ለማስቻል የትምህርት አቀራረቡ በሶስት እርከኖች የተከፋፈለ ነው:: እነዚህም ቅድመ ንባብ (pre-reading)፡ በንባብ ጊዜ (while reading) እና ድህረ ንባብ (post-reading) ናቸው /Squire (184:29)÷ Atwell & Rhodes (1984:703)÷ Aebersold & Field 1997)::

ሀ. ቅድመ ንባብ:- በክፍል ውስጥ ዋናው የንባብ ትምህርት ልምምድ ከመካሄዱ በፊት ለተማሪዎች ቀና መንገድ የሚመቻችበት ነው:: ይኸውም ተማሪዎች ምንባቡን በሚመለከት ያላቸውን ማኛውንም ሃሳብ እንዲያስታውሱና ከምንባቡ ርዕስ ጋር አዛምደው ስለይዘቱ እንዲተነብዩ ለማነቃቃት÷ የንባብ አላማ እንዲኖራቸው ለማድረግና ምንባቡን በጉጉት እንዲያነቡት÷ በተማሪዎች መካከል ባለው ግላዊ የእውቀት መለያየት የተነሳ እውቀቱ የሌላቸውን ተማሪዎች የመነሻ ፍንጭ ለማስጨበጥና አጠቃላይ የተማሪዎችን ትኩረት ለማሰባሰብ የሚያስችሉ ክንውኖች ይፈጸማሉ::

ለ. በንባብ ጊዜ:- በዚህ የንባብ ትምህርት እርከን ዋነኛው ተግባር የንባብ ስልቶችን በስራ መተርጎም ነው:: በመሆኑም ተማሪዎቹ ከምንባቡ ባህርይ ጋር በሚጣጣም መንገድ ተስማሚ የንባብ ስልቶችን ተጠቅመው የምንባቡን መልእክት የሚመረምሩበትን÷ የምንባቡ አወቃቀርና ቅርጽ ለአላማው ስኬት ያበረከተውን አስተዋጽኦ የሚያስተውሉበትን ክንውን ሁሉ ያጠቃልላል::

ሐ. ድህረ ንባብ:- ዋና አላማው በቀዳሚዎቹ ሁለት እርከኖች ያገኙትን ትምህርት የሚያጠናክሩበት ነው:: ተማሪዎቹ ከምንባቡ ያገኙትን እውቀት ለማጠናከር ብቻም ሳይሆን አዲሱን ዕውቀት ከግል ገጠመኛቸው÷ ከቀዳሚ እውቀታቸውና አመለካከታቸው ጋር ለማጣጣም የሚችሉበት ሁኔታም በመልመጃዎች አማካይነት ይመቻቻል:: በመሆኑም አስቀድመው ያካሄዱዋቸው ትምህርታዊ ልምምዶች ከእለታዊ የንባብ ልምዳቸው እንዲጣጣሙ ያለማምዳል::

በክፍል ውስጥ የሚያከናውኑዋቸው ትምህርታዊ ልምምዶች ከእለታዊ የንባብ አጠቃቀማቸው ጋር የሚመሳሰሉ መሆኑን ተረድተው ተማሪዎቹ ለልምምዱ እንዲተጉ ያበረታታል።

ከላይ እንደተመለከተው በእነዚህ ሶስት እርከኖች ተማሪዎችን የሚያበረታቱና ለመማር እድል የሚሰጡ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ። ስለዚህ በዚህ ስልተ-ትውራ ተማሪዎች የዳበረ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያለው አንባቢ የሚጠቀምባቸውን የንባብ ስልቶች እንዲለማመዱ ይደረጋል። በሂደቱም ተማሪዎቹ በቀጥታ ከአንደኛው እርከን ወደ ሶስተኛው እንዲያልፉ ወይም የመጨረሻው ውጤት ማለትም ከንባብ በሁዋላ በሚከናወኑ የውይይት መልመጃዎች ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ አይፈቀድላቸውም። የመምህሩ ተግባርም ለእነዚህ እርከኖች ሚዛናዊ ትኩረት ሰጥቶ ተማሪዎች ደረጃ በደረጃ መለማመዳቸውን እንዲከታተልና እንዲቆጣጠር መሆኑን ስልተ ትውሩ በአጽንኦት ያስገነዝባል።

ተማሪዎቹ በምንባቡ ርዕስ ዙሪያ የሚኖራቸውን ተዛማጅ እውቀት በማሳሰል ከምንባቡ ከሚያገኙት አዲስ መልእክት ጋር በማጣጣም የአዲሱን መልዕክት ወቅታዊነት÷ ተአማኒነትና ግልጽነት በመገምገም የአመለካከት አድማሳቸውን ሊያሰፉ ይችላሉ የሚል አስተያየት በስልተ ትውሩ ልዩ ስፍራ አለው። በመሆኑም ንባብን በማስተማር ረገድ መሰረታዊ ለውጥን እንዳመጣ በርካታ ምሁራን (Carrell 1988÷ Cooper & Petrosky 1976÷ Atwell & Rhodes 1984) ይገልጻሉ። የለውጥ አቅጣጫውም በመማር ማስተማሩ ሂደት÷ ተማሪዎችና መምህሮች እንዲሁም የማስተማሪያ መሳሪያዎች በሚኖራቸው ሚናና ትምህርታዊ ልምምዶች ላይ ይታያል።

በስልት-ተኮር ስልተ-ትወራ የማስተማር ልምምድ የክፍል ውስጥ ትምህርታዊ ክንውኖቹ ባህርይ ከቋንቋ ተኮር ክንውን ወደ ተማሪ-መራሽ ክንውን መለወጡን ለመረዳት አያዳግትም። ከዚህ ለውጥ የተነሳም ተማሪዎች በራሳቸው የንባብ አላማና የምንባብ አይነት የሚስተካከሉ የንባብ ስልቶችን ማዳበርና መጠቀም÷ የተወሰነ አላማ ይዘው እንዲያነቡ÷ የሚያነቡትን ምንባብ በሃያሲ አይን ተመልክተው እንዲገመግሙት ይደረጋል። የንባብ ትምህርት ልምምዱም በመጀመሪያ በግል÷ ከዚያም በቡድን በውይይትና በመረዳዳት መንገድ እንዲከናወን ስልተ ትውሩ አጽንኦት ይሰጣል።

የመምህራኖቹ ድርሻ ጥሩ ወይም አመቺ የትምህርት አውድ በመፍጠር ተማሪዎችን ማበረታታት እንጂ በትምህርት ሂደት ላይ የበላይነት ሚና አይኖራቸውም። ተማሪዎቹ የሚቀርብላቸውን ምንባብ ርእስ አስመልክቶ የሚኖራቸው ቀዳሚ እውቀት የተለያየ ስለሚሆን ሁሉንም በጋራ በሚያሳትፍ መልኩ የመግቢያ ውይይት በማካሄድ÷ በንባብ ጊዜ ተማሪዎቹ

ሊያተኩሩባቸው የሚገቡ ጠቃሚ ፍንጮችን በመጠቆምና ከንባብ በሁዋላ ደግሞ የሁሉንም አስተያየት በመቀበል ማበረታታትና ውይይቱ ፈር እንዳይለቅ መቆጣጠር ነው::

ሁለቱን ስልተ-ትውራዎች ለማየት እንደሞከርነው የመጀመሪያው ተናጠላዊ የንባብ ክሂሎችን በዝርዝር በማስተማር ከሚጠየቁት ጥያቄዎች አንጻር ትክክለኛ መልስ ማግኘት እንዲችሉ ተማሪዎችን የሚያለማምድ ሲሆን ስልት-ተኮሩ ስልተ-ትውራ ደግሞ ተናጠላዊ ክሂሎችን ሳይሆን በተቀናጀ መልኩ ተለጣጣቂ የሆኑ ስልቶችን በማለማመድ ተማሪዎች ጥሩ አንባቢዎች እንዲሆኑ ጥረት ያደርጋል:: የትምህርቱን አቀራረብም በተለያዩ እርከኖች በመከፋፈል የዳበረ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያለው አንባቢ የሚከተላቸውን የንባብ ስልቶች ተማሪዎችም እንዲለማመዱ ያበረታታል:: ብራውን (1994:285) የሁለቱን ትወራዎች ልዩነት ሲያመለክቱ ክሂል-ተኮሩ "ቡቶም አፕ" ስልት-ተኮሩ "ቶፕዳውን" መሆኑን ይገልጻሉ::

## 2.2. የ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል ምንነትና ስነትምህርታዊ መመሪያዎች

Carrell (1988)÷ Silberstein (1994)÷ Nuttall (1996)÷ እና Aebersold and Field (1997) እንደሚያስረዱት÷ ይህ ሞዴል የተመሰረተበት እሳቤ አንድ አንባቢ የሚያነበውን ምንባብ መልዕክት ለመረዳት ቀዳሚ እውቀቱንና ልምዱን መነሻ አድርጎ ቢያነብ የምንባቡን መልዕክት በሚገባ ለመረዳትና አንብቦ የመረዳት ችሎታውን ለማዳበር ይችላል የሚል ነው:: በንባብ ሂደቱም አንባቢው ባለው የቋንቋ ችሎታ÷ ገጠመኝና ስለአካባቢው ባዳበረው ግንዛቤ በመታገዝ የምንባቡን መልዕክት በመተንበይና መላምቶችን (hypothesis) በመተርጎም ከተወሰነ ድምዳሜ ላይ ይደርሳል:: ድምዳሜው አስቀድሞ ከገመተውና በተከታታይ ንባብ ከሚያገኘው ሃሳብ አንጻር አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ሊሆን ይችላል፤ የምንባቡ መልዕክት አንባቢው አስቀድሞ ከገመተውና ከቀዳሚ እውቀቱ ጋር የሚጣጣም ከሆነ አዎንታዊ÷ ካልሆነ ደግሞ አሉታዊ ይሆናል::

በ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል ስነትምህርታዊ መርሆዎች መሰረት ስነልሳናዊ እውቀት (የቃላት÷ የሰዋሰውና የድርሰት-ነክ ባህርያት እውቀት) ብቻውን የምንባብ መልዕክትን አሟልቶ ለመተርጎም ስለማያስችል÷ ይህ እውቀት ስለአለም ካለን ግንዛቤ ጋር ሊዛመድ ይገባዋል:: /Nunan 1993: 67-68/:: በሌላ አገላለጽ አንድን ምንባብ አንብቦ ለመረዳትና መልዕክቱንም ለመተርጎም ስነልሳናዊ እውቀትም ሆነ ይህንን እውቀት ለማዳበር የሚያስችል ተዛማጅ ዳራዊ

እውቀት ያስፈልጋል:: የሁለቱ መደጋገፍ ቀዳሚውን እውቀት ለማሻሻልና በተቻለ መጠን ለማስታወስ ብሎም መጪውን ለመገመት ያግዛል፤ የንባብን መስተጋብራዊ ሂደትም ለማጠናከር ቁልፍ ሚና ይጫወታል:: በዚሁ ሂደትም አንባቢው ዋነኛ የተግባራዊ ክንውኖች ፈጻሚ ነው::

በሞዴሉ ተግባራዊነት የሙከራና ደጋፊ ምርምሮችን ያካሄዱት ምሁራን እንደሚያብራሩት፥ አንድ አንባቢ የሚያነበውን ምንባብ በሚገባ ሊተረጉም የሚችለው የምንባቡን ርዕስ የሚመለከት ዳራዊ እውቀቱን፥ የምንባቡን ድርሰታዊ አቀራረብ የሚመለከት እውቀቱን፥ የቋንቋ አጠቃቀም እውቀቱን፥ መነቃቃቱን (motivation) ፍላጎቱን እና ስለምንባቡና አቀራረቡ አውድ የሚኖረውን ግምት አጣምሮ በማንበብ እንጂ እያንዳንዱን ቃል፥ ሀረግና ዐረፍተነገር በተናጠል በማንበብ አይደለም:: ከዚህ ይልቅ የነዚህ ቅንጅት የሚያስተላልፈውን ሙሉ መልዕክት አስቀድሞ በመገመት ለማጣራት ጥረት ያደርጋል፤ ዋናውን አስቀድሞ ለመረዳት ከቻለ ዝርዝሩን ለማጣራት አያዳግተውምና (Williams (1984፡59)፥ Cross and Paris (1988፡131)፥ Wixson and Lipson (1986፡117):: ዋነኛ አላማውም መልዕክቱን ለመተርጎም በመሆኑ ግምቱ በምንባቡ የሚደገፍ መሆን አለመሆኑን እያጣራ የሚያገኘውን ሃሳብ አመዛዝኖ ለመረዳት ነው:: ስለዚህ ከምንባቡ ውስጥ የተወሰኑ ቃላትና ሀረጋት ቢጓደሉ እንኳን አጠቃላይ የሆነውን መልዕክት ለመረዳት አያዳግተውም (Nunan 1993፡82)::

Goodman (1979፥1988) እንደሚያስረዱት የንባብ ችሎታውን ያዳበረው አንባቢ የንባብ ስልቱ ከላይ የተጠቀሰውን መንገድ የሚከተል ነው:: ተማሪዎችም በትምህርት ቤት በተመሳሳይ መንገድ ትምህርታዊ ልምምዶችን ማካሄድ ይኖርባቸዋል:: ሲያነቡም እያንዳንዱን ቃልና ሀረግ በማንበብ ለመተርጎምና ለመረዳት ከመሞከራቸው በፊት በአጠቃላይ መልእክቱ ላይ ማነጣጠር አለባቸው:: አጠቃላይ መልእክቱን ለመረዳትም ከምንባቡ ርእስ ጀምሮ ደራሲው ምን ሊያቀርብ እንደሚችል፥ እንዴት እንደሚያቀርበው እና በምን በምን ነጥቦች ላይ ማተኮር እንዳለባቸው አስቀድመው በመወሰን ማንበብ አለባቸው:: በሚያነቡበትም ጊዜ ግምታቸው ትክክለኛ መሆን አለመሆኑን እያጣሩ፥ ስህተት ከሆነ ለምን እንደተሳሳቱ ምክንያቱን ይፈልጋሉ:: በአእምሮአቸው የቀረጹት ሃሳብ ትክክል መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥም የቋንቋውን ስነፍቻዊና አገባባዊ ፍንጮች ከአውዳዊ አገባባቸው በማያያዝ የጸሀፊውን መልእክት አቀራረብ በመመርመር የሚፈለገውን መረጃ ለመረዳት ጥረት ያደርጋሉ::

Goodman (1970:260) ከላይ የቀረበውን ነጥብ ጠቅለል አድርገው በሚከተለው የንባብ ብያኔ ያብራራሉ:: Goodman የንባብን ምንነት ሲገልጹ፥

ንባብ የመረጣ ሂደት ነው። ከሚገኘው ስነልሳናዊ ግብአት መካከል የተወሰነውን መርጦ ከአንባቢው ቀዳሚ ግምት ጋር ማጣጣምን ይይዛል። የተመረጠውን ግብአት ከግምቱ ጋር ለማጣጣም የሚደረገው ጥረት ሲቀጥል ጊዜያዊ ከሆኑ ውሳኔዎች ላይ ይደርስና እነዚህም በተራቸው በተከታታይ ንባብ ይረጋገጣሉ፤ ወይም ከቀዳሚው ግምት ካልተጣጣሙ ተወግደው፥ አለበለዚያም ተሻሽለው አንባቢው የምንባቡን መልእክት ይረዳል። ስለዚህ ንባብ የመረጣ፤ የትንበያና የማረጋገጫ ሂደቶችን አጣምሮ የያዘ፥ ተከታታይ ተግባር ነው

ይላሉ።

ከጥቅሱ እንደምንረዳው የምንባቡን ሙሉ መልእክት ለመረዳት ምንባቡ የተዋቀረባቸውን ቃሎች ሙሉ በሙሉ ማንበብ አያስፈልግም። የምናገኘው መልእክት ብቃትና ምሉእነት የሚወሰነው ከምናነበው ምንባብ መልእክት ጋር የተዛመደ አጋዥ እውቀት ሲኖረን ነው። እውቀቱ ካለንና ከምንባቡ የምንፈልገውን አስቀድመን ከለየን ለጠቅላላው ቅድሚያ መስጠት ይገባናል። በሂደቱም የሚያጠራጥር ነገር ካጋጠመን ወይም በጣም ዝርዝር ነገሮችን ለመጨበጥ ከፈለግን ተመልሰን በማንበብ ልናረጋግጥ እንችላለን።

Grellet (1981:6) ከላይ የቀረበውን ሃሳብ ሲያጠናክሩ ቀደም ሲል የነበረውንና ከ1970ዎቹ በሁዋላ የታየውን ለውጥ በማነጻጸር የሚከተለውን ይላሉ፤

> እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አንብቦ የመረዳት ልምምድ ከፍተኛ ትኩረት በአረፍተነገርና ከአረፍተነገር ባነሱ ቅንጣቶች ላይ ነው። ይህ ደግሞ ምንባቡን በጭብጥ የተዛመዱ የተለያዩ አረፍተነገሮች ቅንጅት ያስመስለዋል። ነገር ግን ንባብ ውጤታማ እንዲሆን ከተፈለገ እንደ አንቀጽና አጠቃላይ ምንባብ ያሉ ሰፋፊ መዋቅሮችን መልእክት መገንዘብ አስፈላጊ ነው። ምንባብን የተለያዩ አነስተኛ አካሎች ቅጥልጣይ አድርጎ መገንዘብ ጥሩ ውጤት አያስገኝም። ይህ አይነቱ ግንዛቤ ተማሪው እያንዳንዱን አረፍተነገር ለየብቻ ለመረዳት እንዲጥር ያደርገዋል። ከዚህም በላይ አንድ አረፍተ ነገር የያዘውን ጭብጥ ከቀደመውና ከተከተለው አረፍተነገር ጭብጥ ጋር ማገናዘብ እንዳይችል ያደርገዋል። ስለዚህ ንባብ ሲካሄድ በቃላት ወይም እጅግ ከተወሰኑ ጉዳዮች ከመጀመር ከምንባቡ አጠቃላይ ይዘት ወይም አገልግሎት ወይም አላማ መጀመር ያስፈልጋል።

Squire (1984:29)፥ Wittrock (1984:77) እና Widdowson (1978:63) እንደ Grellet ሁሉ በተመሳሳይ የGoodmanን ሃሳብ ይጋራሉ። በእነ Squire አገላለጽ ስናነብ ፍችን የምንፈጥረው በምንባቡ የተለያዩ ክፍሎች መካከል ትስስር በመፍጠር በመሆኑ በያንዳንዱ ጥቃቅን የምንባቡ ገጽታዎች (አጻጻፍ፥ ቃሎች) ላይ ማነጣጠርና ጊዜ ማባከን አይገባም። ዋናዋናዎቹን ጉዳዮች በማስቀደም ከምናውቀው ጋር ለማዛመድ ጥረት ማድረግ ይገባናል።

የ"ቶፕዳውን" ሞዴል አልፎ አልፎ የስነልቡናዊ ስነልሳን የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል ተብሎ ይታወቃል፤ ምክንያቱም መሰረቱ የስነልቡናዊ ስነልሳን ንድፈ ሃሳብ አመለካከት በመሆኑ ነው። የሞዴሉ መስረቾች ንባብ ከስነልቡናዊ ስነልሳን ተግባራት አኳያ መታየት እንደሚገባው ማመልከታቸውም አብሮ ይወሳልና /Smith 1985፥ Cooper & Petrosky 1976፥ Goodman 1988ን ያገናዝባሉ/።

Goodman ፥ Smith ፥ Higgins Cooper & Petrosky እንደሚያስገነዝቡት፥ በንባብ ሂደት ቁልፍ ስፍራ የሚይዘው ተማሪዎቹ ሲያነቡ የሚኖራቸው የትንበያ (prediction) ችሎታ ነው:: የትንበያው ትኩረትም አስተካክሎ "ማንበብ" ሳይሆን ከሚነበበው ምንባብ ውስጥ በቂ መረጃ፥ ትምህርት እና እውቀት ለማግኘት እማስቻሉ ላይ ነው:: Higgins (1984፡192) መልእክቱን ለማግኘት የሚካሄደውን የትንበያ፥ የማረጋገጫና የመገመቻ ተግባር እንደሚከተለው ይገልጹታል፤

> አንባቢዎች አንድን ምንባብ በቀጥታ ከዳር እስከ ዳር ሊያነቡት ይችላሉ:: የጥሩ አንባቢዎች የንባብ ስልትና ጥረት ግን ወንዝ ከሚሻገር ተጓዥ ጥንቃቄና አካሄድ ጋር ሊመሳሰል ይችላል፤ ተጓዡም በቀጥታ ወደፊት ከመራመድ ይልቅ ሳይሰምጥ የሚሻገርበትን መንገድ ይመርጣል:: እሱ አቅጣጫውን በጥንቃቄ መርጦ እንደሚራመደው ሁሉ አንባቢውም ልዩ ትኩረት የሚሰጠውን የምንባቡን ክፍል ለይቶ ያነባል፥ ግምቱን ለማረጋገጥ ይሞክራል:: ሙከራው ትክክል ካልሆነ ለማረጋገጥ ወይም ከምንባቡ አዲስ ሃሳብ ለመረዳት ይጥራል:: በሌላ አገላለጽ አንባቢው የሚፈልገውን መልእክት የያዘውን ክፍል ይመርጣል፥ ጭብጡን ይገምታል፥ የገመተውን ያረጋግጣል:: ለማረጋገጥ ሲያነብ ጥርጣሬውን እያስወገደ ግምቱን ያጠናክራል:: በመጨረሻም ከምንባቡ የሚፈልገውን ጠቅላላ መረጃ ይረዳል::

በጥቅሱ ውስጥ እንደተመለከተውና Higgins (1984) እና Goodman (1970) እንደሚያስረዱት፥ ንባብ አላማን ወስኖ ማንበብን፥ የምንባቡን መልዕክት አስቀድሞ መገመትን፥ አስቀድሞ የተሰነዘረውን የይዘት ግምት ለማጣራት ማንበብን፥ ግምቱ በምንባቡ መልዕክት ካልተደገፈ በድጋሚ አንብቦ ማጣራትና የምንባቡን መልዕክት ከግል ገጠመኝ ጋር አዛምዶ ተቀባይነቱንና ተጨባጭነቱን መገምገምን ይጠይቃል:: እነዚህን ተዛማጅ ተግባራት Higgins (1984፡192) "leeping from floating log to log" በማለት ሲገልጹት Goodman (1970፡260) ደግሞ "Psycholinguistic guessing game" ይሉታል:: ይህ የሚያመለክተው አንድ አንባቢ ለትምህርት የቀረበለትንም ሆነ የሚመርጠውን ምንባብ ለመረዳት የግድ ቃል በቃል ማንበብ እንደሌለበት ነው:: ለጠቅላላው መልእክት ቅድሚያ በመስጠት ያንን ለመረዳት ጥረት ማድረግ ይኖርበታል::

Clarke (1987፡59-60)፥ Clarke & Silberstein (1977፡136-137)፥ Smith (1985፡43)፥ Rosamn et al (1983፡135)፥ Mcleod and McLaughlin (1986፡114-115) እና Cooper & Petrosky (1976፡199) ከፍ ሲል በዝርዝር የቀረቡትን ነጥቦች ለማጠናከር፥ የሞዴሉ ንድፈ ሃሳባዊ መነሻዎች የሚከተሉት መሆናቸውን ይጠቁማሉ:: እነዚህም፡-

1. የሰው ልጅ የአእምሮ ተግባራትን ሲፈጽም የሚያከናውናቸው ነገሮች በማስታወስ ችሎታው ውሱንነት የተገደቡ ናቸው:: ይህም ማለት አእምሮው በአንድ ጊዜ የሚቀበለው፥ የሚያቀናብረውና በሁዋላም በተፈለገው መጠን ለማስታወስ የሚችለው የተወሰነውን ክፍል ብቻ ነው:: ስለዚህ በርካታ ዝርዝሮችን በመተው አእምሮን በማያስጨንቁ አንኳር ጉዳዮች ላይ ያተኩራል::

አንባቢውም የመረጃ ፍላጎቱን ለማርካት በየገጹ ያለውን ቃል ሁሉ ማጣራት ግዴታው አይሆንም፡፡ በእያንዳንዱ ላይ ጊዜውን የሚያጠፋ ከሆነ ከሚያነበው ምንባብ ውስጥ ከሚጨብጠው ሃሳብ ይልቅ ሳይታወቀው የሚረሳው እንደሚያመዝን Clarke (1987፡59) እና Rosamn et al (1983፡135) ያስረዳሉ፡፡ Breznitz & Share (1992፡193)፥ Shafer (1978፡313) እና Smith (1985፡37-41) አንድን ምንባብ አንብቦ ለመረዳት በሚደረገው ጥረት ትልቅ ድርሻ የሚኖረው የአጭር ጊዜ ትውስታ (Short-term memory) መሆኑን በተጨማሪ ያብራራሉ፡፡ ምክንያቱም አንባቢው ከምንባቡ የሚያገኘው መልዕክት ከቀዳሚ እውቀቱ ጋር እስኪሰናሰል ድረስ ለተወሰነ ጊዜ የሚከማቸው በአጭር ጊዜ ትውስታ ነው፡፡

ከሚነበበው ምንባብ ውስጥ የሚገኘው መልዕክት ከአንባቢው ዳራዊ እውቀት እስኪዛመድ ድረስ በርካታ የአእምሮ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ እነዚህ በርካታ አዕምሮታዊ ተግባራት በአጭር ጊዜ ትውስታ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ፤ በዚህም የአቅም ውሱንነት ይጎላበታል፡፡ የስነትምህርትና የስነአዕምሮ ተመራማሪዎች እንደሚሉትም፥ አንባቢው የሚያነበውን ምንባብ መልዕክት መርምሮ በአጭር ጊዜ ትውስታው ለማቆየት የሚችለው ለ30 ሰኮንዶች ያህል ነው፡፡ ስለዚህ የማስታወስ ችሎታ ውሱንነትን ለመቅረፍ አንባቢው የተለያዩ የንባብ ስልቶችን መጠቀም ይኖርበታል፡፡ የስልቶቹ አስፈላጊነትም የአጭር ጊዜ ትውስታን ግልጋሎታዊ ውሱንነት ለመቅረፍ (minimize the functional limitations of Short-term memory) ነው፡፡ ከነዚህ መካከል ዋነኛው የንባብ ስልት የሚነበበውን ምንባብ በትርጉም-አዘል አሀዶች ደረጃ ማንበብ (chunking) ነው፡፡ Shafer (1978፡313) እንደሚገልጹት፥ በትርጉም-አዘል አሀዶች ደረጃ ማንበብና በትርጉም ላይ ማተኮር የአጭር ጊዜ ትውስታን መጨናነቅ ለመቅረፍ የሚረዳው የንባብ ስልት በተስተካከለ ፍጥነት በማንበብ ሙሉ በሙሉ መልዕክቱ ላይ ማነጣጠር ነው፡፡ ይህንን ለማድረግ ደግሞ ከዝርዝር ነገሮች በፊት ጥቅል ነጥቦችን ማስቀደም ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ አንባቢው ስልቶቹን ተግባራዊ ለማድረግና አንብቦ የመረዳት ችሎታውን ለማዳበር የቋንቋ ችሎታውን (የቋንቋ አጠቃቀሙን፥ አውዳዊ የቃላት አፈታት ችሎታውን፥ ድርሰት-ነክ ዕውቀቱን፥ የሃሳብ አደረጃጀት እውቀቱን) እንዲሁም ርዕስ ተኮር እውቀቱን ማዛመድ አለበት፡፡ ሁለቱን በማዛመድ ምንባቡ የሚያቀርበውን መልዕክት አስቀድሞ ለመገመት መሞከርና ጥያቄዎችን በመጠየቅ፥ በንባብ ትክክለኛውን መልዕክት ለማረጋገጥ፥ እንዲሁም አዳዲስ ቃላትን ከአውዳቸው ለመፍታትና ከአጠቃላይ መልዕክቱ ጋር ለማያያዝ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

2. Clark & Silberstein (1977፡136) Kolers (1969)ን ጠቅሰው እንደሚያስረዱት፥ የንባብ ውጤቱ ማለትም አንብቦ መረዳቱ በአንባቢው ዳራዊ እውቀት ስለሚወሰን አብዛኛውን የምንባቡን ክፍል መከታተል ሳይሆን በሚፈልገው ጉዳይ ላይ ብቻ ማተኮርን ይጠይቃል፡፡ በሌላ አገላለጽ ንባብ እይታ ላይ የሚያተኩረው አልፎ አልፎ ነው፡፡ የእስኪማ ንድፈ ሃሳብ የምርምር ውጤት እዚህ ላይ ሊጤን ይገባዋል፡፡ Goetz et al (1984፡728) እንደሚያስረዱት የአንባቢው ቀዳሚ እውቀት የትኩረት አቅጣጫውን ለማሰባሰብና መስመር ለማስያዝ ይረዳል፡፡ ስለዚህ አንባቢው

የትኩረት አቅጣጫውን ለመወሰንና የሚፈልገውን ለመረዳት የምንባቡን አጠቃላይ ይዘት ምንነት መገመትና መተንበይ ያስፈልገዋል::

የቀዳሚ እውቀቱ ክምችት (እስኪማ) የአንባቢውን የትኩረት አድማስ ለመወሰንና አዲሱን ግብአት ከቀዳሚው እውቀት ጋር ለማጣጣም ያግዛል:: በተለይም አንባቢው በሚያነብበት ጊዜ በስራ ላይ እየዋለ ያለው ተዛማጅ ዳራዊ እውቀት (activated schema) አንባቢው ከሚያገኘው ግብአት መካከል አስቀድሞ በሚገምተው መሰረት ሊያተኩርበት የሚገባውን አስረጅ ክፍል ለመምረጥ ያስችለዋል:: ከዚህ በተጨማሪም Goetz et al (1984) እንዲሁም Rosamn et al (1983) እንደሚያብራሩት የአንባቢው ዳራዊ እውቀት አዲሱን ግብአተ ለመገምገም፥ ተቀባይነትና አስፈላጊነቱን ለማመዛዘን ብሎም ጠቃሚ ከሆነ ለማሻሻልና ለመቀበል ይረዳል::

Clarke & Silberstein (1977፡136-137) ከላይ የቀረበውን የሌሎች ምሁራን አስተያየት ያጠናክራሉ:: እነ Clarke እንደሚሉት፥ አንባቢዎች ከሚያነቡት ጽሁፍ ውስጥ የሚረዱት በየገጹ ካለው ምልክት በስተጀርባ ያለውን ስውር መልእክት ነው:: ይህ መልእክት በሚገባ የሚተረጎመው ደግሞ በምንባቡ ግብአት ብቻ ሳይሆን አንባቢዎች በሚኖራቸው ተዛማጅ ቀዳሚ እውቀት አማካይነት ነው:: ስለሆነም እያንዳንዱን ቃልና ሀረግ ተከታትሎ ማንበብ እንደማያስፈልግ አስተያየታቸውን ያቀርባሉ::

ለአንባቢዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው የቀዳሚ እውቀት ክፍል በጊዜው ከሚያነቡት ርእስ ጉዳይ ጋር የተዛመደውና ስለጽሁፍ አይነት ያላቸውን ፍንጭ የሚያመለክተው እንደሆነ ከነ Goetz (1984) ገለጻ ለመረዳት ይቻላል:: ይህ እውቀት አንባቢዎች አብዛኛውን መረጃ በሚያገኙበት ጊዜ ተአማኒነቱን፥ ጠቃሚነቱንና ወቅታዊነቱን ለመገምገም ያስችላቸዋል:: ምክንያቱም አንባቢዎች የሚያነቡትን ምንባብ ለመረዳት ጥረት ማድረግ ብቻ ሳይሆን ጭብጡን በመገምገም ከቀዳሚ የመረጃ ምንጭ ጋር ያወዳድራሉ፤ ያረጋግጣሉ:: ስለዚህ ለአንብቦ መረዳት ችሎታ መዳበር የቋንቋ ችሎታና ከምንባቡ ጋር የተዛመደ ዳራዊ እውቀት ያስፈልጋል::

3. ንባብ የቀዳሚ እውቀት፥ የቋንቋ ችሎታ እና የምንባብ ግብአት ጥምረት በመሆኑ ቅንጅታቸው ወደሚፈለገው ግብ እንዲያመራ ለተማሪዎቹ ቀጣይና ዘላቂ የሆኑ ስልቶችን የሚያዳብሩ መለማመጃዎች ሊቀርቡላቸው ይገባል:: በተለይም ንባብ የሂደትና የውጤቱ ጥምር ስለሆነ (Lunzar & Gardner 1979) ተማሪዎች ከንባብ በሁዋላ በሚሰሩዋቸው መለማመጃዎች የሚሰጡትን ትክክለኛ መልስ ያህል ግምታቸው፥ ትንበያቸውና ዳራዊ እውቀታቸውን የማገናዘቡ ሙከራ ሊበረታታ ይገባል:: ለተማሪዎች አንድን ምንባብ አቅርቦ ምን ያህል ተረዱ? የሚለውን ጥያቄ ብቻ መጠየቁ የተሙዋላ ውጤት አያስገኝም፤ በውጤቱ ላይ ይወስናልና:: ሊበረታታ የሚገባው Atwell & Rhodes (1984)፥ Cooper & Petrosky (1976)፥ Haverson (1991) እና Wallace (1992) እንደሚያብራሩት የንባብ ሂደትን የማጠናከሩ ተግባር ነው:: ይህ ደግሞ

በተላውጦዎቹ መካከል የሚኖረውን መስተጋብር ከማጠናከሩም በላይ ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት እንዲወያዩና እንዲረዱዱ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ:: ይህም በተራው ውጤቱ እንዲሰምር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል::

4. የስነልቡናዊ ስነልሳን እሳቤ ንባብ መስተጋብራዊ መሆኑንና በንባብ ሂደትም አንባቢው ንቁ ተሳታፊ መሆኑን ይጠቁማል:: የአንባቢው ትኩረትና ጥረት ከሚነበበው ምንባብ ውስጥ ተፈላጊውን መረጃ መረዳት ነው:: በዚሁ እሳቤ መሰረት በክፍል ውስጥ ለትምህርታዊ ልምምድ የሚቀርቡት ምንባቦች በስነ ትርጉም (Semantically) የተሟላ መልዕክት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል:: ምንባቦቹ የሚፈልጉትን የንባብ ስልቶች ለማለማመድ የሚያስችሉ÷ የሚያቀርቡት ጽንሰ ሃሳብ ነክ ሀተታ ምሉዕ የሆነና ርዝመታቸውም ቢሆን ከሚያስተላልፉት መልዕክት አኳያ ታይቶ ያልተቆራረጠና ወጥ መሆን አለበት:: ምንባቦቹ ወጥና የተሟላ መልዕክት የሚያስተላልፉ ሲሆኑ ተማሪዎቹ መልዕክታቸውን ለመመርመርና አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውንም ለማሻሻል አመቺ ሊሆኑላቸው ይችላሉ፤ ለሚታቀዱት ንባብ ነክ ክንዋኔዎችም (tasks) ውጤታማነት የጎላ ድርሻ ይኖራቸዋል::

## 2.2.1. የሙከራ ጥናቶች

ከላይ የተገለጹትን ንድፈ ሃሳብ ነክ መርሆዎች ከግንዛቤ በማስገባት ሞዴሉን ወደ ተግባር ለመለወጥና በጠንካራ የምርምር ውጤት ለመደገፍ የተለያዩ ጥናቶች ተካሂደዋል/Cambourne 1981:91÷ Cziko 1980:102÷ Clarke 1979:122ን ያወዳድሩ/:: የጥናቶቹ ግብ የተለያዩ የአንባቢ አይነቶችን በማሳተፍ የሁሉንም የንባብ ባህርያት እንዲያንጸባርቅ ለማድረግ ነው:: በመሆኑም Clay (1968/72)÷ Goodman (1970)÷ Goodman & Burke (1973) Cavalcanti (1978) በሚከተሉት ተጠኚዎች ላይ የመነሻ ጥናቶችን በስፋት አካሄደዋል::

- በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው (በእንግሊዝኛ አፋቸውን የፈቱ) ጀማሪ አንባቢዎች÷
- የዳበረ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ባላቸው እንግሊዝኛ አፍ ፈት ተማሪዎች÷
- የዳበረ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው ልሳነ-ክልኤ አንባቢዎች (በእንግሊዘኛና በፈረንሳይኛ ጎን ለጎን የሚያነቡ ተማሪዎች)÷
- በተለያየ የክፍል ደረጃ ላይ የሚገኙ እንግሊዘኛ አፍ ፈት ተማሪዎች÷
- የተለየ የመማር ችግር ባለባቸው በእንግሊዝኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች÷
- በዝምታ የሚያነቡ (silent readers) በእንግሊዝኛ አፋቸውን የፈቱና እንግሊዘኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች÷
- የአንድን ቋንቋ (የእንግሊዝኛን) የተለያዩ ዘዬዎች በሚናገሩ አንባቢዎች ላይ የተካሄዱ ናቸው::

አጥኚዎች እንዳመለከቱት በሁሉም ምድብ የሚገኙት ተጠኚዎች ዳራዊ እውቀታቸውን በመጠቀምና ከምንባቡ ርእስ በማዛመድ፥ ይዘቱን ለመተንበይ፥ አዳዲስ ቃላትን ከአውድ ለመፍታትና አንድምታዊ ፍችውን ለመመርመር ጥረት ሲያደርጉ ተስተውለዋል።

በተጠቀሱት ተጠኚዎች ላይ በተካሄዱት ጥናቶች ትንተና እንደተመለከተው፥ ተጠኚዎቹ በሚያነቡበት ጊዜ የሚከተሉትን የንባብ ስልቶች ተግባራዊ ያደርጋሉ / ዝርዝሩን ከAnderson 1991፥ Barnett 1989፥ Clarke 1979፥ እና Aebersold & Field 1997 ያገናዝቡ/። እነዚህም፦

- ቃላትን ከነፍችያቸው በፍጥነት ይለያሉ፥
- የምንባቡን የተለያዩ ገጽታዎች ማለትም ንኡሳን አርእስቶችን፥ የመሸጋገሪያ አገላለጾችንና አረፍተነገሮችን አጠቃቀም ይለያሉ፥
- የምንባቡን ይዘት ምንነት ለመገመት ስለርእሱ ያሰላስላሉ፥
- ስለአካባቢያቸው ያላቸውን እውቀት ከምንባቡ ጭብጥ ጋር ለማዛመድ ይሞክራሉ፥
- አዳዲስ ቃላትን ከአገባባቸው ለመረዳት፥ ለመፍታትና ከይዘቱ አጠቃላይ ገለጻ ጋር ለማያያዝ ጥረት ያደርጋሉ፥
- የምንባቡን አጠቃላይ መልእክት ለመፍጠር በመልእክቱ ላይ አነጣጥረው ያነባሉ፥
- የምንባቡን አጠቃላይ መልእክት ለመገመት ይሞክራሉ፥
- ምንባቡን አንብበው ሲጨርሱ ተፈላጊውን መልእክት መረዳት አለመረዳታቸውን ለማረጋገጥ ጥረት ያደርጋሉ፥
- ምንባቡን የሚያነቡበትን አላማ በአእምሮአቸው ለማሰላሰልና አስቀድመው ለመወሰን ይሞክራሉ። አላማቸውን (ለትምህርት፥ ለመረጃ፥ ለመዝናናት፥ ወዘተ) ከግብ ለማድረስ በትጋት ያነባሉ፥
- ከሚያነቡት ምንባብ ባህርይና ካላቸው የንባብ አላማ ጋር በሚጣጣም መልኩ የንባብ ስልታቸውን ለማስተካከል ጥረት ያደርጋሉ፥
- የምንባቡን አብይና ደጋፊ ጭብጦች ይለያሉ፥ አንዱ ሌላውን እንዴት እንዳብራራውና እንዴት እንደሚደጋገፉ ያስተውላሉ፥
- ምንባቡን አንብበው እስኪጨርሱ ድረስ ግልጽ ያልሆነላቸው ነጥብ ካለ ሳይጨነቁ ጠቅላላውን ሃሳብ ለመመርመር ይሞክራሉ፥
- ጠቅላላውን መልእክት ከጨበጡ ዝርዝሮችን ለመረዳት እንቅፋት ቢያጋጥማቸውም፥ ምክንያቱን ጭምር ለመረዳት በንባባቸው ወደፊት ይገፋሉ።

የ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴልን በጥናት ያጠናከሩት ተመራማሪዎች በጥናት ያረጋገጡዋቸውን ነጥቦችና ጠቃሚ የንባብ ስልቶችን ተማሪዎቹ እንዲያዳብሩዋቸው የሚከናወኑ

ትምህርታዊ ተግባራትንም ይጠቁማሉ። ትምህርታዊ ተግባራቱ ደግሞ በሞዴሉ ከሚተኮርባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች ጋር የተያያዙና የተሳሰሩ በመሆናቸው በዝርዝር እንመለከታዋለን።

1. **<u>ትንበያ (Prediction)</u>**:- ሴልሴ Celce-Murcia (1991:173)፥ Ringe (1989:50)፥ Smith (1975:305-311) እና Nicols (1983:225) እንደሚያስረዱት የአንድን ምንባብ ጠቅላላ መልእክትና ቀጣይ ጉዳዮች አስቀድሞ ለማወቅ መሞከር በንባብ ሂደት ሊያጋጥም የሚችለውን ችግር ከወዲሁ ለማስወገድ ይረዳል። ስለዚህም ይህ ዘዴ ተማሪዎች አንድን ምንባብ በማንበብ ላይ እያሉ ወደፊት ያለውንና ገና ያልደረሱበት የምንባብ ክፍል ስለምን እንደሚገልጽ አስቀድመው እንዲገምቱ የሚያስችላቸው ነው። Ringe (1989:50) "ትንበያ አንባቢዎች አስቀድመው በሚገምቱት መሰረት ግምታቸውን ለማረጋገጥ ሲያነቡ ልዩ ትኩረት በመስጠት ማንበብ ያለባቸውን መለየት እንዳለባቸው ለመጠቆም" መሆኑን ያመለክታሉ።

ተማሪዎች ከሚያነቡት ምንባብ ውስጥ የሚፈለገውን መረጃ ወይም መልእክት ለመረዳት በሚያደርጉት ጥረት ለትንበያ የሚረዳቸው ያላቸው ቀዳሚ እውቀት ነው። ቀዳሚ እውቀታቸውም በሚከተሉት ነጥቦች ላይ የተመሰረተ ነው። እነሱም:-

- በቋንቋው የቀረበውን መልእክት ለመረዳት ያላቸው የቋንቋ ችሎታ፥
- የምንባቡን ርእስ ጉዳይ በተመለከተ የሚኖራቸው ተዛማጅ እውቀት፥
- የምንባቡ የቋንቋ አጠቃቀምና አቀራረብ፥
- የቋንቋው ስርአተ ነጥቦች አገባብ፥
- በቋንቋው ውስጥ የሚገኙትን የዲስኩር አመልካቾች አጠቃቀምና እና
- የምንባቡን ሃሳብ ለማጉላት ወይም ለማብራራት ተብለው የቀረቡ ደጋፊ ፍንጮችን ለምሳሌ እንደ ግራፍ፥ ስእል፥ ሰንጠረዥ፥ ንኡሳን አርእስቶችን የመመልከትና ከምንባቡ ገለጻ ጋር የማዛመድ ችሎታዎች ናቸው /Brown 1994፥ Grabe 1991፥ Nuttall 1996ን ያወዳድሩ/።

እንደ Nuttall 1996) ገለጻ፥ ትንበያ ለትምህርት የቀረበውንም ሆነ በተማሪዎች ምርጫ የሚነበብን ምንባብ ለመረዳት መሳሪያና የግንዛቤያቸውም ምልክት ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል። ይህም ማለት ተማሪዎቹ በቅድሚያ ያነበቡትንና ያዩትን የምንባብ ክፍል ለመረዳት ከቻሉ ቀጥሎ የሚባለውን ለመለየት ይችላሉ ለማለት ነው። የመልእክቱ ትንበያ የሚካሄደው ከተማሪዎቹ ተዛማጅ እውቀት በመነሳት ስለሆነ አዲሱን መልእክት ለመረዳትና ለማለዘብ የተሻለ አጋጣሚ የሚፈጥር መሆኑን ምሁራኑ አክለው ይገልጻሉ።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ትንበያ ተማሪዎች የሚያነቡትን ምንባብ መልዕክት እና ከምንባቡ ጋር የተዛመደውን ቀዳሚ እውቀታቸውን በማጣጣም በምንባቡ ውስጥ የሚካተቱ ነጥቦችን

የሚገምቱበት ትምህርታዊ ልምምድ ነው። አላማውም የተማሪዎችን ትኩረት በማሰባሰብ በምንባቡ ላይ ፍላጎት እንዲያሳድሩ ለማድረግ በመሆኑ የሚከናወነው ከንባብ በፊት ነው። ተማሪዎች የምንባቡን ጠቅላላ መልዕክት ሲገምቱ ለንባብ አላማ እንዲኖራቸው ከማድረግም በተጨማሪ መልዕክቱን በጥንቃቄ እንዲመረምሩ ያስችላቸዋል። የምንባቡን መልዕክት የሚገምቱት ከምንባቡ ርዕስ በመነሳት ስለሆነ የየግል እውቀታቸውን ከምንባቡ መልዕክት ጋር ለማዛመድም ይረዳቸዋል። የምንባቡን መልዕክት በተቻለ መጠን ለመገመት ከሚረዱት የምንባቡ ክፍሎች ዋና ዋናዎቹ የምንባቡ ርዕስ፥ አጋዥ ፍንጮች (ማለትም ስዕሎች፥ ግራፎች፥ ሰንጠረዦች)፥ ጥያቄዎችና ቁልፍ የይዘት ቃላት አገባብን የሚገልጹ ጥቆማዎች ናቸው፤

<u>ርዕስ</u>፡- የምንባቡ ርዕስ አቀራረብ ስለጭብጡ የተወሰነ መጠቆሚያ ሃሳብ ሊያመለክት ይችላል። ከርዕሱ በመነሳት ተማሪዎቹ የተሻለ (በምንባቡ ውስጥ የቀረበውን በትክክል) የምንባብ መልዕክት ግምት እንዲሰነዝሩ መምህሩ ርዕሱን በሰሌዳው ላይ ጽፎ ጥያቄዎችን ማቅረብ ይችላል። በጥያቄዎቹ አማካይነት ተማሪዎቹ በጥንድ፥ በቡድን ወይም በጋራ መልስ በማቅረብ ሊወያዩባቸው ይችላሉ። መምህሩ ውይይቱን ከመምራቱ በፊት ተማሪዎች ያቀረቡትን መልስ በመሰብሰብና አንድ በአንድ ለክፍሉ ተማሪዎች በማቅረብ የሁሉንም ተሳትፎ ማጠናከር ይኖርበታል። ተማሪዎችም በግልም ሆነ በጋራ የመሳተፍ እድል ሲያገኙ በሚቀርብላቸው ትምህርታዊ ክንውን ላይ ፍላጎት ያሳድራሉ። ፍላጎት ካደረባቸው ደግሞ ምንባቡን በትጋት ለማንበብ አስፈላጊውን መነቃቃት (motivation) ያገኛሉ።

<u>ደጋፊ ፍንጮች</u> (**<u>illustrations</u>**)፡- ምንባቡ በስዕሎች፥ በግራፎችና በሰንጠረዦች የሚደገፍ ከሆነ እነዚህን ከርዕሱና ከቀዳሚ እውቀታቸው በማገናዘብ አጠቃላዩን መልዕክት ለመተንበይ ያግዛል። ስለዚህ አጋዥ ፍንጮች ከርዕሱ ማዛመድ የምንባቡን መልዕክት አስመልክቶ የሚሰነዘረውን ግምት የተሻለ ሊያደርገው እንደሚችል Hyland (1995፡40) ይገልጻሉ።

ተማሪዎች አጋዥ ፍንጮችን የሚጠቀሙ ከሆነ መሪ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ተሳትፎአቸውን ማጠናከርና ማበረታታት ይቻላል። ለዚህ ተግባራዊነትም መምህሩ እንደምንባቡ አይነት ተስማሚ ጥያቄዎችን ማሰናዳት ያስፈልገዋል።

<u>የማነቃቂያ ውይይት ማካሄድ</u> (**<u>Warmers</u>**)፡- የምንባቡን ርዕስና ደጋፊ ፍንጮች በጥምረት በመጠቀም የማነቃቂያ ውይይት ማድረግ ተማሪዎችን ንቁ ተሳታፊ ለማድረግ ይረዳል። በማነቃቂያ ውይይቱ የሚነሱት ነጥቦች ከምንባቡ መልዕክት ጋር በቀጥታ የተያያዙ ወይም የተዛመዱ ሊሆኑ ይችላሉ። ውይይቱ በተማሪዎችና በመምህሩ መካከል የትብብር መንፈስ በመፍጠር ተማሪዎችን የሚያነቃቃ ይሆናል።

ቁልፍ ቃላት (Key words):- የምንባቡን ሃሳብ አቀራረብ ግልጽና ጉልህ ለማድረግ ጸሀፊው የሚጠቀምባቸውን ቁልፍ የይዘት ቃላት አገባብ መመርመር ስለምንባቡ ይዘት ምንነት ለመገመት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ የይዘት ቃላቱ አገባብ አውዳዊ በመሆኑ አገባባቸውን ከአጠቃላይ የምንባቡ መልዕክት ጋር በማዛመድ መፍታት መልዕክቱን በተሻለ መንገድ ለመረዳት ያግዛል፡፡ መምህሩ የይዘት ቃላትን መርጦ ከአውዳዊ ፍችያቸው እንዲያዛምዱ ሊያደርግም ይችላል፡፡

በአጠቃላይ፡ የትንበያን ስልት ተግባራዊ ለማድረግ÷

- ስለምንባቡ መልዕክት ጠቋሚ ጥያቄዎች በአጠቃላይ ማቅረብና ተማሪዎችም በግል ወይም በቡድን እንዲገምቱ ማበረታታት፡፡ ከዚህ በኋላ መልዕክቱን ለማረጋገጥ የበለጠ ማንበብ ስላለባቸው የመልዕክቱ ሃሳብ በቅድመ ንባብ ውይይት እንዳይሳሳ የጥያቄዎቹ ቁጥር ከሶስት መብለጥ እንደሌለበት ምሁራኑ ያስረዳሉ፡፡

- ተማሪዎች የመጀመሪያውን አንቀጽ ያነባሉ፡፡ የአንቀጽ መልዕክት ከምንባቡ ርዕስ ይዛመድ እንደሆነም ይመረምራሉ፡፡
- የምንባቡ አንቀጾች የመጀመሪያ አረፍተነገሮች (በአብዛኛው የአንቀጾቹ ሃይለቃሎች ሊሆን ይችላሉ) ካነበቡ በኋላ የመደምደሚያውን አንቀጽ ያነባሉ፡፡ ከዚያም የምንባቡ የሃሳብ አደረጃጀት አንጻር ምን እንደሚመስል÷ ደራሲው መረጃውን እንዴት እንዳቀናበረው እና የሚፈልገውን መረጃ በጽሁፉ ውስጥ ለማብራራት የተጠቀሙበት የአጻጻፍ ቅርጽ ለአላማው ስኬት ያበረከተውን አስተዋጽኦ እንዲመረምሩ ይበረታታሉ፡፡ ከዚህ በኋላ አስቀድመው የገመቷቸው ነጥቦች በምንባቡ ውስጥ መኖር አለመኖራቸውን ለማረጋገጥ ተጨማሪ ማብራሪያ ለማግኘት ምንባቡን በሙሉ ያነባሉ /Nuttall 1996÷ Hyland 1995/፡፡

Hyland (1995) እና Carrell and Eisterhold (1988:87) ከትንበያ ስልት ጋር ተዛምደው ተግባራዊ መሆን ያለባቸውን ተጨማሪ ትምህርታዊ ክንውኖች ይጠቁማሉ፡፡ የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ምንባቡን መቃኘት (Surveying):- የምንባቡን መልዕክትና የምንባቡን አወቃቀር በተቻለ ፍጥነት በመቃኘት የተወሰነ ሃሳብ ለመጨበጥ የሚካሄድ የንባብ ስልት ነው፡፡ ይህ የንባብ ስልት እንደየምንባቡ አይነት አጠቃቀሙ ቢለያይም ዋና ትኩረቱ አንባቢው ዳራዊ እውቀቱን በመጠቀም አስፈላጊ የሆኑ "ኤክስትራ ቴክስት" (extra text) ቁም ነገሮችን በምንባቡ ውስጥ መኖር አለመኖር ማረጋገጥ ነው፡፡ የሚፈለገውን መልዕክት ለመጨበጥም ተማሪዎቹ ደጋፊ ፍንጮችን እና የምንባቡን የአጻጻፍ ቅርጽ (typographical data) ማለትም በምንባቡ ውስጥ የተሰመረባቸው አጽንኦት አመልካች ክፍሎች እና ተዛማጅ የሆኑ ፍንጮች ላይ ማተኮር አለባቸው፡፡

ከትምህርታዊ ልምምድ አተገባበር አኳያ የሚከተሉትን ዘዴዎች በተናጠል ወይም በጥምረት መጠቀም እንደሚቻል Hyland (1995፡104) ይገልጻሉ፤

- ከምንባቡ ርዕስና አጋዥ ፍንጮች በመነሳት ተማሪዎች ምንባቡን ከቃኙ በኋላ ስለአጠቃላይ መልዕክት ምንነት አስቀድመው እንዲገምቱ ጥያቄዎችን መጠየቅ፥
- የምንባቡን አጠቃላይ መልዕክት ከአህጽሮት ጽሁፉ ወይም አጋዥ ማብራሪያዎች እንዲያዛምዱ ጥያቄዎችን መጠየቅ፥
- በምንባቡ ርዕስ አማካይነት በማነቃቂያ ውይይት ጊዜ ለተነሱት ጥያቄዎች ተገቢ መልስ የያዘውን አንቀጽ አስቀድመው እንዲለዩ ማበረታታት
- የምንባቡን መልዕክት በመገመትና ይህንኑ በመነሻነት በመጠቀም መልዕክቱን በይበልጥ የሚያብራራው የምንባቡ አንቀጽ የትኛው እንደሆነ በንባብ እንዲያረጋግጡ መጠየቅ፥
- በክፍል ውስጥ ለልምምድ ከቀረበው ምንባብ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ነጥቦችን አንስቶ በጋራ ውይይት ማድረግ::

<u>የአሰሳ ንባብ (**Skimming**)</u>፡- Hyland እንደሚያብራሩት ምንባቡን መቃኘት የአንባቢውን ዳራዊ እውቀት መሰረት ያደረገ የንባብ ስልት ሲሆን የአሰሳ ንባብ ደግሞ በአብዛኛው ምንባቡን የሚንተራስ ክንውን ነው:: ዋና አላማውም ምንባቡን በፍጥነት በመቃኘት አጠቃላይ መልዕክቱን ለመገመት ነው:: በተጨማሪም ምንባቡን በድጋሚ ለማንበብ ወይም ምንባቡን በጥሞና ለመመርመር የሚያስፈልግ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን የሚረዳ ስልት ነው::

በርካታ ምሁራን (Hyland 1995፥ Aebersold and Field 1997፤ Sequero 1998) እንደሚሉት፥ የአሰሳ ንባብ የትኛው የምንባቡ ክፍል (አንቀጽ) ተፈላጊውን መረጃ እንደያዘ ለመለየትና ይህንኑ በጥንቃቄ አንብቦ ቀዳሚውን ግምት ለማረጋገጥ፥ ይረዳል:: ስለሆነም የምንባቡን አወቃቀር የሚመለከት እውቀት ያስፈልጋቸዋል:: በተለይም ተማሪዎች በርዕሱ ዙሪያ ካላቸው እውቀት በመነሳት ስለአቀራረቡ፥ ስለማብራሪያው፥ ስለንኡሳን አርዕስቶቹ (ካለው) የተወሰነ ግምት ሊኖራቸው ይገባል::

ተማሪዎቹ ስለምንባቡ አወቃቀር ማወቅ አለባቸው ሲባልም የመጀመሪያው አንቀጽና የመደምደሚያው አንቀጽ ጠቃሚ የሆነ ዳራዊ መረጃ የሚሰጡ፥ የምንባቡን መልዕክት አሳጥረው የሚያቀርቡ፥ ማጠቃለያ የሚሰጡ መሆናቸውን፥ እያንዳንዱ አንቀጽም የራሱ የሆነ ሃይለቃል ያለው መሆኑን፥ እና የተጠቀሱትን ነጥቦች እንዴት መከታተል እንዳለባቸው ማወቅ ይኖርባቸዋል ለማለት ነው:: በልምምድ ሂደትም ተማሪዎች እነዚህን ለመለየት ከቻሉ የየአንቀጾቹን መሰረታዊ ተግባራት ለመመርመርና በዋና ጭብጡና በደጋፊዎቹ መካከል ያለውን ትስስር ለመረዳት ይችላሉ:: በዚህም ትስስሩ የተገለጸባቸውን ሰዋሰዋዊ ፍንጮችና ቃላዊ አጠቃቀሞች አጥጋቢ በሆነ መንገድ ለመጠቀም ይችላሉ /Hyland 1995፥ Aebersold and Field 1997/::

የአሰሳ ንባብ ስልትን ተግባራዊ ለማድረግ Nuttall (1996) እና Hyland (1995) እንደሚሉት የሚከተሉትን ትምህርታዊ ክንውኖች መጠቀም ይቻላል፤

- በአንቀጾቹ ውስጥ ተገቢ ቦታቸው የተዛባ የመግቢያ አረፍተ ነገሮችን በትክክለኛ ቦታቸው እንዲያስገቡ ተማሪዎችን መጠየቅ:: ይህ የመልመጃ አይነት ተማሪዎቹ የአንቀጽ አገነባብን፥ የአንቀጽ ሃይለቃልን መገኛ ስፍራና የአንቀጹን ውስጣዊ ግጥምጥምነት ለመረዳት ያስችላቸዋል::
- ቅደም ተከተላቸው የተዘበራረቁ አንቀጾችን አስተካክሎ ማስቀመጥና ለዚህም ማብራሪያ በመስጠት ስለምንባቡ አወቃቀር ያላቸውን እውቀት ሊያዳብሩት ይችላሉ::
- በአንድ ርዕስ ጉዳይ ዙሪያ የቀረቡ የተለያዩ ምንባቦችን በማቅረብ ተማሪዎች አንድ ርዕሰ ጉዳይ በተለያዩ ጸሀፍት በተለያዩ መንገድ ሊብራራ እንደሚችልና የትኛው የርዕሱ ክፍል በይበልጥ እንደተብራራ እንዲያመለክቱ መጠየቅ፥
- ረዘም ያለ ምንባብ ማቅረብና ተማሪዎች አስቀድመው የገመቷቸውን የተወሰኑ ነጥቦች መኖር ለማረጋገጥ እንዲችሉ በነዚሁ ላይ አትኩረው እንዲያነቡ በማድረግ የአሰሳ ንባብ ስልትን ማለማመድ ይቻላል::

<u>የገረፍታ ንባብ (Scanning)</u>:- ከምንባቡ ውስጥ የተወሰነ ሃሳብ ለመፈለግ (ለምሳሌ፥ አመተ ምህረትና ሌሎች አሀዝ ነክ መረጃዎችን) የሚካሄድ ፈጣን የንባብ ስልት ነው:: በትኩረቱም በሚፈለገው ነጥብ ላይ ብቻ በመወሰን የምንባቡን መልዕክት መገመት ነው:: በዚህም ተማሪዎች ዝርዝር ነገሮችን በመተው ተፈላጊውን ሀሳብ ይመረምራሉ:: የገረፍታ ንባብን ስልት ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተሉትን ዘዴዎች መጠቀም እንደሚቻል Hyland (1995፡104) ይገልጻሉ::

- ተማሪዎች አስፈላጊ የሆኑ ቃላት፥ ስሞች፥ ቀናት፥ በምንባቡ ውስጥ የሚገኙበትን ስፍራ እንዲጠቁሙ መጠየቅና ከምንባቡ ሃሳብ ጋር ማዛመድ፥
- ተማሪዎች በምንባቡ ውስጥ የገቡትን አያያዥ ቃላት፥ ሀረጋት እና አባባሎች ለይተው እንዲያመለክቱ መጠየቅ::
- ተማሪዎች አስፈላጊ የሆኑ ቃላትን፥ ስሞችንና ቀናትን በመለየት አንድምታዊ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ መጠየቅ::

ከፍ ሲል የተዘረዘሩት ትምህርታዊ ተግባራት አላማ ተማሪዎች ስለሚያነቧቸው ምንባቦች መልዕክት ምንነት አስቀድመው እንዲገምቱ ማበረታታት ነው:: እንደ ምንባቡ አይነት በተናጠል ወይም በጥምረት ሊሰራባቸው ይችላል:: በተጨማሪም አንዱ በሌላው ሊካተት ስለሚችል በመካከላቸው የነጠረ ልዩነት ለማስቀመጥ አዳጋች ነው::

2. <u>የአንድምታ ንባብ (inferencing)</u>:- እንደ ትንበያ ሁሉ በባህርይው የተለያዩ ንኡሳን ክሂሎችን ለማቀናጀት እንደሚያስችል የምሁራኑ ገለጻ ይጠቁማል:: አንብቦ ለመረዳት ችሎታ መዳበርም ቁልፍ ድርሻ አለው:: ለምሳሌ Chickalanga (1993፡931) የስነልቡናዊ ስነልሳን ተመራማሪዎችን

አስተያየት በመጥቀስ እንደሚያመለክቱት፥ የአንድምታ ንባብ ከማንኛውም የንባብ ክንውን አይነቶች ጋር የተያያዘ ነው። የምንባቡን መልእክት ለመተርጎም፥ ቃሎችን ከአውዳቸው ለመረዳት፥ ሳይገለጽ በውስጠ ታዋቂነት የተቀመጠን መረጃ ግልጽ ለማድረግ ያስችላል።

የአንድምታ ንባብ ለትምህርት በሚቀርበው ምንባብ ውስጥ የተካተቱትን ከበድ ያለ ጽንሰ ሃሳብ የያዙ ቃሎችና ሀረጎች ከአገባባቸው በመመልከት ወይም አገባባዊ (syntactic)፥ ተጠየቃዊ (logical) እና ባህላዊ (cultural) ጉዳዮችን የሚገልጹ አባባሎችን በፍንጭነት በመጠቀም ፍችያቸውን ብሎም በቅንጅት የሚያስገኙትን መልእክት ለመረዳት የሚያስችል የንባብ ስልት ነው (Grellet 1981)። ስለዚህ ለትምህርት በሚመረጠው ምንባብ ውስጥ በቂ አውዳዊ ፍንጭ ቢካተት የተሻለ እንደሚሆን ምሁራኑ ያሳስባሉ።

በአጠቃላይ፥ አንድምታዊ የንባብ ስልት ለተማሪዎች አስፈላጊ የሚሆነው ደራሲው ሁሉንም ነገር በግልጽ ስለማያስቀምጥ ያልተገለጸውን መርምሮ ለመረዳት ነው። ደራሲው በሚጽፍበት ጊዜ ሁሉንም ነገር በግልጽ ስለማያስቀምጥ Nuttall (1982) ተማሪዎችና ደራሲው በሚጋሩት የጋራ ገጠመኝ መነሻነት ሳይነገር፥ ሳይገለጽና ሳይብራራ በውስጠ ታዋቂነት የቀረበውን ስውር መልእክት በጥልቀት በማንበብ (reading between the lines) Lewin (1984) መረዳት ስለሚያስፈልጋቸው ነው። ይህም ተማሪዎች በምንባቡ ግልጽ መልእክት እንዳይወሰኑ፥ የምንባቡን መልእክት ብቃትና ተአማኒነት ለማመዛዘን ጥረት ለማድረግ ያስችላቸዋል (Lunzar & Gardner 1979:39)።

ከትምህርታዊ ትግበራ አንጻር የአንድምታ የንባብ ስልት የሚከናወነው በተለያዩ ጥያቄዎች አማካይነት ነው። አንድምታዊ የንባብ ስልትን በመልመጃ ጥያቄዎች አማካይነት ገቢራዊ ለማድረግ ሶስት አይነት ጥያቄዎችን መጠቀም እንደሚቻል Carrell, Liberto & Pharis (1989:660)፥ Williams (1984:59) እና Chicalanga (1993:931) ያስረዳሉ። እነዚህም፦

ሀ. ውሱን መረጃን የሚመለከቱ የአንድምታ ጥያቄዎች፦ ተማሪዎች ምንባቡን ካነበቡ በኋላ በግንዛቤያቸው መሰረት ተፈላጊውን መረጃ አብራርተው በቃል ወይም በጽሁፍ እንዲያቀርቡ የሚረዱ ጥያቄዎች ናቸው። የሚፈለገው መልስ ከምንባቡ የተለያዩ አንቀጾች ውስጥ በቀጥታ የሚገኝ ሊሆን ይችላል።

ለ. የቀጥተኛ አንድምታዊ ጥያቄዎች (Direct inference Questions)፦ ምንባቡን ካነበቡ በኋላ በምንባቡ ውስጥ በቀረበው መልዕክት አማካይነት ተጠየቃዊ ተቀባይነት ያለው ትንታኔ እንዲሰጡና መደምደሚያ እንዲያቀርቡ የሚጠይቁ ጥያቄዎች ናቸው። የምንባቡን መልዕክት አመዛዝነውና ገምግመው እንዲቀበሉ ወይም እንዲያሻሽሉ፥ ጥያቄዎችን እንዲያቀርቡ ማድረግ የነዚህ ጥያቄዎች ትኩረት ነው።

ሐ. ቀጥተኛ ያልሆኑ የአንድምታ ጥያቄዎች /Indirect inference Questions)፡- በ"ለ" ስር ከተጠቀሱት የአንድምታ ጥያቄዎች የሚለያቸው በምንባቡ አማካይነት ተጠየቃዊ ተቀባይነት ያለው ግምገማና መደምደሚያ ላይ አለማተኮራቸው ነው:: እነዚህ ጥያቄዎች በምንባቡ የቀረበውን ርዕስ የሚመለከት ጻራዊ እውቀትን በመጠቀም ስጥው (given) የሆነውን መረጃ ከተለያዩ አቅጣጫዎች መመርመርን የሚጠይቁ ናቸው:: እነ Carrell እንደገለጹት በምንባብ ውስጥ አሉታዊና አዎንታዊ የሆኑ አስተያየቶች ቢኖሩ ለምን በአሉታ ወይም በአዎንታ መልክ እንደቀረቡ ከአውዳቸውና ከቀዳሚ እውቀታቸው በማገናዘብ ምክንያታዊ ማብራሪያ ለማቅረብ የሚያግዙ ናቸው::

በአጠቃላይ÷ Williams (1984)÷ Carrell, Liberto and Pharis (1989) እና Chicalanga (1993) እንደሚያስገነዝቡት እነዚህን ሶስት የጥያቄ አይነቶች በቅንጅት ወይም በተናጠል በሚዘጋጁት የመልመጃ ጥያቄዎች ውስጥ ማካተት ያስፈልጋል::

3. <u>ንባብን ከቀዳሚ እውቀት ማገናዘብ (use of background knowledge)</u>፡- ንባብ የራስን ቀዳሚ እውቀት ከምንባቡ ጋር ለማገናዘብ መሞከርንም የሚጠይቅ ክንውን መሆኑ በ2.2. ስር በዝርዝር ተገልጾአል:: በመሆኑም ተማሪዎች ይህንን መስረተ ሃሳብ ተረድተው በሚያነቡት ምንባብ ውስጥ የቀረበውን መልእክት ከግል ገጠመኛቸውና ከቀዳሚ እውቀታቸው ጋር አስማምተው ለመረዳት እንዲችሉ የክፍል ትምህርቱ አቀራረብ ወደዚህ ግብ የሚያደርሱ ጥያቄዎች ወይም ልዩ ልዩ ተግባራት ላይ መመርኮዝ አለበት (Grellet 1981፡7÷ Johnston 1988፡25-26÷ Carrell 1988b፡243-252)::

**የአንባቢው ጻራዊ እውቀት ሁለት ክፍሎች እንደሚኖሩት በርካታ ምሁራን** (Carrell & Eisterhold 1988÷ Williams 1984÷ Carrell 1987÷ Wallace 1992÷ Silberstein 1994÷ Aebersold abd Field 1997) **ያመለክታሉ:: እነዚህም ድርስት-ተኮር እውቀት** (formal schemata) **እና ይዘት-ተኮር** (Content schemata) **በመባል ይታወቃሉ::**

**ሀ.** **<u>ይዘት-ተኮር ጻራዊ እውቀት</u>**፡- አንባቢው ከምንባቡ ርዕስ ጋር በተዛመደ መንገድ ያለውን ቀዳሚ እውቀት የሚያመለክት ነው:: የምርምር ውጤቶች እንደሚያመለክቱት የአንባቢው እውቀት ከምንባቡ ይዘት ጋር የሚጣጣም ከሆነ የምንባቡን መልዕክት በቀላሉ ሊረዳ ይችላል /Carrell 1987፡461÷ Williams 1984፡6/:: በይዘት ተኮር ጻራዊ እውቀት ስር የሚከተሉት ሁለት ተዛማጅ ነጥቦች ሊጠቀሱ እንደሚችሉ Williams ያመለክታሉ:: እነዚህም፡-

- **ዳራዊ እውቀትን በመጠቀም የምንባቡን የመልዕክት የመተርጎም ችሎታ፡-** ይህ እውቀት የሚያመለክተው አንባቢው የምንባቡን ግልጽ መልዕክት ተረድቶ በምንባቡ አንቀጾች መካከል ያለውን ትስስር ለመመርመር የሚኖረውን ችሎታ ነው፡፡ ስለዚህ አንባቢው አረፍተ ነገሮችንና ቃላትን በተናጠል ለመተርጎም ከመሞከር ይልቅ የጽሁፉን አላማ፥ የጽሁፉን አደረጃጀት እና በአደረጃጀቱና በአላማው መካከል የሚኖረውን ትስስር ለማገናዘብ መሞከር አለበት፡፡ በዚህም የጸሀፊውን የመልዕክት አቀራረብ ለመከተል ይችላል፡፡
- **ስለአለም ያለውን ግንዛቤ ከምንባቡ ጋር የማዛመድ ችሎታ፡-** ይህ ችሎታ አንባቢው የሚመርጠውን ወይም ተመርጦ የሚቀርብለትን ምንባብ መልእክት ከራሱ እውቀት ጋር አዛምዶ ለመተርጎም ያለውን ችሎታ የሚያመለክት ነው፡፡ ግላዊ እውቀቱ የምንባቡን ርዕስ፥ የጽሁፍ አይነቱን (genre) ወይም አጠቃላይ ዳራዊ እውቀቱን በማስታወስና ከምንባቡ በማዛመድ የምንባቡን መልዕክት ረብ ለማመዛዘን የሚረዳው ይሆናል፡፡

ለ. <u>ድርሰት ተኮር እውቀት</u>፡- ድርሰት ተኮር እውቀት የተለያዩ ምንባቦችን የቋንቋ አጠቃቀምና አወቃቀር ስርአት፥ እና የሃሳብ አደረጃጀታቸውን የሚያመለክት ነው፡፡ አንባቢው ከሚያውቀው የድርሰት (ምንባብ) አቀራረብ ስልት ጋር ተቀራራቢነት ያለው ምንባብ ከቀረበለት ወይም የማነቃቂያ ውይይት ከተከታተለ የምንባቡን መልዕክት በቀላሉ ሊመረምርና ሊረዳ ይችላል፡፡ /Ulijin and Strother 1990:35፥ Silberstein 1994:8፥ Carrell 1987:461/፡፡

ስለዚህ Steffenson and Joag-Dev (1984:54) Anderson, Reynolds, Goetz & Schallert (1977)ን ጠቅሰው እንደሚያስረዱት በመማር ማስተማሩ ሂደት ዳራዊ እውቀት የሚከተሉት ሶስት መሰረታዊ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ እነዚህም፡-

- ተማሪዎች የሚያነቡትን ምንባብ በተሟላ መንገድ ለመተርጎም ይረዳቸዋል፡፡ ምክንያቱም ምሁራን እንደሚገልጹት ማንኛውም ጽሁፍ በራሱ የተሟላ ሳይሆን ለትርጓሜ መነሻ ፍንጭ ነው የሚሰጠው፡፡ ስለዚህ ምንባቡን በተጣጣመና በተሻለ መንገድ ለመተርጎም መልዕክቱ ከአንባቢው ዳራዊ እውቀት መዛመድ ይኖርበታል፡፡
- ተማሪዎች ግልጽ ያልሆኑላቸውንና አሻሚ መልዕክት ሲያጋጥማቸው በጥሞና ለማንበብና ለመተርጎም እንዲሞክሩ ይረዳቸዋል፡፡ ተማሪዎቹ አስቀድመው የሚገምቱት የምንባብ መልዕክት ከምንባቡ መልዕክት ለየት ያለ ከሆነ የሚያጠራጥረውን ክፍል በመለየት ከእውቀታቸው ለማዛመድ ፍንጭ ያገኙበታል፡፡ በሌላ አገላለጽ የምንባቡ መልዕክት ከተማሪዎቹ የቅድሚያ ግምት ካልተጣጣመ የምንባቡን መልዕክት አመዛዝነው በመቀበል መልዕክቱ በተለያየ መንገድ የሚመረመር መሆኑን ሊማሩበት ይችላሉ፡፡
- በሚታወቀው ነገር ማለትም በተማሪዎቹ ቀዳሚ እውቀትና በምንባቡ ውስጥ ስጥው በሆነው መልዕክት መካከል ትስስር በመፍጠር ተማሪዎች የሚፈልጉትን መረጃ መረዳት አለመረዳታቸውን እንዲያረጋግጡ ጠቃሚ ፍንጭ ያገኙበታል፡፡

ስለዚህ Anderson (1994:178) በርካታ ጥናቶችን በመዳሰስ እንደሚያብራሩት ተማሪዎች ዳራዊ እውቀታቸውን እንዲጠቀሙ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋቸዋል:: ይህንን ዝግጅት ለማድረግም የተለያዩ ቅድመ ንባብ ስልቶችን በቅንጅት መጠቀም ያስፈልጋል:: Anderson Mc-NEIL (1987:49)ን በመጥቀስ ስለተማሪዎች ዳራዊ እውቀት ዝግጅት ሲገልጹ "ለተማሪዎች ግልጽ የንባብ አላማ በማመልከትና ግባቸውን እንዲወስኑ ለማድረግ ጥያቄዎችን መጠየቅና ስለይዘቱ እንዲገምቱ በማበረታታት ዳራዊ እውቀታቸውን ለስራ ዝግጁ ለማድረግ ይቻላል" ይላሉ::

Carrell (1988b:245)፥ Wallace (1992:86-102) እና Anderson (1994:179) የተለያዩ የክፍል ክንውን ተግባራትን በመጠቀም ተማሪዎችን ማነቃቃት እንደሚቻል ይጠቁማሉ:: እነሱም:-

ሀ. <u>ቅድመ ንባብ ውይይት</u>:- ቅድመ ንባብ ውይይት በትምህርቱ የሚሳተፉት ተማሪዎች ርዕሱን አስመልክቶ በግል የሚያውቁትን ለማወቅና ሌሎችም ያላቸውን ሃሳብ ለመረዳት እያንዳንዱ ተማሪ የሚያውቀውን ለመናገርና ሌሎችንም ለመስማት ብሎም ለመማማር አመቺ አውድን ለመፍጠር ይረዳል፤ ስለሆነም መምህሩ በምንባቡ ርዕስ ዙሪያ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ተማሪዎችን ማነቃቃት ይጠበቅበታል::

ለ. <u>የምንባቡን አደረጃጀት የሚመለከት መጠነኛ ውይይት ማካሄድ</u>:- የምንባቡን አደረጃጀት አስመልክቶ የሚካሄደው ትምህርታዊ ውይይት ተማሪዎቹ መልዕክቱ ምን ሊሆን እንደሚችልና ይኸው መልዕክት እንዴት እንደተብራራ ለመመርመር የሚያስችላቸው ነው:: ውይይቱ የአያያዥ ቃላትን አገባብ፥ የመሸጋገሪያ አባባሎችን አጠቃቀም የሚገልጽ ሊሆን ይችላል:: ስለዚህም Anderson (1994:179) እንደሚሉት ስለምንባቡ ድርስታዊ አደረጃጀት ውይይት ማካሄድ የተማሪዎቹን ዳራዊ እውቀት በማዘጋጀት ትኩረታቸውን ለመሳብና በንቃት ለማሳተፍ ከመርዳቱም በተጨማሪ ለአንብቦ መረዳት ችሎታቸው መዳበር አዎንታዊ ድርሻ ይኖረዋል::

ሐ. ተማሪዎች ስለርዕሱና ርዕሱ የቀረበበትን የምንባብ አደረጃጀት አስመልክቶ ከተካሄዱት ውይይቶች የገመቱትን መልዕክት በንባብ ለማረጋገጥ ወይም ግምታቸው ስህተት ከሆነ ለማረም እንዲያነቡና ተገቢ መቀስቀስ እንዲኖራቸው ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፤ ተማሪዎችም ከምንባቡ ውስጥ ሊመለስ የሚችል ጥያቄ መጠየቅና ከምንባቡ ማዛመድ እንዲችሉ ማበረታታት ይገባል:: መቀስቀሱ በተራው የንባብ አላማ እንዲኖራቸውና ይህንኑ አላማ ከግብ ለማድረስ እንዲያነቡ ይገፋፋቸዋል:: ስለዚህ ይህ ትምህርታዊ ክንውን ከተከታታይ ትምህርታዊ እርከኖች ጋር የተሳሰረ መሆን አለበት:: በተለይም ተማሪዎች ከንባብ በፊት ስለመልዕክቱ የገመቱት ግምት በምንባብ የሚጠናከር መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ከሚያደርጉት ጥረት ቢዛመድ የተሻለ እንደሚሆን የመስኩ ምሁራን ይገልጻሉ:: በእነዚህ ክንውኖች አማካይነትም ተማሪዎች እውቀታቸውን ከምንባቡ መልዕክት ለማዛመድና የገባቸውንም ሆነ ግልጽ ያልሆነላቸውን ነጥብ ለመለየት ይችላሉ::

ተማሪዎቹ ከሚያነቡት ምንባብ ውስጥ የገባቸውንና ግልጽ ያልሆነላቸውን ነጥብ ከለዩ ደግሞ ጥሩ አንባቢዎች ለመሆን የሚረዳቸውን ችሎታ ለማዳበር እንደሚችሉ Anderson (1994፡182) ያስረዳሉ::

### 2.2.2. የተካሄዱት ቀደምት ደጋፊ ምርምሮች

በክፍል 2.2.1 ስር እንደተመለከተው የ'ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በተለያየ የቋንቋ አውድና የትምህርት ደረጃ የሚማሩትን ተማሪዎች በጥናት በማሳተፍ የተጠናከረ የማስተማሪያ ሞዴል ነው:: ጥናቶቹ እንደተካሄዱበት አውድና በስራ ላይ እንዳዋሉት የማስተማሪያ መሳሪያዎችና ማስተማሪያ ስልቶች የተለያዩና ተቀራራቢ ውጤቶችን አስገኝተዋል:: ከጥናቶቹ መካከል ብዙዎቹ ንድፈ ሃሳባዊ የነበሩትን ትምህርታዊ መርሆዎች በክፍል ውስጥ የተገበሩ በመሆናቸው ዋናዋናዎቹን ጥናቶች ቀጥለን እንቃኛቸዋለን::

#### 2.2.2.1. በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተካሄዱት ምርምሮች

የ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴልን ተግባራዊነት በአፍ መፍቻ ቋንቋ የንባብ ትምህርት አውድ የሞከሩት Billmiller(1970)÷ Clay(1968/72)÷ Goodman (1970÷1973÷1975)÷ Weber (1970)÷ Bever (1970) መሆናቸውን Cziko (1980)÷ Cambourne (1981)÷ Swaffar (1988) እና Roller & Matambo (1992) ያመለክታሉ:: እነዚህ አጥኚዎች በጥናቶቻቸው ለማረጋገጥ የሞከሩትና የጥናታቸው አላማ

- ተጠኚዎች በሚያነቡበት ጊዜ በትርጉም-አዘል አሀዶች ደረጃ የሚያነቡ መሆናቸውን (ቃል በቃል የማያነቡ መሆናቸውን)
- ዳራዊ እውቀታቸውን ከምንባቡ መልዕክት ለማዛመድ መሞከራቸውን
- አንድምታዊ አቀራረብ ያላቸውን ነጥቦች መመርመራቸውን
- አዳዲስና የይዘት ቃላትን ከአገባባቸው ለመፍታትና ከአጠቃላይ መልዕክት ጋር ለማዛመድ የሚሞክሩ መሆናቸውን ለመመርመር ነበር::

Cziko እንደሚያብራሩት የቃኙዋቸው የምርምር ስራዎች የተካሄዱት የዳበረ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ባላቸውና ጀማሪ እንግሊዝኛ አፍፈት ተናጋሪዎች ላይ ነው:: የጥናቶቹ ውጤቶች እንዳመለከቱት ተጠኚዎቹ ተማሪዎች የሚቀርብላቸውን ምንባብ መልእክት ለመረዳትና ለመተርጎም በሚያነቡበት ወቅት እያንዳንዱን ቃልና ሀረግ በተናጠል አያነቡም፤ ቃሎችንም ሆነ ሀረጎችን በተናጠል ከማንበብ ይልቅ አጣምረው (chunk) ትርጉም-አዘል በሆኑ ሀረጎች እና አረፍተነገሮች ትስስር ደረጃ ነው የሚያነቡት:: ትኩረታቸውም የምንባቡን አጠቃላይ መልእክትና ሃሳብ ለመመርመር ነው:: ንባባቸውን ለማፋጠንም ስነፍችያዊ÷ ድርስታዊና አውዳዊ ፍንጮችን ከዳራዊ እውቀታቸው ጋር አጣጥመው ያነባሉ::

Hedge (1985:32) በተመሳሳይ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተካሄዱ የጥናት ውጤቶችን ቃኝተው የዳበረ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች ስለምንባቡ አጠቃላይ መልእክት በመገመትና አስቀድመው በመተንበይ ስለሚያነቡ ከምንባቡ ውስጥ የተወሰኑ ቃሎችና ፊደሎች ቢጎደሉ እንኳን መልእክቱን ለመረዳት እንደማያዳግታቸው ያስረዳሉ:: በጥናታቸው እንደተመለከተውም ተማሪዎቹ ብዙውን ጊዜ በነዚህ ማለትም በቃሎች እና ሀረጎች ላይ በተናጠል አያተኩሩም:: የንባብ ጥረታቸው የማይደናቀፈውም ዳራዊ እውቀታቸውን እና የቋንቋ አጠቃቀም ችሎታቸውን በማቀናጀት የቀረበው ምንባብ መልእክት ምን ምን ሊያካትት እንደሚችል አስቀድመው ስለሚገምቱና ትኩረታቸውንም ወስነው ስለሚያነቡ ነው:: ስለዚህ መላ ትኩረታቸውን የሚያነጣጥሩት ተናጠላዊ የቃሎች ፍችን ለመመርመር ሳይሆን የሚያገኙትን ፍንጭ ሁሉ በመጠቀም የምንባቡን ጠቅላላ መልእክት ለመረዳት ነው::

Cowan (1976:96) የBeverን ጥናቶች ጠቅሰው እንደሚያመለክቱት "የቶፕዳውን" ሞዴል ለንባብ ትምህርት አቀራረብ የተሻለ አስተዋጽኦ ይኖረዋል:: Bever (1970) በCowan እንደተጠቀሰው በእንግሊዝኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ ጠንከር ያለ መልእክት ሲያጋጥማቸው በምንባብ ደረጃ በሚገኙ ፍንጮች ላይ በማተኮር አጠቃላዩን መልእክት ይተነብያሉ፤ ስለመልእክቱም የተወሰነ ግምት ይዘው በማንበብ አስቀድመው የገመቱትን ያጣራሉ:: እያነበቡ እያለም ከደረሱበት ክፍል ቀጥሎ የሚመጣውን ሃሳብ በመገመት ከቀዳሚው ጋር ለማዛመድ ይሞክራሉ:: እስከ ምንባቡ መጨረሻ ድረስ ተራ በተራ ግምታቸውን እያረጋገጡ÷ ጥርጣሬያቸውን እያስወገዱ የቀረበውን ምንባብ መልእክት የሚመረምሩ መሆናቸውን አጥኚው በጥናታቸው ውጤት ያብራራሉ::

ይህ የCowan አስተያየት በCarrell & Floyd (1987:90) የጥናት ውጤትም የተደገፈ ነው:: Carrell & Floyd እንደሚሉት በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተካሄዱት ተዛማጅ ምርምሮች ተማሪዎቹ ቀዳሚ ርእስ ተኮር እውቀት ካላቸው የምንባቡ የቋንቋ አጠቃቀምና አቀራረብ ጠጣር ቢሆንም የምንባቡን መልእክት ለመረዳት አያዳግታቸውም:: ምክንያቱም የምንባቡን መልእክት ለመረዳትና ምንነቱን አስቀድመው ለመገመት እንዲችሉ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው የምንባቡ የቋንቋ አጠቃቀም ቀላል ወይም ከባድ መሆን አይደለም:: ይልቁንም ተማሪዎቹ ይህንን ምንባብ አንብበው ለመረዳት እንዲችሉ አጋዥ የሆነው ተዛማጅ እውቀታቸው መኖር ወይም አለመኖር ነው:: ተማሪዎቹ እውቀቱ ካላቸው የምንባቡን መልእክት ከገጠመኛቸው ጋር አያይዘው ለመረዳት ይችላሉ:: ይህ እውቀታቸው ቀዳሚውን ለማስታወስ÷ ቀጣዩን ለመገመትና ሁለቱን ለማዛመድ ይረዳቸዋልና::

Cowan በጥናታቸው ማጠቃለያ እንደሚገልጹት÷ ተማሪዎቹ ዳራዊ እውቀታቸውን ተጠቅመው በሚያነቡበት ወቅት ስለምንባቡ መልእክት አስቀድመው የገመቱትን በንባብ ሂደት ካልደረሱበት ወደ ሁዋላ ተመልሰው በማንበብ ያለፈውንና ቀጣዩን ያዛምዳሉ:: ቀዳሚ ግምታቸው

ስህተት ከሆነ የስህተቱን መነሻ ለማረጋገጥ ምንባቡን በድጋሚ ይቃኛሉ:: ምንባቡን በድጋሚ የሚቃኙትም ደራሲው የተጠቀመባቸው የተለያዩ ፍንጭ-ሰጭ ክፍሎች መልእክቱን ለመግለጽ የዋሉበትን መንገድ ለመለየትና የመጀመሪያውን ግምት በመለወጥ ወይም በማሻሻል ትክክለኛውን መልእክት ለመረዳት የተሻለ የንባብ ስልት ለመጠቀም እንዲችሉ ነው:: /Weaver 1990:201/::

Roller & Matamboም (1992:129) በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተካሄዱ የሞዴሉን ደጋፊ የጥናትና ምርምር ውጤቶች አጠቃለው ሲገመግሙ "በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተካሄዱት በርካታ ጥናቶች ተማሪዎች ዳራዊ እውቀታቸውን በመጠቀም እስኪማ-ተኮር የሆነውን የ"ቶፕዳውን" የንባብ ስልቶች ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ማረጋገጣቸውን" ይጠቀማሉ:: እስኪማ-ተኮር የንባብ ስልቶች ሲሉም ተማሪዎች ከሚያነቡት ጽሁፍ ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ ያላቸውን ተዛማጅ እውቀት ከምንባቡ መልእክት በማጣጣም ይተረጉማሉ፤ ቃሎችን በተናጠል ከማንበብና ከመጥራት ለመልእክት ልዩ ትኩረት የሚሰጡ፥ መሆናቸውን ለማመልከት እንደሆነ ያስረዳሉ::

## 2.2.2.2. በሁለተኛ ቋንቋ ዘርፍ የተካሄዱ ምርምሮች

በአፍ መፍቻ ቋንቋ የንባብ ትምህርት መስክ የተካሄዱት ጥናቶች የሁለተኛ/የውጭ ቋንቋ የምርምር ዘርፍም አዲስ የጥናት አቅጣጫ እንዲይዝ አድርገዋል (Carrell 1988a:2):: ብዙዎቹ የመስኩ ተመራማሪዎች በወቅቱ ማለትም ከ1960ዎቹ የመጨረሻ አመታት በፊት ለነበረው የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ (ክሂል ተኮር የነበረው) አማራጭ ለመፈለግና በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተገኙትን የጥናት ውጤቶች በሁለተኛ/ውጭ ቋንቋ ለመድገም (replicate) ብሎም ተመሳሳይ ውጤት ለማግኘት አቅደው ምርምሮችን አካሄደዋል:: የተመራማሪዎቹ ጥረት ስራ ተቀባይነት ያገኘውን የ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል ውጤታማነት በመፈተሽ በዘርፉ ይታይ የነበረውን ችግር ለመቅረፍ የታለመ እንደነበረ Carrell ያስረዳሉ::

በሁለተኛ ቋንቋ አውድ በሞዴሉ መርሆዎች መሰረት የማስተማሪያ መልመጃዎችን በማዘጋጀት ውጤታማነቱን ከፈተሹት በርካታ ምሁራን መካከል ዋነኛው የClarke and Silberstein (1977) ጥናት ነው:: Clarke and Silberstein እንደሚያስረዱት በንባብ ትምህርት ሂደት በጸጥታ በማንበብ ተፈላጊውን መረጃ መረዳት ያለባቸው ተማሪዎች በመሆናቸው አብዛኛውን ስራ ማከናወን ይገባቸዋል:: ይህም ማለት በልምምድ ሂደት ተማሪዎቹ ዋነኛ ተዋንያን መሆን እንዳለባቸው ለማመልከት ነው::

ከሚነበበው ምንባብ ውስጥ ተፈላጊውን መረጃ ለማግኘት ደግሞ ተማሪዎች እያንዳንዱን ቃል ለመተርጎም ከመሞከር ይልቅ እውቀታቸውን በመጠቀም አጠቃላይ መልዕክቱን ለመመርመር ይሞክራሉ:: ይህንን ለማድረግም የክፍል መምህሩ አመቺ የትምህርት አውድና ማራኪ የመልመጃ ክንዋኔዎችን ማቀነባበርና መጠቀም ይኖርበታል:: አመቺ የትምህርት አውድና ማራኪ መልመጃ

ስህተት ከሆነ የስህተቱን መነሻ ለማረጋገጥ ምንባቡን በድጋሚ ይቃኛሉ:: ምንባቡን በድጋሚ የሚቃኙትም ደራሲው የተጠቀመባቸው የተለያዩ ፍንጭ-ሰጭ ክፍሎች መልእክቱን ለመግለጽ የዋሉበትን መንገድ ለመለየትና የመጀመሪያውን ግምት በመለወጥ ወይም በማሻሻል ትክክለኛውን መልእክት ለመረዳት የተሻለ የንባብ ስልት ለመጠቀም እንዲችሉ ነው:: /Weaver 1990፡201/::

Roller & Matamboም (1992፡129) በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተካሄዱ የሞዴሉን ደጋፊ የጥናትና ምርምር ውጤቶች አጠቃለው ሲገመግሙ "በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተካሄዱት በርካታ ጥናቶች ተማሪዎች ዳራዊ እውቀታቸውን በመጠቀም እስኪማ-ተኮር የሆነውን የ"ቶፕዳውን" የንባብ ስልቶች ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ማረጋገጣቸውን" ይጠቀማሉ:: እስኪማ-ተኮር የንባብ ስልቶች ሲሉም ተማሪዎች ከሚያነቡት ጽሁፍ ርእስ ጉዳይ ዙሪያ ያላቸውን ተዛማጅ እውቀት ከምንባቡ መልእክት በማጣጣም ይተረጉማሉ፤ ቃሎችን በተናጠል ከማንበብና ከመጥራት ለመልእክት ልዩ ትኩረት የሚሰጡ፥ መሆናቸውን ለማመልከት እንደሆነ ያስረዳሉ::

### 2.2.2.2. በሁለተኛ ቋንቋ ዘርፍ የተካሄዱ ምርምሮች

በአፍ መፍቻ ቋንቋ የንባብ ትምህርት መስክ የተካሄዱት ጥናቶች የሁለተኛ/የውጭ ቋንቋ የምርምር ዘርፍም አዲስ የጥናት አቅጣጫ እንዲይዝ አድርገዋል (Carrell 1988a፡2):: ብዙዎቹ የመስኩ ተመራማሪዎች በወቅቱ ማለትም ከ1960ዎቹ የመጨረሻ አመታት በፊት ለነበረው የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ (ክሂል ተኮር የነበረው) አማራጭ ለመፈለግና በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተገኙትን የጥናት ውጤቶች በሁለተኛ/ውጭ ቋንቋ ለመድገም (replicate) ብሎም ተመሳሳይ ውጤት ለማግኘት አቅደው ምርምሮችን አካሄደዋል:: የተመራማሪዎቹ ጥረት ሰፊ ተቀባይነት ያገኘውን የ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል ውጤታማነት በመፈተሽ በዘርፉ ይታይ የነበረውን ችግር ለመቅረፍ የታለመ እንደነበረ Carrell ያስረዳሉ::

በሁለተኛ ቋንቋ አውድ በሞዴሉ መርሆዎች መሰረት የማስተማሪያ መልመጃዎችን በማዘጋጀት ውጤታማነቱን ከፈተሹት በርካታ ምሁራን መካከል ዋነኛው የClarke and Silberstein (1977) ጥናት ነው:: Clarke and Silberstein እንደሚያስረዱት በንባብ ትምህርት ሂደት በጸጥታ በማንበብ ተፈላጊውን መረጃ መረዳት ያለባቸው ተማሪዎች በመሆናቸው አብዛኛውን ስራ ማከናወን ይገባቸዋል:: ይህም ማለት በልምምድ ሂደት ተማሪዎቹ ዋነኛ ተዋንያን መሆን እንዳለባቸው ለማመልከት ነው::

ከሚነበበው ምንባብ ውስጥ ተፈላጊውን መረጃ ለማግኘት ደግሞ ተማሪዎች እያንዳንዱን ቃል ለመተርጎም ከመሞከር ይልቅ እውቀታቸውን በመጠቀም አጠቃላይ መልዕክቱን ለመመርመር ይሞክራሉ:: ይህንን ለማድረግም የክፍል መምህሩ አመቺ የትምህርት አውድና ማራኪ የመልመጃ ክንዋኔዎችን ማቀነባበርና መጠቀም ይኖርበታል:: አመቺ የትምህርት አውድና ማራኪ መልመጃ

ሲባልም ተማሪዎች በሞዴሉ የሚተኮርባቸውን የንባብ ስልቶችን (የአሰሳ ንባብ፥ የገረፍታ እና የአንድምታ ንባብን እንዲሁም የመልዕክት ትንበያን) ለማለማመድ የሚያስችል መሆን እንዳለበት ለማመልከት ነው:: በትምህርቱ ሂደትም ተማሪዎች ስነአገባባዊ፥ ስነፍችያዊ እና ድርሰታዊ ፍንጮችን ለመጠቀም እንዲችሉ ቅድመ ንባብ ውይይትና የማነቃቂያ ገለጻ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል:: በተጨማሪም ተማሪዎች የምንባቡን መልዕክት ፍሰት በሚገባ እንዲከታተሉና አጠቃላዩን መልዕክት እንዲተረጉሙ ድርሰት ነክ የሆኑ ነጥቦችን ማብራራት ጠቃሚ እንደሚሆንም Clarke and Silberstein (1977፡147) የጥናታቸውን ውጤት ዋቢ በመጥቀስ ያስረዳሉ::

ከላይ የተዘረዘሩትን መርሆዎች ከግንዛቤ በማስገባት Clarke and Silberstein ባካሄዱት ጥናት አዎንታዊ ውጤት ማግኘታቸውን ጠቁመው ለመማር ማስተማሩ ጥረት ስኬታማነት የሚከተሉት ነጥቦች ሊተኮርባቸው እንደሚገባ ያስገነዝባሉ፤

ሀ. የሚቀርቡት ትምህርታዊ የመልመጃ ክንውኖች እንደ አስፈላጊነቱ ሊለዋወጡ የሚችሉና ተፈላጊ የንባብ ስልቶችን በተግባር ለማዋል የሚያስችሉ መሆን አለባቸው::

ለ. ተማሪዎቹ በግል በጸጥታ እንዲያነቡ ልዩ ትኩረት መስጠት አስፈላጊ ቢሆንም የተረዱትንም ሆነ ግልጽ ያልሆነላቸውን ነጥብ እንዲገልጹ በውይይት ማሳተፍ እና አንብበው ያገኙትንም መልዕክት አሳጥረው እንዲያቀርቡ ማበረታታት ተማሪዎች ካነበቡት ምንባብ ውስጥ የተረዱትን ያህል እንዲገልጹ፥ እርስ በርስም ሃሳብ እንዲለዋወጡ ተዘጋጅተው የሚቀርቡላቸው መልመጃዎች የሚያስተላልፉት ሃሳብ የተሟላ መሆን ይኖርበታል:: ተማሪዎች ድርሰት ነክ ፍንጮችን ለመጠቀም የሚችሉትም የተሟላ መልዕክት ያለው ምንባብ ሲያነቡ ነው::

ሐ. በጥናቱ ወቅት የሚመዘገበው ውጤት አስተማማኝ እንዲሆን ተማሪዎች በርካታ የልምምድ ክንውኖች መፈጸም ይኖርባቸዋል:: እነዚህም:-

- ተማሪዎች በተገቢው መንገድ የምንባብ መልዕክትን እንዲገምቱ ከምንባቡ ውስጥ በአሰሳና በገረፍታ ንባብ መልስ የሚፈለግባቸው ጥያቄዎችን አቅርቦ ተማሪዎችን ማነቃቃት ያስፈልጋል:: ጥያቄዎቹም በተቻለ መጠን ከተማሪዎቹ ዕለታዊ የንባብ አላማ ሊመሳሰሉ ይገባል::

- ከንባብ በፊት ለተማሪዎች የሚቀርቡትን ጥያቄዎች በጥንድ፥ በቡድን ወይም በጋራ እንዲወያዩባቸው ማድረግ ያስፈልጋል:: የውይይቱ አላማ ተማሪዎችን በማነቃቃት የምንባቡ መልዕክት እንዲገምቱ ስለሆነ አጠር ያለ ጊዜ መውሰድ አለበት:: ከዚህ በኋላ ተማሪዎች ምንባቡን በጸጥታ ማንበብ ይኖርባቸዋል:: ምንባቡን ካነበቡ በኋላም የተረዱትንና ያልገባቸውን ነጥቦች በዝርዝር አንስተው ውይይት በማካሄድ የራሳቸውን አስተያየት እንዲያክሉ አመቺ አውድ መፍጠር አስፈላጊ ነው::

- ቃላትን ከአውዳቸው በመፍታት ከአጠቃላይ መልዕክቱ ጋር አዛምደው ማብራራት እንዲችሉ ማድረግ ያስፈልጋል።

- ድህረ ንባብ የመልመጃ ስራዎችን በሚሰሩበት ጊዜ ምንባቡን መለስ ብለው በማንበብ መልዕክቱን መገምገም እንዲችሉ ማበረታታት። በዚህም የተማሩትንና የሞከሩትን ለማጠናከር እንዲቻል በምንባቡ መልዕክት ላይ ሰፋ ያለ ውይይት ማካሄድ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ይረዳል።

Clarke and Silberstein (1977:137-138) በጥናታቸው ማጠቃለያ እንደሚሉት በ"ቶፐዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል አማካይነት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ማስተማር ሲታሰብ÷

ሀ. በተወሰነ የንባብ ትምህርታዊ ክንዋኔ ላይ ተማሪዎች የሚያነቡበትን አላማና ግብ ወስነው እንዲለማመዱ አመቺ ሁኔታዎችን ማመቻቸት÷

ለ. እንዲያከናውኗቸው በሚቀርቡላቸው ትምህርታዊ ክንውኖች መሰረት ተማሪዎች ተስማሚ የንባብ ስልቶችን እንዲጠቀሙ ማለማመድ÷ እንዲሞክሩ ዕድል መስጠትና ቢሳሳቱም ይህንን ስህተት በንባብ ማረም ስለሚቻላቸው ተስፋ እንዳይቆርጡ ማበረታታት÷

ሐ. ተማሪዎች የሚቀርብላቸውን ምንባብ መልዕክት አስቀድመው በሚገምቱበት ጊዜ ግምታቸው ስህተት ቢሆንም ደጋግመው መሞከርና ግምታቸውን ማሻሻል÷ መለወጥ ወይም የቀረበውን አመዛዝነው እንዲቀበሉ ማወያየት÷

መ. በሚያነቡበት ጊዜ የምንባቡን አጠቃላይ መልዕክት ከተረዱ ወይም ከጨበጡ የግድ እያንዳንዱን ቃል ለመረዳት እንዳይጨነቁ÷ ከምንባቡ ውስጥ አስፈላጊ ያልሆነውን ነጥብ ለመለየት እንዲችሉ ማበረታታት ተገቢ መሆኑን በአጽንኦት ያመለክታሉ።

በሁለተኛ/ውጭ ቋንቋ የንባብ ትምህርት አውድ የ"ቶፐዳውን" የማስተማሪያ ስልቶችን ገቢራዊ በማድረግ የተካሄዱ የጥናት ውጤቶችን በመቃኘት Swaffar (1988)÷ Roller and Matambo (1992) የማጠቃለያ ሃሳብ ሲያቀርቡ÷ "ከአፍ መፍቻ ቋንቋ የምርምር መንገዶች በተመሳሳይ ዘዴ በሁለተኛ/ውጭ ቋንቋ አውድም የተካሄዱት ምርምሮች በአብዛኛው አዎንታዊ ውጤቶችን አስገኝተዋል።" ይላሉ። ተጠኚ ተማሪዎች ከሚያነቡት ምንባብ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ያላቸውን ተዛማጅ እውቀት በመጠቀም የምንባቡን መልዕክት እንዲሚረዱ÷ አንድምታዊ አስተያየቶችን እንደሚመረምሩ÷ ቃላትን ከአገባባቸው እንደሚፈቱና በአጠቃላይ የ"ቶፐዳውን" የንባብ ስልቶችን እንደሚጠቀሙ በጥናቶቹ ውጤቶች ተመልክቷል። Swaffar (1988:126) የሁለተኛ ቋንቋ

ተጠኚዎችን በማለማመድ ባገኙት ውጤት መሰረትም ተማሪዎቹ ዳራዊ እውቀታቸውን በመነሻነት በመጠቀም የ"ቶፕዳውን" የንባብ ስልቶችን በንባብ ተግባራቸው እንደሚጠቀሙ፥ ትኩረታቸውም በአብዛኛው የምንባቡ መልዕክት መሆኑን፥ ይህንን አጠቃላይ መልዕክት አስቀድመው በመገመት በንባብ ሂደታቸው እንደሚያጣሩ ይገልጻሉ።

በሁለተኛ/ውጭ ቋንቋ አውድ ምርምሮችን ያካሄዱት ምሁራን እንደሚያብራሩት ተማሪዎች የ"ቶፕዳውን" የንባብ ስልቶችን እንዲጠቀሙ በቂ የሆነ ቀዳሚ እውቀት እንደሚያስፈልጋቸው፥ ይህንን እውቀት ዝግጁ ለማድረግና ከሌላቸው ደግሞ መጠነኛ ፍንጭ እንዲያገኙ ቅድመ ንባብ የመግቢያና የማዘጋጃ ውይይቶች ጠቃሚነታቸው የጎላ ነው። ትምህርቱን ውጤታማ በሆነ ዘዴ ተግባራዊ በማድረግና ተማሪዎች የ"ቶፕዳውን" የንባብ ስልቶችን እንዲጠቀሙ የንባብ ስልቶቹን በተለያዩ ምንባቦች አማካይነት በማስተማር ማገበረታታትና ጥሩ ውጤት ማስገኘት እንደሚቻል Roller & Matambo (1992:129) Carrell (1983)ን Hudson (1982)ን Hamp-Lyons (1985)ን በመጥቀስ ያብራራሉ። እነዚህ ምሁራን ትኩረት የሰጡት የተማሪዎችን ዳራዊ እውቀት በማዘጋጀትና ተማሪዎችን በማነቃቃት ከሚያነቡት ምንባብ ውስጥ የሚፈልጉትን መልእክት ለመረዳት የሚያበቃቸውን የንባብ ስልቶችን ማስተማርን ነው። በዚህም የተማሪዎቹን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ይቻላል።

Carrell (1983)፥ Coady (1979)፥ Clarke & Silberstein (1977)፥ Hudson (1982)፥ Carrell & Eisterhold (1983)፥ Lee (1986) በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ የ"ቶፕዳውን" ሞዴል የሚኖረውን ውጤታማነት በመፈተሽ ጥናቶችን አካሂደዋል። ምሁራኑ እንደሚገልጹት በሁለተኛ ቋንቋቸው የሚያነቡ ተማሪዎች (እንግሊዝኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሚማሩ) የቋንቋ ችሎታቸው ከፍ ያለ ከሆነ እንደ አፍ ፈቶቹ የ"ቶፕዳውን"ን የንባብ ስልቶች ይጠቀማሉ። ስለዚህ ተማሪዎቹ አንብቦ ለመረዳት የሚያበቃቸው የቋንቋ ችሎታ ካላቸው (threshold level) ርእስ-ተኮር ገለጻ ሲደረግና በውይይት ሲሳተፉ የቋንቋው ብቃት ማነስና የትምህርት እውቀታቸው ሊካካስ ይችላል።

በሌላ በኩል ደግሞ Coady (1979) እና Hudson (1982) ግን ከዚህ ለየት ያለ አስተያየት ያቀርባሉ። ይኸውም የተማሪዎቹ ዳራዊ እውቀትና የሚመረጠው ምንባብ ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር የሚጣጣም ይዘት ካለው የቋንቋ ችሎታቸው በጣም የመጠቀ ባይሆንም አንብበው ሊረዱ ይችላሉ የሚል ነው። ስለዚህ ምንባቡ ከተማሪዎቹ ዳራዊ እውቀት የሚዛመድና ፍላጎታቸውን የሚገዛ ከሆነ ተማሪዎቹ የ"ቶፕዳውን" ሞዴል የንባብ ስልቶችን ይከተላሉ። Coady አስተያየታቸውን ተግባራዊ ለማድረግና የሞዴሉን ውጤታማነት ለመፈተሽ እንግሊዝኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩት ተማሪዎች ላይ ጥናት አካሂደዋል። የጥናታቸው ውጤትም አዎንታዊ መሆኑንና ተጠኚዎቹ

የ"ቶፕዳውን" የንባብ ስልቶችን የሚጠቀሙ መሆናቸውን ያመለክታሉ:: ይህንኑ የጥናት ውጤት መሰረት በማድረግ ሃሳባቸውን ሲያጠናክሩ የሚከተለውን አቅርበዋል፤

> የሚነበበው ምንባብ መልእክት ከተማሪዎቹ ፍላጎት ጋር በእጅጉ የተቆራኘና ከእውቀታቸው ከተዛመደ÷ ተማሪዎቹ በጉጉት ሊያነቡት ይችላሉ:: የተማሪዎቹ ፍላጎትና ዳራዊ እውቀት መጣጣም ተማሪዎቹ ምንባቡን በተስማሚ ፍጥነት አንብበው እንዲረዱትና የበለጠ ለመመርመር ስለሚያጓጓቸው የሚኖርባቸውን የቋንቋ ችሎታ ማነስ ሊያካክስላቸው ይችላል::

በጥቅሱ ውስጥ እንደተመለከተው የምንባቡ ይዘት ማራኪና አቀራረቡም ከተማሪዎቹ እውቀት ጋር የተዛመደ ከሆነ የማንበብ ፍላጎታቸውን ይገዛል፤ በዚህም የምንባቡን መልእክት ለመረዳት በጉጉት ሊያነቡት ይችላሉ:: ነገር ግን ዳራዊ እውቀታቸው ለአንብቦ መረዳት ከፍተኛ ድርሻ ቢኖረውም የቋንቋ ችሎታቸው ደካማ መሆን የለበትም:: ዳራዊ እውቀታቸው ቋንቋውንም ስለሚያካትት Eskey (1988) ሁለቱን አያይዞ መመልከት የተሻለ ተቀባይነት ይኖረዋል::

### 2.2.2.3. በልሳነ ክልኤዎች ላይ የተደረጉ ጥናቶች

Roller & Matambo (1992) ጥናታቸውን ያካሄዱት ልሳነ ክልኤ የሆኑ አንባቢዎች ዳራዊ እውቀታቸውን በመጠቀም የ"ቶፕዳውን" የንባብ ስልቶችን የሚከተሉ መሆን አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ ነበር:: በጥናቱ የታቀፉት ተማሪዎች በሾና ቋንቋ አፋቸውን ፈተው በእንግሊዘኛ የላቀ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው የሁለተኛ ደረጃ የዚምባብዌ ተማሪዎች ናቸው:: ጥናቱ ሲካሄድ ተጠኚ ተማሪዎቹ በተመሳሳይ መንገድ በሾናና በእንግሊዘኛ ጎን ለጎን እንዲያነቡ ተደርገው የጥናቱ መረጃ ተሰብስቦአል:: በመረጃው ትንታኔም እንደተመለከተው ተማሪዎቹ የቀረበላቸውን ምንባብ ቀዳሚ እውቀታቸውን ከአውዳዊ ፍንጮች ጋር በማገናዘብ በመለማመዳቸው ችሎታቸውን ለማሻሻል ችለዋል:: የንባብ ስልታቸውም ከቋንቋ ይልቅ ትርጉም ተኮር መሆኑን ተመራማሪዎቹ አብራርተዋል::

Roller & Matambo በጥናታቸው ማጠቃለያ እንደሚገልጹት ውጤቱን ሊያገኙ የቻሉት ተማሪዎቻቸው ከንባብ በፊት ተገቢ የመግቢያ ውይይት በማድረጋቸው ሲሆን ውይይቱ ተማሪዎቹ ያለባቸውን ቋንቋ ነክና የእውቀት ማነስ ችግር ለመቅረፍ በማስቻሉ ነው:: በትምህርቱ አሰጣጥ ወቅትም አጥኚዎቹ የተጠቀሙባቸውን የማስተማሪያ ምንባቦች በደጋፊ ፍንጮች ማለትም ስእሎች በማስደገፍ የትምህርቱን አቀራረብ በቅድመ ንባብና÷ በድህረ ንባብ ክንውኖች ከፋፍለው በማቅረባቸው መሆኑን አመልክተዋል::

Clarke (1988:122) እንደ Roller & Matambo ሁሉ በልሳነ ክልኤ ተማሪዎች የንባብ ስልቶች አጠቃቀም ላይ ጥናት አካሂደዋል:: የClarke ትኩረት ተማሪዎቹ የ"ቶፕዳውን" የንባብ

ስልቶችን የሚከተሉት መሆን አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ ሲሆን ለተጠኚ ተማሪዎቹ በእስፓኝና እንግሊዝኛ ቋንቋዎች ጎን ለጎን የንባብ ትምህርት ልምምድ በመስጠት መረጃዎችን አሰባስበዋል:: በሁለቱም ቋንቋዎች የንባብ ትምህርት ልምምዱ ከተካሄደ በሁዋላ በተገኘው መረጃ መሰረት ተጠኚዎቹ የ"ቶፕዳውን" የንባብ ስልቶችን የሚከተሉ መሆናቸውን Clarke ያመለክታሉ::

በአጠቃላይ÷ የ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴልን ተግባራዊነት ለመፈተሽ ጥናት ያካሄዱት ምሁራን የጥናት ውጤቶች ተመሳሳይነት ያላቸው መሆናቸውን Cambourne (1981:94) ሲገልጹ፤

> በጥናቶቹ የታቀፉት ተጠኚዎች ስለሚያነቡት ምንባብ መልእክት ምንነት ይተነብያሉ:: የሚተነብዩት በርእሱ ዙሪያ ካላቸው ዳራዊ እውቀት በመነሳት ሲሆን ለትንበያቸውም ስኬት ማረጋገጫ የሚያደርጉት ምንባቡ ውስጥ የሚያገኟቸውን ስነአገባባዊና አውዳዊ ፍንጮች ነው::

ይላሉ::

እዚህ ላይ ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚገባው ጉዳይ መኖሩን አጥኚዎቹ ያሳስባሉ:: ይኸውም አንባቢዎች በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛው/የውጭ ቋንቋዎች የሚጠቀሙባቸው የንባብ ስልቶች ተመሳሳይ እንዲሆኑ የሁለተኛ/ውጭ ቋንቋ ችሎታቸው የዳበረ መሆን አለበት:: ምክንያቱም በአፍ መፍቻና በሁለተኛ/ውጭ ቋንቋዎች መካከል ልዩነቶች አሉና/Aebersold & Field 1997: Clarke 1979/::

ከፍ ሲል በዝርዝር ለማቅረብ እንደተሞከረው የ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በውጭ ሀገር በአፍ መፍቻና በኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋዎች አውድ አመርቂ ውጤት በማስገኘቱ በስፋት ተሰርቶበታል:: የዚህ ጥናት አቅራቢም ይህንኑ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ሞዴሉ በኢትዮጵያ በአማርኛ ቋንቋ አውድ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር የሚኖረውን ውጤታማነትና ተግባራዊነት ለመመርመር ይሞክራል:: ለዚህ አላማ ስኬትም በሞዴሉ ውጤታማነት ላይ ምርምር ያካሄዱትን የመስኩ ምሁራን የመልመጃዎች አዘገጃጀትና የትምህርት አቀራረብ ዘዴዎችን በመጠቀም ትምህርታዊ ልምምዱን ተግባራዊ ያደርጋል:: በመጨረሻም ልምምዱ ያስገኘውን አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ውጤት ለመግለጽ ይሞክራል::

### 2.2.3. ሞዴሉን አስመልክቶ የተሰነዘሩት አሉታዊ አስተያየቶችና መልሶቻቸው

Wallace (1992:42) የ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በአፍ መፍቻ ቋንቋም ሆነ በሁለተኛ/ውጭ ቋንቋ በስፋት የተሰራበት መሆኑን ጠቁመው በተቃራኒ ወገንም አሉታዊ አስተያየቶች መሰንዘራቸውን ይገልጻሉ:: በተለይም የአሜሪካ የንባብ ትምህርት ተመራማሪዎች ሞዴሉ በግምት ላይ ብቻ ያነጣጥራል የሚል ጥያቄ አንስተዋል:: በዋናነት የሚያነሱዋቸው ጥያቄዎች የሚያተኩሩት በትንበያ (prediction) እና አውዳዊ የቃላት አፈታት (contextual guessing)

ላይ ነው፡፡ ከተቃዋሚዎቹ መካከል Gibson & Levin (1975) እንዲሁም Stanovich (1991) ቀዳሚዎቹ ሲሆኑ ጥያቄዎቻቸው የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፤

- ተማሪው ለትንበያው መነሻ የሚያደርገው ምንድን ነው?
- የትንበያውስ ባህርይ ምን ይመስላል፥ የሚገምተው ወይም የሚተነብየው ተከታታይ ፊደሎችን፥ ቃላትን፥ ሀረጋትን፥ አረፍተነገሮችን ወይስ አጠቃላይ የምንባቡን አቀራረብና ይዘትን? እያነበበ እያለ ወደፊት ይሆናል ብሎ የሚያስበውን ወይስ የደረሰበትን የትኞቹንስ ያስቀድማል?
- ትንበያውንስ እንዴት ያረጋግጣል? በጥንቃቄ አንብቦ ለማረጋገጥ የሚረዳው ያለፈው ወይም ቀጣይ የምንባቡ ክፍል መሆኑንስ እንዴት ይለያል? ተማሪው ከቀዳሚውና ከቀጣዩ የበለጠ አስረጅ መሆኑን ለመለየት የሚያግዘው ምንድን ነው?
- የገመተውን ሃሳብ ማረጋገጡንስ እንዴት ይወስናል? የገመተውስ ስህተት ከሆነ ምን ያደርጋል?

የሚሉት ናቸው፡፡ ለእነዚህና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች Higgins (1984)፥ Goodman (1976)፥ Clarke (1979)፥ Nuttall (1996)፥ Grellet (1981)፥ Smith (1985) እና Walker (1998) መልሶችን ያቀርባሉ፡፡

Clarke(1979:139) ለጥያቄዎቹ በሙሉ በአንዴ መልስ ይሰጣሉ፡፡ መልሳቸውም ከድምጽ ጀምሮ እስከ ምንባቡ አጠቃላይ መልእክት ድረስ ከዚያም አልፎ በምንባቡ ይዘት አማካይነት ስለተገለጸው አንድምታዊ ፍች ያለውን ሁሉ ሊያጠቃልል እንደሚችል ያመለክታሉ፡፡ Goodman (1988:13) በበኩላቸው ስነአገባባዊ ሁኔታዎችን በማጤን ከአንድ ቃል ቀጥሎ ሊመጣ የሚችለውን ሌላ አዲስ ቃል መተንበይ እንደሚቻል ሲገልጹ Smith (1985:309) ደግሞ በአንድ ቃል ውስጥ ተከታትለው ሊመጡ የሚችሉትን ድምጾች ጨምሮ እስከ አጠቃላይ መልእክቱ ምንነት መተንበይ ይቻላል ይላሉ፡፡

ለትንበያው መነሻ የሚሆነው ምንባቡ ለመሆኑ አያከራክርም፡፡ Smith (1985:95) ይህንኑ የምንባብ መነሻነት እንደሚከተለው ያብራሩታል፤

> በንባብ ሂደት ውስጥ አንባቢው የምንባቡን ጠቅላላ መልእክት ይተነብያል፡፡ ይህንኑ ትንበያውን በንባብ ሂደት ያረጋግጣል፡፡ ትንበያውን ሲያረጋግጥም ጥርጣሬውን ያስወግዳል፡፡ እነዚህን ተወራራሽ ተግባራት ለመፈጸምና ምጋቤ-ምላሽ ለማግኘት የሚረዳው መነሻ ምንባቡ ነው፡፡ በዚህም ጥረት ትንበያውን ለማረጋገጥ ሲያነብ የገመተው መልእክት በምንባቡ ይዘት ካልተደገፈ ለስህተቱ ምክንያት ያገኛል፡፡ ስለዚህም የሚያነበው ምንባብ የሚፈልገውን መረጃ ብቻ ሳይሆን ሲሳሳትም ለስህተቱ ማረሚያ አቅጣጫ ያመላክተዋል፡፡ ምንባቡ ሀላፊውን ግምትና ትንበያ ከተከታዩ ለማዛመድም

ያስችለዋል፡፡ በአጠቃላይ ትንበያው የሚመነጨው ከምንባቡ እንደመሆኑ ትክክለኛነቱም የሚረጋገጠው በዚሁ በምንባቡ መልእክት ነው፡፡

"ተማሪዎቹ በትንበያ የሚያተኩሩት ከድምጾች÷ ከቃሎች÷ ከአረፍተነገሮች÷ ከመልእክቱ በየትኛው ላይ ነው?" ለሚለው ጥያቄ መልሱ በአጠቃላይ መልእክቱ ላይ ነው የሚል ነው፤ ምክንያቱም የንባብ ትምህርት ዋነኛ አላማ የምንባቡን መልእክት ለመረዳት በመሆኑ (Goodman 1986÷ Anderson 1994÷ Aebersold & Field 1997) የተማሪዎቹ ትኩረት መልእክቱ መሆን አለበት፡፡ የዳበረ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው አንባቢዎች የትንበያን ስልት የሚጠቀሙበት የቃላትን ቅርጽ ለማረጋገጥ ወይም ለመገመት አይደለም (Grabe 1991)፡፡ በጠያቂዎቹ እንደተመለከተው የትንበያው ስልት በመጀመሪያ ቅድሚያ መስጠት የሚገባው ለአገባብ ህግጋትና ለቃላት ቅርጽ ሳይሆን ለመልእክቱ ምንነት ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ትምህርታዊ ልምምዶቹን ሲያካሂዱ ከምንባቡ ርእስ አቀራረብ በመነሳት በውስጡ ሊካተቱ የሚችሉ ነጥቦችን በማሰላሰል ቀዳሚ ግባቸው መልእክቱ ነው፡፡

"ሲሳሳቱስ" ለሚለውም ጥያቄ እንዲሁ መልስ ተሰጥቶአል፡፡ ለምሳሌ Goodman (1971) እንደሚያብራሩት ጠንቃቃ የሆኑ አንባቢዎች በሚያነቡበት ወቅት ከሚገምቱት መልእክት የተወሰነው ስህተት እንደሚሆን አስቀድመው ይወስናሉ፡፡ ምክንያታቸውም ወደ ሁዋላና ወደፊት ተመላልሰው በማንበብ ትክክለኛውን የምንባቡን መልእክት ለማግኘት ስለሚችሉ ነው፡፡ ስለዚህ የስነልቡናዊ ስነልሳን ተመራማሪዎች እንደሚሉት ተማሪዎች አስቀድመው የሚገምቱት መልእክት ስህተት መሆን ተማሪዎቹ በንባባቸው ደካማነታቸውን አያሳይም፡፡ የሚጤነውም ጉዳይ የትንበያቸው ስህተት መሆን ሳይሆን ትንበያቸው ለምን ስህተት እንደሆነ ለመረዳት መቻላቸውና በንባብ ስህተታቸውን ማረማቸው ነው፡፡

ሌላው የተነሳው ጥያቄ የቃላትን አውዳዊ ፍች የሚመለከተው ነጥብ ነው፡፡ Stanovich (1991:20-21) በ1970ዎቹ በንባብ ትምህርት ዘርፍ በተለይም የአይን እይታ አድማስን (eye movement studies) የተመረኮዙ ምርምሮችን በመጥቀስ ሃሳባቸውን ሲያብራሩ "ተማሪዎች ብዙውን ጊዜ የቃላት አውዳዊ አፈታትን የሚጠቀሙ ከሆነ የቃላት እውቀታቸው ደካማ" እንደሚሆን ያመለክታሉ፡፡ ይህ የእስታኖቪች ትችት የሚያነጣጥረው በSmith (1973) ሃሳብ ላይ ነው፡፡ ይኸውም Smith የዳበረ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች ምንባቡ የተዋቀረባቸውን ቃላት በተናጠል የሚያተኩሩባቸው (fixate) አልፎ አልፎ ነው የሚለው ነጥብ ነው፡፡

Stanovich እንደሚሉት የዳበረ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው ተማሪዎችም ቢሆኑ በሚያነቡበት ወቅት የይዘት ቃላትን በጥንቃቄ ያነቡዋቸዋል፡፡ ስለዚህ እይታቸውን በምንባቡ ላይ አነጣጥረው ግብአቱን ሲመረምሩ የአመራረጥ ስልታቸው አብዛኛዎቹን የይዘት ቃላት የሚመለከት በመሆኑ "አልፎ አልፎ ነው" የሚለው አስተያየት ግልብ መሆኑን ልብ ልንለው እንደሚገባ

ያስጠነቅቃሉ:: ሲያጠቃልሉም "ተማሪዎች ከምንባቡ የሚመርጡት መረጃ በርካታ ነው፤ ውሱን መረጃን ብቻ አይከታተሉም" ይላሉ::

በሌላ በኩል ደግሞ የቃላት አውዳዊ ፍችን ይገምታሉ ሲባል ሊጤን የሚገባው ጉዳይ መኖሩን Anderson (1994)፥ Walker (1998) እና Grabe (1991) ይጠቁማሉ:: እነዚህ ምሁራን የቃላቱን አውዳዊ ፍች መገመት ማለት ከምንባቡ ርእስ ጋር ተዛምደው የሚያስተላልፉትን ፍች መረዳት መሆኑን ይገልጻሉ:: በተለይም ቃላቱ ርእስ-ተኮር (topic-oriented) ከሆኑ ተደጋግመው በምንባቡ ውስጥ ገብተው ይዘቱን ስለሚያጎሉና ተጨማሪ ማብራሪያ ስለሚሰጡ ከገቡበት አውድ ተገናዝበው መፈታት ይኖርባቸዋል:: በነዚህ ላይ ማተኮር ደግሞ የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ደካማ የሚያደርግ አለመሆኑን Aebersold & Field (1997:139) ያብራራሉ::

Brown (1994) ቀደም ብሎ በተገለጸው መንገድ አውዳዊ የቃላት አፈታት ስልት አስፈላጊ መሆኑን ያሰምሩበታል:: ተማሪዎቸ የሚያነቡትን ምንባብ በውል ለማጤንና አውዳዊ ጉዳዮችን ለመረዳት በቀጥታም ሆነ በአንድምታ በቀረቡት ፍንጮች በመታገዝ ለመመርመር ያስችላቸዋል:: ስለሆነም አውዳዊ የፍች ግመታ ዘፈቀዳዊ ሳይሆን የተመረጡ ፍንጮች ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ጠቀሜታው የጎላ ነው::

በተጠቀሱት ጥያቄዎች መነሻነት በሞዴሉ መሰረታዊ ነጥቦቸ ላይ የማሻሻያ ለውጥ ተደርጎበታል:: ይኸውም በተሻለ መንገድ የንባብን ትክክለኛ ባህርያት ለማንጸባረቅ እንዲችልና በመማር ማስተማር ሂደት የሚተኮርባቸውን ነጥቦች በውል ለመጠቆም ነው:: Harrison (1992:5) እንደሚያስረዱት ተሻሽሎ የቀረበው የ"ቶፕዳውን" ሞዴል ለሚከተሉት ስነ ትምህርታዊ መርሆዎችና ትምህርታዊ ክንውኖች ቅድሚያ ይሰጣል:: እነዚህም:-

- ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት ሊያተኩሩበት የሚገባው የቃላትን ቅርጽ ለመተንበይ ሳይሆን በምንባቡ መልእክት ላይ ነው:: ዳራዊ እውቀታቸውን በመነሻነት ተጠቅመው ስለጠቅላላ መልእክቱ ምንነት ማሰላሰል ይጠበቅባቸዋል::
- ሙሉ በሙሉ በትንበያና በአውዳዊ የቃላት ፍች ግመታ እንዳይወሰኑና ዝርዝሩን ችላ እንዳይሉ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ወደ አስፈላጊ ዝርዝር ነጥቦች የሚያመሩ ጥያቄዎችን ማሰናዳትና ማለማመድ ያስፈልጋል::
- በትንበያው ስልትና በምንባቡ ይዘት መካከል ሚዛናዊነትና መደጋገፍ እንዲኖር ከምንባቡ ይዘት የተዛመደውን ቀዳሚ እውቀታቸውን በመቀስቀስ ተማሪዎችን ለንባብ ክንውኖች ማዘጋጀት፥ እና ከአውዳዊ ፍንጮች በመነሳት የምንባቡን አጠቃላይ መልእክት እንዲተነብዩ አመቺ መልመጃዎችን ማዘጋጀትና መጠቀም የሚሉት ናቸው /Cooper & Petroskey 1976፥ Walker 1998/::

- ንባብ ሜካኒካዊ በሆነ መንገድ ቃል በቃል ስለማይካሄድና አንባቢው ከሚነበበው ምንባብ ውስጥ የሚያገኘው መልዕክት በተሟላ መልኩ ሊተረጎም የሚችለው ከቀዳሚ እውቀቱ ሲዛመድ በመሆኑ ለአንባቢው እውቀት ተገቢ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡
- አንባቢው ከዝርዝር ነገሮች በፊት ዋና ዋና ሃሳቦች ላይ በማተኮር የአዕምሮን የማስታወስ ችሎታ ውሱንነት ለማስወገድ ጥረት ማድረግ ያስፈልገዋል፡፡
- ተማሪዎችን የሚያሳትፍ የንባብ ትምህርት ልምምድ መኖር አለበት፡፡ ንባብ አመራማሪ፥ መፍትሄ አመንጪ እና አዕምሮታዊ ተግባር በመሆኑ ተማሪዎች በልምምዱ ሂደት ንቁ ተሳታፊዎች መሆን አለባቸው፡፡

## 2.2.4. የትምህርት አውድ፥ የመምህሩና የተማሪዎች ሚና

### 2.2.4.1. የትምህርት አውድ

Clarke & Silberstein (1977:138)፥ Ellis & Tomlison (1988:143-144)፥ Silberstein (1994:10) እና Williams (1986:43) እንደሚገልጹት የትምህርቱ አውድ ተማሪዎችንም ሆነ መምህሩን በትብብር መንፈስ ለመረዳዳትና ለመማማር የሚያስችልና ከመምህሩ የበላይነት የጸዳ መሆን ይኖርበታል፡፡ አውዱ በነጻ መንፈስ ለመወያየትና ለመረዳዳት የሚችሉበት፥ ከውጭው አለም የንባብ አላማና ከንውን ጋር በተቻለ መጠን ተቀራራቢነት ያለው ሲሆን ልምምዱ ውጤታማ ይሆናል፡፡ ተማሪዎችም በንቃት ለመሳተፍ የተሻለ አጋጣሚ ያገኛሉ፡፡

### 2.2.4.2. የመምህሩ ሚና

Clarke & Silberstein (1977:1390፥ Swaffar, Arnes and Byrnes (1991:70-71)፥ Brown (1994:161)፥ Anderson (1994:192) እና Silberstein (1994:10) **እንደሚሉት በንባብ ትምህርት ክፍል መምህሩ ሶስት መሰረታዊ ተግባራት ሊኖሩት ይችላሉ፡፡ እነዚህ ተግባራት እንደሚከናወኑት ትምህርታዊ ክንውኖች ቢለያዩም እንደ መምህርነቱ፥ እንደተሳታፊነቱ እና በልምምዱ ሂደት እንደረዳትነቱ** (facilitator) **የሚፈጽማቸውን ተግባራት የሚያጠቃልሉ ናቸው፡፡ ይኸውም ተማሪዎች** በልምምዱ ሂደት ምን እንደሚሰሩ፥ ልምምዱን ለምን እንደሚሰሩና እንዴት እንደሚሰሩ ማለትም ተግባሩን፥ አላማውንና አፈጻጸሙን በማመልከት ተማሪዎች ድርሻቸውን በሚገባ እንዲወጡ የሚያደርግበትንና የራሱንም ድርሻ የሚወጣበትን ሂደት ይገልጻል፡፡ ዝርዝሩ ከሶስቱ የንባብ ትምህርት አቀራረብ እርከኖች አኳያ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

**ሀ. በቅድመ ንባብ ጊዜ የመምህሩ ሚና፡-** ቀደም ሲል እንደተገለጸው መስተጋብራዊ በሆነውና ተማሪን ባማከለው የንባብ ትምህርት ልምምድ የመምህሩ ሚና በአብዛኛው ረዳትነት ነው፡፡ ተማሪዎች መስራት ያለባቸውንና አሰራሩን ከነምክንያቱ በመጠቆም ያነቃቃል፡፡ ስለዚህም

ተማሪዎች ከሚቀርብላቸው ምንባብ ጋር አጥጋቢ መስተጋብር እንዲኖራቸው የንባብን ሂደት የሚያጠናክሩ ትምህርታዊ ተግባራትን በማዘጋጀት በክፍል ውስጥ ገቢራዊ ያደርጋል:: በመሆኑም በቅድመ ንባብ ክፍለ ትምህርት መምህሩ

- የምንባቡን ርዕስ በሰሌዳ ወይም ወረቀት ላይ በመጻፍ ተማሪዎቹ በርዕሱ ዙሪያ የሚኖራቸውን ዳራዊ እውቀት እንዲያስታውሱና የምንባቡን መልዕክት እንዲገምቱ ጥያቄዎችን ይጠይቃል፤ በጥያቄዎቹ አማካይነትም የማነቃቂያ ውይይት ከተማሪዎቹ ጋር ያካሂዳል::
- ምንባቡን በገረፍታ አንብበው ከምንባቡ በፊት ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ እንዲፈልጉ ያበረታታል::
- የምንባቡን መልዕክት ከገመቱ በኋላ ከምንባቡ በፊት ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ለመፈለግ የሚተኮርባቸውን የንባብ ስልቶች እንዲለማመዱ ጥረት ያደርጋል::
- ተማሪዎች ከሚያነቡት ምንባብ ውስጥ ተፈላጊውን መረጃ እንዲቀስሙ የተመቻቸ የትምህርት አውድ እንዲኖር ጥረት ያደርጋል:: በዚህም በምንባቡና በተማሪዎች መካከል ከጭንቀት ነጻ የሆነ የትምህርት አውድ ያመቻቻል (Swaffar, Arnes and Byrnes 1991:70-71):: በአጠቃላይ÷ መምህሩ የተጠቆሙትን ተግባራት ካከናወነ በኋላ አላስፈላጊ ከሆነ ጣልቃ ገብነት መጠንቀቅና ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት እንዲማሩ አብዛኛውን ምድብ ሰአት ለነሱ ልምምድ ያውላል::

ለ. በንባብ ጊዜ የመምህሩ ሚና:- በዚህ ክፍለ ትምህርት የመምህሩ ሚና ተማሪዎች የንባብ ስልቶቹን ተግባራዊ እንዲያደርጉ÷ የጸሀፊውን አላማ÷ የምንባቡን ይዘትና የምንባቡን ድርስታዊ አደረጃጀት እንዲመረምሩ አመቺ አውድ መፍጠር ነው:: በዚህ ትምህርታዊ ክንውን መምህሩ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የተማሪዎችን ችሎታ ማዳበር እንደሚችል (Carrell, Liberto and Pharis 1989÷ Aebersold & Field 1997) ያስረዳሉ::

በንባብ ጊዜ መምህሩ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎችን ሊጠቀም ይችላል:: የጥያቄዎቹ አላማ የተማሪዎችን ትኩረት ለማሰባሰብ ነው:: ጥያቄዎቹ አይነታቸው በሶስት ሊፈረጅ ይችላል::

- ቀጥተኛ የሆኑ ጥያቄዎች በምንባቡ ግልጽ መልእክት ላይ የሚያተኩሩ ጥያቄዎች ናቸው::
- ቀጥተኛ ያልሆኑ ጥያቄዎች በአብዛኛው የምንባቡን አወቃቀር የሚመለከቱ ጥያዎችን ይይዛሉ:: ተማሪዎች በምንባቡ ውስጥ ያለውን መልዕክት ለማብራራት የገቡትን የይዘት ቃላትና አያያዦችን ተግባር እንዲጠቁሙ ይጠይቃል::
- አንድምታዊ ጥያቄዎች:- ተማሪዎች በምንባቡ መልእክት አማካይነት ተዛማጅ ስለሆኑ ጉዳዮች እንዲያሰላስሉና ሁለቱን እንዲያዛምዱ የሚረዱ ጥያቄዎች ናቸው:: በተጨማሪም ተማሪዎች የምንባቡን መልእክት መርምረው ረቡን፡ ተአማኒነቱን እና በተገቢው መረጃ

ተደግፎ መብራራቱን እንዲገመግሙ የሚያስችሉ ጥያቄዎችን ሊጠቀም ይችላል:: /Carrell, Liberto & Byrnes 1989÷ Aebersold & Field 1997)::

**ሐ. ከንባብ በኋላ፡-** ተማሪዎች በቀዳሚዎቹ የትምህርት እርከኖች ያካሄዱትን ልምምድ መነሻ በማድረግ የምንባቡን መልእክት መረዳታቸውንና የተማሩትን ተግባራዊ ማድረጋቸውን ያረጋግጣል:: ተማሪዎች ያነበቡትን ምንባብ መልእክት ከግል ገጠመኛቸውና እውቀታቸው በማዛመድ ተጨማሪ ውይይት እንዲያደርጉ ያበረታታል:: እነዚህን አላማዎች ከግብ ለማድረስም መምህሩ የምንባቡን መልዕክት አሳጥረው በቃል ወይም በጽሑፍ እንዲያቀርቡ÷ በመልዕክቱም ላይ ውይይት እንዲያደርጉ÷ የምንባቡን መልዕክት ከሌሎች ተዛማጅ ጽሁፎች ጋር በማያያዝ የተረዱትን መሰረት አድርገው ሁለቱን እንዲያዛምዱ ሁኔታዎችን ያመቻቻል::

### 2.2.4.3. የተማሪዎች ሚና

የንባብ ትምህርት ተማሪዎችን በማሳተፍ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ምቹ ሁኔታን ይፈልጋል:: በትምህርቱ ሂደትም የተማሪዎች ተግባር በልምምዱ በስፋት መሳተፍ ነው:: በስፋት ለመሳተፍም ተማሪዎቹ በጥንድና በቡድን በመደራጀት በልምምዱ ይታቀፋሉ:: የቀረበላቸውን ምንባብ በጸጥታ አንብበው መወያየትና በየቡድኖቹ መካከል የሚኖረውን የምንባብ አተረጓጎም አስመልክቶ ሃሳብ መለዋወጥ ይገባቸዋል:: ይህ ውይይት ተማሪዎቹ ከየተመደቡበት ምድብ ውጭ ያሉት ሌሎች ተማሪዎች የተለያየ አተረጓጎምና ግንዛቤ ስለሚኖራቸው እርስ በርስ ለመማማር ይረዳቸዋል:: Williams (1986:43) የተማሪዎችን ሚና ለማጠናከር "ተማሪዎችን በጥንድና በቡድን አደራጅቶ በምንባቡና ምንባቡን በተንተራሱ ክንዋኔዎች ላይ ማወያየት አስፈላጊ" መሆኑን ያስምሩበታል::

## 2.2.5. የምንባቦች አመራረጥ÷ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች አይነትና ፈተና

### 2.2.5.1. የምንባቦች አመራረጥ

አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር እንዲያገለግል የሚቀርብ ምንባብ በጥንቃቄ መመረጥ ይኖርበታል:: የሚመረጠው ምንባብ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ታይቶ÷ ተመዝኖ እና ተተንትኖ ተስማሚነቱና ወቅታዊነቱ ሲረጋገጥ እንዲሁም ብቃት ያለው ሆኖ ሲገኝ ለተፈለገው አላማ እንዲውል ይደረጋል::

Ball (1976)÷ Nuttall (1982)÷ Williams (1986) እና Silberstein (1994) የማስተማሪያ ምንባብ ሲመረጥ ብዙዎቹን ተማሪዎች የሚስብ መሆን እንዳለበት ይጠቁማሉ:: ምንባቡ ሲመረጥም

ብዙዎቹ ተማሪዎች የሚደሰቱበት ሆኖ ከተማሪዎቹ ሙሉ ተሳትፎና ፍላጎት አንጻር መመረጥ እንደሚገባውም አክለው ይገልጻሉ:: የተማሪዎች ፍላጎት ሲባልም:-

ሀ. የተማሪዎች ግላዊ ፍላጎት:- አንዳንድ ተማሪዎች የሚያውቁትም ነገር ቢሆን የበለጠ ማብራሪያና እውቀት ለማግኘት የተለያዩ ጉዳዮችን የሚያቀርቡ ምንባቦችን ያለመሰልቸት ደጋግመው ሊያነቡ የሚፈቅዱ መሆናቸው፥

ለ. ቡድናዊ ፍላጎት:- ለትምህርት የሚቀርብላቸው ምንባብ ርእስ ጉዳይ የተማሪዎችን ቡድናዊ ህይወት የሚመለከት ቢሆን በፍላጎት ያነቡታል:: ከቡድናዊ ህይወታቸው ጋር ስለሚያያዝም ስለራሳቸው በስፋትና በጥልቀት ለማወቅ መነሻ የሚሆናቸው የመሆኑ እና

ሐ. ተማሪዎች ከሚኖሩበት ማህበረሰብ ባህልና እምነት ጋር የተዛመደ መልእክት የሚያቀርቡ ምንባቦች ሲሆኑ የተማሪዎቹን ፍላጎት የሚያነሳሱ መሆናቸው ናቸው::

Ulijin & Strother (1990:39-40)ም እንዳመለከቱት የማስተማሪያ፥ ምንባብ በተማሪዎች ፍላጎት ላይ መመስረት አለበት:: ፍላጎታቸው ተጠብቆ የማስተማሪያ ምንባብ ከተመረጠ ለተማሪዎች ትምህርት አቀባበል ከፍተኛ መቀስቀስ ይሰጣል:: የመቀስቀሱ መኖር ደግሞ ለትምህርቱ ሂደት ስኬታማነት አዎንታዊ ድርሻ ይኖረዋል:: ስለዚህ መምህሩ የማስተማሪያ ምንባብ ሲመርጥ የተማሪዎችን ፍላጎት ለመግዛት እንዲችል የሚከተሉትን ነጥቦች ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት /Nuttall (1982:30)፥ Silberstein (1994:101)፥ Clarke & Silberstein (1977:140-144):: የሚመረጠው ምንባብ፥

- ከተማሪዎቹ ማህበረ-ባህላዊ አውድ ጋር የሚጣጣም ይዘት ያለው፥
- ተማሪዎች አያውቁትም ተብሎ የሚገመት ርእስ ጉዳይን ወይም መልእክትን ያዘለ፥
- የሌሎች ሰዎችን አመለካከት ከራሳቸው ጋር እንዲያነጻጽሩ የሚያግዝ፥
- አንድን ጉዳይ በጥልቀት ለመመርመር እንዲነሳሱ የሚገፋፋ፥
- የረጅም መልእክቶችን ፍጻሜ ለማወቅ የሚያጓጓ፥
- ከተማሪዎች እውቀት አድማስ ጋር የሚጣጣም ይዘት ያለው ወይም አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን የሚፈታተን፥
- ለደረጃቸው የሚመጥኑ የተወሰኑ እንግዳ ቃላትን ያካተተና ያንዳንዶቹ ፍችም ከአውዳቸው ሊታወቅ የሚችል፥
- ምርምራዊ ለሆነ ቀጣይ ንባብ የሚያነሳሳ፥
- የፈሊጦችን፥ የዘይቤዎችን፥ የምሳሌያዊ አነጋገሮችን ወዘተ. አገባባዊ ሚና ለማስተማር የሚረዳ፥
- በቂ የሆነ ስነፍችያዊና አገባባዊ ፍንጮችን ያካተተና መካከለኛ ርዝመት ያለው፥ መልእክቱም ያልተቆራረጠና የተሙዋላ፥

- ለክርክርና ለውይይት በር የሚከፍት፥
- አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎችን ለማዘጋጀት አመቺ የሆነ፥
- ካርታ፥ ግራፍ፥ ሰንጠረዥ በመሳሰሉት መግለጫዎች ሊደገፍ የሚችል መሆን አለበት።

በተጨማሪም የማስተማሪያ ምንባቦች በደረጃው ለሚገኙት ተማሪዎች ተስማሚ ይዘት ያላቸውና የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር የሚረዱ ስልቶችን ለማስተማር የሚያግዙ መሆን አለባቸው። ተማሪዎች ራሳቸውን የቻሉ ውጤታማ አንባቢዎች ለመሆን የሚችሉት በቋንቋ ይዘት ማስተላለፍ የሚቻልና በቋንቋ የተላላፈውን ይዘት ከቋንቋው ውስጥ ለመረዳት የሚያስችሉ የንባብ ስልቶችን ሲያዳብሩ ነው። Nuttall (1982:31) እንደሚሉት ምንባቦቹ መመረጥ ያለባቸው እነዚህን ስልቶች ለማዳበር ከሚኖራቸው ድርሻ አንጻርም ታይተው ነው።

ቀደም ሲል ከተጠቀሱት የምንባብ መምረጫ መስፈርቶች ቢቻል ሁሉንም፥ ባይቻል ደግሞ በከፊል የሚያሟሉ ምንባቦች ሊመረጡ ይችላሉ። የሚኖርባቸውን ክፍተት ለማጥበብ በመልመጃዎችና ተዛማጅ ስራዎች ሊጠናከሩ ይገባቸዋል።

## 2.2.5.2. አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች (መልመጃዎች) አይነት

ንባብ የተለያዩ ስልቶችን ያካትታል። እነዚህን የተለያዩ ስልቶች በአንድነት ለማዳበር ደግሞ በተለያዩ ጥያቄዎች መገልገል አስፈላጊ ነው። በተለያዩ ጥያቄዎች የመገልገሉ ሀሳብም የሚመነጨው ሁለት አበይት ጠቀሜታዎች ስላሉት ነው (Grellet 1981:5)።

ሀ. የምንባቡን አወቃቀር ለመረዳት፡- ጥያቄዎቹ የምንባቡን አወቃቀር አስመልክተው ሊቀርቡ ይችላሉ።

ለ. የምንባቡን ይዘት ለመረዳት፡- ጥያቄዎቹ የምንባቡን ይዘት አስመልክተው ይቀርባሉ። የምንባቡን ይዘት በተመለከተ የሚቀርቡት ጥያቄዎች በምንባቡ ውስጥ በቀጥታ የተገለጹ እውነታዎችን የሚጠቁሙ አለያም እነዚህን እውነታዎች በማገናዘቢያነት በመጠቀም የሚመለሱ ሊሆኑ ይችላሉ።

Brumift et al (1980:105) ለማስተማር የሚዘጋጁ ጥያቄዎች በርከት ብለው መዘጋጀት እንዳለባቸው ይገልጻሉ። እነዚህ ጥያቄዎች በአይነታቸው በአምስት ሊመደቡ እንደሚችሉ ደግሞ Nuttall (1982:132) ጠቁመው እንደሚከተለው ይዘረዝሩዋቸዋል። እነዚህም፤

ሀ. ቀጥተኛ ጥያቄዎች (**Questions of Literal Comprehension**)፡- እነዚህ ጥያቄዎች ከሚቀርበው ምንባብ ውስጥ በቀጥታ ሃሳቡን ቃል በቃል በመውሰድ የሚመለሱ ናቸው።

ለ. ማገናዘብና ማቀናበርን የሚፈልጉ ጥያቄዎች (Questions involving reorganization or reinterpretation):- ተማሪዎች የተለያዩ ሃሳቦችን ከምንባቡ በመፈለግ የተጠቃለለ ሃሳብ እንዲያቀርቡ የሚያግዙ ናቸው:: በተጨማሪም ተማሪዎች የምንባቡን ፍሬ ሃሳብ ተረድተው በራሳቸው አባባል እንዲያቀርቡ የሚያደርጉ ጥያቄዎችን ያካትታሉ::

ሐ. አንድምታዊ ግንዛቤ የሚፈልጉ ጥያቄዎች (Questions of inference):- እነዚህ ጥያቄዎች በክብደት ደረጃቸው ከላይ ከተጠቀሱት ላቅ ያሉ ናቸው:: ተማሪዎች የምንባቡን አጠቃላይ መልእክት በዝርዝር ለመረዳት ምንባቡን በጥልቀት እንዲመረምሩ የሚጠይቁ መሆናቸውን Nuttall ይጠቁማሉ::

መ. የግምገማ ጥያቄዎች (Questions of evaluation):- የምንባቡን ጠቅላላ መልእክት በመገንዘብ ገምግመው የራሳቸውን አስተያየት እንዲያክሉ፥ ከደራሲው ሃሳብ እንዲስማሙ ወይም እንዲተቹ የሚጋብዙትን ጥያቄዎች ያካትታሉ፡

ሠ. የግል አስተያየትን የሚጠይቁ ጥያቄዎች (Questions of personal response):- በዚህ ስር የሚመደቡት ጥያቄዎች የተማሪዎቹን የግል አስተያየትና አመለካከት የሚፈልጉ ናቸው::

Nuttall የሚያቀርቡዋቸው አምስቱ የመልመጃ አይነቶች በመግቢያ የተዘረዘሩትን መሰረታዊ አንብቦ የመረዳት ዘርፎች የሚያዳብሩና በቀጥታም የሚዛመዱ ናቸው:: የመልመጃ ጥያቄዎቹን እንደአስፈላጊነቱ በተናጠል ወይም በቅንጅት መጠቀም ይቻላል:: በመሆኑም በአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ዝግጅት የሚተኮርባቸው ነጥቦች ናቸው::

#### 2.2.5.3. አንብቦ የመረዳት ፈተና (reading comprehension test) አይነቶች

አንብቦ የመረዳት ፈተና አላማ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ ለመመርመርና በተማሪዎቹ መካከል የችሎታ መበላለጥ መኖር አለመኖሩን እንዲሁም ከልምምዱ በኋላ ልምምዱ ያስገኘውን ውጤት ለመለካት ነው:: ስለዚህ አንብቦ የመረዳት ፈተና ሶስት ነገሮችን ማሟላት አለበት:: እነዚህም ምንባብ፥ ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎችና የጥያቄዎቹ መልሶች ናቸው:: ከዚህም ሌላ ምንባቡም ሆነ ጥያቄዎቹ ከተማሪዎቹ ዳራዊ እውቀት ወይም ችሎታ ጋር ሊገናዘቡ ይገባቸዋል:: እንደ ምሁራኑ አገላለጽ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት የሚወሰነው በቀረበው ምንባብ፥ ከምንባብ በወጡ ጥያቄዎችና ተማሪዎቹ ምንባቡን በተመለከተ በሚኖራቸው ዳራዊ እውቀት ነው:: በዚህም የተነሳ ሶስቱ ነጥቦች ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ እንደሆነ Weir (1993)፥ Madeson (1983) እና Hughes (1989) ያስረዳሉ::

አንብቦ የመረዳት ችሎታን በተለያዩ የጥያቄ አይነቶች መገምገም ቢቻልም ዋና ዋናዎቹ ምርጫ-ሰጭ (multiple-choice) እና ክፍት ጨራሽ (open questions) መሆናቸውን Madeson ሲገልጹ Brumfit et al (1980)፥ Seliger & Shohamy (1989)፥ Heaton (1988)፥ Wixson & Lipson (1986)፥ Carrell et al (1989) ደግሞ የእውነት/ሀሰት (true/false)፥ ከዐረፍተነገሮች ሃሳቦች ጋር እስማማለሁ ወይም አልስማማም (agree/disagree) የሚሉትን ሊጨምር እንደሚችል ይጠቁማሉ።

### 2.2.5.3.1. የምርጫ-ሰጭ ጥያቄዎች

Madeson (1983፡89) አንብቦ መረዳትን ለመገምገም ተመራጩ መንገድ ምንባቡ በምርጫ-ሰጭ ጥያቄዎች ታጅቦ የሚቀርብበት እንደሆነ ይጠቁማሉ። በፈተናው ውስጥ የሚካተቱት ምንባቦች ብዛት የሚወሰነው እንደፈተናው አላማ ሲሆን የጥያቄዎቹ ብዛት ደግሞ ለፈተናው በቀረቡት ምንባቦች ብዛትና ርዝመት ይወሰናል። በሌላም በኩል የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የምንባቡ ክብደት ለጥያቄዎቹ ብዛት መሰረት ሊሆን ይችላል። ለፈተናው የተመረጠው ምንባብ የተለያዩ ሃሳቦችንና ዝርዝር ሁኔታዎችን በማነጻጸር ከ100 ቃላት የማይበልጥ ከሆነ ከ3-4 ጥያቄዎች ሊወጡበት ይችላል። የጥያቄዎች ብዛት ከተጠቀሰው በላይ ከሆነ አላስፈላጊ ዝርዝር ውስጥ ስለሚያስገባ መብለጥ የለበትም፤ ከዚህ ካነሰም ተማሪዎች በትክክል መረዳታቸውን ለመለካት አስተማማኝ አይሆንም (Madeson 1983፡90)።

Brumfit et al (1980፡107) ደግሞ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመለካት የሚዘጋጅ የምርጫ ሰጭ የምንባብ ፈተና ከ10-12 የሚሆኑ ጥያቄዎቹ ሊወጡት እንደሚገባው ያመለክታሉ።

በምርጫ ሰጭም ሆኑ በሌሎች ጥያቄዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመለካት መሰረቱ ምንባቡ እንደመሆኑ መረጣው ላይ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን Madeson (1983፡95) እና Brumfit et al (1980፡105) ያስገነዝባሉ። ይህም ምንባቦቹ ለተወሰኑ ተማሪዎች የተለየ ጥቅም የሚሰጡ እንዳይሆኑ ምንባቦቹ ከተለያዩ ምንጮች የተመረጡ ቢሆኑ የተሻሉ እንደሚሆኑ ለመጠቆም ነው።

ምርጫ-ሰጭ ጥያቄዎች በስፋት ቢሰራባቸውም ደካማ ጎን እንዳለባቸውም ምሁራኑ ሳይጠቅሱ አላለፉም። እነሱም፡-

ሀ. የተማሪዎችን ንቁ ተሳትፎ አለመጠየቃቸው።

ለ. ተማሪዎችን ለስህተት ማጋለጣቸው።

ሐ. ተማሪዎች ምንባቡን ሳያነቡ በግምት እንዲመልሱዋቸውና ትክክለኛ መልስ የሚያስገኙ መሆናቸው ናቸው /Madeson 1985፡95፥ Hughes 1989፡116-132/።

### 2.2.5.3.2. ክፍት ጨራሽ ጥያቄዎች

በምርጫ ሰጭ ጥያቄዎች ላይ የተጠቆሙት ድክመቶች በመኖራቸው ምክንያት ድክምታቸውን በሌላ ለማጠናከርና ለማደጋገፍ ሲባል ክፍት ጨራሽ ጥያቄዎችን መጠቀም እንደሚያስፈልግ Madeson ይገልጻሉ:: እነዚህ ጥያቄዎች ተማሪዎችን የበለጠ እንደሚያሳትፉ Madeson ጠቁመዋል:: ጠንካራ ጎናቸውም በግምት በትክክል የማይመልሱ መሆናቸው ነው:: አቀራረባቸው በቀጥታ በምንባቡ የተገለጸውን መልእክት ከመጠየቅ በተጨማሪ ማገናዘብንና ማብራራትን እስከ መጠየቅ ሊለያይ ይችላል:: ክፍት ጨራሽ ጥያቄዎች በጽሁፍ የሚመለሱ በመሆናቸው ከንባብ የበለጠ ወደ ጽህፈት ያደላሉ የሚል አሉታዊ አስተያየት ይሰነዘርባቸዋል::

### 2.2.5.3.3. የእውነት/ሀሰት ጥያቄዎች

የእውነት/ሀሰት ጥያቄዎች ተፈታኞች ባነበቡት መልዕክት ላይ ተመስርተው የሚቀርቡ ሲሆኑ የቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ሃሳብ እውነት ወይም ሀሰት መሆኑን እንዲያመለክቱ የሚጠይቁ ናቸው:: የምንባቡን ሃሳብ አገናዝበው እንዲመልሱ ስለሚጋብዝ አንብቦ የመረዳት ችሎታን በተሻለ መንገድ ለመመዘን የሚያስችሉ ጥያቄዎች መሆናቸውንም Heaten (1988፡113) ያስረዳሉ:: ጥያቄዎቹ ለአስተራረምና ለውጤት አመዛጋገብ ስለማያስቸግሩ ከእውነት/ሀሰት የፈተና አይነት የሚገኘው ውጤት አስተማማኝ ነው:: ይሁን እንጂ በግምት ሊመለሱ ይችላሉ የሚል አሉታዊ አስተያየትም ይሰነዘርባቸዋል::

ከላይ ከተጠቀሱት የፈተና አይነቶች ጋር አልፎ አልፎ የቃላት ጥያቄዎች ሊታከሉ ይችላሉ:: ቃላቱ ከምንባቡ አጠቃላይ መልእክት ጋር ተዛምዶው ሊፈቱ በሚችሉበት መንገድ

ቀርበው÷ በምርጫ ሰጭ ጥያቄዎች መልክ ቢዘጋጁ የተሻለ እንደሚሆን Madeson (1983፡16) ያብራራሉ::

# ምእራፍ ሶስት

## የአጠናን ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋነኛ አላማ የ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ እንደ አንድ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማዳበሪያና ማስተማሪያ ዘዴ ቢያገለግል የሚኖረውን ተግባራዊነትና ውጤታማነት መመርመር ነው:: ለዚህም ጥናቱ የተከተለው አቢይ የአጠናን ዘዴ መላምቶችን በመምታት ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ በስታትስቲካዊ ትንታኔ በመታገዝ በተግባር የተደገፈ ምርምር የሚካሄድበት መጠናዊ የምርምር ዘዴን (Quantitative Method) መከተል ነው:: ለተግባራዊነቱም የእውን ፍትነት (True-experiment) አካል የሆነውን የሁለት ቡድን የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት ፈተና የአጠናን ዲዛይን (The before-after two group design) በስራ ላይ ውሏል:: የዚህ የአጠናን ዲዛይን ጽንሰ ሃሳብ ሁለት ተጠኚ ቡድኖች ምንም ሳይማሩ በወሰዱት ፈተናና በተለያየ ሁኔታ ከተማሩ በኋላ በሚወስዱት ፈተና የሚያሳዩት የችሎታ ልዩነት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የሚያሳይ ነው (Dyer 1995:205÷ Koul 1996:467÷ Seliger & Shohamy 1989:141)::

Seliger & Shohamy (1989)÷ Dyer (1995) እና Hatch & Farhady (1982) እንደሚሉት የሁለት ቡድን የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት ፈተና የአጠናን ስልት አንድ አዲስ የማስተማሪያ ዘዴ (በሙከራዊ ሁኔታ ብቻ) በስራ ላይ በሚውልበት ጊዜ በሁለቱ ተጠኚ ቡድኖች መካከል የታየ የውጤት ለውጥ ካለ የሚገመገምበት ነው:: ስለዚህ ጥናቱ በሚከተለው ቅደም ተከተል መሰረት ተግባራዊ ሆኗል፤

1. በእጣ ናሙና ሁለት ተጠኚ ቡድኖችን በመምረጥ÷
2. ሁለቱን ተጠኚ ቡድኖች በእጣ የምደባ ስልት በሙከራዊ ሁኔታ /Experimental Condition/ እና በቁጥጥር ሁኔታ (Control Condition) በመመደብ÷
3. ለሁለቱም ቡድኖች ተመሳሳይ የቅድመ ትምህርት ፈተና (T1) ሰጥቶ እስታትስቲካዊ መረጃዎችን ማለትም አማካዩን (Mean) እና መደበኛ ልይይቱን (Standard deviation) በማውጣት በመካከላቸው የችሎታ መበላለጥ መኖር አለመኖሩን በማረጋገጥ÷
4. በሙከራዊ ሁኔታ የተመደቡትን ተጠኙ ተማሪዎች ለስድስት ሳምንታት በአዲሱ የማስተማሪያ ዘዴ (በ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል የትምህርት አቀራረብ መርሆዎች) በማስተማር÷

5. በቁጥጥር ሁኔታ የተመደቡትን ተማሪዎች ደግሞ ተጠኚዎቹን ለማስተማር በተዘጋጁት ምንባቦችና መልመጃዎች በመደበኛው መምህር ቀደም ብሎ ይጠቀምበት በነበረው ዘዴ (ልማዳዊው የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ) ለስድስት ሳምንታት እንዲማሩ በማድረግ፥
6. ለሁለቱም ተጠኚ ቡድኖች ተመሳሳይ ድህረ ትምህርት ፈተና (T2) ሰጥቶ የሁለቱን ቡድኖች የፈተና ውጤት በማነጻጸር በተለይ በሙከራዊ ሁኔታ ውስጥ የተመደቡት ተማሪዎች ከአዲሱ የማስተማሪያ ዘዴ የተነሳ ያመጡት የውጤት ለውጥ በቁጥጥር ቡድኑ ውስጥ ከተመደቡት የተሻለ ከሆነ ከቅድመ ትምህርት ውጤት ጋር በማነጻጸር እስታትስቲካዊ መረጃዎችን በማጠናቀር፥
7. በተጠኚ ቡድኖች መካከል የታየው የውጤት ለውጥ እስታትስቲካዊ ጉልህነት (Statistical Significance) እንዳለው በእስታትስቲካዊ የስሌት ስልት በማረጋገጥ፥
8. ድህረ ሙከራ አስተያየት ለመሰብሰብ እንዲቻል በሙከራዊ ሁኔታ የተማሩትን ተማሪዎች ስለልምምዱ ያላቸውን ሃሳብ እንዲገልጹ የጽሁፍ መጠይቅ በማስሞላት፡፡

ከላይ የተጠቆሙትን የአጠናን ቅደም ተከተሎች በመጠቀም በኢትዮጵያ ትቅደም ቁጥር አንድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9$^{I}$ የሚገኙትን ተማሪዎች በሙከራዊ ሁኔታ (experimental Condition) እንዲማሩ የ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል የትምህርት አቀራረብ ዘዴን በመከተል፥ በ9$^{A}$ የሚገኙትን ተማሪዎች ደግሞ በቁጥጥር ሁኔታ (Control Condition) በማስተማር የተለያዩ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

ሙከራዊ የምርምር ዘዴን በመከተል በሙከራዊ ሁኔታ የተመደቡትን ተጠኚ ተማሪዎች በተጠቀሰው የማስተማሪያ ዘዴ አጥኚው ለስድስት ሳምንታት እያስተማረ በክፍል ውስጥ የሚካሄደው የንባብ ትምህርት ልምምድ ጠቅላላ አፈጻጸም፥ ተግባራዊነትና በመጨረሻም የሚያስገኘው ውጤት ምን እንደሚመስል ለማሳየት የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ የትምህርት ቤትና የተማሪዎች አመራረጥ፥ የምንባቦች አመራረጥና የመልመጃዎች ዝግጅት ዘዴ፥ የመረጃ መሰብሰቢያ እና የመረጃ አተናተን ዘዴዎች ይቀርባሉ፡፡

## 3.1. የትምህርት ቤትና የተማሪዎች አመራረጥ

### 3.1.1. የቅድመ ሙከራ ጥናት

በቅድመ ሙከራ ጥናት መረጃዎችን ማሰባሰብ ለሙከራ ምርምር የሚጠቅሙ መነሻ ሃሳቦችን ለማግኘት እንደሚረዳ Cohen & Manion (1980:158-159) እና Hatch & Farhady (1982:19) ይገልጻሉ፡፡ ስለሆነም የቅድመ ሙከራው አቢይ አላማ በአሁኑ ወቅት በአማርኛ

ትምህርት ክፍለ-ጊዜ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር በተግባር የሚውለውን የንባብ ትምህርት አቀራረብና ክንውን ይዞታ በቅድሚያ በመቃኘት ዳራዊ መረጃ ማግኘት ነው::

የቅድመ ሙከራ ጥናቱ የተካሄደው በአዲስ አበባ ከተማ ሲሆን በክልሉ ከሚገኙት የመንግስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በአመቺነት ንሞና (Convenience Sampling) በተመረጡት የእንጦጦ የቀለም፥ የሙያና የቴክኒክ ትምህርት ቤት፥ በየካቲት 12 አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፥ በምኒሊክ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በኮልፌ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ1991 ዓ.ም ከተማሩት የዘጠነኛ ክፍል ምድቦች መካከል በትምህርት ቤቶቹ ቅደም ተከተል መሰረት አራት አራት በአጠቃላይ አስራ ስድስት የመማሪያ ምድቦች በእጣ ተመርጠው ምልከታ ተካሄዶባቸዋል::

### 3.1.2. የሙከራ ጥናት

የዚህ ጥናት መነሻ ሀሳብ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር በክፍል ውስጥ በማስተማር የ"ቶፕዳውን" ሞዴል ምን ያህል ተግባራዊነትና ውጤታማነት እንደሚኖረው ማረጋገጥ ሲሆን ለጥናቱ የሚያስፈልገውን ክፍለ ጊዜ በተራ የእጣ ናሙና (random sampling) ማግኘት አስቸጋሪ በመሆኑ የአመቺነት ናሙና ዘዴን (convenience sampling) (Zinser 1984:142) እና Cohen & Manion (1980:76) መጠቀም አስፈላጊ ሆኖአል:: ስለሆነም ለጥናቱ የሚያስፈልገውን ክፍለ-ጊዜ በመፍቀድ የኢትዮጵያ ትቅደም ቁጥር አንድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለጥናቱ ተባባሪ ሆኖ በመገኘቱ ተመርጦአል:: ትምህርት ቤቱ የተመረጠው ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ክፍለ-ጊዜ ለመስጠት ፈቃደኛ በመሆኑ፥ የሙከራ ምርምሩ (Pilot Study) የተካሄደበትና ዋናው ጥናት ተጀምሮበት የነበረው የኮልፌ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በድጋሚ ትብብር ተጠይቆ ባለመስማማቱ ነው::

በናሙና በተመረጠው ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የትምህርት ደረጃችው 12+2 የሆኑ ሁለት መምህራን የሚያስተምሩባቸው 14 የዘጠነኛ ክፍል ምድቦች (sections) ይገኛሉ:: ከነዚህ ምድቦች መካከል ሰባት በጠዋት፥ ሰባት ደግሞ ከሰአት በሁዋላ ፈረቃ የሚገኙ ናቸው:: ይሁንና የሙከራ ምርምሩን በሚገባ ለማካሄድም ሆነ ቅድመና ድህረ ልምምድ ፈተናዎችን በተመሳሳይ ሰአት ለመስጠት እንዲቻል ከሁለቱ ፈረቃዎች የጠዋት ፈረቃ በእጣ ተመርጦአል:: በዚህ ፈረቃ ከሚገኙት ሰባት ምድቦች መካከል $9^I$ እና $9^A$ በእጣ ተመርጠው በተመሳሳይ ዘዴ $9^I$ የሙከራ (experimental group) ቡድን፥ $9^A$ የቁጥጥር ቡድን (control group) እንዲሆኑ ተደርጎአል::

በጥናቱ የሚሳተፉት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው:: ተጠኚዎቹ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች እንዲሆኑ የተመረጡበት ምክንያት

ሀ. አብዛኞዎቹ ከተለያዩ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተሰባሰቡ ጀማሪዎች በመሆናቸው ከቀጣዮቹ የክፍል ደረጃዎች በተሻለ መልኩ የወካይነት ባህሪን (representativeness) ስለሚያሙዋሉ እና

ለ. ተማሪዎቹ የሁለተኛ ደረጃ ጀማሪዎች በመሆናቸው በሞዴሉ የትምህርት አቀራረብ ዘዴ ትምህርታቸውን እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ በተከታታይ ልምምድ ቢያደረጉ ጥሩ አንባቢዎች እንዲሆኑ ለመርዳት እንደሚቻል በመታመኑ ነው::

### 3.1.3. የምንባቦች አመራረጥና የመልመጃዎች አዘገጃጀት

የጥናቱ አላማ በ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል መርሆዎች አማካይነት በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ማስተማር ስለሚቻልበት ሁኔታ ለመፈተሽ መሆኑ በጥናቱ ዳራ በአላማው ስር ተገልጿል:: ማስተማር ሲታሰብ ደግሞ ከተማሪዎች ገጠመኝ፥ እውቀትና ፍላጎት የሚዛመዱ ምንባቦችን መርጦ መጠቀም ያስፈልጋል:: ለዚሁ ተግባራዊነትም የመምረጫ መስፈርቶችን ማገናዘብ እንደሚያስፈልግ አያጠያይቅም::

በመርህ ደረጃ የምንባቦች አመራረጥና የሚመረጡት ምንባቦች ማሟላት ያለባቸው መምረጫ መስፈርቶች በምዕራፍ ሁለት በዝርዝር ቢገለጽም፥ ለዚህ ጥናት እንዲውሉ የተመረጡት ምንባቦች የተመረጡበትን መንገድና ምክንያት ማመልከቱ አስፈላጊ ይሆናል::

በሙከራ ጥናቱ (pilot study) ወቅት ለማስተማሪያነት የዋሉት አምስት ምንባቦች ነበሩ:: የመጀመሪያው፥ "የቋንቋ ተግባራት" በሚል ርዕስ ከመደበኛው የመማሪያ መጽሃፋቸው የተወሰደ ነው:: ሁለተኛው፥ "የንግግር ችሎታ" በሚል ርዕስ የቀረበና <u>ታላላቅ ሰዎች</u> ከሚለው የከበደ ሚካኤል መጽሃፍ የተመረጠ ነበር:: ሶስተኛው፥ "የጥንቱ የአኑዋኑዋርና የአስተሳሰብ ስርዓት" የሚል ርዕስ የተሰጠውና ከሀዲስ አለማየሁ <u>የልምዣት</u> መግቢያ የተወሰደ፥ አራተኛው፥ "ኤድስና የመከላከያ ዘመቻ" በሚል ርዕስ <u>በአዲስ ዘመን ጋዜጣ</u> ላይ ከታተመ ጽሁፍ የተወሰደና አምስተኛው ደግሞ "ወጣትነት፥ ማህበራዊ ችግሮቹና የመፍትሄ አቅጣጫዎች" በሚል ርዕስ የቀረበና <u>ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ</u> የተወሰደ ነው:: የምንባቦቹ ምንጮች ለተጨማሪ ንባብ በመማሪያ መጽሃፍ አዘጋጆች የተጠቆሙት መጻህፍትና በብዛት ተነባቢ ከሆነው <u>አዲስ ዘመን ጋዜጣ</u> ነው:: ስለሆነም ትምህርቱ ከስርአተ ትምህርቱ ውጭ እንዳይሆን የሚከተሉትን ነጥቦች ከግንዛቤ ውስጥ ለማስገባት ጥረት ተደርጓል፤

- ተማሪዎች የተለያየ ፍላጎትና ዝንባሌ ስላላቸው ምንባቦቹም የተለያዩ ጉዳዮችን መዳሰሳቸው ለብዙዎቹ ተማሪዎች ጥቅም ሲባል ጥሩ እንደሚሆን በመታሰቡ፥

- በልዩ ልዩ ያጻጻፍ ስልት የተጻፉ ምንባቦች ለመልመጃነት ቢቀርቡ የተሻለ ውጤት ሊያስገኝ እንደሚችሉ በመታመኑና
- በምንባቦቹ አማካይነት አጠቃላይ የሆኑ ጉዳዮችን ለማቅረብና ተማሪዎችን ለማሳተፍ እንደሚቻል በመታመኑ ምንባቦቹ ከተለያዩ ምንጮች ተወስደዋል::

በተጨማሪም በርካታ ምሁራን (Clarke & Silberstein 1977÷ Silberstein 1994÷ Aebersold & Field 1997÷ Hyland 1995) እንደሚያብራሩት ከመግቢያ ውይይትና ከማነቃቂያ ዝግጅት በኋላ ተማሪዎች የንባብ ልምምዳቸውን ማካሄድ ያለባቸው በግል በጸጥታ ንባብ ስልት በመሆኑ ለያንዳንዱ ተማሪ የየምንባቦቹን ቅጅ የያዙ ወረቀቶች ታድለዋል:: በዚህ መሰረት በልምምድ ወቅት ተማሪዎች በምን በምን ነጥቦች ላይ ማተኮር እንደሚገባቸውና ምንስ ማከናወን እንደሚኖርባቸው ተገልጾላቸዋል::

ተዘጋጅተው የተሰጡት ምንባቦች በአንድ በኩል የማስተማሪያ ሞዴሉ ተግባራዊ ክንውን መመሪያዎች የሚጠይቁትን የአዘገጃጀት ዘዴ እንዲከተሉና በሌላ በኩል ደግሞ የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ እንዲመጥኑ አድርጎ ማዘጋጀት ጥንቃቄ የጠየቀ ተግባር ነበር:: ለዚህም እንዲረዳ የምንባቦቹ አመራረጥና የመልመጃዎቹ አቀራረብ ቀደም ሲል በሞዴሉ ትምህርታዊ ዕሳቤዎች አማካይነት ጥናት ያካሄዱ ምሁራን ካዘጋጇቸው መልመጃዎች የአቀራረብ ቅርጽ እንዲገናዘብ የተደረገ ሲሆን በዋናነትም Silberstein (1994)÷ Grenall & Swan (1986)÷ Wallace (1992) እና Sequero (1998) ባዘጋጇቸው መልመጃዎች ላይ ተመስርተው እንዲዘጋጁ ተደርገዋል::

ምንባቦቹና መልመጃዎቹ የተማሪዎቹን የክፍል ደረጃ መመጠናቸውን ለማረጋገጥም አንደኛ÷ ከሶስት አመት በላይ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋን ያስተማሩ መምህራን እንዲገመግሟቸውና አስተያየት እንዲሰጡ÷ ሁለተኛ÷ ጥናቱ በተካሄደበት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ አምስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እንዲተቹባቸው ለያንዳንዳቸው የምንባቦቹ ቅጅዎች ታድለዋል:: ስለአዘገጃጀታቸውም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል መምህራን የሆኑ ባለሙያዎች አስተያየት እንዲሰጡባቸውና እንዲገመግሟቸው ተደርጓል ከዚያም ለቁጥጥር ቡድኑ ማስተማሪያነት የሚውሉትን መልመጃዎች የትምህርት ቤቱ መምህራን ከዚህ በፊት በመማሪያ መጽሃፋቸው ውስጥ በቀረቡት መልመጃዎች አቀራረብ መልክ ያዘጋጁ ሲሆን ለሙከራው ቡድን ደግሞ አጥኚው አዘጋጅቷል:: በመጨረሻም ከሙከራው ጥናት የተገኘውን ግንዛቤና ከባለሙያዎች አስተያየት የተገኘውን ገንቢ ሃሳብ በማዛመድ ተገቢነት ያላቸው መልመጃዎች እንዲዘጋጁና ለተጠኚዎቹ እንዲሰራጩ ተደርጓል (ለዝርዝሩ አባሪ መ1 ገጽ 129 እስከ 141 አባሪ መ2 ገጽ 141 እስከ 151 ይመለከቷል)::

በሙከራው ወቅት፥ ሁለቱም ምድቦች ለክፍል ደረጃቸው የሚመጥን ተመሳሳይ የትምህርት ይዘት የተማሩ ሲሆን በመማር ማስተማሩ ሂደት የትምህርት ልምዶች አቀራረብ ልዩነት እንዳይፈጠር አስፈላጊው ጥንቃቄ ሁሉ ተደርጓል::

## 3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

የዚህ ጥናት መረጃዎች የተጠናቀሩት በሚከተሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ነው፤

1. የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎችን ሰጥቶ ውጤቶችን መመዝገብ
2. ጥናቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ስለተከናወኑት ስራዎች የስድስት ሳምንታት የማስተማር ሂደትን የክፍል ውስጥ ክንውን የሚገልጽ የምልከታ ማስታወሻ፥ እና
3. በሙከራዊ ሁኔታ የተጠኑትን ተማሪዎች በ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል ንባብን ከመማራቸው በፊት የነበራቸውን ዳራና ከተማሩ በኋላ ያላቸውን አስተያየት ለማወቅ የጽሁፍ መጠይቅ ማስሞላትና መመዝገብ ሲሆን የእያንዳንዱን መሳሪያ አዘገጃጀትና አጠቃቀም ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን::

### 3.2.1. የፈተና አዘገጃጀትና አፈታተን

በጥናቱ ሂደት የተሳተፉት ተማሪዎች ሁለት ፈተናዎችን ተፈትነዋል:: በቅድሚያ በቁጥጥር ምድቡ (Control group) እና በሙከራው ምድብ (experiemental group) መካከል የችሎታ መበላለጥ የማይታይ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚረዳ ቅድመ ትምህርት ፈተና (Pre-test) በአጥኚው ተዘጋጀ:: ፈተናው የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የተሰናዳ ሲሆን ሁለት ምንባቦችና በስራቸው የተካተቱ አርባ ጥያቄዎችን በተለያዩ ክፍሎች ይዟል:: ፈተናው ተባዝቶ ለተማሪዎቹ ከመሰራጨቱ በፊትም በትምህርት ቤቱ በሚያስተምሩ አምስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና የትምህርት ደረጃቸው ኤም.ኤ. በሆኑ ሶስት ባለሙያዎች ተገምግሞ በተሰጠው አስተያየት እና ተዛማጅ ጽሁፎች ሃሳብ መሰረት ተሻሽሎ ቀርቧል /አባሪ <u>ሀ</u> ገጽ <u>110</u> ይመለከቷል/::

ፈተናው ከተዘጋጀ በኋላ የቁጥጥሩም ሆነ የሙከራው ቡድን አባላት በተመሳሳይ ቀንና ሰአት ከፈረቃ ውጭ ለሁለት ሰአት ያህል እንዲፈተኑት ተደርጓል:: ፈተናው የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ ለማወቅ የታለመ በመሆኑ ተማሪዎቹ ጥያቄዎቹን ከመስራታቸው በፊት ምንባቦቹን በጥሞና ማንበብ እንዳለባቸው ተገልጾላቸዋል:: በተጨማሪም ተፈታኞቹ ፈተናውን በተገቢው መንገድ በጥንቃቄ እንዲሰሩት ለማድረግ መደበኛ መምህራን ፈተናው ከመሰጠቱ አስቀድሞ በሁለቱም ቡድኖች ዘንድ ተገኝተው በአንደኛ ሴሚስተር ውጤታቸው ላይ እንደሚደመርላቸው ገልጸውላቸዋል:: የፈተና ወረቀቶቹ ተሰብስበው ከታረሙ በኋላ በተገኘው ውጤት መሰረት በሁለቱ ቡድኖች መካከል የችሎታ መበላለጥ የማይታይ መሆኑን ለመረዳት ተችሎአል:: (ሰንጠረዥ 2 ገጽ 69 ይመልከቱ)::

ከዚህ ቀጥሎ አጥኚው የቁጥጥሩን ምድብ ለሚያስተምረው መምህር የአተገባበሩን ዝርዝር በመግለጽ ምድቡን በተለመደው ዘዴ ብቻ እንዲያስተምር ካሳሰበ በኋላ ተግባራዊነቱን ለመከታተል ምልከታ አድርጓል። የሙከራ ቡድኑን ግን በ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል የትምህርት አቀራረብ ዘዴ በሳምንት ሶስት ክፍለ ጊዜያት፥ ባጠቃላይ ለስድስት ተከታታይ ሳምንታት ማለትም ከመስከረም 23/1992 እስከ ህዳር 8/1992 ድረስ ትምህርታዊ ልምምዱን እንዲከታተሉ ተደርጓል።

በመጨረሻም ልምምዱ ከተጠናቀቀ በኋላ በቅድመ ልምምድ የተሰጠውን ፈተና በድህረ ልምምድም እነ Carrell & Floyed (1987:91)፥ Carrell, Liber to & Pharis (1989:660) Seliger & Shohamy (1989:102) እና Bejarano (1987:490) እንደሚሉት በተመሳሳይ መንገድ እንዲፈተኑት ተደርጓል።

የድህረ ልምምድ ፈተናው አላማ በ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል የትምህርት አቀራረብ ዘዴ የተማረው የሙከራው ቡድን በችሎታ ብልጫ አሳይቶ እንደሆነ ለማወቅ በመሆኑ ተጠኚዎቹ ፈተናውን በጥንቃቄ እንዲሰሩት አስፈላጊው ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል። ከማስጠንቀቂያውና ከማብራሪያው ቀጥሎ እንደ ቅድመ ልምምድ ፈተናው ሁሉ ተማሪዎቹ በተመሳሳይ ቀንና ሰአት ከፈረቃ ውጭ ለሁለት ሰአት ተፈትነውታል። በአጠቃላይ፥ የፈተናዎቹ አዘገጃጀት ተጨባጭ በመሆኑ (ለምዘናው የተመረጡት የጥያቄ አይነቶች የምርጫ-ስጭ፥ የእውነት/ሀሰት፥ የቃላት ፍች እና የክፍት ጨራሽ ጥያቄዎች ናቸው) ለአስተራረም ስለማያስቸግር (Madesen 1983፥ Carrell and Floyed1987፥ Hughes 1989፥ Weir 1990) በአጥኚው ታርመዋል።

### 3.2.2. ለተማሪዎች የተሰራጨ የጽሁፍ መጠይቅ

ለተማሪዎች የተሰራጨው የጽሁፍ መጠይቅ የሚከተሉት አላማዎች ነበሩት። አንደኛ፥ በሙከራው ቡድን ውስጥ የታቀፉትን ተጠኚ ተማሪዎች ዳራ የአፍ መፍቻ ቋንቋ፥ ዕድሜ፥ ጾታ፥ የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የተከታተሉበትን ትምህርት ቤት ለማወቅ፥ ሁለተኛ በ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል ንባብን ከመማራቸው በፊትና ከተማሩ በሁዋላ ስላለው ሁኔታ የተማሪዎችን አጠቃላይ አስተያየት ለማወቅ የቀረበ ነበር። በዚሁ መሰረት መጠይቁ ሁለት ክፍሎች እንዲኖሩት ተደርጎአል። የመጀመሪያው ክፍል የተማሪዎችን እድሜ፥ ጾታ፥ አፍ የፈቱበትን ቋንቋና በትምህርት ቤታቸው የስነጽሑፍ፥ የጋዜጠኝነት፥ እና የሚኒሚዲያ ክበባት ተሳትፎ ማድረግ አለማድረጋቸውን የሚጠይቁ ጠቅላላ መረጃን የሚሹ ጥያቄዎችን ይዞአል።

ሁለተኛው ክፍል ሀያ አንድ ጥያቄዎች ሲኖሩት ከአንድ እስከ አምስት ያሉት ቅድመ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን የሚመለከት መረጃ ለማግኘት የቀረቡ ሲሆኑ ከስድስት እስከ ሀያ አንድ ያሉት ጥያቄዎች ደግሞ ከልምምድ በሁዋላ ተማሪዎቹ ስለልምምዱ አቀራረብ

ያላቸውን አስተያየት ለማወቅ የቀረቡ ናቸው፡፡ የጥያቄዎቹ አቀራረብ በጥያቄዎቹ ሃሳብ መስማማትንና አለመስማማትን የሚጠይቅ ነበር፡፡ ይህንንም ለመጠየቅ የቀረቡት አማራጮች የሚከተሉት ናቸው፤

ሀ. በጣም እስማማለሁ

ለ. እስማማለሁ

ሐ. አልስማማም

መ. በጣም አልስማማም

በክፍል ሁለት የቀረቡት እነዚህ ጥያቄዎች በሊከርት የደረጃ እስኬል (Likert rating scale) መሰረት የተዘጋጁ ሲሆን ተማሪዎች በመልስ አሰጣጡ ወቅት ወደ ገለልተኛው እንዳያዘነብሉ ለመከላከል ሲባል ምርጫዎቹ ከአምስት ወደ አራት ዝቅ እንዲሉ ተደርገው ቀርበዋል /Seliger & Shohamy 1989:173/፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ተማሪዎቹ ስለ "ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል ምንነት ተገልጾላቸው ልምምድ ካካሄዱ በሁዋላ የሚኖራቸውን ተጨማሪ አስተያየት እንዲሰጡ በ21ኛው ጥያቄ ስር ክፍት ቦታ ተትቶአል፡፡ ጥያቄዎቹ ተዘጋጅተው በእስቴንስል ከመቀረጻቸው በፊት ሁለት መምህራንና ሁለት የትምህርት ስነልቡና የድህረ ምረቃ ተማሪዎች እንዲገመግሙዋቸው ተደርጎአል፡፡ በዚህም ሂደት በመጠይቁ የቀረቡትን ጥያቄዎች ግልጽነትና የአቀራረብ ቅርጽ ትክክለኛነት ውጫዊ በሆነ መንገድ ለማረጋገጥ ጥረት ተደርጎአል፡፡ /አባሪ ለ ገጽ 116 ይመለከቷል)፡፡

በአጠቃላይ፥ መጠይቁ የተዘጋጀው ለሙከራ ምርምሩ አጋዥ የሚሆኑ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ስለሆነ፥ በመጠይቁ ውስጥ የተካተቱት ጥያቄዎች በክለሳ ድርሳናት ወቅት በተመራማሪዎች የተነሱት ነጥቦች ባህሪያትና የሞዴሉን ስነትምህርታዊ መርሆዎች ከግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ ሆነው ተዘጋጅተዋል፡፡ መጠይቁም ከመሞላቱ በፊት ስለመጠይቁ አላማ፥ ስለመጠይቁ ክፍሎች፥ ጥያቄዎች እና ስለጥያቄዎች አመላለስ በምሳሌ የተደገፈ ማብራሪያ በአጥኚው ተሰጥቶአል፡፡ ከማብራሪያው ቀጥሎ መጠይቁ በክፍል ውስጥ ተሞልቶ ሲያበቃ ወዲያው ተሰብስቦአል፡፡ ተሞልቶ የቀረበውን መጠይቅ ውጤት አስተማማኝነት ለማረጋገጥም እስታትስቲካዊ ስሌት በመጠቀም ለማረጋገጥ ተሞክሮአል፡፡ ለዚህም የ Cornback Alpha ቀመር የአስተማማኝነት ፍተና (relaibality testing) በመጠቀም የተገኘው ውጤት (0.98) ሆኖአል፡፡ ይህ ውጤት Seliger & Shohamy (1989:187) ከሚጠቀሙት 0.7 በላይ በመሆኑ ለተማሪዎቹ የቀረበላቸውን መጠይቅ አስተማማኝነት የሚያረጋግጥ ነው፡፡ (አባሪ ሠ ገጽ 152-153 ይመለከቷል)፡፡ መጠይቁም የተሞላው የንባብ ትምህርት ልምምዱ ካበቃና ተማሪዎች ድህረ ልምምድ ፈተና ከተፈተኑ ከሁለት ቀን በሁዋላ ነው፡፡

በመማሪያ ክፍል ውስጥ ገቢራዊ የሚሆነውን የማስተማሪያ ዘዴ የሚመለከት መረጃ ለመሰብሰብ ከሚያገለግሉት መሳሪያዎች አንዱ ምልከታ መሆኑን Koul (1996:168) እና Seliger & Shohamy (1989:165) ይገልጻሉ:: በአማርኛ የንባብ ትምህርት የሙከራ ልምምድ ክፍለ-ጊዜ የተካሄደው ምልከታ አላማም ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ተረድተው በስራ መተርጎማቸውን፥ እንዲሁም በክንውኑ ወቅት ተማሪዎቹ የስራ ድርሻቸውን በሚገባ ማከናወናቸውን ለማወቅ የሚረዳ አጋዥ መረጃ ለመሰብሰብ በመሆኑ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ነጥቦች በውሱን ጽሁፋዊ ምዝገባ (Written ethnography) በመጠቀም በዝርዝር እንዲመዘገቡ ተደረገ (Richards & Nunan 1990):: ለዚህም ሲባል ምልከታው በተሳታፊ ተመልካችነት (Participant Observer) መልክ እንዲካሄድ የተደረገ ነው:: ምክንያቱም የሞዴሉ ስነ ትምህርታዊ መርሆ ተማሪዎችን በማሳተፍ ልምምዱን በስሩት ማካሄድ ስለሚፈልግ አጥኚው በሂደቱ የአስተባባሪነት ሚና በመጫወቱ ነው::

ስለዚህም ለምልከታው ስኬት በአባሪ ሐ ገጽ 119 እስከ 128 እንደተመለከተው የሚከተሉት ተግባራዊ ሆነዋል::

ሀ. ተማሪዎች በትምህርታዊ ልምምዶቹ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የልምምዱ አላማና ሂደት ተገልጾላቸዋል::

ለ. ተማሪዎች በንባብ ልምምድ ወቅት ስለሚያነቡት ምንባብ ይዘት እንዲገምቱና ከምንባቡ ያገኙትን ሃሳብ ከግምታቸው ጋር እንዲያስተያዩ፥ በዚህም ላይ ውይይት እንዲያደርጉ በጥንድና በቡድን ማደራጀት አስፈላጊ በመሆኑ ተማሪዎች በቡድን ተደራጅተዋል::

ሐ. ተማሪዎች የንባብና አንብቦ የመረዳት ችሎታን ምንነት፥ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር የሚደረገውን ልምምድ፥ እንዲሁም በ"ቶፕዳውን" የማስተማሪያ ሞዴል የሚተኮርባቸውን ዋና ዋና ነጥቦች አስመልክቶ ትምህርት ተሰጥቶአቸዋል:: በዚህም ተማሪዎች የዘዴውን ምንነትና አጠቃቀም አውቀው በልምምዱ ወቅት ተግባራዊ እንዲያደርጉዋቸው ለመርዳት ነው::

መ. የልምምድ መልመጃዎችን በግልም በቡድንም በሚሰሩበት ጊዜ ለሚያቀርቡዋቸው መልሶች ከምንባቡ ተጨማሪ ማብራሪያ ማቅረብ እንደሚገባቸውና የምንባቡን መልእክት እንዲገመግሙት ማብራሪያ ቀርቦላቸዋል::

## 3.3. የክፍል ውስጥ የትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች

የጥናቱ መሰረታዊ አላማ በክፍል ውስጥ ገብቶ በማስተማር የ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴልን ተግባራዊነት መፈተሽ ስለሆነ ለአሰራሩ ትኩረት በመስጠት ትምህርቱ በሚከተሉት መንገዶች ተግባራዊ ሆኗል::

1. ትምህርቱ ከመጀመሩ በፊት ተማሪዎችን ለትምህርቱ ዝግጁ ማድረግ ስለሚያስፈልግ የማነቃቂያ ገለጻ ተደርጎላቸዋል:: ትምህርቱም ከመስጠት አስቀድሞ የሁለቱም ቡድኖች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ እንዲቻል የቅድመ ትምህርት ፈተና ተሰጥቶአል::
2. በየምንባቡ መጀመሪያ ማለትም ተማሪዎቹ ምንባቦቹን በዝርዝር ከማንበባቸውና በይዘቶቻቸው ላይ ውይይት ከማድረጋቸው በፊት በጥያቄዎችና የማነቃቂያ ውይይት አማካይነት ስለምንባቦቹ መልዕክት በግልም በቡድንም እንዲገምቱ አመቺ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ጥረት ተደርጓል:: በነዚህ አማካይነት ተማሪዎቹ ለንባብ አላማ እንዲኖራቸውና እንዲነቃቁ ከተደረገ በኋላ ምንባቦቹን በጸጥታ አንብበው የቀረቡትን የማጠናከሪያ የመልመጃ ጥያቄዎች በግል ሞክረው እንዳበቁ ያገኙትን መልስ ለውይይት እንዲያቀርቡ ተበረታተዋል:: ምንባቦቹን አይተው የሚፈልጉትን ትምህርታዊ ክንውኖች ለመፈጸም እንዲያመችና የግል ተሳትፎን ለማጠናከር ክፍለ-ጊዜ ባላቸው ጊዜ ሁሉ ወረቀቶችን እንዲያመጡ ተነግሯቸው በዚሁ ላይ ቁጥጥር ተደርጓል::
3. ከያንዳንዱ የመልመጃ ምንባብ ስር የተዘጋጁትን ጥያቄዎች በግል ሞክረው ከጓደኞቻቸው በቡድንና በጥንድ እንዲወያዩባቸው፥ ለሚያቀርቧቸው መልሶች ከዕውቀታቸውና ከምንባቡ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ተነግሯቸዋል:: ልምምዱም በዚህ መሰረት ተግባራዊ ሆኗል::
4. በቁጥጥር ሁኔታ የተጠኑት ተማሪዎችም የተዘጋጁት ምንባቦችና መልመጃዎች በመምህራቸው በኩል በነፍስ ወከፍ እንዲደርሳቸው ተደርጓል::
5. በሙከራዊ ሁኔታ የተጠኑት ተማሪዎች በግልም ሆነ በቡድን የሚያቀርቧቸው መልሶችና ከምንባቡ ያገኙት መልዕክት ከቅድመ ንባብ ግምታቸው ጋር የማይጣጣሙ ወይም ሁለቱ የተለያዩ ሲሆን ልዩነቱ ለምን እንደተከሰተ፥ ምንባቡን በድጋሚ አንብበው እንዲመረምሩ፥ ስህተታቸውን እንዲያርሙና በስህተቶቻቸው ላይ እንደገና እንዲወያዩ በማድረግ የቀረቡላቸውን ምንባቦች በሚገባ እንዲመረምሩ ትምህርት ተሰጥቷል::
6. የትምህርቱ አቀራረብ በቅድመ ንባብ፥ በንባብ ጊዜ እና ከንባብ በኋላ በሚከናወኑ ተግባራት ተከፋፍሎ ቀርቧል:: ትኩረቱም ተማሪዎች ትምህርታዊ ልምምዱን ተግባቦታዊ በሆነ መንገድ እንዲለማመዱ መንገድ በማሳየት የቀረበውን ዝርዝር ስራ ተማሪዎች እንዲያከናውኑ አመቺ ሁኔታዎችን መፍጠር ነው (ስለመምህሩና ተማሪዎች ሚና 2.2.4.1. እና 2.2.4.2ን ይመለከቷል)::
7. ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትንና የቋንቋ አጠቃቀምን በምንባቡ ውስጥ ሲያገኙ ከአገባባቸው እንዲፈቱአቸውና በአጠቃላይ መልዕክቱ ላይ እንዲያተኩሩ ጥረት ተደርጓል:: የየግል አስተያየታቸውን በተቻለ መንገድ እንዲሰጡና ይህንንም ከምንባቡ መልዕክት እንዲያዛምዱ በማድረግ በያንዳንዱ አስተያየት ላይ ተጨማሪ ውይይት ተደርጓል::
8. ከአንብቦ መረዳት ልምምዱ ጋር ተዛምዶ የሚነሳው ጉዳይ ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት በተግባር ማዋል አለማዋላቸውን የመከታተሉ ጥረት ነው:: ይኸውም በሞዴሉ የሚተኮርባቸውን የንባብ ስልቶች ተምረው በራሳቸው ጥረት የሚተገብሯቸው

መሆናቸውን መከታተልን የሚጠቁም ነው:: ስለሆነም ለትምህርታዊ ልምምዱ ውጤታማነት የንባብ ስልቶቹን ምንነትና አጠቃቀም አስቀድመው ተምረዋል:: ይህም የተደረገው Barnett (1989)÷ Carrell et al (1989)÷ Swaffar et al (1991) ተማሪዎች እንደምንባቦቹ አቀራረብ የሚጠቀሙባቸውን የንባብ ስልቶች ማለማመዱ ሊተኮርበት እንደሚገባ በመጠቆማቸው የሚኖረው አዎንታዊ ድርሻ ከፍተኛ ሆኖ በመገኘቱ ነው:: (አባሪ ሐ ገጽ 119-128 ይመለከቷል)::

Anderson (1994) እንደሚያስገነዝቡት የተላለፈው ትምህርት ከግብ ደርሶ እንደሆነ ለማረጋገጥ አጥጋቢ መግለጫና ውይይት ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ የሚከተሉት ተግባራት በልምምዱ ወቅት በቅደም ተከተል ተግባራዊ ሆነዋል፤

ሀ. በንባብ ማስተማሪያ ሞዱሉ የሚተኮርባቸውን የንባብ ስልቶች ምንነት የሚመለከት አጥጋቢ ማብራሪያ በየምንባቦቹ ትምህርታዊ ገለጻ ጊዜ ተሰጥቷል::

ለ. ተማሪዎች እንዲማሯቸው የሚታሰቡትን የንባብ ስልቶች ለምን መማር እንዳለባቸው አውቀው ለጥረቱ ስኬት እንዲተጉ የማነቃቂያ ገለጻ ተደርጎላቸዋል::

ሐ. የሚተኮርባቸውን የንባብ ስልቶች እንዴት መጠቀም እንደሚገባቸው በየመልመጃዎቹ አማካይነት ገለጻ ተደርጎላቸዋል::

መ. የንባብ ስልቶቹ በተቻለ መጠን በተማሪዎቹ መተግበራቸውን ለማረጋገጥ ጥረት ተደርጓል:: ለዚህም ተግባራዊነት ውይይት÷ ጥያቄና መልስ ዘዴዎችን በመጠቀም ልምምዳቸውን ለማጠናከር ተሞክሯል::

## 3.4. የመረጃ አተናተን

### 3.4.1. ከጽሁፍ መጠይቅና ምልከታ የተገኘ ውጤት

ለተጠኚዎቹ ተማሪዎች በተሰራጨው የጽሁፍ መጠይቅ ላይ የቀረበው ተጨማሪ አስተያየት የሚፈልግ ጥያቄ ትኩረት ከሚሰጥበት ጉዳይ አንጻር ተለይቶ ከተመደበ በኋላ ለያንዳንዱ ጥያቄ የተሰጠው አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ምላሽ ተቆጥሮ በብዛትና በመቶኛ ተመዝግቧል:: ተጨማሪ አስተያየት ለሚፈልገው ጥያቄም ከተሰጡት አስተያየቶች መካከል በአብዛኞቹ መላሾች የተሰነዘሩት ሀሳቦች በመረጃነት ተወስደዋል::

ከምልከታ ማስታወሻ የተገኙት መረጃዎች ደግሞ የተማሪዎችንም ሆነ የመምህሩን ሚና እንዲሁም የትምህርት አሰጣጡን ውጤታማነት በሚመለከቱ ነጥቦች አማካይነት ተገቢ በሆኑ ቦታዎች እንዲገቡ ተደርጓል::

### 3.4.2. የፈተና ውጤቶች

ለቁጥጥሩም ሆነ ለሙከራው ምድብ የተሰጠው ቅድመ ትምህርት ፈተና ታርሞ ውጤቱ ከተመዘገበ በኋላ የሁለቱን ምድቦች ውጤት ለማነጻጸር አመቺ በሆነው እስታትስቲካዊ ቀመር ወይም ቲ-ቴስት የትንተና ስልት (T-test) ከተሰላ በኋላ የችሎታ መበላለጥ የማይታይባቸው መሆኑ ተረጋገጠ:: የልምምዱ ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ የተሰጠው የድህረ ልምምድ ፈተናም በተመሳሳይ ዘዴ ታርሞና የተገኘው ውጤት ተጠናቅሮ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው የእስታትስቲክስ ስልት ተሰልቶአል::

# ምዕራፍ አራት

## የጥናቱ ውጤት ትንተና

በምእራፍ አንድ እንደተገለጸው፥ ይህ ጥናት የተካሄደበት አቢይ አላማ የ"ቶፕዳውን" የንባብ የማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር እንደ አንድ የማስተማሪያ ዘዴ ቢያገለግል የሚኖረውን ውጤታማነትና ተግባራዊነት ለመመርመር ነው። ስለዚህ የጥናቱ ትኩረት የሞዴሉን ተግባራዊነትና ውጤታማነት በመፈተሽ "በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል" የተባለውን የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከፍ ለማድረግ የሚቻልበትን አቅጣጫ ለማመልከት ነው። ለዚህም የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ እንደታቀደ በክፍል 1.2. በጥናቱ አላማ ስር ተጠቅሶአል።

- ሞዴሉ በአማርኛ ቋንቋ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል ይረዳልን?
- ተማሪዎች የተለያዩ የንባብ ስልቶችን (የምንባብ መልእክት ትንበያን፥ አንድምታዊ ንባብን፥ አውዳዊ የቃላት አፈታትን፥ ንባብን ከቀዳሚ እውቀት ማገናዘብን) የንባብ አላማ (ለትምህርት፥ ለመረጃ፥ ለመዝናናት) መሆኑን አውቀው ሊጠቀሙባቸው ይችላሉን?
- ተማሪዎች ከ"ቶፕዳውን" የንባብ ትምህርት አቀራረብ ልምምድ በሁዋላ የሚቀርብላቸውን ትምህርትና ልምምድ ይወዱት ይሆን? ለምን?

እነዚህን መሰረታዊ የጥናት ጥያቄዎች ለመመለስ በመጀመሪያ የመነሻ ጥናት (pilot study) ተካሂዶአል። በዚህ ጥናት ከቅድመና ድህረ ልምምድ ፈተናዎች እና ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች ለዋናው ጥናት ጠቃሚ ፍንጭ አስገኝተዋል። በተለይም የፈተናዎቹ ውጤቶች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና ልምምዱ ያስገኘውን አበረታች ውጤት አመልክተዋል። በዚህም የልምምዱ መልመጃዎች በአይነትና በብዛት በርከት ብለው እንዲዘጋጁና መጠነኛ የአቀራረብ ለውጥ እንዲደረግባቸው ረድቷል።

ለመረጃ አቀራረብና አተናተን ያመች ዘንድ ይህ ምእራፍ በሁለት አቢይ ንኡሳን ክፍሎች ተከፋፍሎአል። የመጀመሪያው ንኡስ ክፍል የመጀመሪያውን የጥናት ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችሉ ከፈተና ውጤቶች የተገኙ መረጃዎቸ ተጠቃለው አማካይ፥ ልይይትና የአማካይ ግምት ልዩነት ከወጣላቸው በሁዋላ በሙከራው ቡድንና በቁጥጥር ቡድን መካከል ያለው የውጤት ልዩነት በt-ቴስት ተሰልቶ ቀርቦአል። በሁለተኛው ንኡስ ክፍል ደግሞ የተቀሩትን ሁለት የጥናት ጥያቄዎች ማለትም 1.2.2 እና 1.2.3ን ለመመለስ ከመጠይቁ እና ከምልከታ ማስታወሻ የተገኙ መረጃዎች ተብራርተው ቀርበዋል።

ዋናው ጥናት በኢትዮጵያ ትንደም ቁጥር አንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለስድስት ሳምንታት ሲካሄድ ጥናቱ ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ የተከናወኑት ስራዎች በቅደም ተከተል የሚከተሉት ናቸው::

በ23/01/1992 ዓ.ም. ከትምህርት ቤቱ ነባር የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጋር በናሙና በተመረጡት ምድቦች ክፍል ተገኝቼ ምልከታ አድርጌአለሁ:: በምልከታው ወቅት ከመምህራኑ ጋር ክፍል በመገኘት ከተማሪዎቹ በስም ተዋውቀን የመጣሁበትን አላማ ነግሬያቸው በሚቀጥለው ጊዜ በተጠኚነት ቢመረጡ ሁሉም ተማሪዎች በፈቃደኝነት የጥናቱ ተሳታፊዎች እንደሚሆኑ ስምምነታቸውን ገልጸዋል:: ከትውውቁ በኋላ በማግስቱ ፈተና እንደሚሰጥ ተነግሮአቸው የዕለቱ ውይይት አብቅቷል:: ከዚያም በ25/01/92 ዓ.ም. ሁለቱም ምድቦች በተመሳሳይ ጊዜ የቅድመ ልምምድ ፈተና ተፈትነዋል::

በ27/01/1992 ዓ.ም. መደበኛው ልምምድ ተጀምሮአል:: የሙከራ ምድቡን አጥኚው ሲያለማምድ የቁጥጥር ምድቡን ደግሞ አጥኚው በተመልካችነት በሚገኝበት ፈቃደኛ የሆኑ አንድ የትምህርት ቤቱ ነባር መምህር አለማምደዋል:: ከመምህሩ ጋር በተደረገው ውይይት በሙከራውና በቁጥጥር ቡድኖች መካከል ሊኖር የሚገባውን ስነትምህርታዊ ልዩነትና የልምምድ አካሄድ ተገልጾላቸው በዚሁ መሰረት ተግባራዊ አድርገዋል::

በሙከራው ቡድን ውስጥ የሚገኙት ተማሪዎች ስለ ንባብ ምንነት፥ ስለአንብቦ መረዳት ችሎታና ምንነት፥ ይህንን ችሎታ ለማዳበር ስለሚደረገው ልምምድ አስፈላጊነት በአጥኚው በኩል ሰፋ ያለ ገለጻ ተደርጎላቸው በተነሱት ነጥቦች ላይ ውይይት ተካሂዶአል:: ተማሪዎች ንባብን ሲያካሂዱ የንባባቸው አላማ ከምን አንጻር መታየት እንደሚገባው፥ ጸሀፊው ስለሚያቀርበው ምንባብ ያለው አስተያየት፥ የጸሀፊው የሃሳብ አገላለጽ፥ የመልእክቱ ተአማኒነት መገምገም እንዳለበት፥ ግምገማውን ለማካሄድም ከምንባቡ ርዕስ በመነሳት ስለይዘቱ አስቀድመው መገመት እንደሚኖርባቸው፥ የሚያነቡትን ምንባብ መልእክት ከግል ገጠመኞቻቸውና ቀዳሚ እውቀታቸው ማገናዘብ እንደሚገባ ትምህርቱ በዝርዝር ተሰጥቶአቸዋል:: በትምህርታዊ ልምምዶቹ ወቅትም ልምምዶቹን በቅድመ ንባብ፥ በንባብ ጊዜና በድህረ ንባብ በመከፋፈል ተግባራዊ ለማድረግ ተሞክሮአል::

በአጠቃላይ፥ በውይይቱ ወቅት በተነሱት ነጥቦች አማካይነት ስለ "ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል መሰረታዊ እሳቤዎች፥ በሞዴሉ ስለሚተኮርባቸው ትምህርታዊ ጉዳዮችና የመልመጃ ተግባራት እንዲሁም በልምምዱ ወቅት ስለተማሪዎች ሚና የመነሻ ግንዛቤ እንዲያገኙ ጥረት ተደርጎአል::

ተማሪዎች ከቀረበላቸው የንባብና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምንነት ትምህርት በተጨማሪ በሚያነቡበት ጊዜ አንብበው የተረዱትን ሃሳብ በጥንድና በቡድን ሆነው መወያየትና መጠያየቅ እንደሚገባቸው፥ መረዳዳቱና መወያየቱ እርስ በርስ ለመማማር አመቺ መሆኑ ተገልጾላቸው ለዚሁ ዝግጁ እንዲሆ የማነቃቂያ ገለጻ ቀርቦላቸዋል። (ይህንን ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን Williams (1986:43) እና Clarke & Silberstein (1977:140) ያስረዳሉ)። በመጨረሻም ልምምዱ ለስድስት ሳምንታት ከተካሄደ በሁዋላ በ9/03/1992 የማጠቃለያ ድህረ ልምምድ ፈተና ተሰጥቶአል።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው፥ ተማሪዎቹ ስለ ንባብ ትምህርት አስፈላጊነት፥ ስለ አንብቦ መረዳት ምንነት፥ ስለተማሪዎች ሚና ገለጻ ከተደረገላቸውና ልምምዱን ከተከታተሉ በሁዋላ በጥናቱ አላማ ስር ለተነሱት ጥያቄዎች የተገኙትን መልሶች ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን። ለጥያቄዎች የተገኙት መልሶች ለጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያነት ከዋሉት መሳሪያዎች ማለትም ከቅድመ ልምምድና ከድህረ ልምምድ የፈተና ውጤቶች፥ ከጽሁፍ መጠይቅ እና ከምልከታ ማስታወሻ መረጃዎች ነው። ትንተናው ከላይ በተገለጸው ቅደም ተከተል መሰረት ቀጥሎ ይቀርባል።

## 4.1. አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤቶች ትንተና

በዚህ ንኡስ ክፍል ተማሪዎች ልምምዱን ካካሄዱ በሁዋላ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን መሻሻል የሚያሳይ የፈተና ውጤት ትንታኔ የሚቀርብ ሲሆን ለዚህም የተማሪዎቹ ቅድመና ድህረ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤቶች ስሌት በቅደም ተከተል ይተነተናሉ።

### 4.1.1. የቅድመ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት

በምእራፍ ሶስት እንደተገለጸው ተማሪዎች በ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል አማካይነት ልምምድ በማካሄድ ያሳዩትን የችሎታ መሻሻል ለመመዘን ያገለገለው ዋነኛው መንገድ በቅድመና ድህረ ልምምድ የተሰጡትን አንብቦ የመረዳት ፈተናዎች በማረም በሙከራው ቡድንና በቁጥጥር ቡድን መካከል የተገኘውን የውጤት ልዩነት በስሌት ማመልከት ነው። ለዚህም እንዲረዳ በሁለቱም ቡድኖች መካከል በሁለቱም ፈተናዎች ($T_1$ እና $T_2$) የተገኙትን ውጤቶች አማካይ፥ ልይይትና የአማካይ ግምት ልዩነት በማስላት የውጤቱን ልዩነት ጉልህነት በ"t-ቴስት" ለማረጋገጥ ተሞክሮአል። ቀጥለን በዝርዝር እንመልከት።

### ሰንጠረዥ 1:- የቅድመ ትምህርት (Pre-test) ውጤት

| የቁጥጥር ምድብ (Control Group) | | |
|---|---|---|
| 1. 42 | 28. 69 | 55. 52 |
| 2. 54 | 29. 74 | 56. 57 |
| 3. 63 | 30. 56 | 57. 66 |
| 4. 36 | 31. 78 | 58. 59 |
| 5. 60 | 32. 56 | 59. 66 |
| 6. 60 | 33. 74 | 60. 90 |
| 7. 58 | 34. 76 | 61. 41 |
| 8. 52 | 35. 46 | 62. 56 |
| 9. 70 | 36. 58 | 63. 67 |
| 10. 69 | 37. 58 | 64. 62 |
| 11. 58 | 38. 57 | 65. 66 |
| 12. 58 | 39. 66 | 66. 55 |
| 13. 54 | 40. 59 | 67. 60 |
| 14. 56 | 41. 60 | 68. 56 |
| 15. 56 | 42. 65 | 69. 51 |
| 16. 58 | 43. 54 | 70. 48 |
| 17. 54 | 44. 26 | 71. 68 |
| 18. 74 | 45. 42 | 72. 82 |
| 19. 58 | 46. 72 | 73. 54 |
| 20. 66 | 47. 72 | 74. 66 |
| 21. 60 | 48. 61 | 75. 72 |
| 22. 56 | 49. 76 | 76. 64 |
| 23. 65 | 50. 50 | 77. 60 |
| 24. 66 | 51. 66 | 78. 59 |
| 25. 52 | 52. 28 | 79. 78 |
| 26. 42 | 53. 64 | 80. 68 |
| 27. 72 | 54. 70 | |

N = 80

$\overline{X} = 60.31$

S = 10.46

| የሙከራ ምድብ (Experimental Group) | | |
|---|---|---|
| 1. 40 | 28. 44 | 55. 82 |
| 2. 62 | 29. 32 | 56. 59 |
| 3. 73 | 30. 76 | 57. 61 |
| 4. 54 | 31. 44 | 58. 52 |
| 5. 62 | 32. 38 | 59. 64 |
| 6. 85 | 33. 38 | 60. 72 |
| 7. 60 | 34. 48 | 61. 44 |
| 8. 73 | 35. 60 | 62. 80 |
| 9. 64 | 36. 85 | 63. 70 |
| 10. 46 | 37. 52 | 64. 62 |
| 11. 56 | 38. 70 | 65. 76 |
| 12. 48 | 39. 62 | 66. 88 |
| 13. 66 | 40. 68 | 67. 64 |
| 14. 38 | 41. 54 | 68. 72 |
| 15. 80 | 42. 34 | 69. 68 |
| 16. 46 | 43. 51 | 70. 89 |
| 17. 70 | 44. 44 | 71. 72 |
| 18. 67 | 45. 58 | 72. 56 |
| 19. 72 | 46. 60 | 73. 60 |
| 20. 50 | 47. 56 | 74. 58 |
| 21. 75 | 48. 71 | 75. 74 |
| 22. 56 | 49. 44 | 76. 62 |
| 23. 70 | 50. 26 | 77. 78 |
| 24. 61 | 51. 74 | 78. 52 |
| 25. 60 | 52. 82 | 79. 64 |
| 26. 81 | 53. 48 | 80. 60 |
| 27. 58 | 54. 66 | |

N = 80

$\overline{X} = 60.81$

S = 13.67

ሰንጠረዥ 1 የሚያሳየው በቁጥጥሩም ሆነ በሙከራው ቡድን ውስጥ የሚገኙት ተጠኚዎች በቅድመ ትምህርት ፈተናው ያስመዘገቡትን ዝርዝር ውጤት ነው:: በዚሁ ሰንጠረዥ ላይ በግልጽ እንደሚታየው ለጥናቱ በተመረጡት ለቁጥጥር ቡድን (control group) እና ለሙከራው ቡድን (experimental group) የተሰጠውን ቅድመ ልምምድ ፈተና (pre-test) መሰረት በማድረግ ሁለቱም ቡድኖች በትምህርት አቀባበልና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ የጎላ ልዩነት የማይታይ መሆኑን ለመለካት ተሞክሮአል:: ልዩነት የማይታይ መሆኑን ለመለካት ያስፈለገበት ምክንያት የሁለቱም ቡድኖቹ አባላት (ተማሪዎች) በእኩል የክፍል ደረጃ ላይ ቢገኙም ከሰው ሰው ያለው የችሎታ ልዩነት በቡድኑ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንዳያሳድር የሁለቱንም ቡድኖች የችሎታ ተመጣጣኝነት ማወቅ አስፈላጊ በመሆኑ ነው::

በዚህ መሰረት የቁጥጥር ቡድኑ አጠቃላይ ድምር ውጤት (aggregate Sum) 4825 ሲሆን የቡድኑ ጠቅላላ አማካይ (Grand Mean) 60.31 ነው:: የቡድኑ መደበኛ ልይይት (Standard deviation) 10.46 ሲሆን ልይይቱ ደግሞ 109.57 ነው:: የሙከራው ቡድን ጠቅላላ ድምር 4865 እና አማካይ 60.81 ሆኗል:: የሙከራው ቡድን ልይይት 187÷ መደበኛ ልይይቱ ደግሞ 13.67 ሆኖ ተመዝግቧል:: የሁለቱም ቡድኖች ተጠኚዎች ቁጥር እኩል ሲሆን ይኸውም 80 ነው::

ከዚህ ቀጥሎ የተገኙትን የቅድመ ልምምድ ውጤቶች በማነጻጸሪያ ነጥቦች ማለትም የቁጥጥር ቡድን አማካይ 60.31 እና የሙከራው ቡድን አማካይ 60.81 በመያዝ ውጤቱን በ"t-ቴስት" ለማረጋገጥ ልይይታቸው እንደቅደም ተከተላቸው የቁጥጥር ቡድኑ 109.57 እና የሙከራው ቡድን 187 እና የአማካይ ግምት ልዩነታቸው (standard error of the mean) 12.17 መሆናቸው ተሰላ:: በዚህ ቅደም ተከተል የt-ስሌት ዋጋ (t-obtained) ሲሰላ 0.260 ሆኖ የተገኘ ሲሆን በ0.05 የጉልህነት ደረጃ (significance level)÷ በ158 የነጻነት ደረጃ የt-ሰንጠረዥ ዋጋ (t-critical) ደግሞ ከt-ስርጭት ሰንጠረዥ (T-distribtuion) ላይ እንደሚነበበው 1.960 ሆኖ ተገኝቷል:: ይህ ስሌት እንደሚያመለክተው የተገኘው ውጤት 0.260 ከt-ሰንጠረዥ ዋጋ 1.960 ያነሰ ነው:: ይህም በተማሪዎቹ የቅድመ ልምምድ ፈተና ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ያመለክታል:: በዚህም አሰራር የተገኘው የቅድመ ልምምድ የፈተና ውጤት የሚከተለውን ይመስላል::

ሰንጠረዥ 2:- የቅድመ ፈተና የt-ስሌት ማጠቃለያ

| ፈተና | የቁጥጥር ቡድን ጠቅላላ ውጤት | | | የሙከራው ቡድን ጠቅላላ ውጤት | | | የተሰላ የt-ዋጋ | የt-ሰንጠረዥ ዋጋ* | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | $N_1$ | $\bar{X}_1$ | $SD_1$ | $N_2$ | $\bar{X}_2$ | $SD_2$ | | | |
| ቅድመ ልምምድ ፈተና | 80 | 60.31 | 10.46 | 80 | 60.81 | 13.67 | 0.260 | 1.960 | የለውም |

* P<0.05

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ ውጤት ለመረዳት እንደሚቻለው በቡድኖቹ የቅድመ ልምምድ ፈተና ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አልተመዘገበም:: የዚህም ምክንያት ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ÷ አንደኛ÷ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ ተጠኚዎችን ለማግኘትና የተመረጡትንም በሙከራዊ ሁኔታና በቁጥጥር ሁኔታ ለመመደብ ያገለገለው የናሙና አወሳሰድ ስልት የእጣ ናሙና ስልት በመሆኑ በአመራረጥ ሂደት የተጠኚዎች አወሳሰድ ዘብ (bias) ባለመኖሩ ሲሆን÷ ሁለተኛ÷

በቅድመ ልምምድ ፈተናው የተገኘው ውጤት በእስታትስቲካዊ ስሌት ስልት ሲመረመር ተመሳሳይ ደረጃ ላይ መገኘታቸውን መጠቆሙ ናቸው::

ቀደም ሲል እንደተመለከተው፥ በሙከራውና በቁጥጥር ቡድኑ መካከል አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ የጎላ ልዩነት አለመኖሩ ስለተረጋገጠ ቡድኖቹ ተመሳሳይነት ያለውን የትምህርት ይዘት እንዲከታተሉና በትምህርት ይዘት አቀራረብ በኩል ልዩነት እንዳይፈጠር ጥረት ተደርጓል:: ለማስተማሪያነት የቀረቡትም ምንባቦች ማሟላት የሚገባቸውን መሰረታዊ መስፈርቶች (ዝርዝሩን በቀዳሚው ክፍል በ2.2.5 ስር ይመለከቷል) ተዛማጅ ጽሁፎችን መሰረት በማድረግ የተመረጡ ናቸው:: በነዚሁ ምንባቦችና መልመጃዎች በመጠቀም ልምምዱ ለስድስት ሳምንታት ከተካሄደ በኋላ የድህረ ልምምድ ፈተና ተሰጥቷል::

### 4.1.2. የድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት ትንተና

በዚህ ንኡስ ክፍል ተማሪዎች ከልምምዱ በኋላ ያሳዩት የችሎታ ዕድገት እና ውጤት የሚቀርብ ሲሆን ለዚህም የሁለቱም ቡድኖች ድህረ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት ስሌት ይተነተናል:: የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ በድህረ ልምምድ ፈተና ያስመዘገቡት ዝርዝር ውጤትም በሚቀጥለው ሰንጠረዥ ላይ ተመልክቷል::

## ሰንጠረዥ 3:- የድህረ ልምምድ ፈተና (Post-test) ውጤት

| የቁጥጥር ቡድን (Control Group) | | |
|---|---|---|
| 1. 75 | 28. 68 | 55. 73 |
| 2. 83 | 29. 70 | 56. 60 |
| 3. 78 | 30. 48 | 57. 68 |
| 4. 63 | 31. 38 | 58. 73 |
| 5. 60 | 32. 78 | 59. 73 |
| 6. 48 | 33. 58 | 60. 55 |
| 7. 65 | 34. 58 | 61. 58 |
| 8. 50 | 35. 65 | 62. 83 |
| 9. 78 | 36. 80 | 63. 45 |
| 10. 78 | 37. 60 | 64. 58 |
| 11. 75 | 38. 60 | 65. 60 |
| 12. 63 | 39. 78 | 66. 73 |
| 13. 70 | 40. 45 | 67. 60 |
| 14. 70 | 41. 65 | 68. 48 |
| 15. 48 | 42. 58 | 69. 55 |
| 16. 63 | 43. 58 | 70. 70 |
| 17. 48 | 44. 40 | 71. 73 |
| 18. 43 | 45. 48 | 72. 58 |
| 19. 50 | 46. 55 | 73. 60 |
| 20.53 | 47. 48 | 74. 70 |
| 21. 63 | 48. 63 | 75. 48 |
| 22. 65 | 49. 70 | 76. 65 |
| 23. 63 | 50. 73 | 77. 55 |
| 24. 68 | 51. 58 | 78. 68 |
| 25. 55 | 52. 68 | 79. 70 |
| 26. 38 | 53. 68 | 80. 45 |
| 27. 50 | 54. 73 | |

$N_1 = 80$

$\bar{X}_1 = 61.78$

$S^2_1 = 122.04$

SD = 11.03

| የሙከራ ቡድን (Experimental Group) | | |
|---|---|---|
| 1. 63 | 28. 55 | 55. 68 |
| 2. 63 | 29. 65 | 56. 53 |
| 3. 70 | 30. 43 | 57. 65 |
| 4. 70 | 31. 73 | 58. 70 |
| 5. 65 | 32. 70 | 59. 73 |
| 6. 48 | 33. 78 | 60. 65 |
| 7. 75 | 34. 63 | 61. 70 |
| 8. 85 | 35. 50 | 62. 53 |
| 9. 73 | 36. 70 | 63. 85 |
| 10. 65 | 37. 78 | 64. 68 |
| 11. 48 | 38. 85 | 65. 50 |
| 12. 78 | 39. 73 | 66. 73 |
| 13. 60 | 40. 80 | 67. 53 |
| 14.73 | 41. 93 | 68. 48 |
| 15. 60 | 42. 85 | 69. 78 |
| 16. 68 | 43. 70 | 70. 63 |
| 17. 55 | 44. 75 | 71. 48 |
| 18. 68 | 45. 73 | 72. 55 |
| 19. 68 | 46. 75 | 73. 70 |
| 20. 65 | 47. 80 | 74. 80 |
| 21. 85 | 48. 75 | 75. 58 |
| 22. 75 | 49. 93 | 76. 65 |
| 23. 83 | 50. 60 | 77. 53 |
| 24. 95 | 51. 48 | 78. 70 |
| 25. 68 | 52. 60 | 79. 55 |
| 26. 76 | 53. 63 | 80. 45 |
| 27. 70 | 54. 75 | |

$N_2 = 80$

$\bar{X}_2 = 67.43$

$S2^2 = 136.87$

SD = 11.69

በሰንጠረዥ 3 ላይ እንደሚታየው የሙከራ ቡድኑ አባላት በአማካይ ነጥብና በመደበኛ ልይይት ከቁጥጥር ቡድኑ አባላት ልቀው ተገኝተዋል:: ሁለቱም የጥናት ቡድኖች ያስመዘገቡት አማካይ ነጥብና መደበኛ ልይይት እንደ ቅድመ ልምምድ ፈተናው ሁሉ የt-ቴስት ቀመር የሚሻቸውን መሰረታዊ ጉዳዮች ከግምት ውስጥ በማስገባት ውጤታቸውን ለማነጻጸር ተሞክሯል:: በፈተናው የተገኙትን አማካይ ነጥቦች የቁጥጥር ቡድኑ 61.78 እና የሙከራው ቡድኑ 67.43 እንዲሁም የአማካይ ግምት ልዩነት 11.36 በመያዝ ውጤቱን በt-ቴስት ለማረጋገጥ ልይይታቸው

እንደቅደም ተከተላቸው የቁጥጥር ቡድኑ 122.04 እና የሙከራው ቡድን 136.87 መሆናቸው ተሰልቶ በዚሁ ቅደም ተከተል የt-ስሌት ዋጋ 3.173 ሆኖ የተገኘ ሲሆን በ0.05 የጉልህነት ደረጃ እና በ158 የነጻነት ደረጃ የt-ሰንጠረዥ ዋጋ ደግሞ ከt-ስርጭት ሰንጠረዥ ዋጋ ላይ እንደሚነበበው 1.960 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህ ስሌት እንደሚያመለክተው የተገኘው ውጤት 3.173 ከt-ሰንጠረዥ ዋጋ 1.960 የበለጠ ነው፡፡

በአጠቃላይ በድህረ ልምምድ ፈተናው የሙከራው ቡድኑ አማካይ ነጥብ 67.43÷ መደበኛ ልይይቱ 11.68÷ ሲሆን የቁጥጥሩ ቡድን አማካይ ነጥብ 61.78÷ መደበኛ ልይይት ደግሞ 11.03 ሆኗል፡፡ ይህ ውጤት በt-ቴስት የንጽጽር ስልት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት የሙከራው ቡድን በድህረ ልምምድ ፈተና ከቁጥጥር ቡድኑ የላቀ ውጤት ማስመዝገቡን ያመለክታል፡፡ በዚህ አሰራር የተገኘው የድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት ስሌታዊ ንጽጽር በሚከተለው ሰንጠረዥ ተጠቃሎ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 4፡- የቡድኖቹን የድህረ ልምምድ ፈተና የt-ስሌት ውጤት ማሳያ

| ፈተና | የቁጥጥር ቡድን ጠቅላላ ውጤት | | | የሙከራው ቡድን ጠቅላላ ውጤት | | | የተሰላ የt-ዋጋ | የt-ሰንጠረዥ ዋጋ* | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | $N_1$ | $\bar{X}_1$ | $SD_1$ | $N_2$ | $\bar{X}_2$ | $SD_2$ | | | |
| ድህረ ልምምድ ፈተና | 80 | 61.75 | 11.03 | 80 | 67.43 | 11.69 | 3.173 | 1.960 | አለው |

* $P<0.05$

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ መግለጫ ውጤት መረዳት እንደሚቻለው በሁለቱ ቡድኖች መካከል በድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት ላይ የጎላ ልዩነት አለ፡፡ የተሰላው የt-ዋጋ ከሰንጠረዥ t-ዋጋ የበለጠ በመሆኑ የሙከራው ቡድን ከቁጥጥር ቡድኑ የበለጠ ውጤት አስመዝግቦአል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በ5% የይሁንታ ነጥብ (Probability level) በመተው የተገኘው 3.173 የሚያመለክተው ከመቶ 95 እጅ የተመዘገበው የውጤት ልዩነት የአጋጣሚ ለውጥ ሳይሆን በተሰጠው ትምህርት ውጤታማነት የተነሳ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ በልምምድ ወቅት ገቢራዊ በሆነው የማስተማሪያ ዘዴ ሳቢያ የሙከራው ቡድን በችሎታ ልቆ መገኘቱን ስሌቱ የሚያረጋግጥ ሲሆን ይህ ውጤት ደግሞ የ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማሻሻል የሚረዳ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ ስለሆነም አጥኚው የዚህን የማስተማሪያ ዘዴ ውጤታማነት በሚመለከት ይዞት የተነሳውን ባዶ መላምት (Ho) ለማስወገድ አስችሏል፡፡

በክፍል 2.2.2. ስር በቀደምት ደጋፊ ምርምሮች ቅኝት እንደተመለከተው የሞዴሉን ውጤታማነት ለመፈተሽ በአፍ መፍቻ ቋንቋ፥ በሁለተኛ/ውጭ ቋንቋ እንዲሁም በልሳነ ክልኤዎች ላይ ምርምር ተካሂዷል፡፡ በሁሉም አውድ የተካሄዱት ምርምሮች አዎንታዊ ውጤት ማስገኘታቸውም ተጠቁሟል፡፡ ይሁንና በዚህ ጥናት በሙከራው ቡድን ውስጥ በተጠኚነት ከተሳተፉት ተማሪዎች 72ቱ በአማርኛ አፋቸውን የፈቱ ሲሆኑ 8ቱ ይህንኑ ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩት ናቸው፡፡ /ሰንጠረዥ 6 ገጽ __ ይመለከቷል/፡፡ በመሆኑም የተገኘው ውጤት ከሁለቱ የቋንቋ አውዶች የትኛው የተሻለ እንደሆነ ለመለየትና ልዩነቱንም በስሌት ለማረጋገጥ ተሞክሯል፡፡ በተገኘው ውጤት መሰረትም በሁለቱ አውዶች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን የተማሪዎች ውጤት አመልክቷል፡፡ ይህ ሊሆን የቻለው በልምምዱ ወቅት ሁሉንም ተሳታፊዎች በሚያቀራርብ መልኩ ልምምዱ በመካሄዱ፥ የተመረጡት ምንባቦች የሚያቀርቧቸው ይዘቶች ከፍላጎታቸው ጋር የተዛመዱ በመሆናቸው የተሰጠውን ትምህርት ተግባራዊ በማድረጋቸው እና አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩት ተጠኚዎችም በአዲስ አበባ ከአምስት አመታት በላይ የኖሩ በመሆናቸው የቋንቋ ችሎታቸው የዳበረ በመሆኑ እንደሆነ ይታመናል፡፡

### 4.1.3. የመላ ምት ፍተና (Hypothesis Testing)

በዚህ ጥናት አላማ 1.2. ስር ለአላማው ፍተሻ ሁለት መላምቶች ቀርበው ነበር፡፡ እነዚህም፤

$H_0$ = ከሙከራው በኋላ በቁጥጥሩ ቡድን እና በሙከራው ቡድን መካከል የችሎታ መበላለጥ አይታይም፤

$H_1$ = ከሙከራው በኋላ በቁጥጥሩ ቡድን እና በሙከራው ቡድን መካከል የጎላ የችሎታ መበላለጥ ይኖራል፤ የሚሉት ነበሩ፡፡

በአማራጭነት የቀረበው መላምት ($H_1$) የተወሰነ የውጤት ድምዳሜ አቅጣጫን የሚያመለክት ባለመሆኑ (non-directional hypothesis) two-tailed የt-ስሌት የንጽጽር ስልት ለመላ ምት ፍተናው ተግባራዊ ሆኖአል፡፡ በዚህ መሰረት በተዛምዶ የተሰራበት የጉልህነት ደረጃ 0.05 ነው፡፡ ቀጥሎ በሁለት የፈተና ውጤቶች መካከል ያለውን ንጽጽራዊ ልዩነት በማሳየት የመላ ምት ፍተናውን እንመለከታለን፡፡

ሰንጠረዥ 5፡- የመላምት ፍተና (hypothesis testing) ውጤት ማሳያ

| ፈተና | የጥብቅ ቡድን ጠቅላላ ውጤት | | | የሙከራው ቡድን ጠቅላላ ውጤት | | | የተሰላ የt-ዋጋ | የt-ሰንጠረዥ ዋጋ* | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | $N_1$ | $X_1$ | $SD_1$ | $N_2$ | $X_2$ | $SD_2$ | | | |
| ቅድመ ልምምድ | 80 | 60.31 | 11.10 | 80 | 60.81 | 13.60 | 0.260 | 1.960 | የለውም |
| ድህረ ልምምድ | 80 | 61.75 | 11.03 | 80 | 67.43 | 11.69 | 3.173 | 1.960 | አለው |

$P^* < 0.05$

ከሰንጠረዥ 5 እንደምንረዳው በድህረ ልምምድ የፈተና ውጤት መሰረት በጥናት ቡድኖቹ መካከል የጎላ የውጤት ልዩነት ታይቶአል፡፡ በልዩነቱም ብልጫ ያለው ውጤት ያስመዘገበው የሙከራው ቡድን ነው፡፡ በዚህም በሁለቱ ቡድኖች መካከል በድህረ ልምምድ ፈተና የውጤት ልዩነት አይታይም የሚለው የመጀመሪያው ባዶ መላምት ($H_o$) ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ይህ የሚያመለክተው ደግሞ አማራጩ መላምት ($H_1$) ተቀባይነት ያለው መሆኑንና የተሰጠው ትምህርት ውጤታማ መሆኑን ነው፡፡ የተሰጠው ትምህርት ውጤታማነትም በአጋጣሚ የተከሰተ ሳይሆን ገቢራዊ ከሆነው የማስተማሪያ ዘዴ ውጤታማነት የተነሳ ነው፡፡ ለውጤቱ መለያየት የሚከተሉትን በምክንያት መጥቀስ ይቻላል፡፡ እነዚህም፤

1. በሙከራው ቡድን ውስጥ በተጠኚነት የተሳተፉት ተማሪዎች ልምምዱን ሲያካሂዱ የንባብ አላማ እንዲኖራቸው፥ ሲያነቡም በትርጉም ላይ አትኩረው በትርጉም-አዘል አሀዶች ደረጃ እንዲያነቡ፥ ያልገባቸውን ነጥብ ከመምህራቸው እና ከጉዋደኞቻቸው ጋር በመወያየት በምንባቦቹ ይዘቶችና ይዘቶቹን ለመመርመር የሚረዱ የንባብ ስልቶችን አጠቃቀም በስፋት በመለማመዳቸው፥
2. አዳዲስ ቃላትንና አባባሎችን ከምንባቦቹ አጠቃላይ ገለጻና አቀራረብ ጋር አጣምረው መመርመራቸው፥ ምንባቦቹን በዝርዝር ከማንበባቸው በፊት ስለይዘቶቻቸው ለማወቅ ጥረት ማድረጋቸው ጠቃሚ ልምድ ስላስጨበጣቸው ይህንኑ እውቀት በፈተናው አሰራር ላይ ተግባራዊ ለማድረግ በመቻላቸው፥ እና ጥሩ ውጤት ማስመዝገባቸውለውጤቱ መለየት መንስኤ እንደሆነ ይታመናል፡፡

በአጠቃላይ፥ የሙከራው ቡድን ከቁጥጥር ቡድኑ የተሻለ ውጤት ማስመዝገቡ ለጥናቱ አንደኛው ጥያቄ አዎንታዊ መልስ አስገኝቷል፤ ምክንያቱም የፍትነታዊ ምርምሩ ውጤት የ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማሻሻል የሚረዳ መሆኑን አመልክቶአል፡፡

ቡድኖቹ በድህረ ልምምድ ፈተና ያሳዩትን የችሎታ መሻሻል ስንመለከት የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ልምምድና ድህረ ልምምድ የፈተና ውጤት ልዩነት በt-ቴስት ሲሰላ የt-ስሌት ዋጋ 0.82 ነው:: የሁለቱን የፈተና ውጤቶች አማካይ 60.31 እና 61.75 በቅደም ተከተል በመያዝ ልይይታቸው 123.21 እና 122.04 መሆናቸው ታውቆአል:: የt-ስሌት ዋጋ 0.82 ሲሆን በ0.05 የጉልህነት ደረጃ እና በ79 የነጻነት ደረጃ የt-ሰንጠረዥ ዋጋ 1.980 ነው:: በዚህ ስሌት መሰረት የt-ሰንጠረዥ ዋጋ ከt-ስሌት ዋጋ የበለጠ ሆኖ በመገኘቱ የቁጥጥር ቡድኑ አባላት ያስመዘገቡት ድህረ ልምምድ የፈተና ውጤት ከቅድመ ልምምዱ ውጤት ያለው ልዩነት ጉልህ ሆኖ አልተገኘም::

በሌላ በኩል ደግሞ የሙከራው ቡድን የቅድመ ልምምድና ድህረ ልምምድ የፈተና ውጤት ልዩነት ጉልህነት በt-ቴስት ሲሰላ 3.31 ነው:: የሁለቱ ፈተና ውጤቶች አማካይ ነጥቦች 60.81 እና 67.43 ሲሆኑ ልይይታቸው 185.23 እና 136.87 መሆናቸው ታውቆአል:: በዚሁ ቅደም ተከተል የt-ስሌት ዋጋ 3.31 ሲሆን በ0.05 የጉልህነት ደረጃ፥ በ79 የነጻነት ደረጃ ከt-ሰንጠረዥ ዋጋ የበለጠ ነው:: ይህም የሚያሳየው የሙከራው ቡድን በድህረ ልምምድ የፈተና ውጤት ያስመዘገበው የውጤት ልዩነት በእስታትስቲክስ ስሌት ጉልህ መሆኑን ነው:: ስለዚህም ተማሪዎቹ የተከታተሉት ትምህርታዊ ልምምድ ችሎታቸውን ለማሻሻል አዎንታዊ አስተዋጽኦ አበርክቷል::

ባጠቃላይ፥ የሁለቱ ቡድኖች የቅድመና ድህረ ልምምድ የፈተና ውጤቶች ሲነጻጸሩ በመሀከላቸው የታየውን ልዩነት እንደሚከተለው ማጠቃለል ይቻላል::

ሀ. የቁጥጥር ቡድኑ በድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት ያስመዘገበው ልዩነት ከቅድመ ልምምድ ሲነጻጸር ጉልህ ልዩነት አላሳየም::

ለ. የሙከራው ቡድን በድህረ ልምምድ የፈተና ውጤት ያሳየው የውጤት ለውጥ ከቅድመ ልምምድ ውጤቱ ሲነጻጸር ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን ስሌቱ ያመለክታል:: ስለዚህም የሙከራው ቡድን በድህረ ልምምድ ፈተናው ከቀዳሚው ውጤቱ የበለጠ ከማስመዝገቡም በላይ ቀደም ሲል እንደተመለከተው ከቁጥጥር ቡድኑ ጋር ሲነጻጸር የጎላ የውጤት ልዩነት አሳይቶአል::

## 4.2. ለተማሪዎች ከተሰራጨው የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

### 4.2.1. በክፍል አንድ ለቀረቡት ጥያቄዎች ውጤት ማብራሪያ

የጽሁፍ መጠይቁን ስለሞሉት ተማሪዎች ማንነት ለማወቅ ይረዳ ዘንድ በቅድሚያ የሚከተለሰውን ሰንጠረዥ እንመልከት::

ሰንጠረዥ 6:- የቁጥጥርና የሙከራ ቡድን አባላት ጾታ፥ የአፍ መፍቻ ቋንቋና ዕድሜ

| ተ.ቁ. | ምድብ | ጾታ | | ብዛት | የአፍ መፍቻ ቋንቋ | | | | ብዛት | እድሜ | | ብዛት | የስነጽሁፍ፥ የድራማ፥ የጋዜጠኝነትና የሚኒ ሚዲያ አባል | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | | አማርኛ | ኦሮምኛ | ትግርኛ | ጉራግኛ | | 13-15 | 16-19 | | | |
| 1 | ቁጥጥር | 42 | 38 | 80 | 75 | 2 | 2 | 1 | 80 | 35 | 45 | 80 | ነኝ | አይደለሁም |
| 2 | ሙከራ | 38 | 42 | 80 | 72 | 3 | 3 | 2 | 80 | 52 | 28 | 80 | 6 | 74 |
| ድምር | | 80 | 80 | 160 | 147 | 5 | 5 | 3 | 160 | 87 | 73 | 80 | 80 | |

በሰንጠረዥ 6 ላይ በዝርዝር እንደቀረበው ከቁጥጥር ቡድኑ አባላት መካከል 42ቱ ማለትም 52.5%፥ ከሙከራው ቡድኑ አባላት ደግሞ 38ቱ ማለትም 43.5% የሚሆኑት ወንዶች ናቸው:: በዚሁ ሰንጠረዥ ላይ እንደተመለከተው ከቁጥጥር ቡድኑ አባላት 38ቱ ማለትም 43.5% የሚሆኑት እና ከሙከራው ቡድኑ ደግሞ 42ቱ ማለትም 52.5፤ ሴቶች ናቸው:: በተመሳሳይ መንገድ ከቁጥጥር ቡድኑ 75ቱ ወይም 93.75% የሚሆኑት በአማርኛ፥ 2 ተማሪዎች በኦሮምኛ፥ 2 በትግርኛ፥ 1 ተማሪ በጉራግኛ አፋቸውን የፈቱ ናቸው:: ከሙከራ ቡድኑ አባላት መካከልም 72ቱ ወይም 90% የሚሆኑት በአማርኛ፥ 3 በኦሮምኛ፥ 3 በትግርኛ፥ 2 በጉራግኛ አፋቸውን የፈቱ ናቸው:: እድሜያቸውን በተመለከተም፥ ከቁጥጥር ቡድኑ 35 ተማሪዎች ወይም 43.75% የሚሆኑት፥ ከሙከራው ቡድን ደግሞ 52ቱ ወይም 65% የሚሆኑት ከ13-15 የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሲሆኑ፤ ከቁጥጥሩ 45ቱ ወይም 56.25% እና ከሙከራው 28ቱ ወይም 35%ከ16-19 ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ ስለሚገኙ ከጾታና ከዕድሜ አንጻር ተቀራራቢ መሆናቸውን ለመረዳት አያዳግትም:: ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ የሙከራ ቡድኑ አባላት በ1991 ዓ.ም. የትምህርት ዘመን የተማሩበትን መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለማወቅ በተደረገው ጥረት ደጋሚዎቹን ተማሪዎች ጨምሮ ከዘጠኝ የተለያዩ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተሰባሰቡ መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል:: ከተማሪዎቹ የተገኘው አጠቃላይ መረጃ እንደሚያመለክተው ከሙከራው ቡድኑ አባላት 72ቱ በአማርኛ አፋቸውን የፈቱ ናቸው:: በመሆኑም በልምምዱ ሂደት የተሳተፉት ተጠኚዎች በአማርኛ አፋቸውን የፈቱ ናቸው ለማለት የሚያስደፍር ነው:: በአጠቃላይ መጠይቁን ስለሞሉት ተማሪዎች ይህን ያህል ማብራሪያ ከተመለከትን የተገኘውን መረጃ ቀጥለን በዝርዝር እንመልከት::

በሰንጠረዥ 6 ላይ በግልጽ እንደሰፈረው፥ ተማሪዎች ከክፍል ትምህርት ውጭ በግል ጥረት የሚያነቡ መሆናቸውን እና የተጓዳኝ ትምህርቶች ክበባት፥ ለምሳሌ የስነጽሁፍ፥ የድራማ፥ የጋዜጠኝነት እና የሚኒሚዲያ አባልነታቸውን ለማወቅ ለቀረበው ጥያቄ (92.5% ) "አባል አይደለሁም" በማለት መልሰዋል:: የቀረበው ሃሳብ ትኩረት በነዚህ ክበባት ተሳታፊ ከሆኑ በሚኖራቸው የዝግጅት መርሀ ግብር ለተማሪዎች ቁምነገሮችን ለማካፈል ስለሚሞክሩ የተለያዩ ጽሁፎችን በግላቸው ፈልገው የሚያነቡ እንደሆነ ለማወቅ ነበር:: ይሁን እንጂ የተማሪዎቹ መልስ አሉታዊ በመሆኑ በግል የሚያደርጉት ልምምድ አነስተኛ እንደሆነ ለመረዳት አያዳግትም::

### 4.2.2. በክፍል ሁለት ከ1-5 ከቀረቡት ሃሳቦች የተገኙ መረጃዎች ውጤት

በዚህ ክፍል ተማሪዎቹ በቀረቡላቸው ጥያቄዎች ሃሳቦች ላይ መስማማታቸውንና አለመስማማታቸውን ለማረጋገጥ የተሞከረ ሲሆን ሃሳቦቹን የሚወክሉት አራት አማራጮች፤

ሀ. በጣም እስማማለሁ፥

ለ. እስማማለሁ፥

ሐ. አልስማማም፥

መ. በጣም አልስማማም፥

የሚሉት አማራጮች ናቸው::

በነዚህ አማራጮች ለቀረቡት ሃሳቦች የተሰጡትን መልሶች በሚቀጥለው ሰንጠረዥ እንመለከታለን::

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

## ሰንጠረዥ 7:- የተማሪዎች ቅድመ ልምምድ አስተያየት የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| | | የስምምነት ምርጫዎች | | | | ያለመስማማት ምርጫዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | |
| ተ.ቁ | የቀረቡ ሃሳቦች | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 1 | የተለያዩ መጻህፍት፥ ጋዜጦችንና መጽሄቶችን በየጊዜው እንዳነብ ወላጆቼ ሁኔታዎችን ያመቻቹልኝ ነበር፡፡ | - | - | 5 | 6.25 | 23 | 28.75 | 54 | 65 |
| 2 | ቀደም ሲል የተለያዩ ጽሁፎችን በማንበብ የተረዳሁትን ሃሳብ ከጉዋደኞቼ ጋር በጋራ እንወያይባቸው ነበር፡፡ | 9 | 11.25 | - | - | 22 | 27.5 | 49 | 61.5 |
| 3 | የተለያዩ የንባብ ስልቶችን (የአሰሳ ንባብ፥ የገረፍታ ንባብ፥ ጥልቅ ንባብን ከግል ገጠኝ ማዛመድና ስለምንባብ ይዘት መገመትን) ከዘጠነኛ ክፍል በፊት በአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት ተምሬአለሁ | 2 | 2.5 | 14 | 28 | 28 | 35 | 36 | 45 |
| 4 | በንባብ ትምህርት ጊዜ ያነበብነውን ምንባብ አጠቃላይ መልእክት አስመልክቶ ውይይትና ክርክር በማካሄድ የየራሳችንን ሃሳብ እንድንገልጽና የምንባቡን ይዘት እንድንገመግም ሁኔታዎች ይመቻቹልን ነበር፡፡ | 1 | 1.25 | 9 | 11.25 | 27 | 33.75 | 43 | 53.75 |
| 5. | በአማርኛ የመማሪያ መጽሃፍ ውስጥ ከሚገኙት ምንባቦች በተጨማሪ መምህራችሁ መጽሀፍ፥ ጋዜጣ፥ መጽሄትና የተለያዩ ጽሁፎችን አንብባችሁ ያገኛችሁትን ሃሳብ እክፍል አምጥታችሁ እንድትወያዩባቸው ያደርጉ ነበር፡፡ | 2 | 2.5 | 9 | 11.25 | 17 | 21.25 | 52 | 65 |

* በመጠይቁ ላይ የተሰጣቸውን ቁጥር ያመለክታል

** አሉታዊ ሲሆን ለምርጫዎቹ የሚሰጠው ዋጋ ሀ= 1 ለ= 2 ሐ= 3 መ= 4
አዎንታዊ ሲሆን ደግሞ ሀ= 4 ለ= 3 ሐ= 2 እና መ= 1 ነው፡፡

መደበኛ ባልሆነ መንገድ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር የሚረዳው በተማሪዎች መኖሪያ አካባቢ የቤተሰቦቻቸው አንባቢዎች መሆን ነው፡፡ Aebersold & Field (1997:6) Heath (1983)ን ጠቅሰው እንደሚገልጹት ቤተሰቦች የተለያዩ ጋዜጦችን፥ መጽሄቶችን እና መጻህፍትን ካነበቡ ልጆችም የወላጆቻቸውን ልምድ ያዳብራሉ፤ ለተማሪ ልጆቻቸውም ለማንበብ የተሻለ አጋጣሚ ይፈጥርላቸዋል፡፡ ይህንን ሃሳብ ከግንዛቤ በማስገባት "ቤተሰቦቼ ሁኔታዎችን ያመቻቹልኝ ነበር" ለሚለው ጥያቄ (1ኛ ተራ ቁጥር) የተገኘው መልስ 6.25%. የእስማማለሁ አዎንታዊ ምላሽ ሲሆን 93.75% የአልስማማም አሉታዊ ምላሽ ነው፡፡

በሌላም በኩል ትምህርቱን በተማሪዎች ዘንድ እንዲወደድ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ የመምህሩ ጥረት ተማሪዎችን የሚያሳትፍ መሆን ነው፡፡ ተማሪዎች ከተለያዩ ምንጮች አንብበው የተረዱትን ሃሳብ በጽሁፍ አቅርበው በክፍል ውስጥ እንዲያነቡና እንዲነጋገሩበት ቢደረግ ተማሪዎች የበለጠ ለማንበብና የተሻለ የንባብ ልምድ ለማዳበር ጠንካራ ፍላጎት ሊያድርባቸው ይችላል፡፡ በዚህም ተማሪዎች ችሎታቸውን ያዳብራሉ፡፡ ለጥረታቸውም የተወሰነ ዋጋ ቢሰጠው በመሀከላቸው

የሩክክር ስሜት ስለሚፈጥር ሁሉም ይሳተፉበታል:: ከዚህ ግንዛቤ በመነሳት የአማርኛ ቋንቋ መምህሮቻቸው የተለያዩ ጽሁፎችን ከጋዜጦች፥ ከመጽሄቶች እና ከመጻህፍት አንብበው ያገኙትን ሃሳብ በክፍል ውስጥ አቅርበው እንዲወያዩባቸው ያደርጋሉ ለሚለው ሃሳብ የአዎንታ መልስ የሰጡት ከመላሾቹ 13.75% የሚይዝ ሲሆን 86.25% ግን የአሉታ መልስ ነው:: ይህ የሚያሳየው መምህራኑ የተለያዩ ይዘትና የአቀራረብ ቅርጽ ያላቸውን ጽሁፎች በማዘጋጀት ወይም ተማሪዎችን በማዘዝ የማያለማምዱ መሆናቸውን ነው::

በቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች የሚያነቡትን ጽሁፍ እንዳለ ዝም ብለው የሚቀበሉ መሆን የለባቸውም:: አዳዲስ አስተያየቶችን አፍላቂ፥ ጥያቄዎችን አቅራቢና በምንባቡ መልእክት መነሻነት መተንበይ መቻል አለባቸው /Williams 1984:3/:: በተጨማሪም የምንባቡን መልዕክት ገምግመው ከሚያውቁት ነገር ጋር ለማዛመድ መሞከር ይገባቸዋል:: ይህንን መሰረታዊ ነጥብ ተግባራዊ ለማድረግ ተማሪዎቹ በተለያዩ ጽሁፎች አማካይነት ልምምድ ሊያደርጉ ይገባል:: ተጠኚዎቹ ተማሪዎች በዚህ መልክ ልምምድ ለማድረግ ሁኔታዎች ይመቻቹልን ነበር ለሚለው ሃሳብ 87.5% በአሉታ ሲመልሱ 12.5% በአዎንታ መልሰዋል:: ከዚህ የምንረዳው ተማሪዎቹ ከመማሪያ መጽሀፋቸው በተጨማሪ ከተለያዩ ጽሁፎች ጋር እንዲተዋወቁ አመቺ ሁኔታዎች አለመመቻቸታቸውን ነው:: የተለያዩ ይዘቶችንና አቀራረቦች ያሉዋቸው ጽሁፎችን በስፋት አለማንበብ ደግሞ ተዛማጅ የሆኑ የንባብ ስልቶችን ለመለማመድ አያስችልም:: ለ3ኛው ሃሳብ የተሰጠው የተማሪዎች አስተያየት ይህንኑ ነጥብ የሚያጠናክር ነው:: የተሰጠው አስተያየት የሚያመላክተው ተማሪዎቹ በቂ ልምምድ አለማድረጋቸውን ሲሆን፥ የልምምድ ማነስም አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን በማዳበር ላይ ተጽዕኖ እንደሚኖረው ነው::

ከተማሪዎቹ መልሶች ለመረዳት እንደሚቻለውም የአማርኛ ቋንቋ መምህሮቻቸው ከተለያዩ ምንጮች ልዩ ልዩ ምንባቦችን እየወሰዱ ወይም እያዘጋጁ ለተማሪዎቻቸው እንዲመጥን አድርገው በማቅረብ እና ተማሪዎችም ካነበቡት ጽሁፍ ጭብጥ ጋር የሚዛመዱ ምንባቦችን ፈልገው እንዲያመጡ ሁኔታዎችን በማመቻቸትና የተለያዩ የንባብ ስልቶችን በማለማመድ የተማሪዎቻቸውን ችሎታ ለማዳበር የሚረዳ ምቹ የትምህርት አውድ አይፈጥሩም:: ይህም ሰለሞን (1989:38) ተፈራ (1990:26) እና በየነ (1985:37) ለመምህራንና ለተማሪዎች ባቀረቡዋቸው ተዛማጅ ጥያቄዎች ካገኙት መልስ ጋር የሚጣጣም ሆኖ ተገኝቷል::

በሰንጠረዥ 7 እንደተቀመጠው የመላሾቹን አስተያየት አስተማማኝነት የአመለካከት መለኪያ በሆነው ቀመር (formula) ውጤቱ ከተሰላ በሁዋላ በt-ቴስት ስሌት በ0.05 የጉልህነት ደረጃ ለመገምገምና ለማረጋገጥ ተሞክሮአል:: ውጤቱ በ79 የነጻነት ደረጃ (degree of freedom) ማለትም N-1 ከሚነበበው የt-ሰንጠረዥ ዋጋ ከ1.980 የበለጠ ነው:: በመሆኑም የተሰላው የt-ዋጋ 26.28 ከ1.980 ያለው ብልጫ የሚያመለክተው ተማሪዎቹ ቅድመ ልምምድ በቂ የንባብ ትምህርት ልምምድ እንዳልተከታተሉ ነው::

ተጠኚዎቹ ተማሪዎች በ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል የንባብ ትምህርት ከተከታተሉና ልምምድ ካደረጉ በሁዋላ የተማሩትን ምን ያህል ተቀብለው ተግባራዊ አድርገዋል? ልምምዱንስ ወደውታል? የሚሉትን ጥያቄዎች ቀጥለን እንመለከታለን:: ለጥያቄዎቹ የመልስ ትንታኔ ከመጠይቁ ክፍል ሁለት ከ6-21 ካሉት ሃሳቦች ከተገኘው የተማሪዎች ምላሽና ከምልከታ ማስታወሻ ከተገኙት መረጃዎች አኩዋያ ይቀርባል:: ትንታኔውም በጥናቱ ለተነሱት ጥያቄዎች 1.2.2. እና 1.2.3 መልስ ለመስጠት ያስችላል::

### 4.2.3. በክፍል ሁለት ከ6-21 ላሉት ሃሳቦች የተገኘ ውጤት መግለጫ

በሚቀጥሉት ሰንጠረዦች ላይ እንደተመለከተው÷ ከተራ ቁጥር 6 ጀምሮ ላሉት ሃሳቦች የተሰጡት አስተያየቶች በጥናቱ አላማ ስር ለቀረበው የጥናት ጥያቄ ማለትም የተማሩትን በተግባር ሊያውሉ ይችላሉን? ለሚለው አዎንታዊ እና አበረታች ምላሽ አስገኝተዋል:: ተማሪዎች ልምምዱን ደጋግመው በማካሄዳቸውና በክፍል ውስጥ ከቀረቡት የማስተማሪያ ምንባቦች ጋር በጭብጥ የሚዛመዱ ጽሁፎችን ከልምምዱ አዛምደው በማንበባቸው በተማሩት ትምህርት መሰረት ንባባቸውን ተግባራዊ ለማድረግ ፍላጎት እንዳላቸው ለመረዳት ተችሎአል::

ተማሪዎች የተዘጋጁትን የመለማመጃ ምንባቦች ከማንበባቸው በፊት ከርዕሶቻቸው ስለይዘታቸው መገመት÷ ዋና ዋና ነጥቦችን ለማግኘት ምንባቦቹን መቃኘት እና በሁዋላም ምንባቡቹን አንብበው ያገኙትን መልእክት ከቀዳሚው ግምታቸውና እውቀታቸው ጋር ማገናዘብ የምንባቦቹን ይዘት አመዛዝኖ ለመረዳት ያስችላቸዋል:: እነዚህ ትምህርታዊ ተግባራት በአጥኚው በየልምምዱ ክፍለ ጊዜ በውይይት በስራ እንዲተረጎሙ በገለጻ መልክ ለተማሪዎች ማብራሪያ ተሰጥቶአል:: በማብራሪያዎቹ በመታገዝም ልምምዱ ተካሄዶአል:: ተማሪዎች የተማሩትን በስራ መተርጎማቸውን አስመልክቶ ለቀረቡላቸው ሃሳቦች የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ቀርቦአል፤

ሰንጠረዥ 8፥ ለልምምድ በቀረቡት ምንባቦችና መልመጃዎች አማካይነት የተማሩትን የንባብ ስልቶች ተግባራዊ ማድረጋቸውን የሚገልጽ ሰንጠረዥ

| | | የስምምነት ምርጫዎች | | | | ያለመስማማት ምርጫዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | |
| ተ.ቁ. | የቀረቡ ሃሳቦች | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 6 | ከተለያዩ ጋዜጦች፥ መጽሀፍትና መጽሄቶች የተወሰዱ ምንባቦችን በትምህርቱ ወቅት በክፍል ውስጥ በማንበብ፥ መልመጃዎችን በቡድን በመስራት የንባብ ስልቶችን (መልዕክት ትንበያን፥ የአሰሳ ንባብን፥ የምንባብ መልእክትን ከግል እውቀት ማዛመድን፥ አንድምታዊ ንባብን) ተግባራዊ ለማድረግ ችያለሁ:: | 39 | 48.75 | 31 | 36.75 | 9 | 11.25 | 1 | 1.25 |
| 10 | በግል በማነብበት ጊዜ የማገኛቸውን አዳዲስ ሃሳቦች ካለኝ ገጠመኝና እውቀት ለማዛመድና መልእክቱን ለመገምገም ሞክሬአለሁ:: | 52 | 65 | 24 | 30 | 3 | 3.75 | 1 | 1.25 |
| 11 | በግል የማነበውን ጽሁፍ በዝርዝር ከማንበቤ በፊት ስለአጠቃላይ ይዘቱ ምንነት ለማወቅ ጥረት አድርጌአለሁ | 56 | 70 | 19 | 23.75 | 3 | 3.75 | 2 | 2.5 |
| 15 | በግሌ በማነብበት ጊዜ እንደቀረቡልኝ ምንባቦችና ጽሁፎች አይነት የንባብ ስልቶችን ለመለማመድና በተቻለ መጠን የምንባቦቹን ፍሬ ሃሳብ ለመረዳት ጥረት አድርጌአለሁ | 56 | 70 | 17 | 21.25 | 7 | 8.75 | - | - |

Williams (1984:3) እና Nuttall (1996:167) እንደሚሉት ተማሪዎች እንደሚያነቡት ጽሁፍ አላማና አቀራረብ እንዲሁም እንደይዘቱ አስፈላጊነት ተስማሚ የንባብ ስልቶችን መለማመድ አለባቸው:: የሚያነቡትንም ጽሁፍ በሃያሲ አይን ተመልክተው መገምገምና መልእክቱንም መመርመር ይኖርባቸዋል፤ የሚያነቡትን ጽሁፍ መልእክት ዝም ብለው መቀበል የለባቸውም:: ለዚህም ልምምድ ያስፈልጋል:: ተጠኚዎቹ ከልምምዱ በሁዋላ የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል ተግባራዊ እንዳደረጉ በውል ለመረዳት አስተያየታቸውን እንዲሰጡ በሰንጠረዥ 8 ለቀረበው ለ6ኛው ጥያቄ 87.5% ወይም 70 ተማሪዎች፥ ለ10ኛው 95% ወይም 79 ተማሪዎች፥ ለ11ኛው 93.75% ወይም 75 ተማሪዎች እና ለ15ኛው 95% ወይም 79 ተማሪዎች "ተግባራዊ አድርጌአለሁ" ለሚለው ሃሳብ "በጣም እስማማለሁ" እና "እስማማለሁ" በማለት ተግባራዊ ማድረጋቸውን አረጋግጠዋል::

በልምምዱ ወቅት እንደታየው፥ ለልምምዱ የቀረቡት መልመጃዎች በተማሪዎች ላይ ፍላጎትን የሚያሳድሩ ስለነበሩ ከምንባቦቹ ጋር የሚዛመዱ የንባብ ስልቶችን ተግባራዊ ለማድረግና ለመለማመድ አመቺ ነበሩ:: በዚህም ተማሪዎች በራሳቸው አነሳሽነት በክፍል ውስጥ በተወያዩባቸው የውይይት ነጥቦች አማካይነት ጽሁፎችን ከጋዜጦችና መጽሄቶች ፈልገው ከልምምዱ ተዛማጅ ጥያቄዎችን በማንሳት በየምንባቡ በቀረቡላቸው ይዘቶች ላይ የበለጠ ለማንበብ የተሻለ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ተስተውለዋል:: የልምምዱ ክፍልም በውይይትና በመረዳዳት ላይ ያተኮረ ነበር::

ከአተገባበር አንጻርም ተማሪዎቹ መልመጃዎቹን ምን ያህል ተግባራዊ እንዳደረጉ ለቀረቡላቸው ሃሳቦች የሚከተለው ውጤት ተገኝቶአል።

ሰንጠረዥ 9:- የመልመጃዎችን አፈጻጸም የሚያሳይ የተማሪዎች መልሶች

| ተ.ቁ. | | የስምምነት ምርጫዎች | | | | ያለስማማት ምርጫዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | |
| | | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 7 | ለልምምድ የቀረቡት መልመጃዎች ለውይይትና ለመረዳዳት አመቺ የሆኑ፥ አዳዲስ ቃላትንና አባባሎችን የያዙ በመሆናቸው አውዳዊ አፈታታቸውን ለማጤንና የተማርኩትን የንባብ ስልት ተግባራዊ በማድረግ ከጓደኞቼ ጋር ለመረዳዳት አስችለውኛል | 55 | 68.75 | 19 | 23.75 | 3 | 3.75 | 3 | 3.75 |
| 8 | ለልምድድ የቀረቡት ምንባቦች ይዘትና በነዚህ ላይ የተመሰረቱት መልመጃዎች ከማውቀው ነገር ጋር የተዛመዱ ተጨማሪ ንባብ ለማካሄድና ጥያቄዎቹን በመስራት በይዘቱ ላይ የበለጠ ለመመራመር ረድተውኛል ብዬ አምናለሁ | 46 | 57.5 | 23 | 28.75 | 11 | 13.75 | - | - |

ለንባብ ትምህርት መለማመጃነት የሚመረጡት ምንባቦች ለተማሪዎች ፍላጎት የቀረቡ፥ ይዘታቸው ተስማሚነት ያለው፥ በስራ ሊተረጎም የሚችልና ለተማሪዎች መቀስቀስ (motivation) የሚሰጥ መሆን አለበት (Nuttall 1996:170-171)። እነዚህን የሚያሙዋሉ ይዘት ወይም መልእክት ካላቸው ተማሪዎቸ በጉጉት ሊያነቡዋቸው ይችላሉ። በተጨማሪም ይዘቱ ተማሪዎች ከሚያውቁት ነገር ጋር የተዛመደና ለቀጣይ ምርምራዊ ንባብ የሚጋብዝ መሆን አለበት። በዚህ መሰረት ለተማሪዎቹ የቀረቡት የልምምድ ምንባቦችና መልመጃዎች ፍላጎታቸውን የሚገዙ መሆናቸውንና በነዚህም አማካይነት የተማሩትን ትምህርት በስራ ላይ ማዋላቸውን ለማወቅ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ለ7ኛው 74 ተማሪዎች (92.5%) እና ለ8ኛው 69 ተማሪዎች (86.25%) "በጣም እስማማለሁ" እና "እስማማለሁ" በማለት ተግባራዊ ማድረጋቸውን አመልክተዋል። የምንባቦቹ ይዘቶች ከፍላጎታቸው የተዛመደ መሆን የትምህርቱ አውድ ይበልጥ በመረዳዳት ላይ እንዲመሰረት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጎአል። ተማሪዎችም የየግል ግንዛቤያቸውን ተንተርሰው ባነበቡት ምንባብ ይዘት ላይ አስተያየት ለመስጠት አስችሎአቸዋል። በዚህ መልክ ከተካሄደው ልምምድ ተጠቃሚ መሆናቸውን በመጠይቁ ለቀረቡት ሃሳቦች የሰጡት አዋንታዊ ምላሽ የልምምዱን ውጤታማነት ይጠቁማል።

በሌላ በኩል ደግሞ በልምምዱ ወቅት ተማሪዎች ምንባቦቹን አንብበው የተረዱትንና ያልገባቸውን ጥያቄ ለውይይት ከማቅረባቸው በፊት በግል በጸጥታ እንዲያነቡ ትኩረት ተሰጥቶበት ነበር። ይህም የተደረገው የተሳታፊዎቹ የንባብ ፍጥነት የተለያየ በመሆኑ በራሳቸው የፍጥነት ደረጃ አንብበው መልእክቱን እንዲገመግሙ፥ ከእውቀታቸው እንዲያዛምዱና ያልገባቸውን ጥያቄ በውል እንዲለዩ አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር ሲባል ነው። በተጨማሪም ለመልእክት ትርጎማ

የሚረዳው የንባብ መንገድ የጸጥታ ንባብ በመሆኑ (Greenwood 1992÷ Brown 1994÷ Nuttall 1996÷ Aebersold & Field 1997) የጸጥታ ንባብ እንደዋነኛ የልምምድ አካል ሆኖ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት በስራ ላይ ውሎአል:: በጸጥታ የንባብ ልምምድ ማካሄዳቸው ምን ያህል እንደረዳቸውና ትምህርት እንዳገኙበት ለቀረበላቸው ሃሳብ ተማሪዎች የሚከተለውን መልስ ሰጥተዋል::

ሰንጠረዥ 10:- በጸጥታ ማንበብ ምን ያህል እንደረዳቸው የተማሪዎችን መልሶች የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| | | የስምምነት ምርጫዎች | | | | ያለመስማማት ምርጫዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | |
| ተ.ቁ. | | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 9 | በጸጥታ በማነብበት ጊዜ የማነበውን ምንባብ መልእክት በመገመት÷ የመልእክቱን ተአማኒነትና ወቅታዊነት በመገምገም በምንባቡ የተለያዩ አንቀጾች መካከል ያለውንም ትስስር በማጤን ያልገባኝን ነጥብ ለመለየትና መልእክቱን በሚገባ ለመረዳት ረድቶኛል:: | 49 | 61.25 | 23 | 28.75 | 6 | 7.5 | 2 | 2.5 |

Grant (1987) እና Nuttall (1996) እንደሚያብራሩት÷ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ውጭ በእለታዊ ህይወታቸው የተለያዩ ጽሁፎችን ለተለያዩ አላማዎች ሊያነቡ ይችላሉ:: በውጭ በኢ-መደበኛ መልኩ የሚያካሂዱት ንባብና የክፍል ውስጥ ልምምዱም እንዲመሳሰል ለልምምድ የሚመረጡት ምንባቦች በአይነት የተለያዩ ቢሆኑ ይመረጣል:: በተጨማሪም ተማሪዎች ምንባቦቹን ለማንበብ የንባብ አላማ ሊኖራቸው እንደሚገባ÷ የንባብ አላማ ካላቸው ደግሞ የሚያነቡትን ምንባብ በጥሞና ለመመርመር እንደሚያስችላቸው÷ የንባብ አላማም እምዲኖራቸው በቅድመ ንባብ የትምህርት ክንውን ለልምምድ የቀረቡትን ምንባቦች አቀራረብና አላማቸውን የሚመለከት የመግቢያ ገለጻ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን Weir (1993:65) እና Grabe (1991:378) ያመለክታሉ:: በዚህ የውይይት ወቅትም ተማሪዎች በንባብ ጊዜ የሚያተኩሩባቸውን ነጥቦች አስቀድመው እንዲለዩና ምናልባትም በተለያዩ ጸሐፊዎች የቀረበ ርዕሰ ጉዳይ ለትምህርት ከተመረጠ ወይም ተማሪዎች ፈልገው ካመጡ ርዕሰ ጉዳዩ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ሊቀርብ የሚችል መሆኑን÷ የአቀራረብ ቅርጹን (ልብወለድ÷ ኢ-ልብወለድ) በመለየት በመልእክቱ ላይ እንዲያተኩሩ ትክክለኛ አቅጣጫ ሊያመለክታቸው ይችላል:: እነዚህን ነጥቦች ለይተው ካነበቡ የቀረቡላቸውን ምንባቦች መልእክት ለመፈለግ አላማ ይኖራቸዋል፤ ምንባቦቹንም ይበልጥ ለመመርመር ይችላሉ:: ያነበቡትንም መልእክት ከሚያውቁት ሃሳብና ከሚያውቁት የአገላለጽ መንገድ ጋር ለማነጻጸር ይሞክራሉ:: ይህንን አስመልክቶ ለተማሪዎች ለቀረቡት ጥያቄዎች ለ14ኛው ጥያቄ 75 ተማሪዎች (93.75%)÷ ለ12ኛው 75 ተማሪዎች (93.75%)÷ ለ13ኛው ጥያቄ ደግሞ 73 ተማሪዎች (91.25%) "እስማማለሁና" "በጣም እስማማለሁ" በማለት አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል:: ዝርዝሩን ቀጥለን በሰንጠረዥ እንመለከታለን::

ሰንጠረዥ 11፡- የንባብ አላማን፥ የምንባብ አይነትን መለየትና የመልእክት ትንበያን ክንውን ውጤት የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| | | የስምምነት ምርጫዎች | | | | ያለመስማማት ምርጫዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | |
| ተ.ቁ. | | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 14 | በልምምድ ወቅት የቀረቡልኝን ምንባቦች በዝርዝር ከማንበቤ በፊት በውይይት የተነሱትን ነጥቦች ከምንባቡ ውስጥ ለመፈለግ፥ ግምቴን ለማረጋገጥ እና ተጨማሪ እውቀት ለማግኘት ስል አነባቸው ነበር። | 51 | 63.75 | 24 | 30 | 3 | 3.75 | 2 | 2.5 |
| 12 | በልምምድ ወቅት የቀረቡልኝን ምንባቦች አይነት (ልብወለድ፥ ኢ-ልብወለድ) ለይቼ የሚያቀርቡትን መልእክት አላማና ጠቀሜታ ለመገምገም ጥረት አድርጌአለሁ። | 53 | 66.75 | 21 | 26.25 | 4 | 5 | 2 | 2.5 |
| 13 | በልምምዱ ወቅት በተማርኩበት ትምህርት መሰረት በተለያዩ ደራሲያን የቀረበ ርዕሰ ጉዳይ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚተነተንባቸውን መንገዶች በማጤን የጸሀፊዎቹን የመልእክት አቀራረብና አገላለጽ ለማወዳደር ጥረት አድርጌአለሁ። | 53 | 66.25 | 20 | 25 | 6 | 7.5 | 1 | 1.25 |

በዚህ ጥናት በክፍል ሁለት እንደተብራራው ተማሪዎች አንድን ምንባብ ሲያነቡ ቃል በቃል ሳይሆን ትርጉም-አዘል በሆኑ አሀዶች ደረጃ ቃላቱንና ሀረጋቱን አጣምረው ማንበብ ይኖርባቸዋል። Grellet (1981፡6) እና Boiarsky (1993፡57) እንደሚያብራሩት፥ በትርጉም-አዘል አሀዶች ደረጃ መልእክቱ ላይ አትኩረው የሚያነቡ ከሆነ የምንባቡን መልእክት ለመረዳትና በምንባቡ የተለያዩ አንቀጾች መካከል የሚኖረውን የጭብጥ ትስስር ለመገንዘብ ይረዳቸዋል። በሚያነቡበት ጊዜም ግልጽ ያልሆነ ነጥብ ሲያጋጥማቸው ምንባቡን ወደ ሁዋላ ተመልሰው በድጋሚ በማንበብ ወይም ከጉዋደኞቻቸውና ከመምህሮቻቸው ጋር በመወያየትና በመጠያየቅ የሚፈልጉትን መልእክት ሊጨብጡ ይችላሉ። ትምህርቱን ከተከታተሉ በሁዋላ የተጠቀሱትን ነጥቦች ተግባራዊ ማድረግ አለማድረጋቸውን ለማወቅ ለቀረቡት 16ኛና 17ኛ ሃሳቦች ተማሪዎች የሰጡት መልስ አዎንታዊ ሆኖ ተገኝቶአል። ለ16ኛው 75 ተማሪዎች (93.75%) ተግባራዊ ማድረጋቸውን ሲገልጹ 5(6.25%) ያህሉ ደግሞ በአሉታ ምላሻቸውን አመልክተዋል። በተመሳሳይ መንገድ ለቀረበው 17ኛ ሃሳብ 75(93.75%) ተማሪዎች በአዎንታ ሲመልሱ 5(6.25%) ተማሪዎች በአሉታ መልሰዋል። ብዙዎቹ ተማሪዎች የአዎንታ መልስ መስጠታቸው የተማሩትን ትምህርት ተግባራዊ ማድረጋቸውን ያመላክታል።

ሰንጠረዥ 12፡- በትርጉም-አዘል አሀድ ደረጃ በማንበብና የምንባቡን መልዕክት በድጋሚ በማንበብ ለመረዳት የሚደረገውን ጥረት የሚያሳይ

| | | የስምምነት ምርጫዎች | | | | ያለመስማማት ምርጫዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | |
| ተ.ቁ. | | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 16 | በማነብበት ጊዜ ግልጽ ያልሆነልኝ ነገር ሲያጋጥመኝ ከጉዋደኞቼ ወይም ከመምህሬን ጋር በመወያየት እና ምንባቡን ደግሚ በማንበብ መልእክቱን ለመረዳት ጥረት አድርጌአለሁ፡፡ | 60 | 75 | 15 | 18.75 | 3 | 3.75 | 2 | 2.5 |
| 17 | በማነብበት ጊዜ ትርጉም አዘል በሆኑ አሀዶች ደረጃ በማንበብና በምንባቡ አንቀጾች መካከል ያለውን የመልዕክት ትስስር በማጤን ጠቅላላውን መልእክት ለመረዳት ጥረት አደርግ ነበር፡፡ | 64 | 80 | 11 | 13.75 | 5 | 6.25 | - | - |

ባጠቃላይ፥ ተማሪዎቹ ከልምምዱ በሁዋላ ስላካሄዱት ልምምድና ከልምምዱም ያገኙትን እውቀት በተግባር ማዋላቸውን ለማወቅ በቀረቡላቸው የጽሁፍ መጠይቅ ሃሳቦች አብዛኛዎቹ የተማሩትን ተግባራዊ ማድረጋቸውንና የተሻለ መማራቸውን ከመልሶቻቸው ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም ልምምዱ አዎንታዊ መልስ አስገኝቷል፡፡ ይህም የሙከራ ምርምሩን የሚያጠናክር ነው፡፡

ይህንን ነጥብ በተጨማሪ የሚያጠናክረው ድህረ ልምምድ አስተያታቸውን ለማወቅ በመጠይቁ ለቀረቡት ጥያቄዎች የተገኘው መልስ ነው፡፡ የጥያቄዎቹ ትኩረት በሞዴሉ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ትምህርቱን ከተከታተሉ በሁዋላ ትምህርቱ በራሳቸው ምርጫ ለማንበብ ይረዳቸው እንደሆነ፥ ልምምዱን በመረዳዳት ማካሄዳቸው ልምድ አስጨብጧቸው እንደሆነና በዚህም ልምምዱን ወደውት እንደሆነ የሚሰጡትን መልስ ለመገምገም ነው፡፡ ለጥያቄዎቹ የተገኙት መልሶች በሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርበዋል፡፡

ሰንጠረዥ 13፡- ጠቅላላ ልምምዱን መውደድ አለመውደዳቸውን አስመልክቶ የቀረቡ የተማሪዎች መልሶች

| | | የስምምነት ምርጫዎች | | | | ያለመስማማት ምርጫዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | |
| ተ.ቁ. | | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 19 | ንባብን በ"ቶፕዳውን" ዘዴ ልምምድ ማድረጌ በራሴ ምርጫና ፍላጎት የተለያዩ ጽሁፎችን ለማንበብ ያስችለኛል ብዬ አምናለሁ፡፡ | 56 | 70 | 19 | 23.75 | 4 | 5 | 1 | 1.25 |
| 20 | በልምምዳችን ወቅት መምህሩ ያደረጉልኝ ግልጽና በቀላሉ የሚገባ የተማርነውንም ልምምድ በተግባር ላይ ለማዋል የማያስቸግር ነበር፡፡ | 49 | 61.25 | 23 | 78.75 | 7 | 8.75 | 1 | 1.25 |
| 21 | በ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስረማሪያ ዘዴ የተሰጠኝን ትምህርትና ልምምድ ወድጄዋለሁ፡፡ | 49 | 61.25 | 23 | 78.75 | 8 | 10 | - | - |
| 18 | ከክፍል ጓደኞቼ ጋር በመሆን በየግላችን አንብበን የተረዳነውን ሃሳብ በጋራ እንድንወያይበት ከእውቀታችን እንድናዛምደውና እንድንገመግመው መደረጉ በት/ቱ ሂደት ራሳችንን ችለን የመስራት ልምድ እንድናዳብር የሚረዳን ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ | 48 | 60 | 20 | 25 | 11 | 13.75 | 1 | 1.25 |

ከመጠይቁ የተገኙትን መረጃዎች አስተማማኝነት ለማረጋገጥ በCornbach Alpha ቀመር ተሰልቶ ውጤቱ 49.2 ሲሆን በ79 የነጻነት ደረጃ ከt-ሰንጠረዥ ከሚነበበው 1.980 የበለጠ በመሆኑ ተማሪዎቹ ያቀረቡት አስተያየት አስተማማኝነት ይኖረዋል፡፡

የተማሪዎቹ አስተያየተ በስሌቱ አማካይነት አስተማማኝነት ካለው ደግሞ ተማሪዎቹ የተማሩትን ትምህርት ተግባራዊ አድርገዋል ለማለት የሚያስደፍር ነው፡፡ ለማጠቃለልም ተማሪዎች ትምህርቱን ተከታትለው የተማሩዋቸውን የንባብ ስልቶች አጠቃቀም አውቀው ተግባራዊ ሊያደርጉ ወይም ሊጠቀሙባቸው ይችላሉን? ለሚለው ጥያቄ አዎንታዊ መልስ ለመስጠት እንደሚቻል የተማሪዎቹ አስተያየትና የምልከታው ማስታወሻ (በ4-3 ስር ይመልከቱ) ውጤት ያሳያል፡፡ በተግባር እንደታየውም ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት በስራ ላይ በማዋል ከተማሩት ትምህርት ተጠቃሚ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተችሎአል፡፡

## 4.3. ከምልከታ ማስታወሻ የተገኘ ውጤት ትንተና

የአጥኚው የምልከታ ማስታወሻ ከ20/01/1992 እስከ 09/03/1992 ባለው ጊዜ ውስጥ አጥኚው በተሳታፊ ተመልካችነት በልምምዱ ወቅት መዝግቦ የያዛቸውን ውሱን ምልከታዎች የያዘ ነው /አባሪ ሐ ገጽ 119 እስከ 128 ይመልከቱ/፡፡ የምልከታው ማስታወሻ ከተማሪዎች ጋር የተደረገውን ትውውቅ፥ የተደረገላቸውን የማነቃቂያ ገለጻ፥ ስለ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል የትኩረት ነጥቦች የተሰጠውን ትምህርትና የተደረገውን የአጥኚውን እገዛ፥ ተማሪዎች

ስላካሄዱት ልምምድ፥ ለተማሪዎቹ ስለተሰጡት ቅድመ ልምምድና ድህረ ልምምድ ፈተናዎች አሰጣጥ አጠቃሎ የያዘ ነው:: በነዚህ መረጃዎች አማካይነት በጥናት አላማነት ለቀረበው 1.2.2. የጥናት ጥያቄ የተገኘውን መልስ ከመጠይቁ ቁጥር 6-21 ከተገኘው መልስ አዛምደን እንመለከታለን::

በ1.2.2. ስር የተነሳው የጥናት ጥያቄ "ተማሪዎች የተለያዩ የንባብ ስልቶችን (የምንባብ መልእክት ትንበያን፥ አንድምታዊ ንባብን፥ አውዳዊ የቃላት አፈታትን፥ ንባብን ከቀዳሚ እውቀት ማገናዘብን)፥ ንባብ የሚካሄድበትን አላማ (ለትምህርት፥ ለመረጃ መሻት፥ ለመዝናናት ወዘተ.) መሆኑን አውቀው ሊጠቀሙበት ይችላሉን?" የሚለው ሲሆን መልሱ እንደሚከተለው ጠቅለል ባለ መልኩ ቀርቦአል::

በንባብ ትምህርት ለተማሪዎች ሊደረግ የሚገባው በሚያነቡበት ጊዜ ምቹ የትምህርት አውድን መፍጠር ነው፤ በትምህርቱ ሂደት ተማሪዎች ማድረግ የሚገባቸውን በመግለጽ፥ ልምምዱን ሲያካሂዱ የሚያጋጥማቸው እንቅፋት ካለ በመለየትና በማስወገድ ተገቢ መፍትሄ መስጠት ነው:: Silberstein (1994:10) እና Clarke & Silberstein (1977:137) እንደሚያብራሩት፥ ተማሪዎች ጥሩ አንባቢዎች እንዲሆኑና ያለመምህር እገዛ ራሳቸውን ችለው እንዲያነቡ ብሎም መሰረታዊ የሆኑ የንባብ ስልቶችን እንዲጠቀሙ መልጃዎችን እንደአስፈላጊነቱ ለዋውጠ በማዘጋጀት መጠቀም ያስፈልጋል:: ከሚያነቡት ምንባብ ውስጥ ምን ያህል መልእክት እንደተረዱም በሚያቀርቡዋቸው የመልመጃ መልሶች ስለሚገልጹ በመግቢያ ውይይት ጊዜ ጥያቄዎችን በቃል ማቅረብና ማነቃቃት በንባብ ጊዜ የሚያተኩሩባቸውን ነጥቦች ሊያመለክታቸው ይችላል:: ከዚህ በተረፈ አብዛኛውን ስራ መፈጸም ያለባቸውና የሚፈጽሙትም ተማሪዎች ናቸው::

ከላይ እንደተገለጸው፥ ተማሪዎቹ መሰረታዊ የሆኑ የመነሻ ሃሳቦችን እንዲጨብጡና በተከታታይ በልምምድ ሂደት እንዲያጠናክሩዋቸው ትምህርት ከተሰጣቸው በሁዋላ የተማሩትን ምን ያህል በተግባር ላይ አውለዋል? የሚለውን ጥያቄ ከሶስት አቅጣጫዎች መመልከት ተገቢ መሆኑን Koul (1996:164) ይጠቁማሉ:: እነዚህም አንደኛ ተማሪዎች ከወሰዱት የፈተና ውጤት አኩዋያ ተግባራዊነቱን መለካት ይቻላል:: የፈተናውን ውጤት በሚመለከት የታየው የችሎታ መሻሻል በ4.1 ስር በዝርዝር ተብራርቶአል:: ሁለተኛው በጥናቱ ተሳትፈው ልምምዱን ከተከታተሉት ተማሪዎች አስተያየት ነው:: የተማሪዎች አስተያየት በክፍል 4.2 በሰንጠረዥና ማብራሪያዎች አማካይነት ቀርቦአል:: ሶስተኛው ደግሞ ከተማሪዎች ልምምድና ልምምዱ ካስገኘው ውጤት ሲሆን ይህንን ደግሞ በአባሪ ሐ ከገጽ 119 እስከ 128 ከቀረበው የምልከታ ማስታወሻና ከተገኙት መረጃዎች አኳያ ማየት ይቻላል::

በልምምዱ ምልከታ ሂደት ለመረዳት እንደተቻለው አብዛኞዎቹ ተማሪዎች በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ማከናወን የሚገባቸውና የሚያተኩሩባቸው ነጥቦች ከተገለጸላቸው በኋላ ልምምዱን በተሳካ

ሁኔታ በማካሄድ የተማሩትን በተግባር ለማዋል ችለዋል:: ትምህርቱን በተግባር ማዋላቸውን፥ የተደረገላቸውን ገለጻ መረዳታቸውንና ከልምምዱ ተጠቃሚ መሆናቸውን አስመልክቶ ለቀረቡት 20 ና 21 ጥያቄዎች የሰጡት መልስ ይህንን አስተያየት የሚያጠናክር ነው:: በልምምዱ ወቅትም የትምህርት አቀራረቡ በሚከተሉት መንገዶች ተከፋፍሎ ተግባራዊ ሆኖአል:: በ2.1.2 ስር እንደተገለጸው የተማሪዎች ሙከራና ጥረትም ከነዚህ ክንውኖች አፈጻጸም አኳያ የቀረበ ነው:: እነዚህም በቅድመ ንባብ፥ በንባብ ጊዜና በድህረ ንባብ የተከናወኑትን ይይዛሉ::

ሀ. ከቅድመ ንባብ ክንውኖች አኳያ:- በዚህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች በመጀመሪያ በግል የሚያውቁትን ነጥብ በማስታወሻ እንዲያሰፍሩና በሁዋላም በቡድን ያገኟቸውን ነጥቦች በጋራ ለክፍሉ እንዲያቀርቡ የመነሻ ጥያቄዎች ቀርበውላቸዋል:: ምክንያቱም ተማሪዎች የቀረቡላቸውን ምንባቦች በዝርዝር ከማንበባቸው በፊት ስለምንባቦቹ አጠቃላይ ይዘቶች እንዲያስላስሉ፥ እንዲገምቱና በርዕሶቹ ዙሪያ የሚያውቁትን እንዲያስታውሱ ጥያቄዎችን መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን Greenwood (1992)፥ Williams (1984) Nuttall (1996) እና Hyland (1995) ስለሚያመለክቱ ጠቃሚነቱ ስለታመነበት ነው:: ይህም ተማሪዎች ያላቸውን ርዕስ-ተኮር እውቀት አስታውሰው እንዲጠቀሙና ከምንባቦቹም የሚፈልጉትን እንዲረዱ፥ የሚሰሩትንና አሰራሩን ለመጠቆም እንዲሁም ምንባቦቹን አንብበው ለመጨረስ መቀስቀስ እንዲኖራቸው ለማድረግ ይረዳል::

በተጨማሪም ቅደመ ንባብ ትምህርታዊ ክንውኖች ተማሪዎች ምንባቡን በትጋት እንዲያነቡ፥ የምንባቡን ይዘት ከእውቀታቸው፥ ከፍላጎታቸውና ከንባብ አላማቸው በማዛመድ ተማሪዎችን በክንውኖቹ በስፋት የሚያሳትፉ ይሆናሉ:: በዚህም የዳበረ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው አንባቢዎች የሚያነቡትን ጽሁፍ የሚመረምሩበትን ሂደት ሊያለማምዱዋቸው ይችላሉ:: ከነዚህ ነጥቦች አኳያ የምልከታ ማስታወሻው ውጤት እንደሚያሳየው ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ተግባራዊ ማድረጋቸውን ማረጋገጥ ይቻላል:: ይኸውም ለልምምድ የቀረቡላቸውን የማስተማሪያ ምንባቦች በዝርዝር ከማንበባቸው በፊት ርዕሶቻቸው በሰሌዳ ላይ ተጽፈው በርዕሶቹ ላይ የሚኖራቸውን ተዛማጅ ቀዳሚ እውቀት የሚመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበውላቸዋል:: ተማሪዎቹ በጥያቄዎቹ አማካይነት ስለ ርዕሶቹ የሚያውቁትን፥ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ሲነገር የሰሙትንና በተለያዩ ጊዜያት ተጽፈው ያገኟቸውን ሃሳቦች በግልም በቡድንም በአጭር በአጭሩ በመግለጽ ከሞላ ጎደል በምንባቦቹ ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ ነጥቦችን በውይይት አቅርበዋል:: የምንባቦቹን ይዘት አስቀድመው በመገመታቸው ይህንኑ ለማረጋገጥ እና በምንባቦቹ ውስጥ የተገለጸውን ሃሳብ ለመረዳት እንደሚያነቡም አላማቸውን ጠቁመዋል::

ለ. በንባብ ጊዜ ከተከናወኑት ተግባራት አኳያ:- ተማሪዎች በቅድመ ንባብ በዝግጅት መልክ ከምንባቡ አጠቃላይ ይዘት ጋር እንዲተዋወቁ ውይይት ከተካሄደ በሁዋላ በቀጥታ ያከናወኑት ምንባቡን በጸጥታ ማንበብ ነው:: ይህንን ተግባራዊ ለማድረግም በመጀመሪያ በግል እንዲያነቡ፥

# ምእራፍ አምስት

## የጥናቱ ግኝት ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳቦች

### 5.1. የጥናቱ ግኝት ማጠቃለያ

ለዚህ ጥናት መነሻ ምክንያት የሆነው የ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ ንባብን ለማለማመድና የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር የሚኖረውን ተግባራዊነትና ውጤታማነት ለመመርመር መሆኑ በምዕራፍ አንድ ተጠቅሷል፡፡ የሞዴሉን ውጤታማነትና ተግባራዊነት ለመመርመር ደግሞ በተለያዩ መልመጃዎችና ምንባቦች መጠቀም እንደሚያስፈልግ በክፍል ሁለት ተገልጿል፡፡ በሞዴሉ ስነ ትምህርታዊ መመሪያዎች አማካይነት በተዘጋጁት ምንባቦችና መልመጃዎች በመጠቀምም ሞዴሉ የሚኖረው ተግባራዊነትና ውጤታማነት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

በክፍል 1.2 ስር እንደተጠቀሰው የሞዴሉን ተግባራዊነትና ውጤታማነት በመፈተሽ በጥናቱ ለመመለስ የተሞከሩት ጥያቄዎችም የሚከተሉት ነበሩ፡፡

- ሞዴሉ በአማርኛ ቋንቋ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል ይረዳልን?
- ተማሪዎች የተለያዩ የንባብ ስልቶችን (የምንባብ መልእክት ትንበያን፥ አንድምታዊ ንባብን፥ አውዳዊ የቃላት አፈታትን፥ ንባብን ከቀዳሚ እውቀት ማገናዘብን)፥ ንባብ የሚካሄድበትን አላማ ለትምህርት፥ ለመረጃ ፍላጎት፥ ለመዝናናት፥ ወዘተ) መሆኑን አውቀው ሊጠቀሙባቸው ይችላሉን?
- ተማሪዎች ከ"ቶፕዳውን" የንባብ ትምህርት አቀራረብ ልምምድ በሁዋላ የቀረበላቸውን ትምህርትና ልምምድ ይወዱት ይሆን? ለምን?

እነዚህን የጥናት ጥያቄዎች ለመመለስ በአንድ በኩል የስድስት ሳምንታት የትምህርት አሰጣጡ በሞዴሉ ትምህርታዊ መርሆዎች መሰረት ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን የምልከታ መረጃዎችም ተመዝግበዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተማሪዎች መጠይቅ እንዲሞሉ የተደረገ ሲሆን ተማሪዎች የወሰዱዋቸው የቅድመ-ልምምድና የድህረ-ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤቶች ንጽጽራዊ ውጤት በእስታትስቲካዊ ስሌት መሰረት እንዲተነተኑ ተደርገዋል፡፡ በተገኘውም ውጤት መሰረት የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ተመልሰዋል፡፡

### 5.1.1. የትምህርት አሰጣጡን ተግባራዊነትና ውጤታማነት በሚመለከት

የማስተማሪያ ሞዴሉን ውጤታማነትና ተግባራዊነት ለመፈተሽ የተመረጠው የጥናት ስልት ፍተነታዊ የምርምር ስልት ነው። ፍተነታዊ ምርምሩን ተግባራዊ ለማድረግም በናሙና በተመረጠው ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በእጣ ናሙና ከተወሰዱት ሁለት የዘጠነኛ ክፍል የመማሪያ ምድቦች ውስጥ የሚገኙ 160 ተማሪዎች በእጣ የምደባ ስልት የሙከራውና የቁጥጥር ቡድን ተብለው ሁለት የጥናት ቡድኖች ተደራጅተዋል። በሁለቱም ቡድኖች አባላት የትምህርት አቀባበልና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ የጎላ ልዩነት የማይታይ መሆኑን ለማረጋገጥ ቅደመ ልምምድ ፈተና ተሰጥቶአል። በሰንጠረዥ 2 ገጽ 69 በተገለጸው ውጤት መሰረት ለጥናቱ ተመርጠው በተደራጁት በቁጥጥር ቡድንና በሙከራው ቡድን መካከል የትምህርት አቀባበልና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ የጎላ ልዩነት የሌላቸው መሆኑን ለመለካት ተሞክሮአል። በተገኘው እስታስቲካዊ የስሌት ውጤት መሰረት ሁለቱም ቡድኖች ተመጣጣኝ ችሎታ ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል።

በቡድኖቹ መካከል ተመጣጣኝ ችሎታ መኖሩ ከተረጋገጠ በሁዋላ ሁለቱም ቡድኖች ተመሳሳይ ይዘት ያለውን የንባብ ትምህርት ልምምድ ለስድስት ሳምንታት ተከታትለው ሲያበቁ ድህረ ልምምድ ፈተና ተፈትነዋል። በዚህ የፈተና ውጤት መሰረት በሁለቱ ቡድኖች መካከል የጎላ የውጤት ልዩነት ተዝግቦአል። በፈተናው የሙከራው ቡድን ጠቅላላ ድምር 5394፥ አማካይ ውጤቱ 67.43፥ ልይይቱ 136.87 እና መደበኛ ልይይቱ ደግሞ 11.69 ሆኖአል። በተመሳሳዩ ፈተና የቁጥጥር ቡድኑ ጠቅላላ ድምር 4943፥ አማካይ ውጤቱ 61.78፥ ልይይቱ 122 እና መደበኛ ልይይቱ 11.04 ነው።

የሙከራው ቡድን ልይይት 136.87 ሲሆን የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ 122 ሆኖአል። መደበኛ ልይይታቸው እንደቅደም ተከተላቸው፥ የሙከራ ቡድኑ 11.69፥ የቁጥጥር ቡድኑ 11.04 ተመዝግቧል። በነዚህ መረጃዎች አማካይነት የቡድኖቹ የአማካይ ግምት ልዩነት 11.37 መሆኑ ከተሰላ በኋላ የሙከራውንና የቁጥጥር ቡድኑን ውጤት በt-ቴስት ለማነጻጸር ተሞክሯል (ሰንጠረዥ 4 ገጽ 72 ይመለከቷል)።

ከዚህ በላይ በተገለጹት የልዩነት ማሳያ ግምገማ ውጤቶች እንደሚታየው የሙከራው ቡድን ከቁጥጥር ቡድኑ ሲነጻጸር የሙከራው ቡድን በድህረ ልምምድ ፈተና የተሻለ ውጤት አስመዝግቧል።

ፍትነታዊ ምርምሩን ለመፈተሽ የቀረቡት መላምቶች፥ በድህረ ልምምድ የፈተና ውጤት መስረት በቁጥጥርና በሙከራው ቡድን መካከል የችሎታ መበላለጥ አይታይም የሚለው ባዶ መላምት (Ho) እና በድህረ ልምምድ የፈተና ውጤት መስረት በቁጥጥር ቡድኑና በሙከራው ቡድን መካከል የጎላ የችሎታ መበላለጥ ይኖራል የሚለው አማራጭ መላምት ($H_1$) ነበሩ::

ከፍትነታዊ ምርምሩ ውጤት ሰንጠረዥ 5 ገጽ 74 በተገኘው ግንዛቤ መሰረት የመጀመሪያው መላምት ተቀባይነት አላገኘም:: ስለዚህ የጥናቱ ግኝት እንደሚከተለው ሊጠቃለል ይችላል፤

በ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል የተማሩት ተማሪዎች በልማዳዊ የማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩት የበለጠ ውጤት አስመዝግበዋል:: በሙከራው ቡድን (በ"ቶፕዳውን" የትምህርት አቀራረብ የተማሩት) ውስጥ የሚገኙት ተማሪዎች በቁጥጥር ቡድኑ ውስጥ ከሚገኙት የበለጠ ውጤት በማስመዝገባቸው የ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል እንደ አንድ የማስተማሪያ ስልት ቢያገለግል የተሻለ ውጤት ይኖረዋል::

### 5.1.2. ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ተቀብለው ተግባራዊ ከማድረጋቸው አንጻር

የ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል ያለውን ተግባራዊነትና ውጤታማነት ለመፈተሽ የተካሄደውን ፍትነታዊ ምርምር ለማዳበር ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት አጋዥ የሆኑ የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶችን መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቶአል:: በዚህ መሰረት በሙከራው ቡድን ውስጥ በተጠኚነት የተሳተፉትን ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ በማስሞላት ቅድመና ድህረ ልምምድ አስተያየታቸውን ለማወቅና በልምምድ ወቅት የታዩትን የተማሪዎች ጥረቶች ለመግለጽ ከምልከታ ማስታወሻ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በቅንጅት ለመጠቀም ጥረት ተደርጎአል::

ተማሪዎች በሞዴሉ ስነትምህርታዊ መመሪያዎች አማካይነት በተዘጋጁት ምንባቦችና የመልመጃ ጥያቄዎች ልምምድ ከማድረጋቸው በፊትና ከልምምድ በሁዋላ ስለነበራቸው ችሎታ ለማወቅ በቀረበው መጠይቅና ከምልከታ ማስታወሻ በተገኘው መረጃ ትንታኔ መሰረት የሚከተሉት መሰረታዊ ነጥቦች ተጠቃለው ቀርበዋል፤

- መምህራኑ ለትምህርት የቀረቡትን ምንባቦች ከማስነበባቸው በፊት ከምንባቦቹ ርዕሶች ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ለንባብ እንደማያዘጋጇቸው እና በምንባቦቹ አማካይነትም የተለያዩ የንባብ ስልቶችን እንማያለማምዷቸው፥

- ተማሪዎች ብዙውን ጊዜ በመጽሐፋቸው ውስጥ የሚገኙትን የመልመጃ ጥያቄዎች በመስራት ላይ ብቻ የተወሰኑና ተጨማሪ ምንባቦችን አምጥተው ወይም ተዘጋጅተውላቸው በክፍል ውስጥ አንብበው እንደማይወያዩባቸው፣
- በመደበኛም ሆነ በኢ-መደበኛ መንገድ የሚያደርጉት የንባብ ልምምድ መጠነኛ እንደነበረ፣
- የተለያዩ የንባብ ስልቶችን፣ የንባብ አላማና ምንነትን ለይቶ ማንበብ እንዲሁም የምንባብ መልእክትን ከእውቀታቸው ጋር አገናዝበው ለማንበብ መሞከር የተሻለ ግንዛቤ እንዲሰጣቸው፣
- አንድን ምንባብ በዝርዝር ከማንበባቸው በፊት ስለምንባቡ መልእክት አስቀድመው የተወሰነ ግምት ማሳደር ለንባብ ተግባር የተሻለ እንደሆነ፣
- ንባብን በጸጥታ ማካሄድ ከሚነበበው ምንባብ ውስጥ የሚያገኙትን መልእክት ለመረዳትና የንባብ ፍጥነታቸውን ለመጠበቅ አመቺ የንባብ ስልት መሆኑን፣
- በልምምድ ወቅት አንብበው የተረዱትን ከጉዋደኞቻቸው ጋር ለመወያየት አመቺ የትምህርት አውድ ስለተመቻቸላቸው የተሻለ ልምድ ማግኘታቸውን፣
- በውይይት በመሳተፋቸው ምንባብ እንደአንባቢው እውቀትና ግንዛቤ ሊተረጎም መቻሉንና ማንኛውም ምንባብ በተመሳሳይ መንገድ እንደማይነበብ መረዳታቸውን፣
- በሚያነቡበት ጊዜ የምንባቡን መልእክት ለመረዳት ቅድሚያ መስጠት እንዳለባቸውና የምንባቡ መልእክት በአንድ ጊዜ ንባብ ብቻ ሊጨበጥ ካልቻለ ዋና ዋና ፍንጮችን በመጠቀም በድጋሚ ማንበብና ለመረዳት ጥረት ማድረግ ተገቢ መሆኑን፣
- የሚያነቡትን ምንባብ መልዕክት እንዳለ ከመቀበል ተአማኒነቱን ለመመርመርና አመዛዝኖ ለመረዳት መሞከር የተሻለ የንባብ ስልት መሆኑን የሚጠቁሙ መረጃዎች ተገኝተዋል፡፡

በተጠቀሱት መረጃዎች (በመጠይቁ የቀረቡት አስተያየቶች እና የምልከታ ማስታወሻ) መሰረት የንባብ ማስተማሪያ ሞዴሉ የትምህርት አቀራረብ የተማሪዎቹን አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንዳሻሻለ አዎንታዊ መልስ ተገኝቶአል፡፡ በዚህም ተማሪዎች ትምህርቱን ተከታትለው የተማሩትን የንባብ ስልቶች ለይተው ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ? ልምምዱንስ ይወዱት ይሆን? ለሚሉት ጥያቄዎች አዎንታዊ መልስ ለመስጠት እንደሚቻል የተማሪዎቹ አስተያየትና የምልከታው ማስታወሻ ውጤት ያሳያል፡፡ በልምምዱ ወቅት በተግባር እንደታየውም ሆነ ተጠኚ ተማሪዎቹ በሰጡት አስተያየት እንዳመለከቱት አብዛኞዎቹ የተማሩትን ትምህርት በተግባር ላይ አውለዋል፡፡ ይህም ተጠኚዎቹ ተማሪዎች፣ በአዲሱ የማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩት ትምህርት ተጠቃሚ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው፡፡

## 5.2. የመፍትሄ ሀሳቦች

በማስተማሪያ ሞዴሉ ተግባራዊነት ላይ የተካሄዱትን የሙከራና ደጋፊ ምርምሮችን ውጤቶች እና ትምህርታዊ ክንውን መመሪያዎች ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ሞዴሉ የተማሪዎችን

አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል የሚኖረውን ውጤታማነትና ተግባራዊነት ለመፈተሽ ተሞክሮአል፡፡ ከልምምዱ በመነሳትም በልምምዱ ሂደት የተሳተፉትን ተማሪዎች ቅድመና ድህረ ልምምድ አስተያየት ለማሰባሰብ ጥረት ከመደረጉም በተጨማሪ ትምህርታዊ ክንውኑን የሚገልጽ የምልከታ መረጃ ተመዝግቦአል፡፡ በተገኙት መረጃዎች ትንታኔም የንባብ ማስተማሪያ ሞዴሉ ከልማዳዊው የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ የተሻለ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሎአል፡፡ ስለሆነም ሞዴሉ ረዘም ላለ ጊዜ በስፋትና በጥልቀት ቢሰራበት ተማሪዎችን ጥሩ አንባቢዎች ለማድረግ እንደሚቻል የጥናቱ ውጤት ይጠቁማል፡፡

ከጥናቱ ግኝት በመነሳት የሚከተሉት የፍትሄ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

- ከተጠኚ ተማሪዎችና ተማሪዎችን ከሚያስተምሩት ነባር መምህራን ጥቆማ ለመረዳት እንደተቻለው ቀደም ሲል ተማሪዎች ከሚያነቡት ምንባብ ውስጥ የቀረበውን መልእክት ለመረዳት የሚያስችል በቂ ልምምድ አልተሰጣቸውም፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት ከጽሁፍ መጠይቅ፥ ከምልከታ ማስታወሻና ከፈተና ውጤቶች ለመረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎችን በስፋት በማሳተፍ ትምህርቱን ከሚያውቁት ነገር ጋር በማያያዝ ማስተማርና ማለማመድ ተግባራዊነቱ የጎላ በመሆኑ ሌሎች ተማሪዎችም በዚህ ዘዴ ቢማሩ ችሎታቸው ሊሻሻል እንደሚችል አጥኚው እምነት አለው፡፡
- ተጠኚ ተማሪዎች በዚህ የማስተማሪያ ሞዴል የትምህርት አቀራረብ የተከታተሉትን ትምህርት ከመውደዳቸው የተነሳ የተለያዩ ተዛማጅ ጽሁፎችን ከልምምዱ በማጣመር አንብበው ልምድ በማግኘታቸው ልምምዱ በስፋት ቢለመድና ለሌሎችም ቢሰጥ ጥሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ስለዚህ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ዋነኛ ተዋንያን የሆኑት መምህራን ተማሪዎቻቸውን የበለጠ ለመርዳት የሚሻሉበትን መንገድ ቢሞክሩ ትምህርቱን ተወዳጅ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡
- በሞዴሉ መርሆዎች አማካይነት ተማሪዎች የሚያውቁትን በመነሻነት በመጠቀም የሚያነቡትን ምንባብ ገምግመውና በውይይት ተረዳድተው እንዲሰሩ በመደረጉ ልምድ መለዋወጣቸውንና በቡድኖቹ መካከል የፉክክር ስሜት በመፍጠሩ በትጋት መለማመዳቸው ጥሩ ውጤት አስገኝቶአል፡፡ እርስ በርስ መወያየቱ የሚያነቡትን ምንባብ በውል ለመመርመር ስለሚያስችል አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ቁልፍ ሚና ይኖረዋል፡፡ ስለዚህ የማስተማሪያ ሞዴሉ በስፋት ቢለመድ ተማሪዎችን መርዳት እንደሚቻል የጥናቱ ውጤት አመልክቶአል፡፡
- ተማሪዎች በትምህርት ቤትና ከትምህርት ቤት ውጭ ንባብን እንዲወዱ የሚያበረታቱ ሁኔታዎች እንዲኖሩ በክፍል ውስጥ የሚካሄደውን ልምምድና በውጭ የሚያነቡትን ማዛመድ ያስፈልጋል፡፡ ይህንን በማድረግ በየጊዜው ያሳዩትን መሻሻል ለማረጋገጥ መመዘኛዎችን በመስጠት ክትትል ማድረግ ስለሚቻል መምህራን ጥረት ቢያደርጉ የተሻለ ውጤት ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ አንብቦ የመረዳት ችሎታም እንዲሁ ተገብይቶ የሚያበቃ ጉዳይ ባለመሆኑ የተለያዩ ተጨማሪ መልመጃዎችን በማዘጋጀት ለተማሪዎቻቸው ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ምሁራን እንደሚያብራሩት የንባብ ትምህርት ቀዳሚ አላማ ተማሪዎች ለንባብ ማስተማሪያነት የተመረጡትን ምንባቦች እንዲያነቡ ማድረግ መሆን አለበት፡፡ የመምህራኑ ሚናም ተማሪዎች የሚቀርብላቸውን ጽሁፍ ለምን አላማና እንዴት እንደሚያነቡት የተገነዘቡና በራሳቸው ጥረት

የሚገጥማቸውን ችግር ለማስወገድ የሚችሉ ብቁ አንባቢዎችን ለማፍራት በመሆኑ አሳስፈላጊ ከሆነ ጣልቃ ገብነት መታቀብ አለባቸው:: በዚህም አብዛኛውን ምድብ የትምህርት ሰአት ለተማሪዎቹ ማዋል ይኖርባቸዋል:: ተማሪዎቹም መምህሩ የሚያነብላቸውን ጽሁፍ እንዲያዳምጡ፥ የመልመጃ ጥያቄዎችን ብቻ እንዲሰሩ፥ ከምንባብ መልእክት ትርጎማ ወደ ንበት እንዲያዘነብሉ ከማድረግ ተቆጥበው አብዛኛውን ምድብ ሰአት ተማሪዎች ራሳቸው በጸጥታ እንዲያነቡ ማበረታታትና ምቹ የትምህርት አውድን ለመፍጠር ጥረት ማድረግ ያስፈልጋቸዋል::

- ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን እንዲያዳብሩባቸው ለማስተማሪያነት የሚመረጡት ምንባቦችና የሚዘጋጁት መልመጃዎች አቀራረብ ከተማሪዎች እውቀትና የንባብ አላማ ጋር የተዛመዱ እንዲሆኑ በአመራረጣቸውና አዘገጃጀታቸው ላይ ጥንቃቄ ቢደረግበት የተሻለ ይሆናል::

# ዋቢዎች


Aebersold, J. and M. Field. 1997. From Reader or reading teacher: Issues and Strategies. for Second Language Classrooms. Cambridge: Cambridge University Press.

Alderson, J.C. and A.H. Urquhart (eds.) 1984. Reading in a foreign language. Harlow: Longman.

Andersen, N.J. 1991. ''Individual Differences in Strategy use in Second Language reading and teaching'' in Modern Language Journal 75(4): 460-472.

___________ 1994. ''Developing Active Readers: A pedagogical framework to the second language reading class'' in system 22(2): 177-194.

Atwell, M.A, and L. Rhodes. 1984. ''Strategy Lessons as alternatives to skill lessons in Reading.'' In Journal of Reading 27(8): 700-705.

Ball, G.H. 1976. ''Standards for Materials Selection'' in Journal of Reading. 20(2): 205-211.

Barnett, M.M. 1989. More than Meets the eye: Foreign language reading theory and practice. Englewood Cliffs, New Jersey: Prentice Hall Regents.

Bejararno, Y. 1987. "A Cooperative Small Group Methodology in the Language Classroom" in TESOL Quarterly 21(3):489-504.

Breznitz, Z. and D. Share. 1992. "Effects of Accelerated reading rate on Memory for text" in:- Journal of Educational Psychology. 84(2): 193-199.

Brown, D.H. 1994. Teaching by Principle: an interactive approach to language pedagogy. Englewood cliffs, New Jersey. Prentice Hall Regents.

Brumfit, C. et al. 1980. Teaching English as a foreign language (second edition). Routledge: London and New York.

Boiarsky, C. 1993. Technical Writing: Contexts, Audiences and Communities. Allyn and Bacon. Nedham heights, M.A.

Cambourne, B. 1981. ''oral and written Relationships: A reading perspective'' in Exploring Speaking - Writing Relationships, connections and Contrasts. J.vann (ed). Thimble Press.

Carrell, P.L. 1983. ''Three Components of background knowledge in reading comprehension'' in Language Learning. 33(2): 183-107

_________. 1988a. ''Introduction'' in P.L. Carrell, J, Devine and D.E. Eskey (eds). Interactive approaches to second language reading. Cambridge. Cambridge University Press.

_________. 1987. "Context and Formal schemeta in ESL Reading" in: TESOL Quarterly. 21(3): 461-482.

_________. 1988b. ''Interactive text processing: implications for ESL reading classrooms'' in P.L. Carrell, J. Darine and D.E. Eskey (eds). Interactive approaches to second language reading. Cambridge: Cambridge University Press

Carrell, P.L., J. Devine and D.Eskey. (eds). 1988. Interactive approaches to second language reading. Cambridge: Cambridge University Press.

Carrell, P.L. and J.C. Eisterhold 1983/1988. ''Schema theory and ESL reading pedagogy'' reprinted in Carrell, P.L., J. Devine and D.E. Eskey (eds) 1988. Interactive approaches to second language reading. Cambridge: Cambridge University Press.

Carrell, P.L. and P. Floyed. 1987. ''Effects on ESL reading of teaching cultural content schemeeta'' in Language Learning 37(1): 89-108.

Carrell, P.L., B. Pharis and J. Liberto. 1989. "Metacognitive Strategy training for ESL Reading" in: TESOL Quarterly. 23(4): 647-678.

Cavalcanti, M. 1987. "Investigating FL reading performance through pause protocols" in: C. Faerch and G. Kasper (eds.) Introspection in SL research. Bristol. Multilingual Matters.

Celce-Murcia, M (ed) 1991. Teaching English as a second/Foreign language. Boston: Heinel and Heinel

Chicalanga, W.I. 1993. ''Exploring inferencing ability of ESL readers'' in Reading in a Foreign Language. 10(1): 931-950

Clarke, J.L. 1987. Curriculum Renewal in School Foreign language. Oxford: Oxford University Press.

Clarke, M.A. 1977. ''Reading in Spanish and English: Evidence from adult ESL students'' in Language Learning . 29(1):121-150.

Clarke, M.A. and S. Silbertein. 1988. ''Towards a realization of psychololinguistic principles in the ESL reading class'' in Language Learning. 27(1): 135-154.

Clay, M.M. 1968/1972. ''A syntactic analysis of reading errors'' in Mackay, R., B. Berkman and R.R. Jordan (eds). Reading in a Second Language. Rowley, Massachusetts: Newbury House

Cohen, L. and L. Manion. 1980. Research Methods in Education. London: Croomitelm.

Coady, J. 1979. "A Poycholinguistic model of the ESL reader" in: Reading in A Second Language. R. Mackay, S. Barkman (eds.)

Cooper, C.R. and A.R. Petrosky. 1976. ''A Psycholinguistic view of the fluent reading process'' in Journal of Reading. 20(3): 184-207.

Cowan, R.J. 1976. ''Reading, perceptual strategies and contrastive analysis'' in Language Learning. 26(1): 95-110.

Cross, D, and S. Paris, 1988. "Developmental and Instrumental Analyses of Chiddren's metacognition and reading comprehension" in: Journal of Educational Psychology 80(2). 131-141.

Cziko, A. 1980. ''Language Competence and reading strategies: A Comparison of L1 and L2 oral reading errors'' in Language Learning. 30(1): 101-116.

Dyer, C. 1995. Beginning Research in Psychology: A Practical Guide to Research Methods and Statistics. Oxford. Blackwell Publishers.

Eskey, D. 1988. ''Holding in the bottom: an interactive approach to the language problems of second language readers'' in carrell, P.L., J. Davine, and D. Eskey (eds) Interactive approaches to second language reading. Cambridge: Cambridge University Press.

Gibson, E.J. and Levine,H. 1975. The Psychology of Reading . Cambridge; MA: MIT Préss.

Goodman, K. 1970. ''Reading a psycholinguistic quessing game'' in Theoretical models and the process of reading. H Singer and R.B. Ruddell (eds). Newyork, Delaware: International Reading Association.

__________. 1971. ''Psychololinguistic Universals in the reading process'' in The Psychology of Second Language Learning. P. Prinseleur and T. Quinn (eds). Cambridge: Cambridge University Press.

__________. 1988. ''The Process of reading'' in P.L. Carrell, J. Devine and D. Eskey (eds). Interactive approaches to second language reading. Cambridge: Cambridge University Press.

__________. 1979. "The know-more and the know-nothing movements in reading: a personal response'' in Language Arts. 55(16): 657-613.

Goodman, K.S. and C. Burke 1973. Theoretically based studies of patterns of miscues in Oral reading performance. New York Macmillan.

Goetz, E.T., Reynolds, R., and Schallert, D. 1983. ''Reading in Perspective: what real cops and pretend Burglars look for in a story'' in Journal of Educational Psychology. 75(4): 500-510.

Grabe, W. 1988. ''Reassessing the term interactive'' in P.L. carrell, J. Devine and D, Eskey (eds). Interactive approaches to SL reading. Cambridge: Cambridge University Press.

________. 1991. "Current Development in Second Language Reading Research" in: TESOL Quarterly. 25(3): 375-406.

Grant, N. 1987. Making the most of your textbook. London: Longman.

Grellet, F. 1981. Developing Reading Skills: A practical guide to reading comprehension exercises. New York: Cambridge University Press.

Greenall, S. and M. Swan., 1986. Effective reading: A Practical Guide to Reading Comprehension Exercises. Cambridge: CUP.

Greenwood, J. 1992. ''Comprehension and Reading'' in Teaching English as an international language: A practical guide. G. Abbott et al (eds). London: Routledge.

Harrison, C. 1992. "The Reading Process and Learning to Read: What a Teacher Using a 'realbooks' approach needs to know" in: The Reading for Real Hand Book. London and New York: Routledge.

Hatch, E. and H. Farhady. 1982. Research Design and Statistics for Applied Linguistics. Newbury House Publishers, INC.

Haverson, W.W. 1991. ''Adult Literacy Training'' in Teaching English as a second/Foreign Language, Celce-Murcia, M. (ed). Boston: Heinel and Heinel.

Heaton, J. 1988. Writing English Language Tests. (New Edition) London: Longman UK Group Ltd.

Hedge, T. 1985. Using readers in Language Teaching. London: Macmillan Publishers Ltd.

Higgins, J. 1984. ''Reading and Risk taking: a role for the computer'' in ELT Journal 38(3): 192-198.

Hudson, T. 1982. ''The effects of induced schemata on the'' short-circuit'' in L2: non-decoding factors in L2 reading performance'' in Language Learning 32(1): 1-31.

Hughes, A 1989. Testing for language teachers. Cambridge: Cambridge University Press.

Hyland, K. 1995. "Purpose and Strategy. Teaching Extensive Reading Skills" in: Selected Articles from the Creative Classroom Activities 1989-1993 (ed.) Thomas Kral; English Language Program Division: (USIA)

Johnston, B. 1988. ''Active Reading'' in Moderns English teacher 16(1): 18-27.

Koul, L. 1996. Methodology of Educational Research (Second Edition) Uikas Publishing House Pvt. Ltd.

Lee, J.F. 1986. ''The Effects of three components of background knowledge and L2 reading'' in Modern Language Journal 70(4): 350-354.

Lewin, B.A. 1984. ''Reading between the lines'' in ELT Journal 38(2): 121-126.

Lunzar, E and K. Gardner. 1979. The Effective Use reading. London: Heinemann Educational Books/The Schools council.

Madeson, H.S. 1983. Techniques in Testing. Oxford: Oxford University Press.

McGarry, K. 1991. Literacy, Communication and Libraries: A study Guide. London: Library Association Publication Ltd.

Mcleod, B. And B. Maclaughlin. 1986. ''Restructuring or Automatically? Reading in a second Language'' in Language Learning. 36(2): 109-124.

Mendida Berkessa. 1988. ''A comparision of the reading level of Bahir Dar teachers'' College Freshman Students with the reading levels expected of them'' M.A. Thesis presented to the school of Graduate studies, A.A.U.

Moran, C. And E. Williams. 1993. ''Survey review: recent materials for the teaching of reading at the intermediate level and above'' in ELT Journal. 47(1): 64-84.

Munby, J. 1968. Read and Think: Training in intensive reading skills. Harlow: Longman.

Nicols, J.N. 1983. ''Using Prediction to increase content area interest and understanding'' in Journal of Reading. 27(3): 225-228.

Nunan, D. 1991. The Methodology of Language Teaching. A text book for teachers. Prentice Hall International (UK) Ltd.

________. 1993. Introducing Discourse Analysis. Penguire English.

Nuttall, C. 1982. Teaching Reading Skill in a Foreign Language. Heinemann Educational Books.

________. 1996. Teaching Reading Skills in a Foreign Language. (Second edition). Heinemann educational books.

Olen, I. and M. Machet. 1997. "Research Project to determine the effect of free Uoluntary reading on Comprenehsion" in South African Journals of Library and Information Science. 65(2):85-92.

Paran, A. 1996. ''Reading in ELT: Facts and Fiction'' ELT Journal 50(1): 25-34.

Parrot, M. 1993. Tasks for Language Teachers: A resource book for training and development. Cambridge: Cambridge University Press.

Richards, J.C. and D. Nunan. 1990. Second Language Teacher Education. Cambridge: Cambridge University Press.

Richards, J.C., J. Platt and H. Platt. 1992. Language Teaching and Applied Linguistics (second edition) London: Longman. UK Ltd.

Ringe, C. 1989. The Effective Teaching of Modern Languages. London: Longman UK Ltd.

Roller,, C.M. and A.R. Matambo. 1992. ''Bilinguals use of background knowledge in learning from text'' in TESOL Quarterly 26(1): 129-139.

Rossamn, T.B. Maclaughin and B. Mcleod. 1983. ''Second Language Learning: An information processing perspective'' in Language Learning. 33(2): 135-158.

Seliger, H, and E. Shohamy. 1989. Second Language Research Methods. Oxford. Oxford University Press.

Sequero, W. 1998. "A ready-made Reading class: Warming-up for reading" in: FORUM 36(1): 29-31.

Silbertstein, S. 1994. Techniques and Resources in Teaching Reading. New York: Oxford University Press.

Smith, F. 1973. Psycholinguistcs and Reading. New York: Rinehart. and Winston.

_______. 1985. Reading (second edition). Cambridge: Cambridge University Press.

Squire, J. 1984. ''Composing and Comprehending: two sides of the same basic process'' in Composing and comprehending. J.J. Jensen (ed) ERIC clearing house on Reading and Communication Skills.

Stanovich, K.E. 1991. ''Changing model of reading and reading acquisition'' in Reieben and C. Perfetti (eds) Learning to read: basic research and its implications: Hilldale, New Jersey: Lawrence Erlbaum.

Steffenson, M. and C. Joag-Dev. 1984. "Cultural Knowledge and reading" in: Reading in a Foreign Language. J. Alderson and Urquhart (eds.) Harlow: Longman.

Stillie, M and A. Lynskey. 1984. Further Comprehension: Book one . London: Basil Blackwell Ltd.

Swaffar, J. 1988. ''Readers,. Texts and second language students: the interactive process'' in Modern Language Journal. 72(1): 123-149.

Swaffar, J., K.Arnes, and H. Byrnes. 1991. Reading for Meaning: an An interactive approches to language learbning. Cliffs: N.J. Englewood.

Tomlinson, B. and R. Ellis. 1988. Teaching Secondary English a Guide to the Teaching of English as a Second Language. London: Longman.

Ulijin, M.J. and J.B. Strother 1990. ''The effects of syntatic simplification of EST texts in L1 and L2'' in Journal of Research on Reading 13(1): 38-54.

Vance, J. 1990. ''Developing Comprehension and Thinking in Whole-language Classrooms'' inc. Weaver (ed). Understanding whole-language: from principle to practice. Irwin publishing, Torento:Canada.

Walker, C. 1998. ''Books on reading: Survey review'' in ELT Journal 52(2): 169-173.

Weaver, C. (Ed). 1990. Understanding Whole-Language: from principle to practice. Irwin Publishings Toronto; Canada.

Wallace, C. 1992. Reading. Oxford: Oxford University Press.

Weir, C. 1993. Understanding and Developing Language Tests . Prentice Hall (UK) Ltd.

Widdowsen, H.G, 1978. Teaching Language as Communication. Oxford: Oxford University Press.

_______________. 1979. Explorations in Applied Linguistics. New York: Cambridge University Press.

Williams, E. 1984. Readin in the language classroom. London: Macmillan Publishers.

Williams, R. 1986. '' 'Top-ten' principles for teaching of reading'' in ELT Journal 40(1): 42-45.

Wittrock, M.C. 1984. ''Writing and the teaching of reading'' in Jensen, J.J. (ed) Reading and Comprehending ERIC clearing house on reading and communication skills.

Wixson, K.K. and M. Y. Lipson 1986. ''Reading Disability Research: an interactionist perspective'' in Review of Educational Research. 56(1): 111-136.

Zamel, V. 1992. "Writing one's way into reading" in: TESOL Quarterly . 26(3): 463-486.

Zinser, O. 1984. Basic principles of Experimental psychology. McGraw Hill INC.

ማስተዋል ውበቱ። 1989። "የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ፥ በአዲስ አበባ በሚገኙ በአራት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት" ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

ሰለሞን ሀለፎ። 1989። "አማርኛን በማስተማሪያ ዘዴነት የቃል ጽህፈት ሚና" ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፥ አዲስ አበባ ዩኒቨስቲ።

__________። 1990። "በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚሰጠው የቋንቋ ትምህርት የንባብ ክሂልን እንዴት ማዳበር ይቻላል?" መጽሄተ ትምህርት ቅጽ 4 ቁ. 6።

በየነ ማሞ። 1985። "በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች የቋንቋውን ክሂሎች የሚያዳብሩ ናቸው?" ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

በድሉ ዋቅጅራ:: 1988:: "ተሳታፊነት-ጭምትነት የሰብዕና አይነት ከድርሰት መጻፍና ከአንብቦ የረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ፤ በሶስት ኮሌጆች ተማሪዎች ላይ የተደረገ ጥናት" ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት÷ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ::

ተስፋዬ ሸዋዬ:: 1986:: አንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታን ማዳበር:: አዲስ አበባ፤ ትምህርት መሳሪያዎችና ማከፋፈያ ድርጅት::

ተፈራ በጋሻው:: 1990:: "ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ንባብ ትምህርት አቀራረብ" ዲማጽ አዲስ አበባ ዩኒበርስቲ::

አለማየሁ ፀጋዬ:: 1986:: "በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚፈጸሙ ስህተቶች ዋና ዋና ምንጮች" ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት÷ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ::

አጥናፍ ዋሴ:: 1989:: "መጽሃፍ ፐብሊሺንግ በኢትዮጵያ" መጽሄት ትምህርት ቅጽ 3 ቁጥር 5::

ጌታቸው አዱኛ:: 1986:: "ለአስረኛ ክፍል የተመረጡ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ምንባቦች የብቃት ደረጃ" ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት÷ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ::

ግርማ አውግቸው:: 1988:: "በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ቋንቋዎች ስነጽሁፍ ክፍል በበሳል ድርሰትና በሌሎች ኮርሶች ተማሪዎች በአማርኛ የሚከውኑዋቸው የጽህፈት ስራዎች ንጽጽራዊ ጥናት" ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት÷ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ::

የኔሰው ደሴ:: 1990:: "በኦሮምኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ተራክቦአዊ ሞዴልን በክፍል ውስጥ ተጠቅሞ ማስተማር ያለው አስተዋጽኦ" ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት÷ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ::

ሀ

# በኢትዮጵያ ትቅደም ቁጥር አንድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለዘጠነኛ ክፍል ለቅድመ ትምህርት የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና

ስም__________________ ምድብ_______________ ተራ ቁጥር__________

የተፈቀደው ሰዓት 1:20

I. *የሚከተለውን ምንባብ ካነበብህ በሁዋላ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ መርጠህ አመልክት::*

የህዝብ ብዛትና የሚያስትከትላቸው ችግሮች

ብዙ የመንግስት ሰራተኞች፥ በንግድ በኢንዱስትሪ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች፥ ምሁራንና በአጠቃላይ ህበረተሰቡ የህዝብ ብዛት መጨመር ከእርምጃና ከልማት ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ ያምናሉ:: እየበዛ የሚሄድ ህዝብ ለጠንካራና ለጤናማ ህብረተሰብ አስፈላጊ ነው የሚል አመለካከት አላቸው:: በእነዚህ ሰዎች አመለካከት እየበዛ የሚሄደው ህዝብ አገርን ለመከላከል፥ ለደራና እየተስፋፋ ለሚሄድ ኢኮኖሚ፥ እየጨመረ ለሚሄድ ፍጆታ፥ ለምርታማ የሰራተኛ ሀይል አሰራርን ለማሻሻል፥ ለባህል ጥንካሬ አስፈላጊነት አለው::

በብዙ አጋጣሚዎች እንደታየው ግን የህዝብ ብዛት መጨመር ብቻውን ለእርምጃና ለልማት አያበቃም:: ከዚህም በላይ የህዝብ ብዛት እየጨመረ ሲሄድ ከአቅም በላይ መኖርን ያስከትላል:: አሁን ያለው የዲሞግራፊ ምጣኔ በመሰረቱ ሳይለወጥ ከቆየ በሚቀጥሉት ምእተ አመታት የህዝብ ብዛት በከፍተኛ መጠን ይጨምራል:: ለምሳሌ እ.ኤ.አ. ከ1990 እስከ 1995 የነበረው የውልደት መጠን ለቀጣዩ አንድ ምዕተ አመት ተኩል ባለበት ቢቆይ የአለም ህዝብ እ.ኤ.አ. በ2150 ሁለት መቶ ዘጠና ስድስት ቢሊዮን ይደርሳል:: በግልጽ "አይለወጤ የመውለድ ገጽታ" ተብሎ ሊጠቀስ የሚችለው ሁኔታ የህዝብ ብዛት ወደ 296 ቢሊዮን ስላደገ እርምጃም ልማትም አይደለም::

ከዚህም በላይ የስነ ህዝብ ክስተቶች በባህርያቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ ተደጋጋፊና አለማቀፋዊ እየሆኑ በመሄድ ላይ በመሆናቸው በመስተዳድራዊ ድንበሮች ሊለዩ አይችሉም:: ዛሬ የመገናኛ ቴክኖሎጂ እየተራቀቀ በመምጣቱ አለም እያነሰች ባለችበትና ህዘቦቿ ከመቼውም ይበልጥ ተደጋጋፊ እየሆኑ ባለቡት ዘመን የሀገሮችን የህዝብ ብዛት በብሄራዊ ድንበሮች ብቻ ወስኖ ማየት አስቸጋሪ ሆኖአል:: የአለም ህዝቦች ፖለቲካዊ ኢኮኖሚኖዊና ማህበራዊ ህይወት አለማቀፋዊ ባህርይ ተቀዳጅቷል:: ወደፊት ይበልጥ እተቀዳጀ ይሄዳል:: ለምሳሌ እጦት፥ ግጭትና እንዲሁም ማህበራዊ ሁከት የብዙ ተፈናቃዮችን ጥገኝነት ጠያቂዎችንና ስደተኞችን ፍልሰት ያስከትላል:: እነዚህ የሰው ልጅ ከቦታ ወደ ቦታ የሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች በጎረቤት አገሮች ላይ ብቻ ሳይሆን ርቀው በሚገኙ አገሮችም ላይ ትልቅ ተጽዕኖ ያደርጋሉ::

ከፍልሰት የተሻለ ሌላ ማሳያ የጤና ጉዳይ ነው:: አለማቀፋዊ ድንበሮች ወይም መስተዳድራዊ ወሰኖች በሽታን፥ ቫይረስን፥ ተሃዋሲያንን፥ ተስቦን፥ እንዲሁም አየር በካዮችን አይገድቡም:: እነዚህ የጤና ጠንቆች ለድንበርና ለሉአላዊነት አይበገሩም:: ከመንገድም ከተሰወረ የአለም ስርቻ የሚነሳ የጤና ጠንቅ ርቀው ወደሚገኙ ህዝቦች ተዛምቶ በፍጥነት ሊሰራጭ ይችላል:: /ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ የካቲት 17, 1991 የተወሰደ/::

1. የአንደኛው አንቀጽ ፍሬ ሃሳብ የቱ ነው?
   ሀ. የሰለጠነ የሰው ሀይል ለማግኘት የህዝብ ቁጥር መጨመር አስፈላጊ ነው::
   ለ. የህዝብ ቁጥር መጨመር ለኢኮኖሚ እድገት ትልቅ ድርሻ አለው::
   ሐ. ስለ ህዝብ ቁጥር መጨመር የተሳሳተ አመለካከት መኖር ለእድገት እንቅፋት ነው::
   መ. የህዝብ ቁጥር መጨመር ጎጂ ጎኖች ጎልተው ይታያሉ::

2. የሁለተኛው አንቀጽ ፍሬ ሃሳብ የቱ ነው?
ሀ. የህዝብ ቁጥር መጨመር ብሄራዊ እንጂ አለማቀፋዊ ገጽታ የለውም::
ለ. የህዝብ ቁጥር መጨመር አለማቀፋዊ ገጽታ አለው::
ሐ. የህዝብ ቁጥር መጨመር ለተለያዩ ችግሮች የሚያጋልጥ ማህበራዊ ክስተት ነው::
መ. የህዝብ ቁጥር መጨመር ሀገርን ከጥቃት ለመከላከል ጠቃሚ ነው::

3. በአንደኛው አንቀጽ ውስጥ የተገለጸው ሃሳብ የተሳሳተ ነው የተባለው ______ በመሆኑ ነው::
ሀ. የህዝብ ቁጥር መጨመር ለማኅበራዊ፥ ለኢኮኖሚያዊና ሌሎች ችግሮች የሚያጋልጥ መሆኑ ባለመጤኑ
ለ. የህዝብ ቁጥር መጨመር ለደራ ገበያ፥ ለኢኮኖሚ ዕድገት፥ ለሀገር መከላከል አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት
ሐ. የህዝብ ቁጥር አለማቀፋዊ ችግሮች ጎልተው ስለተገለጹ
መ. የህዝብ ቁጥር መጨመር ለሚቀጥለው ምዕተ አመት እየቀነሰ የሚሄድ መሆኑ ስለታመነበት

4. የህዝብ ቁጥር እየጨመረ መሄድ አለማቀፋዊ ገጽታ የሚኖረው ለምንድን ነው?
ሀ. ከአቅም በላይ መኖርን ስለሚያስከትል
ለ. ህዝብ ለችግር ሲጋለጥ ከቦታ ቦታ ስለሚንቀሳቀስ
ሐ. ለስልጣኔ መስፋፋት አጋዥ በመሆኑ
መ. ሀገርን ለመከላከል ትልቅ አስተዋጽኦ ስላለው

5. የዚህ ምንባብ አቀራረብ
ሀ. ቀስቃሽ ነው
ለ. አስጠንቃቂ ነው
ሐ. ዘርዛሪ ነው
መ. መልሱ የለም

6. የምንባቡ አቅራቢ የህዝብ ቁጥር ከሚፈለገው በላይ እንዳይሄድ መፍትሄ ነው የሚለው፤
ሀ. የሰዎችን እንቅስቃሴ መገደብ
ለ. የውልደት መጠንን መቀነስ
ሐ. እጦትና ማህበራዊ ችግሮችን ማስወገድ
መ. ግጭቶችን ማስወገድ

7. በህዝብ ብዛት መጨመር የተነሳ የሚከሰት የህዝብ ፍልሰት አስጊ የሚሆነው፥
ሀ. በፍጥነት ስለሚስፋፋና አለማቀፋዊ ገጽታ ስላለው
ለ. በሀገሮች ድንበር ሊወሰን በመቻሉ
ሐ. በቀላሉ የሚገታ በመሆኑ
መ. መፍትሄ ሊገኝለት የማይችል በመሆኑ

8. የህዝብ ቁጥር መጨመር አስፈላጊ መሆኑን የሚያምኑት ሰዎች ______ ይገልጻሉ::
ሀ. የሰለጠነ የሰው ሀይል ምንጭ መሆኑን
ለ. ለመከላከያ ሀይል ምንጭ መሆኑን
ሐ. የኢኮኖሚ እድገትን እንደሚያፋጥን
መ. ሁሉም መልስ ሊሆን ይችላል::

9. እጦት፥ ግጭትና ማህበራዊ ሁከት፥
ሀ. ለህዝብ ቁጥር መጨመር ምክንያቶቸ ናቸው
ለ. ለስልጣኔ እንቅፋቶች ናቸው
ሐ. ለህዝብ መፈናቀል መንስኤዎች ናቸው
መ. ለውልደት መጠን መጨመር ምክንያቶች ናቸው

10. ከሚከተሉት ውስጥ በምንባቡ ያልተገለጸው ሃሳብ የቱ ነው?
ሀ. ስደት፥ ግጭትና የህዝብ ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወርና መፈናቀል በሀገሮች ደረጃ የሚወሰን አይደለም
ለ. የህዝብ መጨመር ምንም የከፋ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር የለውም
ሐ. ስደትና ፍልሰት ለማህበራዊ፥ ለዚኮኖሚያዊና ለጤና ነክ ችግሮች መንስኤዎች ናቸው
መ. እጦትና ግጭት እንዲሁም ስደት የህዝብ ቁጥር መጨመር ውጤቶች ናቸው

11. "...እርምጃም ልማትም አይደለም::" የተባለው ምንድን ነው?
ሀ. ከአቅም በላይ መኖር
ለ. የህዝብ ቁጥር መጨመር
ሐ. ስደትና መፈናቀል
መ. ግጭትና እጦት

12. የሶስተኛውና የአራተኛው አንቀጾች ሃሳብ ሲጠቃለል ______ የሚል መልእክት ይሰጣል::

ሀ. የመገናኛ ዘዴዎች ፍጥነት የተሻሻለ በመሆኑ ህዝብ በቀላሉ ከቦታ ወደ ቦታ ሊዘዋወር ይችላል

ለ. የመገናኛ ፍጥነት የተሻሻለ በመሆኑ ህዝብ በብዛት ሲንቀሳቀስ አብረውት የተለያዩ ማህበራዊና ጤና ነክ ጉዳዮኖች ሊዛመቱ ይችላሉ

ሐ. የመገናኛ ዘዴዎች ፍጥነት የተሻሻለ በመሆኑ የህዝብን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች መቅረፍ ቀላል ነው

መ. የህዝብ ብዛት መጨመርና አለማቀፋዊ ገጽታ መያዝ ለድንበር ዘለል ጤና ነክ ችግሮች መስፋፋት ትልቅ ድረሻ አለው::

13. የምንባቡ ደራሲ ____________ የሚል አቋም አለው::

ሀ. የህዝብ ቁጥር መጨመርና የኢኮኖሚ እድገት የተለያዩ ናቸው

ለ. የህዝብ ቁጥር መጨመርና የልማት እንቅስቃሴ እንዲጣጣም የህዝብ ብዛት በተወሰነ ደረጃ መገታት አለበት::

ሐ. የህዝብ ቁጥር መጨመር ለመጪው ጊዜ አስጊ አይደለም

መ. የህዝብ ስደት በኢኮኖሚ ላይ ያለው ጫና እንዲቀንስ ያደርጋል

*II. የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች በምንባቡ መሰረት እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልስ::*

______ 14. የህዝብ ቁጥር መጨመር አለማቀፋዊ ገጽታ ያለው ችግር የሚፈጥረው በማኅበራዊ ችግሮች መበራከት የተነሳ ስደት ስለሚስፋፋ ነው::

______ 15. የህዝብ ቁጥር መጨመር ከኢኮኖሚ እድገት ጋር ቢያያዝ ምንም አይነት ችግር አያስከትልም::

______ 16. የህዝብ ቁጥር እንዲቀንስ ማህበረሰቡን ማስተማር ጠቀሜታው የጎላ ይሆናል

______ 17. የህዝብ ቁጥር ለሰለጠነ የስራ ሀይል አስፈላጊ መሆኑን መቀበል ተገቢ አስተያየት ነው::

______ 18. በምንባቡ ደራሲ አስተያየት የህዝብ ቁጥር መጨመር ከሚያስከትላቸው ችግሮች ዋነኛው የጤና ችግር ነው::

*III. ለሚከተሉት ቃሎችና ሀረጎች ሐሳብ ሳያዛንፉ ተመሳሳይ የሚሆነውን ፍቺ መርጠህ አመልክት::::*

19. ከአቅም በላይ መኖር
ሀ. ከፍተኛ ችግር
ለ. ከእጅ ወደ አፍ
ሐ. ከፍተኛ ወጭ
መ. ያልሆኑት መሆን

20. የዲሞግራፊ ምጣኔ
ሀ. የህዝብ እድገት መጠን
ለ. የኢኮኖሚ እድገት መጠን
ሐ. የስደትና የግጭት መጠን
መ. የህዝብና የኢኮኒሚ እድገት መጠን

21. አይለወጤ
ሀ. ለውጥን የሚቃወም
ለ. እየጨመረ የሚሄድ
ሐ. እርስ በርስ የማይስማማ
መ. ሁከት ብጥብጥ የሚፈጥር

22. ማሳያ
ሀ. ማስገንዘቢያ
ለ. መጠቆሚያ
ሐ. ማሳሳቻ
መ. መክፈቻ

# ምንባብ ሁለት

## የጎጂ ልማዶች ተጽዕኖ

በጠቅላላ አነጋገር የሚስማሙትና የሚዋደዱት ለመገናኘት፥ የማይዋደዱትና የማይስማሙት ለመለያየት ሲጥሩ፥ ሲግሩ የሚኖሩ መሆናቸው የታወቀ ነው:: ነገር ግን ጣልቃ እየገቡ የሚያሰናክሉና የሚከለክሉ ልዩ ልዩ ተቃራኒ ሀይሎች ስላሉባቸው ለመገናኘትም ሆነ ለመለያየት ከሚፈልጉት ሁሉ ወደ ሚፈልጉት ግብ ለመድረስ የሚችሉት ሰዎች የመንፈስ ነጻነት የፈቃድ ብርታትና ቆራጥነት ያላቸው ጥቂት ናቸው:: የሚበዙት በስልጣን፥ በባህል፥ በልማድና እነዲን በመሳሰሉት ልዩ ልዩ አስገዳጅ ሀይሎች ተገድደው፥ የማይፈልጉትንና የሚጠሉትን ኑሮ ተሸክመው እንደተሸገሩ፥ እዳማረሩ የሚኖሩ ናቸው:: የሚስማሙት ለመገናኘት፤ የማይስማሙት ለመለያየት ሲፈልጉ ፍላጎታቸው እንዳይፈጸም ጣልቃ እየገቡ የሚከለክሉ፥ አስገዳጅ ሀይሎች ባይኖሩ ኖሮ በቤተሰብ፥ በማህበር፥ ከዚያም አልፎ በአለም አለመግባባት ወይም ሁከት ባልኖረ ነበር::

ደመቀችና በሻህ፥ የመንፈስ ነጻነት፥ የፈቃድ ብርታትና ቆራጥነት ካላቸው ጥቂት ሰዎች መሀከል መሆናቸውን ታሪካቸው ይመሰክራል:: እንዳገሩ ባህልና እንደልማዱ፥ የልጆችን የጋብቻ ኑሮ ለመወሰን ሙሉ ስልጣን ያላቸው ወላጆች በመሆናቸው የደመቀች አባት እንኩዋንስ አብራው መኖር ፊቱን ላንድ አፍታ ማየቱ ለሚያስጠላት ባል ድረው፥ አብራው እንድትኖር ስላስገደዱዋት ባባትዋ ስልጣን፥ በባህሉ፥ በልማዱ፥ በሁሉ ሽፍታ 'ባል' የሚባለው ሁሉ ያን የጠላችውን ባልዋን መስሎ ስለታያት ዳግመኛ ባል ላታገባ ምላ፥ በልጅነትዋ ልጅ አዝላ ወደማታውቀው አገር የተሰደደች ነበረች:: በተሰደደችበት አገርም ለነጻ ምርጫዋና ለፈቃድዋ ዋጋ ሳይሰጡ፥ የራሳቸውን ፈቃድ ብቻ ለማስፈጸም የተፈታተኑዋትን ሁሉ ባጠገብዋ አላደርስ ያለች በመሆንዋ 'የነብር አራስ' የተባለ ስም የወጣላት ነበረች::

በሻህም ቢሆን ገና ለጋ ወጣት ሳለ ጀምሮ፥ ለሁሉም ያካልና የመንፈስ ነጻነትንና እንደየችሎታው ሰርቶ የመኖር መብትን አጥብቆ የሚመኝ ባንጻሩ የግፍ የጭቆናና ያድልዎ ስራ በማንም ላይ ሲሰራ ባየ ቁጥር እንደ እግር እሳት የሚያንገበግበውና የሚያመው ነበር:: በኋላም እየበሰለና እያስተዋለ ሲሄድ የያንዳንዱ ነጻነትም ሆነ መብት መታፈንና የግፉ፥ የጭቆናው ያድልዎው ቀንበር በህዝቡ ላይ መጫን፥ ሁሉም የጠቅላላው ስራት ዘርፎችና ቅርንጫፎች ስለሆነ ያ የሁሉም ስር፥ የሁሉም መሰረት የሆነው ጠቅላላው ስርአት ካልተለወጠ ምንም ቢሆን የኢትዮጵያ ህዝብ ለነጻ ህዝብ የሚገባውን ነጻነት ሆነ መብት ሁሉ ማግኘትና ከጭቆና ሁሉ ነጻ መውጣት እንደማይችል አመነ::

/ሀዲስ አለማየሁ የልምዣት/ ገጽ 592-592/

*በምንባቡ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ::*

1. በምንባቡ መሰረት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ስምምነት የሚታጣው ______ ነው::
   ሀ. የማህበረሰቡ አባላት ፍላጎታቸውን በነጻነት ማሳካት ቢችሉ፥
   ለ. የማህበረሰቡ አባላት ፍላጎታቸውን በነጻነት ማሳካት ሲያቅታቸው
   ሐ. የማህበረሰቡ አባላት ራስ ወዳዶች ሲሆኑ
   መ. በማህበረሰቡ ውስጥ መተማመንና መረዳዳት ሲጠፋ
2. የማህበረሰቡን ተጽእኖ ተቋቁመው ፍቃዳቸውን የሚፈጽሙ ምን አይነት ሰዎች ናቸው?
   ሀ. እርስ በርስ መተባበር የማይወዱ
   ለ. የማህበረሰቡን ባህልና ልማድ የሚያከብሩ
   ሐ. የመንፈስ ነጻነትና ብርታት ያላቸው
   መ. ለባህልና ለልማድ ተገዢ የሆኑ
3. በምንባቡ ሁለተኛ አንቀጽ ውስጥ "...የነብር አራስ..." ሲል ______ ማለቱ ነው::
   ሀ. ደመቀች ጨካኝ ናት ለ. ፍላጎቷ እንዲከበር ትጥራለች
   ሐ. በልጅነቷ ልጅ ወልዳለች መ. የማትፈልገውን የትዳር ኑሮ ጀምረች

4. በምንባቡ አንደኛ አንቀጽ ውስጥ የስምምነት መጥፋት መነሻዎች የሆኑት ________ ናቸው::
ሀ. የሰዎችን ነጻነት የገድቡ ማህበራዊ የልማድ ሀይሎች
ለ. የመንፈስ ነጻነትን የሚሰጡ የልማድ ሀይሎች
ሐ. የወላጆች የልጆቻቸውን የጋብቻ ህይወት የመወሰን ልማዶች
መ. ሰዎች ለመለያየትና ለመዋደድ ነጻነት ሲቀዳጁ የሚደሰቱ ሀይሎች
5. በምንባቡ የመጨረሻ አንቀጽ የተገለጸው የበሻህ አስተሳሰብ ለውጥ መነሻ________ ነው::
ሀ. የማስተዋልና የመብሰል ውጤት ለ. ግፍን ለመታገስ አለመቻል
ሐ. የመንፈስ ነጻነትን መፈለግ መ. የሰዎች አለአግባብ መበደል
6. ከሚከተሉት አረፍተነገሮች መሀከል በምንባቡ መሰረት ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ. የሚስማሙም ሆኑ የማይስማሙ ሰዎች የሚደርሱበት የየግል ግብ አላቸው::
ለ. የሰዎችን ነጻነት የሚገድቡ ሀይሎች በቤተሰብም ሆነ በማህበረሰብ ውስጥ በስፋት ተንሰራፍተው ይገኛሉ::
ሐ. በማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ልዩ ልዩ ሀይሎች የማህበሩን አባል ከግብ ሊያደናቅፉ ይችላሉ::
መ. የመንፈስ ነጻነትና ብርታት ያላቸው ሰዎች በማህበረሰቡ አስገዳጅ ሀይሎች ከግባቸው ይደናቀፋሉ::
7. ከአቅም ማነስ ምክንያት የበሻህ የወጣትነት ምኞቶች በርካታ ቢሆኑም አልተሳኩም:: ካልተሳኩት የበሻህ ምኞቶች መካከል ዋነኛው የቱ ነው?
ሀ. አስተዋይና ብልህ መሆን::
ለ. ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት ሰርቶ የመኖር መብት እንዲያገኙ ማድረግ::
ሐ. ብዙ ጊዜ የሚያስቆጨውን ሃሳብ በተግባር ለማዋል መመኘት ነበር::
መ. ኑሮ እንዲሳካለት የመንፈስ ነጻነት መመኘት ነበር::
8. ደመቀችና በሻህ ምን አይነት ሰዎች ናቸው?
ሀ. ሁለቱም በማህበረሰባቸው ባህል ላይ አምጸዋል::
ለ. ሁለቱም የየራሳቸውን እምነትና ፍላጎት ለመፈጸም ይፈልጋሉ::
ሐ. ሁለቱም ከትውልድ ከተማቸው ሸሽተዋል::
መ. ሁለቱም የማህበራቸው የልማድ ተጠቃሚዎች ነበሩ::
9. በምንባቡ ጸሀፊ እምነት ሁሉም የፈቀደውን እንዳይፈፅም የሚያግደው ማህበራዊ ልማድ __________ አለበት::
ሀ. በእኩልነት ላይ መመስረት ለ. ጨርሶ መጥፋት
ሐ. መለወጥና መሻሻል መ. ወጣቶችን መጫን
10. በሻህን እንደ እግር እሳት የሚያንገበግበው ምንድነው?
ሀ. የማህበረሰቡ አድሎአዊ ባህል ሐ. የደመቀች ያለዕድሜዋ መዳር
ለ. የሰዎች በአጉል ልማድ መበደል መ. የደመቀች ከሀገርዋ መሰደድ
11. በበሻህ እምነት የማህበረሰቡ አባል ነጻነት እንዲያገኝ________ ያስፈልጋል::
ሀ. የማህበረሰቡ አባላት ባህልና ልማዳቸውን ማክበር
ለ. በጊዜው የነበረውን ስርአት መቀየር
ሐ. እርስ በርስ መተሳሰብና መረዳዳት
መ. ወጣቶች የቤተሰቦቻቸውን ባህል መቀበል
12. ደመቀች "ባል" የጠላችው÷
ሀ. እድሜዋ ሳይደርስ ስላገባች ሐ. አባቱዋ ለማትወደው ሰው ስለዳርዋት
ለ. ከሀገርዋ ስለተሰደደች መ. ማህበረሰቡ ስለበደላት
13. የምንባቡ አንደኛ አንቀጽ ከሚከተሉት ሃሳቦች በየትኛው ሊጠቃለል ይችላል?
ሀ. የሰዎችን ግላዊ ፍላጎት የሚጨቁኑ ልዩ ልዩ ልማዶች አሉ::
ለ. ለመስማማትም ሆነ ለመለያየት ስምምነት አስፈላጊ ነው::
ሐ. የሁከትና የችግር ምንጩ የስምነት አለመኖር ነው::
መ. የፈለጉትን ለመፈጸም የመንፈስ ቆራጥነት ያስፈልጋል::

14. ከሚከተሉት የበሻህን አጠቃላይ ባህርይ የማይገልጸው የቱ ነው?
ሀ. የነበረው ስርአት ጠናከር እንዳለበት ያምናል::
ለ. የራሱን ፈቃድ ለመፈጸም ጉጉት የለውም::
ሐ. ለወገን ነጻነትን ይመኛል::

መ. ለነበረው ስርአት መጥፎ አመለካከት ነበረው::

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልስ::*

15. የምንባቡን አጠቃላይ ሀሳብ በራስህ አባባል በአምስት አረፍተ ነገሮች ግለጽ::
16. የምንባቡ ጸሀፊ የሰዎች ነጻነት የሚረጋገጠው እንዴት ነው ይላል?
17. የጠሉትንና የማይወዱትን ኑሮ የሚሸከሙት እነማን ናቸው?
18. በምንባቡ መሰረት ወላጆች የልጆችን የጋብቻ ኑሮ የሚወስኑ ለምንድነው?
19. በልጅነትዋ ልጅ አዘለች ሲል ምን ለማለት ነው?

# አባሪዎች

## ለ

# በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
# የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር (1991 ዓ.ም.)

## በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ

ውድ ተማሪዎች፥

የዚህ መጠይቅ አላማ በ"ቶፕዳውን" (top down) ሞዴል ንባብን ማስተማር ያለውን ተግባራዊነትና ውጤታማነት ለማጥናት ተዛማጅ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነው:: ከመጠይቁ የሚገኘው መረጃ ለታቀደው ጥናት አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል:: ትክክለኛውን መረጃ ማግኘት ጥናቱ ወደ ግቡ እንዲደርስ አጋዥ ስለሆነ፥ ትክክለኛ መስሎ የሚታያችሁን መልስ በመስጠት እንድትተባበሩኝ እጠይቃለሁ:: ይህንን መጠይቅ በመሙላት ለምታደርጉልኝ ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ::

ማሳሰቢያ:-

ሀ. በመጠይቁ ላይ ስም፥ ክፍልና ተራ ቁጥር መጻፍ አያስፈልግም::
ለ. መጠይቁን በሌላ ሰው ማስሞላት፥ ከጓደኛ ጋር ተመካክሮ ወይም ከሌላ ጓደኛ አይቶ መሙላት የጥናቱን ውጤት ስለሚያዛባ የተከለከለ ነው::

## *ክፍል አንድ*

*በባዶው ቦታ ላይ ተፈላጊውን መረጃ በመሙላት አመልክት/ች::*

1. ጾታ__________ 2. እድሜ__________
3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ__________________
4. ሌላ የምታውቀው/ቂው ቋንቋ/ቋንቋዎች
   4.1. __________ 4.2__________
   4.3. __________
5. የትህርት ቤቱ የስነጽሁፍ፥ የድራማ፥ የጋዜጠኝነትና የሚኒ ሜዲያ ክበባት አባል
   ሀ. ነኝ ለ. አይደለሁም
6. ባለፈው አመት (1991) 8ኛ ክፍል የተማርክበት/ሽበት ትምህርት ቤት ስም ______________

## *ክፍል ሁለት*

*ቀጥሎ ለቀረቡት ሃ ቦች ከተሰጡት አማራጮች መካከል መልስ ሊሆን የሚችለውን ሆሄ ከመረጥህ/ሽ በኋላ ሆሄውን በመክበብ አመልክት:: በጥያቄዎቹ ግርጌ የተሰጡት ሆሄያት የሚወክሉት*

ሀ. በጣም እስማማለሁ
ለ. እስማማለሁ
ሐ. አልስማማም
መ. በጣም አልስማማም

የሚሉት ሃሳቦች ነው::

ስለዚህ ሃሳቦቹን ካነበብህሽ በሁዋላ መልስ የሚሆነውን መርጠህ ሆሄውን በመክበብ አመልክት::

1. የተለያዩ መጻህፍትን፥ ጋዜጦችና መጽሄቶችን በየጊዜው እንዳነብ ወላጆቼ ሁኔታዎችን ያመቻቹልኝ ነበር።

ሀ. ለ. ሐ. መ.

2. ቀደም ሲል የተለያዩ ጽሁፎችን በማንበብ የተረዳሁትን ሃሳብ ከጓደኞቼ ጋር በጋራ እንዲወያዩባቸው ነበር።

ሀ. ለ. ሐ. መ.

3. የተለያዩ የንባብ ስልቶችን (የአሰሳ ንባብ፥ የገረፍት ንባብ፥ ጥልቅ ንባብ፥ ንባብን ከግል ገጠመኝ ማዛመድንና ስለምንባቡ ይዘት መገመትን) ከዘጠነኛ ክፍል በፊት በአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት ተምሬአለሁ።

ሀ. ለ. ሐ. መ.

4. በንባብ ትምህርት ጊዜ ያነበብነውን ምንባብ አጠቃላይ መልእክት አስመልክቶ ውይይትና ክርክር በማካሄድ የየራሳችንን ሃሳብ እንድንገልጽና የምንባቡን ይዘት እንድንገመግም ሁኔታዎች ይመቻቹልን ነበር።

ሀ. ለ. ሐ. መ.

5. በአማርኛ የመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ከሚገኙት ምንባቦች በተጨማሪ መምህራችሁ መጽሀፍ፥ ጋዜጣ፥ መጽሄትና የተለያዩ ጽሁፎችን አንብባችሁ ያገኛችሁትን ሃሳብ እክፍል አምጥታችሁ እንድትወያዩባቸው ያደርጉ ነበር።

ሀ. ለ. ሐ. መ.

6. ከተለያዩ መጻህፍት፥ መጽሄቶችና ጋዜጦች የተወሰዱትን ምንባቦች በትምህርቱ ወቅት በክፍል ውስጥ በማንበብ፥ መልመጃዎችን በቡድን በመስራት የንባብ ስልቶች (መልእክት ትንበያን፥ የምንባብ መልእክትን ከግል እውቀት ማዛመድን አንድምታዊ ንባብን) ተግባራዊ ለማድረግ ችያለሁ።

ሀ. ለ. ሐ. መ.

7. ለልምምድ የቀረቡት መልመጃዎች ለውይይትና ለመረዳዳት አመቺ የሆኑ፥ አዳዲስ ቃላትንና አባባሎችን የያዙ በመሆናቸው አውዳዊ አፈታታቸውን ለማጤንና የተማርኩትን የንባብ ስልቶች ተግባራዊ በማድረግ ከጓደኞቼ ጋር ለመረዳዳት አስችለውኛል።

ሀ. ለ. ሐ. መ.

8. ለልምምድ የቀረቡት ምንባቦች ይዘትና በነዚህ ላይ የተመሰረቱት መልመጃዎች ከማውቀው ነገር ጋር የተዛመዱ፥ ተጨማሪ ንባብ ለማካሄድና ጥያቄዎችን በመስራት በይዘቶቹ ላይ የበለጠ ለመመራመር ረድተውኛል ብዬ አምናለሁ።

ሀ. ለ. ሐ. መ.

9. በጸጥታ በማነብበት ጊዜ የማነበውን ምንባብ መልእክት በመገመት፥ የመልእክቱን ተአማኒነትና ወቅታዊነት በመገምገም፥ በምንባቡ የተለያዩ አንቀጾች መካከል ያለውንም ትስስር በማጤን፥ ያልገባኝን ነጥብ ለመለየትና መልእክቱን በሚገባ ለመረዳት ረድቶኛል።

ሀ. ለ. ሐ. መ.

10. በግል በማነብበት ጊዜ የማገኛቸውን አዳዲስ ሃሳቦች ካለኝ ገጠመኝና እውቀት በማዛመድ መልእክቱን ለመገምገም ሞክሬአለሁ።

ሀ. ለ. ሐ. መ.

11. በግል የማነበውን ጽሁፍ በዝርዝር ከማንበቤ በፊት ስለ አጠቃላይ ይዘቱ ምንነት ለማወቅ ጥረት አድርጌአለሁ።

ሀ. ለ. ሐ. መ.

12. በልምምድ ወቅት የቀረቡልኝን ምንባቦች አይነት (ልብወለድ፥ ኢ-ልብወለድ) ለይቼ የሚያቀርቡትን መልእክት አላማና ጠቀሜታ ለመገምገም ጥረት አድርጌአለሁ።

ሀ. ለ. ሐ. መ.

13. በልምምዱ ወቅት በተማርኩት ትምህርት መሰረት በተለያየጠ ደራሲያን የቀረበ ርዕሰ ጉዳይ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚቀነተንባቸውን መንገዶች በማጤን የጸሀፊዎቹን የመልእክት አቀራረብና አገላለጽ ለማወዳደር ጥረት አድርጌአለሁ።

ሀ. ለ. ሐ. መ.

14. በልምምዱ ወቅት የቀረቡልኝን ምንባቦች ከማንበቤ በፊት በውይይት የተነሱትን ነጥቦች ከምንባቡ ውስጥ ለመፈለግ፥ ግምቴን ለማረጋገጥና ተጨማሪ እውቀት ለማግኘት ስል አነባቸው ነበር።

ሀ. ለ. ሐ. መ.

15. በግሌ በማነብበት ጊዜ እንዳቀረቡልኝ ምንባቦቹና ጽሁፎች አይነት የንባብ ስልቶችን ለማስተካከልና በተቻለ ጠን ፍሬ ሃሳባቸውን ለመረዳት ጥረት አድርጌአለሁ::

ሀ. ለ. ሐ. መ.

16. በማነብበት ጊዜ ግልጽ ያልሆነልኝ ነገር ሲያጋጥመኝ ከጓደኞቼ ወይም ከመምህሬ ጋር በመወያየት እና ምንባቡን ደግሜ በማንበብ መልዕክቱን ለመረዳት ጥረት አድርጌአለሁ::

ሀ. ለ. ሐ. መ.

17. በማነብበት ጊዜ ትርጉም-አዘል በሆኑ አሀዶች ደረጃ በማንበብ በምንባቡ አንቀጾች መካከል ያለውን የመልእክት ትስስር በማጤን ጠቅላላውን መልእክት ለመረዳት ጥረት አድርጌአለሁ፥፥

ሀ. ለ. ሐ. መ.

18. ከክፍል ጓደኞቼ ጋር በመሆን በየግላችን አንብበን የተረዳነውን ሃሳብ በጋራ እንድንወያይበት፥ ከእውቀታችን እንድናዛምደውና እንድንገመግመው መደረጉ በትምህርቱ ሂደት ራሳችንን ችለን የመስራት ልምድን እንድናዳብር የሚረዳን ነው ብዬ አምናለሁ::

ሀ. ለ. ሐ. መ.

19. በልምምዳችን ወቅት መምህሩ ያደረጉልን ገለጻ ግልጽና በቀላሉ የሚገባ፥ የተማርነውንም በተግባር ላይ ለማዋል የማያስቸግር ነበር::

ሀ. ለ. ሐ. መ.

20. ንባብን በ"ቶፐዳውን" ዘዴ ልምምድ ማድረጌ በራሴ ምርጫና ፍላጎት የተለያዩ ጽሁፎችን ለማንበብ ያስችለኛል ብዬ አምናለሁ::

ሀ. ለ. ሐ. መ.

21. በ"ቶፐዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ የተሰጠኝን ትምህርትና ልምምድ ውድጄዋለሁ::

ሀ. ለ. ሐ. መ.

ለ21ኛው ሃሳብ ለሰጠኸው/ሽው መልስ ተጨማሪ አስተያየት አክልበት/አክይበት::

________________________________________

________________________________________

________________________________________

የምልከታ ማስታወሻ

ቀን 20-01-92
ሰአት 4:00
ትምህርት ቤት፡- ኢትዮጵያ ትቅደም ቁጥር አንድ ከፍተኛ
ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

በ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል ውጤታማነትና ተግባራዊነት ላይ የሚካሄደው የሙከራ ጥናት የአጥኚውን በክፍል ውስጥ ተገኝቶ ተማሪዎችን ማለማመድ የሚጠይቅ በመሆኑ የመጀመሪያው ጥረት ፈቃደኛ የሆነ ትምህርት ቤት ማግኘት ነበር፡፡

በፊት ተጠይቆ ፈቃደኝነቱን የነፈገው ኮልፌ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነበር፡፡ ስለዚህ ይህንን ሙከራ ለማካሄድ ፈቃደኛ ትምህርት ቤት የማግኘትን ችግር ለመቅረፍ ሌላ ትምህርት ቤት በማፈላለግ ላይ እንደነበርኩ በኢትዮጵያ ትቅደም ቁጥር አንድ የቀድሞ መምህር የነበረ የማውቀው ግለሰብ ትምህርት ቤቱ እንደሚተባበረኝና ሁኔታዎችን ለማመቻቸት እንደሚረዳኝ ገልጾልኝ አብረን በመሄድ ጠየቅን፡፡ ከዚሁ የትምህርት ቤቱ የቀድሞ መምህር ጋር በመሆን ወደ ትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ቢሮ አመራን፡፡ ከርዕሰ መምህሩ ጋር ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ስለመጣሁበት ጉዳይ በዝርዝር ተወያየን፡፡ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህርም ሙሉ ተባባሪ መሆናቸውን እንዳረጋገጡልኝ ከአዲስ አበባ ዩኒበርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነጽሁፍ ክፍል የትብብር መጠየቂያ ደብዳቤ በመውሰድ ስለጥናቱ አላማና ስለሚያስፈልጉኝ ነገሮች አስረድቼ ተማሪዎችንም ለመተዋወቅ እንዲቻል በ23-01-92 ዓ.ም. ከጠዋቱ 2:40 ኢትዮጵያ ትቅደም ቁጥር አንድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደረስኩ፡፡

ከዚያም ወደ ምክትል ርዕሰ-መምህሩ ቢሮ በመሄድ ደብዳቤዬን አቀረብኩ፡፡ እርሳቸውም፥ ጥናቱ ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ፥ ለጥናቱ ስንት ምድቦች እንደሚያስፈልጉኝ፥ በሳምንት ለስንት ክፍለ-ጊዜ ልምምዱ እንደሚካሄድና በጥናቱ የሚሳተፉት የስንተኛ ክፍል ተማሪዎች እንደሚሆኑ ጠይቀውኝ ካስረዳሁ በኋላ ወደ ፈረቃ መሪው ቢሮ ይዘውኝ በመሄድ አስተዋውቀውን አስፈላጊውን መርሀ ግብር ከእርሳቸው ጋር እንድናስተካክል በመንገር ወደ ቢሮአቸው ተመለሱ፡፡

የፈረቃ መሪውም የምፈልገውን ክፍል እንዴት እንደምመርጥ ጠይቀውኝ ተማሪዎቹ በውጤታቸው መሰረት በየክፍሉ አለመመደባቸውን ካረጋገጥኩ በኋላ በመጀመሪያ ከሁለቱ ፈረቃዎች አንዱን በእጣ እንደምመርጥ ነግሬአቸው እጣ ጣልን፡፡ በወጣው እጣ መሰረትም የጠዋት ፈረቃ ተመረጠ፡፡ በዚሁ ፈረቃ ከሚገኙት ሰባት የመማሪያ ምድቦች መካከል በተመሳሳይ ዘዴ $9^{I}$ እና $9^{A}$ ለዚህ ልምምድ ሊውሉ እንደሚችሉ ከተስማማን በኋላ የክፍሎቹ የአማርኛ ቋንቋ መምህርት የሆኑት ወ/ሮ ጸጋነሽ ማሞን ልናነጋግር ወደ መምህራን ማረፊያ ሄድን፡፡

ለመምህርነት ጸጋነሽ ማሞም የጠቅላላ ጥናቴን አላማና አሰራር በዝርዝር ካስረዳሁ በኋላ በ25-01-92 ዓ.ም. የቅድመ ልምምድ ፈተና ስለምሰጥ በፈተናው ሰአት በመፈተን ሊያግዙኝ ተስማምተን አመስግኜ ከተመረጡት ምድቦች ተማሪዎች ሊያስተዋውቁኝ በ4:15 ወደ $9^{I}$ እና በ4:55 ደግሞ ወደ ሁለተኛው ምድብ ማለትም $9^{A}$ ተራ በተራ ገብቼ በስም ከተዋወኳቸው በኋላ በዕለቱ ምልከታ አድርጌአለሁ፡፡ ከትውውቁ በኋላ በቀጣዩ ጊዜ ሁሉም በጥናቱ ይተባበሩኝ እንደሆነ ፈቃደኝነታቸውን በጠየቅሁ ጊዜ ሁሉም እጃቸውን በማውጣት ስምምነታቸውን አሳውቀዋል፡፡ መምህርቷ ለተማሪዎቻቸው ባቀረቡት ማሳሰቢያ ለስድስት ሳምንታት ለየት ያለ ልምምድ በመከታተል እንደሚቆዩ ከነገሯቸው በኋላ ልምምዱን በትጋት እንዲከታተሉ፥ በመጨረሻም ሁለት ፈተናዎችን ተፈትነው ውጤቱ በአንደኛው መንፈቀ አመት ውጤት ላይ እንደሚደመርላቸው፥ የተቀረውን ከኔ እንዲወያዩ በማለት ጥለውን ሄዱ፡፡ በውይይቱ ወቅትም ተማሪዎች ማድረግ የሚጠበቅባቸውን ነገር አውቀው እንዲዘጋጁ ማብራሪያ ቀርቦላቸዋል፡፡

ረቡዕ 25/01/92
የመግቢያ ሰአት 2:00
ክፍለ ጊዜ 1ኛ ና 2ኛ

ለጥናቱ የተመረጡት ተማሪዎች በዛሬው እለት የመጀሪያውን ፈተና ከፈረቃቸው ውጭ ተፈትነዋል:: ፈተናውን ተጋግዘን ለመፈተን አስቀድሜ ትብብር የጠየኩዋቸው መምህራንና ተማሪዎች በሰዓቱ መምጣታቸውን አረጋግጬ ተማሪዎችን ወደ ክፍል አስገብተን ካስቀመጥናቸው በሁዋላ የፈተና ወረቀት አደልናቸው:: የጥያቄ ወረቀት ካደልናቸው በሁዋላ ከመስራታቸው በፊት ምንባቡቹን በሚገባ ማንበብ እንዳለባቸውና ፈተናውን ሰርተው ለመጨረስ 1:20 እንደተሰጣቸው ተብራርቶላቸው ፈተናውን መስራት ጀመሩ በመጨረሻ የተፈቀደው ሰአት ሲገባደድ መጨረሳቸውን ስንጠይቅ እንደጨረሱ አስታወቁ:: 9:15 ሲሆን ሰአት በማለቁ ወረቀቶቻቸውን በየወንበራቸው አቀምጠው ወጡ: የፈተና ወረቀቶችን ሰብስቤ የረዱኝን መምህራን አመስግኘ ወደ ት/ቤቴ መጣሁ::

አርብ 27-1-92 ዓ.ም.
የመግቢያ ሰአት 2:00
ክፍል ጊዜ 1ኛ

በዚህ እለት የልምምዱ መደበኛ የመጀመሪያ ቀን እንደመሆኑ የሙከራ ምድቦችን እኔ ማለማመድ የጀመርኩበትና የጥብቅ ምድቡን ደግሞ ነባር የት/ቤቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህር በተመሳሳይ ቀን ስራቸውን ጀመሩበት ነው:: ልምምዱ መምህር ባልተመደበበት ክፍለ ጊዜ ጭምር ክፍል ተፈቅዶ የሚካሄድ በመሆኑ ለልምምዱ አመቺ ሁኔታ ነበር:: ስራችንን ከመጀራችን በፊት በሙከራውና በቁጥጥር ቡድኑ መካከል በትምህርት አቀራረብ በኩል ሊኖር የሚገባውን ልዩነት በዝርዝር ተወያይተን በቁጥጥር ቡድኑን መምህሩ በተቻላቸው መጠን ዘወትር የሚጠቀሙበትን የማስተማሪያ ዘዴ ከምልከታ ካገኘሁዋቸው ፍንጮች በማዛመድ ተግባራዊ እንዲያደርጉና እኔም በተመልካችነት እንደምገኝ ተስማምተን ስራውን ጀምረናል::

የሙከራው ቡድን ተሳታፊዎች አካላዊና አዕምሮአዊ ዝግጅት በማድረግ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚጠበቅባቸውን ነገር አውቀው እንዲዘጋጁ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ውይይት አድርገናል::

- ማንኛውም ምንባብ በተመሳሳይ መንገድ ስለማይነበብ ማለትም እንደሚነበብበት አላማ በገረፍታ÷ በአሰሳ÷ በአንድምታ ሊነበብ ስለሚችል ይህንኑ አውቀው በልምምዱ ወቅት በስራ እንዲተረጉሙ÷
- በልምምዱ መሳተፍ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማዳበር የሚረዳቸው መሆኑን ለዚህም ተደጋጋሚ ልምምድ ማካሄድ እንደሚገባና እንዲያካሄዱ÷
- ንባብን በሚያካሄዱበት ጊዜ ምንባቡን በዝርዝር ከማንበባቸው በፊት እንዲገምቱ ከዚያም የገመቱት ሃሳብ በንባብ እንዲያረጋግጡ÷ ግምታቸው በምንባቡ ከተረጋገጠ ስለመልእክቱ ያገኙትን ሃሳብ በንባብ ተአማኒነት እንዲገመግሙ÷ ግምታቸው እና የምናባቡ ይዘት ከተለያዩ የምንባቡን መልእክት በሚገባ ለመረዳት በጥንቃቄ ደግሞ ማንበብና ጠቃሚ ፍንጭ ሰጭ አባባሎችን ማስተዋል እንደሚገባ÷
- የንባብ አላማ (ለመረጃ÷ ለመልመጃዎች ስራ÷ ለጥናት÷ የፈጠራ ስራዎችን በማንበብ ለመዝናናት÷ ወዘተ.) ወስነው ማንበብና ትኩረታቸው አላማቸውን ከግብ ለማድረስ መሆን እንዳለበት÷
- በሚያነቡበት ጊዜ ድምጻቸውን ሳያሰሙ ማንበብ እንደሚገባቸው÷ ይኸውም የሚያነቡትን ምንባብ ሃሳብ ለመረዳት ስለሚያግዛቸውና ፍጥነታቸውን ስለማይገታ የንባብ ስልታቸውን ማስተካከል እንዳለባቸው÷
- በሚያነቡበት ጊዜ ቃል በቃል ሳይሆን በትርጉም አዘል አሀዶች ደረጃ ማንበብ እንዳለባቸው÷
- በግል አንብበው የተረዱትን በጥንድና በቡድን ቢወያዩባቸው ለመማማር ስለሚረዳ መተባበር እንዳለባቸው ተገልጾላቸዋል:: ለዚሁም ሲባል ቡድኖች ተደራጅተዋል::
- መልመጃዎችን ሲሰሩ በየቡድናቸው ተወያይተው ለሚያቀርቡዋቸው መልሶች ማስረጃ ማቅረብ እንደሚገባ÷
- ሲያነቡ ያልገባቸው ነገር ካለ በጥያቄ መልክ መያዝና በውይይት ጊዜ ማቅረብ እንደሚገባ÷
- አዳዲስ ቃላትንና አባባሎችን ሲያኙ ከምንባቡ አጠቃላይ ገለጻ ጋር በማዛመድ መፍታት ጠቃሚ መሆኑ ተገልጾላቸዋል::

አንብቦ መረዳትና አስተካክሎ ማንበብ የተለያዩ መሆናቸውን አንደኛው የምንባቡን መልእክት መገንዘብ ላይ የሚያተኩርና ሁለተኛው የተጻፈውን መጥራት መሆኑ ተብራርቶላቸዋል:: በአጠቃላይ አንብቦ መረዳት ከሚነበበው ምንባብ ውስጥ ተፈላጊ የሆነውን መልዕክት አመዛዝኖ መረዳት ነው:: መልእክቱ ተገቢ ነውን? በሚገባ ተብራርቶአልን? አላማውስ ምንድነው? ለምንስ አነበዋለሁ? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት መቻል መሆኑን ከዚህ አላማና ተግባር ውጭ የሆነ ጥረት በአብዛኛው አንብቦ መረዳት አለመሆኑ ተብራርቶአል:: ስለዚህ ማንበብ ሲባል የቃሉ አጠቃቀም ከመረዳት ጋር መያያዝ እንደሚገባው ተብራርቶላቸዋል:: አስተካክሎ መጥራት ቅድሚያ የሚያስፈልገው ንበትን በመለማመድ ደረጃ ላይ ለሚገኙት እንደሆነ ተገልጾላቸዋል::

በተነሱት ነጥቦች አማካይነት በ"ቶፕዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል የሚተኮርባቸው መርሆዎች በዝርዝር ተነስተው ሰፊ ውይይት ተደርጎአል::

ከውይይቱ በሁዋላ በጥያቄና መልስ ወቅት ሁለት ተማሪዎች ስለተነጋገርንባቸው ጉዳዮች ጥያቄ አንስተዋል:: የአንደኛው ጥያቄ አስተካክሎ መጥራትና አንብቦ መረዳት ያላቸውን ልዩነት የሚመለከት ነበር:: በምላሹም አንብቦ መረዳት ጸሀፊው ለማስተላለፍ የፈለገውን ጭብጥ አመዛዝኖ መቀበል መሆኑንና ትኩረቱም መልእክቱ እንደሆነ፥ አስተካክሎ ማንበብ ግን የተጻፈውን ቃል መጥራት (decode) መሆኑ በድጋሚ በምሳሌዎች አማካይነት ተገልጾአል::

ሌላው ተማሪ ደግሞ "በመጽሃፋችን የመጀመሪያው ምንባብ ውስጥ አንድ ሰው አስተካክሎ ማንበብ ከቻለ የማህበረሰቡ አባል ይሆናል" ይላልና መጽሃፋችን ስህተት ነውን?" የሚል ጥያቄ አንስቶ ነበር:: እኔ ተማሪው የጠየቀውን ምንባብ በማየት እንዳረጋገጥኩት ተማሪው እንዳለው አስተካክሎ ማንበብ የሚለው ሀረግ አገባብ መረዳት ሳይሆን መጥራትን የሚገልጽ ነበር:: በመሆኑም የመጽሀፉ አጠቃቀም የተሳሳተ ነበር::

በመጨረሻም 2:40 ሆኖ ክፍለ ጊዜው በማለቁ ውይይቱ በዚሁ አብቅቶአል::

ሰኞ 30-01-92
የመግቢያ ሰአት 2:20
ክፍለ ጊዜ 3ኛ
የትምህርቱ ርዕስ፦ ጥንታዊ የጋብቻና የአኑዋኑዋር ስርአት

በዛሬው ዕለት የሙከራ ምድቡን ነው ያለማመድኩት:: በዚህም ባለፈው ክፍለ ጊዜ የተወያየንባቸውን ነጥቦች በአጭር በአጭሩ በመከለስ መሰረታዊ በሆኑ ነጥቦቸ ላይ በጥያቄና መልስ ማብራሪያዎች ቀርበዋል:: ከውይይቱ በሁዋላ እንዲጠይቁ ቢፈቀድላቸውም የተነጋገርንባቸው ነጥቦች ግልጽ ናቸው ስላሉ በቀረው ሰአት የቤት ስራ የሚሆን ጥያቄ ተሰጣቸው:: ጥያቄውም:-

"ጥንታዊ የጋብቻና የአኑዋኑዋር ስርአት" በሚለው ርዕስ ዙሪያ ምን ምን ነጥቦች ተካተው በተሟላ ምንባብ ውስጥ ሊቀርቡ እንደሚችሉ አጠር አጠር ያሉ 5 ነጥቦችን ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ አምጡ የሚል ነበር:: ነጥቦቹን ለመዘርዘር 10 ደቂቃ ስለተሰጣቸው ይሆናል ያሉትን አንስተው ብዙዎቹ ለጥያቄው የየራሳቸውን መልስ ለመስጠት ይሽቀዳደሙ ነበር:: ተደውሎ ከክፍል እስክወጣ ለተወሰኑት ተማሪዎች እድሉን በመስጠት መልሶቻቸውን ተናግረው የተቀሩት ደግሞ ለቀጣዩ ጊዜ ጽፈው እንዲመጡ ነግሬያቸው ክፍለ ጊዜው እንዳለቀ በ4:15 ከክፍል ወጣሁ::

ረቡዕ 02/02/92
የመግቢያ ሰአት 2:00
ክፍለ ጊዜ 1ኛ

ቀደም ባለው ጊዜ በተጀመረው ውይይት መሰረት ተጨማሪ ውይይትና የዝግጅት ጊዜ በመውሰድ አመቺ አውድ ለመፍጠር ስለርዕሰ ትምህርቱ ሁሉም የሚያውቁትን ተናግረው ሲያበቁ በጸጥታ የተሰጣቸውን ምንባብ እንዲያነቡ አዘዝኩ:: አንብበው ለመጨረስ 20 ደቂቃ ተሰጥቶአቸው እየተዘዋወርኩ ልምምዳቸውን መመልከት ቀጠልኩ::

ከሃያ ደቂቃ በሁዋላ መጨረሳቸውን ሲጠየቁ ሁሉም መጨረሳቸውን ሲገልጹ አስቀድመው በተነገራቸው መሰራት ከምንባቡ ውስጥ ያገኙትን በማስታወሻ መልክ ይዘው ስለነበር በቅድሚያ የገመቱትንና ከምንባቡ ውስጥ ያገኙትን እንዲያነጻጽሩና በሁለቱ መካከል ያለውን አንድነትና

ልዩነት በተራ ገልጸዋል። ከዚያም በነጥቦቹ ላይ ውይይት ተደርጎ የመልመጃዎቹን የመጀመሪያ ክፍል ሞክረው እንዲመጡ የቤት ስራ በቡድን ተሰጥቶአቸው የዕለቱ ትምህርት አበቃ።

አርብ 04-02-92
የመግቢያ ሰአት 3:20
ክፍለ ጊዜ 4ኛ
የትምህርቱ ርዕስ፦ ካለፈው የቀጠለ የመልመጃ ውይይት

ከምንባቡ ጋር በቀረቡት ጥያቄዎች አማካይነት በመልእክቱ አቀራረብ፥ ወቅታዊነትና አላማ ላይ ውይይት አድርገዋል። የምንባቡ አንድምታዊ መልእክት ምን እንደሆነ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሚከተለውን መልስ ሰጥተዋል። ይኸውም በምንባቡ ውስጥ የተገለጸው የአኑዋኑዋርና የጋብቻ ስርአት ከአሁኑ ዘመን አስተሳሰብ ጋር ስለማይሄድ ህብረተሰቡን ማስተማር፥ መቀስቀስና መለወጥ ተገቢ መሆኑን ለማሳወቅ የቀረበ ነው የሚል ነበር።

ሰኞ 07-02-92
የመግቢያ ሰአት 3:20
ክፍለ ጊዜ 3ኛ
የትምህርት ርዕስ፦ ኤድስን የከላከል ዘመቻ

ተጨማሪ አስተያየት ወይም ጥያቄ ያለው ይኖር እንደሆነ በማሰብ ይህንኑ ለተማሪዎች አቀረብኩ። ያለፈው ትምህርት ቀደም ላሉት ክፍለ ጊዜያት በስፋት የተካሄደ ስለነበር ጥያቄም አስተያየተም አልነበረም።

ጥያቄ አለመኖሩን እንዳረጋገጥኩ የእለቱን ትምህርት ርዕስ በሰሌዳ ላይ ጽፌ የሚከተለውን ጥያቄ አከልኩ። ጥያቄው የሚከተለውን ምንባብ በመቃኘት ቀጥሎ የተዘረዘሩት አመተ ምህረቶች የተከሰተባቸውን አቢይ ጉዳይ ግለጽ የሚል ነበር።

ሀ. መስከረም 1991 ዓ.ም.
ለ. 1998 እ.ኤ.አ.
ሐ. 1977 ዓ.ም.
መ. 1981

በምንባቡ ውስጥ ከቀረበው አጠቃላይ መልዕክት አኳያ የተዘረዘሩት ዓመተ ምህረቶች የነበራቸው ፋይዳ ከተገለጸ በኋላ ስለምንባቡ መልዕክት እንዲገምቱ የሚከተለውን ጥያቄ አቀረብኩላቸው።

> ስለኤድስ ምንነት የመተላለፊያ መንገዶችና የመከላከያ ዘዴዎች ሲነገር የሰማችሁትና ያነበባችሁት ነገር ምን ምን ያካትታል? ስለምንነቱ፥ ስለመተላለፊያ መንገዶቹና መከላከያ ዘዴዎች ያላችሁን ሃሳብ በአጭር በአጭሩ ግለጹ /10 ደቂቃ አላችሁ/ የሚል ነበር።

ተማሪዎች በተሰጣቸው የ10 ደቂቃ ጊዜ የሚያውቁትንና በምንባቡ ውስጥ ሊካተቱ ይችላሉ ብለው የገመቱትን ሁሉ አስፍረው አንድ በአንድ አቀረቡ። ከሞላ ጎደል የሁሉም ተመሳሳይ ነበር።

ከውይይቱ በሁዋላ የተዘጋጀውን ሸት በየወንበሩ ለቡድን አባላት ሰጥቼ በዝምታ እንዲያነቡ አሳሰብኩዋቸው። ምንባቡን አንብበው ለመጨረስ 15 ደቂቃ ተሰጥቶአቸው ንባባቸውን ቀጠሉ። ከ15 ደቂቃ በሁዋላ የሚከተለውን ጥያቄ አቀረብኩላቸው።

ከማንበባችሁ በፊት የዘረዘራችሁዋቸው ነጥቦች በሙሉ በምንባቡ ውስጥ ተጠቃለዋል? ያልተጠቃለሉት የትኞቹ ናቸው?

ሁሉም በግልም በቡድንም በቅድመ ንባብ የገለጹትንና ከምንባቡ ያገኙዋቸውን ነጥቦች አስተያይተው ተመሳሳይ የሆኑትን በመግለጽ ውይይት እንደተጀመረ ሰአት በማለቁ ጥያቄውን በይበልጥ መርምረው ተጨማሪ ፅሁፍ ፈልገው እንዲያመጡና በመልመጃዎቹ መጨረሻ ከቀረበው ሰንጠረዥ አገናኝተው እንዲያቀርቡት በቤት ስራነት እንዲሞክሩት፥ በመጨረሻም እንደምንወያይበት ተገልጾላቸው ከክፍል ወጣሁ።

ረቡዕ 09-02-1992
የመግቢያ ሰአት 5:50

የትምህርቱ ርዕስ:- ኤድስን የመከላከል ዘዴ (ካለፈው የቀጠለ)

ባለፈው ክፍለ ጊዜ የመጀመሪያውን ክፍል ተወያይተውበት ስለነበር በቀጥታ ከቆምንበት ነው የጀመርነው:: በመሆኑም ውይይቱንና የምንባቡን መልእክት በማዛመድ የምንባቡ አጠቃላይ ጭብጥ ምንድነው? የጽሁፉ አላማስ የሚሉት ጥያቄዎች በክፍል ስራነት ተሰጥተው ተማሪዎች የሚከተሉትን መልሶች አቅርበዋል::

> ስለኤድስ አስከፊነት፣ ስለፈጣን ስርጭቱ፣ እንዲሁም ይህንን ቀሳፊ በሽታ ለመከላከል ስርጭቱንም ለመግታት ማድረግ የሚገባንን ይገልጻል:: ይህም በሽታውን ለመከላከል የማህበረሰባችንን አመለካከት ለመለወጥ ማስተማር አስፈላጊ መሆኑንና ለማስተማርም ቀዳሚ ሚና መጫወት የሚገባቸውን ቡድኖች ይጠቁማል የሚል ጭብጥ ማግኘታቸውን የሚገልጽ ነበር:: ይህም መልስ የብዙዎቹ አስተያየት ነበር::

በርዕሱ ላይ አንድ ተማሪ ጥያቄም አስተያየትም አቀረበ:: አስተያየቱም በምንባቡ ውስጥ "የመገናኛ ብዙሀን በማስተማር ረገድ ቀዳሚ ሚና ሊኖራቸው ይገባል" በሚለው ሃሳብ የማይስማማ መሆኑን በመግለጽ ከመገናኛ ብዙሀን ይልቅ የሃይማኖት ድርጅቶችና የስራ ማህበራት ቀዳሚ ሚና ሊጫወቱ ይገባል የሚል ነበር::

እኔም አስተያየቱ ጥሩ መሆኑን በመግለጽ የተለየ ምክንያት ይኖረው እንደሆነ ማብራሪያ ከሱም ከሌሎች ተማሪዎችም ጠየኩ::

ተማሪውም ሲመልስ "የኤድስ በሽታ ወደ ገጠሩም እየተዛመተ ስለሆነ የገጠሩን ህዝብ ለማዳን ደግሞ ጋዜጣም ሆነ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ጠቃሚነታቸው እምብዛም ነው:: ምክንያቱም አብዛኛው ህዝብ በትምህርት ስላልገፋ፣ እነዚህን ዘዴዎች ለመጠቀም አቅሙ ውሱን በመሆኑ በዚያውም በእምነት ላይ ጠንከር ስለሚል የምንባቡን ደራሲ እንዳለው የሃይማኖት ድርጅቶችን ማስቀደሙ የተሻለ መሆኑ ስለሚሰማኝ ነው:: በተረፈ የማይገኘውንና ሁሉንም ህዝብ የሚያዳርሰውን መጠቀም ትርፍ የለውም ብዬ ነው" የሚል ስጋት አከል አስተያየቱን ደመደመ::

የተቀሩት ተማሪዎች በሃሳቡ ቢስማሙም እንደአመቺነቱ መጠቀም ያስፈልጋል በማለታቸው ውይይቱ በዚሁ አብቅቶ ወደመልመጃዎቹ ተሻገርን::

በአጠቃላይ የጽሁፉ አላማ ምንድነው? ለሚለው የግምገማ ጥያቄ ሲመልሱ "የኤድስ በሽታ በሀገራችንና በአለም ዙሪያ በፈጣን ሁኔታ እየተዛመተ በመሆኑ ሰለባ ለመሆን ጥንቃቄ እንደሚያስፈልግና ህዝቡ ራሱን ከበሽታው እንዲከላከል ማስተማርና መቀስቀስ ተገቢ መሆኑን ለማሳወቅ የቀረበ ነው:: ያስጠነቅቃል፣ ይቀሰቅሳል:: የሚል የጋራ መልስ ሰጥተዋል::

በርዕሱ የቀረበውን ምንባብ አንብበው በተዘጋጁትም ሆነ በክፍል ውስጥ በተነሱት ጥያቄዎች ላይ ሰፊ ውይይት ከተካሄደ በሁዋላ በተመሳሳይ ርዕስ ላይ የተጻፈ ጽሁፍ በየቡድናቸው ከጋዜጣ፣ ከመጽሄት ያገኙትን እንዲያመጡና አንብበው ያገኙትን እንዲገልጹ፣ ከመልመጃው ምንባብ አቀራረብ እንዲያወዳድሩ ማሳሰቢያ ተሰጥቶአቸው ሰአት ስላለቀ ከክፍል ወጣሁ::

> አርብ 11-02-1992
> የመግቢያ ሰአት 2:00
> ክፍል ጊዜ 1ኛ
> የትምህርቱ ርዕስ:- የቋንቋ ተግባራት

እንደቀደሙት ጊዜያት ሁሉ ያለፈውን ትምህርት በመከለስ ከአዲሱ ጋር ለማያያዝ ተማሪዎች ጥያቄዎችን እዲጠይቁ ፈቀድኩላቸው:: ጥያቄው የመምህሩን የግል አስተያየት የሚመለከት ስለነበር ካነበብኩዋቸው አንዳንድ ጽሁፎች ጋር የምንባቡን ሃሳብ በማገናዘብ ማብራሪያ ሰጥቻቸው ወደሚቀጥለው የዕለቱ ልምምድ አለፍን::

የዕለቱ የልምድ ርዕስ ስለቋንቋ ተግባራት የሚገልጽ ነበር:: ስለዚህ ስለቋንቋና ተግባራቱ የተዘጋጀውን ምንባብ ከማደሌ በፊት ስለርዕሱ የሚያቀውቁትንና የሚያስቡትን ይገልጹ ዘንድ ጠቋሚ የትንበያ ጥያቄዎችን አቀረብኩላቸው:: ጥያቄዎቹም የሚከተሉት ናቸው::

1. ቋንቋን ማወቅ ሲባል ምን ምን ያጠቃልላል?
2. የቋንቋ ተግባራት ምን ምን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ?

ለጥያቄዎቹ መልስ የሚሆኑትን ሃሳቦች ለማስታወስ 10 ደቂቃ ተሰጥቶአቸው ስራቸውን በቡድን በቡድናቸው ሆነው በውይይት ጀመሩ:: የየቡድኑ ሀላፊ የጋራ የሆነውን መልስ በመስጠት ሌሎች ተጨማሪ አስተያየት እንዲያክሉ ተራ በተራ ጥያቄ እንደሚጠየቁ ተነግሮአቸው ስለነበር ሁሉም የሚፈልጉትን አስተዋጽኦ ለማድረግና የተማረውን በተግባር ለማዋል ጥረት ያደርግ ነበር:: የተሰጠው 10 ደቂቃ ሲያልቅ መልሶቻቸውን አቅርበው በጋራ ከተወያየንባቸው በሁዋላ ምንባቡን የያዘው ወረቀት ታድሎ ምንባቡን ወደ ማንበብ ተሸጋገሩ::

ምንባቡን አንበበው ለመጨረስና ያልገባቸውን በጥያቄ መልክ አስፍረው እንዲያነቡ 20 ደቂቃ ተሰጣቸው:: አንብበው ሲጨርሱ በምንባቡ ውስጥ የተገኙትን ነጥቦች ከቅድመ ንባብ ውይይት ሃሳቦች ጋር በማዛመድ ተጨማሪ ውይይት አደረጉ::

በመልመጃ ጥያቄዎቹ ውስጥ የሞቀ ውይይት የተደረገበት ጥያቄ ነበር:: ጥያቄው ከሰው ልጆች በስተቀር ቋንቋን ለመጠቀም የሚችሉ የእንስሳት ዝሪያዎች አሉ? የሚል ሲሆን ተማሪዎች ለሁለት ተከፍለው አንደኛው ቡድን አለ ሌላኛው የለም የሚሉ የተለያዩ አስተያየቶችን ሰንዝረዋል:: የሚናገሩ እንስሳት አሉ የአሉት ተማሪዎች በቀቀን የምትባለዋን ወፍ ሲጠቅሱ ሌሎቹ የሰዎችን ንግግር መኮረጅ እንጂ በራሱ አለመናገርዋን አስረድተው ለተመተማመን ችለዋል:: የልምምዱ ክፍለጊዜ በዚሁ አብቅቶ ከክፍል ወጥቼ ወደ ትምህርት ቤት ተመለስኩ::

ሰኞ 14-02-1992
የመግቢያ ሰአት 2:00
ክፍለ ጊዜ 1ኛ
የትምህርቱ ርዕስ:- <u>የንግግር ስርአትና ችሎታ</u>

ተማሪዎች በቀደሙት ጊዜያት የሰሩዋቸው መልመጃዎች ውይይት ተካሄዶባቸው ምንባቦቹን በሚገባ ከገመገሙዋቸው በሁዋላ ተጨማሪ የጥያቄና የአስተያየት ጊዜ ተፈቅዶ ጥያቄም ሆነ አስተያየት ባለመኖሩ በቀጥታ ወደ አዲሱ ትምህርት ገባን::

አዲሱን ምንባብ ከማንበባቸው በፊት በርዕሱ ላይ የሚኖራቸውን እውቀት እንዲያስታውሱና ምንባቡን በጥንቃቄ እንዲያስታውሱ ቅድመ ንባብ ውይይት ማድረግ አስፈላጊ ነበር:: ውይይት ማድረጉ በሌሎቹ ክፍለ ጊዜያት እንዳደረግነው የተለመደ ስለነበሩ ለዚሁ እንዲያግዝ የሚከተሉትን ጥያቄዎች አቀረብኩላቸው:: እነሱም:-

1. አንድ ሰው ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን ምን ምን ያስፈልገዋል?
2. የንግግር ችሎታን ለማሳደግ ልምምድ ያስፈልጋል? ወይስ አያስፈልግም? የሚሉት ነበሩ::

በነዚህ ጥያቄዎች አማካይነት የምንባቡን መልእክት የሚነኩና ንባባቸውን ቀና የሚያደርጉ ነጥቦች ተነስተዋል:: በእርግጥ መደበኛ መጽሀፋቸው ውስጥ ስለንግግር የአባሪ መልክ የቀረበላቸውና በምንባቡ ውስጥ የተገለጸው የልምምድ መንገድ የተለያየ አቀራረብ ስለነበራቸው ብዙ ጥያቄዎች ተነስተዋል:: ተሳታፊዎቹ ባነሱዋቸው ነጥቦች አማካይነት ማብራሪያዎችን አክለው መልስ በመስጠታቸው ይዘቱን መገመት ብቻ ሳይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ የተገለጹ የአንድምታ ሃሳቦች ጭምር ተዘርዝረዋል:: ይህም ምንባቡን ሲያነቡ ሊተኮርባቸው የሚገቡ ነጥቦችን ለመመርመር አስችሎአቸዋል::

ከመግቢያ ውይይቱ በሁዋላ ምንባቡን በጸጥታ እንዲያነቡ÷ አንብበው ለመጨረስም 15 ደቂቃ ተሰጥቶአቸው ምንባቡን የያዘው ወረቀት ታድሎአል:: አንብበው እንደጨረሱ የምንባቡን አጠቃላይ መልእክት ሲገመግሙ የምንባቡ ባለታሪክ ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን የተጠቀመባቸውን መንገዶችና ያቀደውን አላማ እንዴት እንዳሳካ በዝርዝር ገልጸዋል:: አላማውም አንድ ሰው ጠንክሮ ያለመታከት ከሰራ ካሰበበት ግብ ሊደርስ እንደሚችል የሚጠቁም ሆኑን አስረድተዋል:: በጨረሻም ሰአት በማለቁ ከምንባቡ ጋር ተዛማጅ ሃሳብ ካገኙ አዘምደው ለውይይት የሚሆኑ ጥያቄዎችን እንዲያመጡ ተነግሮአቸው የደወል ድምጽ እንደተሰማ ከክፍል ወጥቼ ሄድኩኝ::

ረቡዕ 16-02-1992
የመግቢያ ሰአት 2:00

ክፍለ ጊዜ - 1ኛ

የትምህርቱ ርዕስ:- የንግግር ስርአትና ችሎታ(ካለፈው የቀጠለ)

በዛሬው እለት በአብዛኛው የሰራናቸው ስራዎች በምንባቡ ውስጥ የገቡትን አዳዲስ ቃሎችና አባባሎችን ከምንባቡ ጠቅላላ ገለጻ አኳያ በመፍታትና የምንባቡን መልእክት ለማጉላት ያበረከቱት ድርሻ ለመገምገም ነው:: ተማሪዎች ቃሎቹን ከምንባቡ ገለጻ ጋር አዛምዶ መፍታትና አውዳዊ አገባባቸውን መመርመር የበለጠ ጠቃሚ የንባብ ስልት መሆኑን በማመልከት በውይይት ጊዜ የተማሩትን ትምህርት ተግባራዊ ለማድረግ ጥሩ ሙከራ አድርገዋል:: የመልመጃዎቹ በተለይም በምንባቦቹ ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት በአገባባዊ ፍችያቸው መቅረባቸውን የሚጠይቁ በመሆናቸው ቃሎቹ በገቡበት አውድ የሚሰጡት ፍች በቁማቸው ከሚሰጡት የተለየ መሆኑን በውል አጢነዋል፤ የመልመጃ ጥያቄዎቹንም ሰርተዋል::

በመጨረሻም በተመሳሳይ ርዕስ የቀረበ ጽሁፍ ያገኙ ልጆች የምንባቦቹን አቀራረብ አስመልክቶ ጥያቄዎችን አቅርበዋል:: እነዚህን የተማሪ ጥያቄዎች ከምንባቡ ጥያቄዎች አዛምደን ከተሰሩ በሁዋላ ሰአቱ በማለቁ ለቀጣዩ ጊዜ የተቀሩትን የመልመጃ ጥያቄዎች ሰርተው እንዲመጡ ነግሬያቸው ከክፍል ወጥቼ ሄድኩ::

ሰኞ 21/02/1992

**የመግቢያ ሰዓት** 4:55-5:35

ክፍለ ጊዜ - 5ኛ

የትምህርቱ ርዕስ ወጣትነት፥ ማህበራዊ ችግሮችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች እንደተሰለመደው ተማሪዎችን ለማዘጋጀትና በንባብ ጊዜ የትኩረት ነጥባቸውን ለማሰባሰብ እንዲችሉ ቅድመ ንባብ ውይይት ለማካሄድ የሚረዳ መሰረታዊ ጥያቄ አቅርቤላቸው ነበር:: ጥያቄውም

> በአሁኑ ጊዜ ስለወጣቱ የማህበረሰብ ክፍል ችግሮችና የችግሮቹ መንስኤዎች ተብለው ሊጠቀሱ የሚችሉ ነጥቦች የትኞቹ ናቸው?

የሚል ነው:: ለቀረበላቸው ጥያቄ መልስ የሚሆን የየግል አስተያየታቸውን ለማቅረብ 10 ደቂቃ ተሰጣቸው:: ተማሪዎቹም የየራሳቸውን ምክንያትና የሚጠቀሱ ምክንያቶችን ከርዕሱ አዛምደው ችግሮቹን እስኪዘረዝሩ ድረስ እየተዘዋወርኩ ተመለከትኩ:: የተፈቀደላቸው 10 ደቂቃ ሲያልቅ ሁሉም የየራሳቸውን ሃሳብ እንዲያቀርቡ ተራ በተራ በመጠየቁ ውይይቱ ተጀመረ:: በውይይቱ ወቅትም የተጠቀሱት ነጥቦች በአብዛኛው የተመሳሰሉ ነበሩ:: የወጣቱ ችግሮች በማለት በተማሪዎቹ የተጠቀሱት

- ሥራ አጥነት
- አጉል ልማዶች ለምሳሌ - መጠጣት፥ ማጨስ፥ ጫት መቃም፥ የሚሉት

ዋናዎቹ ሲሆኑ ለነዚህ ችግሮች መንስኤ የሚሆኑት ደግሞ በቂ የስራ መስክ አለመኖር፥ ወጣቶች ትርፍ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉበት አመቺ የመዝናኛ ስፍራ አለመዘጋጀት፥ ቤተሰብ ልጆቻቸውን ለመቆጣጠር ያላቸው ፍላጎት መጠነኛ መሆን፥ በቂ የስነተዋልዶ ትምህርት አለማግኘት የሚሉት እንደሆኑ ተማሪዎቹ ጠቅሰዋል::

ተማሪዎቹ ቅድመ ንባብ የመልዕክት ግምታቸውን ካቀረቡ በኋላ አንድ ተጨማሪ ጥያቄ አቀረብኩላቸው:: የወጣቱን የህብረተሰብ ክፍል ችግሮችና መንስኤዎች ቀደም ብላችሁ ጠቅሳችኋል:: ችግሮቹን ለማስወገድ ምን ማድረግ ይገባል የሚል ጥያቄ ነበር የቀረበላቸው:: የጥናቱ ተሳታፊዎች ችግሮቹን ለማስወገድ ይረዳል በማለት ያቀረቧቸው ነጥቦች በምንባቡ ውስጥ በአንድምታ ከቀረበው መልዕክት ጋር የተያያዙና በሁለት የተከፈሉ ነበሩ:: የመጀመሪያው የወጣቱ ችግሮች እንዳይበራከቱ፥ ተበራክተውም ስር እንዳይሰዱ ወጣቱን ማስተማርና አመለካከቱን በመለወጥ ማለትም በስራ ክቡርነት ሲሆን ሁለተኛው ነጥባቸው ደግሞ ዕድሜው ለስራ የደረሰውን የወጣት ክፍል ስራ ማስያዝ የሚል ነበር:: ተማሪዎቹ ያቀረቡት ሁለተኛው ነጥብ ለተጨማሪ ውይይር አመቺ ነበር:: ስለዚህ ተማሪዎች ሀሳቡን በይበልጥ እንዲያብራሩና ማስረጃ እንዲያቀርቡ ጠየኳቸው:: ባቀረቡተት አስተያየት መሰረት ተማሪዎቹ በሁለት ተከፍለው ነበር:: አንዱ ወገን "ለወጣቱ በሙሉ በቂ የስራ መስክ አመቻችቶ ሥራ ለማስያዝ አስቸጋሪ በመሆኑ፥ የሀገር የእድገት ደረጃም ስለማይፈቅድ ሁሉንም አንዴ ስራ ለማስያዝ አይቻልም" ሲል ሃሳቡን አሳማኝ በሆነ መንገድ በማቅረብ ማስተማሩና ወጣቱን በአዕምሮ ማዘጋጀቱ ጠቃሚ መሆኑን ገልጿል:: በዚህ ነጥብ ላይ ሰፋ ያለ ውይይት ከተካሄደ በኋላ ምንባቡን የያዘው ሽት ለያንዳንዳቸው ታድሏል::

ለልምምዱ የቀረበው ምንባብ አቀራረብ ከሌሎቹ ምንባቦቹ አቀራረብ የተለየ ነበር። የምንባቡ አወቃቀር ቅደም ተከተሉ የተዛነፈ ስለነበር በቅድሚያ በቤት ስራነት የተሰጣቸው ይህንኑ ቅደም ተከተል ማስተካከልና ማብራሪያ መስጠት ነበር።

ረቡዕ 23/02/1992
የመግቢያ ሰአት 2:00-2:40
ክፍለ ጊዜ - 1ኛ
የትምህርቱ ርዕስ:- <u>ወጣትነት፣ ችግሮቹና የመፍትሄ አቅጣጫዎች</u>

የዕለቱ ልምምድ ካለፈው የቀጠለ ነበር። በመሆኑም በተሰጣቸው የቤት ስራ ላይ የተመሰረተ ውይይት ተካሄዷል። ተማሪዎቹም የምንባቡን አወቃቀር በቡድናቸው በጋራ በቅደም ተከተል አስተካክለው ማብራሪያ አቅርበዋል። ተማሪዎቹ የተሰጣቸውን ስራ መስራታቸውን ጠይቄ ካረጋገጥኩ በኋላ የመልስ ወረቀቶችን ሰብስቤ ከየቡድኑ አንዳንድ አባል የተቀሩትን ወክሎ መልስ ሰጥተዋል። የቡድኑ ተወካይ አባላት የጋራ የሆነውን መልስ ተናግረው ካበቁ በኋላ ሌሎች አባላት (ለክፍል መልስ ያልሰጡት) ተጨማሪ ማብራሪያ አቅርበው ውይይቱ ተቋጭቷል። ከውይይቱ ቀጥሎ የተስተካከለውን ምንባብ መልዕክት አሳጥረው በአምስት ዐ.ነገሮች እንዲያቀርቡና አጠቃላይ አላማውን እንዲገመግሙ አዘዝኳቸው።

ተማሪዎችም የምንባቡን አላማ በተመለከተ ለቀረበላቸው የክፍል ስራ ጥያቄ ሲመልሱ "የምንባቡ ጸሀፊ ወጣቱ የተደቀኑበትን፣ ማህበራዊና የጤና ችግሮች ዘርዝሮ ከነምክንያታቸው በማቅረብ ወጣቱና አጠቃላይ ማህበረሰቡ መውሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች በመጠቆም ለማስጠንቀቅና ለማስተማር ያቀረበው" መሆኑን ገልጸዋል። በመጨረሻም ከምንባቡ መልዕክት በመነሳት ተጨማሪ አስተያየት ተጠይቀው ሲመልሱ" የጤናም ሆነ የማህበራዊ ችግሮችን ለመቅረፍ ወጣቱንም ወላጆችንም በማቀራረብ ማስተማር፣ የአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣት ጥረት ማድረግ" እንደሚገባ ይህንን ለማድረግም ጊዜ የሚሰጠው፣ ይደር የሚባል አለመሆኑን በአጽንኦት ገልጸዋል።

ዓርብ 25/02/1992
የመግቢያ ሰአት 2:00
ክፍለ ጊዜ 1ኛ
የትምህርቱ ርዕስ:- <u>ወጣትነት፣ ችግሮቹና የመፍትሄ አቅጣጫዎች</u>

ባለፈው ክፍለ ጊዜ በተካሄደው ውይይት መሰረት ተማሪዎች ምንባቡን አስተካክለው ከነማብራሪያው አቅርበዋል ተማሪዎቹ የሰሩትን የመልመጃ ስራ እያንዳንዳቸው ማምጣታቸውን መሞከራቸውን በሚገባ ለማረጋገጥ ሰብስቤ ለማረም ወረቀቶቻቸውን ወሰድኩ። ከዚያም ተማሪዎች ሙከራቸውን እንዲገልጹ፣ ተጨማሪ አስተያየትም ካላቸው እንዲያቀርቡ እድል ሰጠኋቸው። ከተማሪዎቹ መካከል እጃቸውን ያወጡትን ሁለት ልጆች አስቀድሜ እንዲመልሱ አደረኩ። በተማሪዎቹ መልስ በመጀመርም በምንባቡ ላይ ውይይት ከተካሄደ በኋላ የምንባቡን ጠቅላላ መልዕክት በአምስት አረፍተነገሮች አሳጥረው በማቅረብ እንዲገመግሙት አጠር ያለ የክፍል ስራ ሰጠሁ። የምንባቡን ጠቅላላ ጭብጥ አሳጥረው ካቀረቡ በኋላ አላማውን በሚመለከት የሚከተለው ነበር። ተማሪዎች

> ምንባቡ ለማስተማር የቀረበ ነው። በተለይም በወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል ላይ እየደረሰ ያለውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የጤና ጠንቅ በማመልከት እነዚህ ችግሮች የሚወገዱበትን የመፍትሄ አቅጣጫዎች ያመለክታል። ችግሮቹን ለመቅረፍ ደግሞ ወጣቱን ማስተማር፣ የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲያመጣ ማነቃቃትና በተለያዩ የሙያ መስኮች እንዲሳተፍ፣ ሀገሩንና ራሱን እንዲረዳ፣ በማህበረሰቡም ተገቢውን ሚና እንዲጫወት ማበረታታት ያስፈልጋል። ቤተሰብም የወጣቱን ችግሮች ጠንቅቆ ለማወቅ ጥረት ማድረግ እንዳለበት ካልሆነ የሚከተለውን ችግር ዘርዝሮ ያስጠነቅቃል በማለት የግምገማ አስተያየት አቅርበዋል።

ሰኞ 28/02/1992
የመግቢያ ሰአት 4:55
ክፍለ ጊዜ 5ኛ

በዛሬው እለት ተማሪዎቹ እስከ አሁን የቀረቡላቸውን ምንባቦች አቀራረብና የመልዕክታቸውንም ተጠባጭነት አጠቃላይ በሆነ መልኩ እንዲገመግሙ የማጠናከሪያ ስራዎችን እንዲሰሩ የክፍል ሥራ ተሰጥቷቸዋል:: የተሰጡት ጥያቄዎች የሚከተሉት ነበሩ:: እነዚህም

1. ስለኤድስ የቀረቡት ጽሁፎች በተለያዩ ሰዎች የተጻፉ ናቸው:: ከነዚህ ጽሁፎች ስለበሽታው የበለጠ ማብራሪያ የሚያቀርበው የትኛው ነው? ምን ማስረጃስ መጥቀስ ትችላላችሁ? የሚለው አንደኛው ነው:: የሁለቱን ጽሁፎች አቀራረብ ከመመረመሩ በኋላ ባቀረቡት የግምገማ አስተያየት ከሁለቱ ምንባቦች ስለበሽታው አስከፊነት ሰፋ ያለ ማብራሪያ የሚያቀርበው ሁለተኛው ምንባብ ነው:: ምክንያቱም ጸሀፊው ማህበረሰባችን ስለበሽታው የነበረውን የተሳሳተ ግምት÷ በሽታው በሀገራችን ከተከሰተበት ጊዜ አንስቶ እስከአሁን ድረስ እያደረሰ ያለውን እልቂት፤ በሽታውን ለመቆጣጠር የሚደረገውን ጥረት አስቸጋሪ ስለሚያደርጉት ጉዳዮችና መደረግ ስለሚኖርበት መከላከል ሁሉ በሚገባ ስለሚያቀርብ ነው:: ስለዚህ የበለጠ ያስተምራል፤ ያነቃል÷ ተጨማሪ ዝግጅቶች በሬዲዮና በቴሌቢዥን ሲተላለፉ ለመከታተል አንቅቶናል ሲሉ አስተያየታቸውን በማቅረብ ከቀረቡት ጽሁፎች ቁም ነገር መቅሰማቸውን አመልክተዋል::

2. ስለኤድስ የቀረበውን ምንባብና ስለወጣትነት÷ ማህበራዊ ችግሮቹና መፍትሄዎች የቀረበውን ምንባብ ሃሳብ በማነጻጸር የሁለቱም ምንባቦች መልዕክት ወጣቱን ይመለከት እንደሆነ አብራሩ:: የጽሁፎቹን አላማም አያይዛችሁ ጠቁሙ የሚለው ሁለተኛው የክፍል ሥራው ጥያቄ ነበር::

ተማሪዎችም የተሰጠውን የክፍል ስራ ከሰሩ በኋላ የምንባቦቹ መልዕክት ተመሳሳይነት እንዳለው÷ ሁለቱም ወጣቱ ጥንቃቄ እንዲያደርግ የማስተማርና የማሳወቅ አላማ እንዳላቸው÷ ጠቁመው ይበልጥ ሃሳባቸውን ሲያብራሩ

> ስለ ኤድስ የቀረበው ምንባብ ስለኤድስ አስከፊነት በማስተማር÷ ወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል ከበሽታው ራሱን እንዲከላከል የመከላከያና የመተላለፊያ ዘዴዎችን ይጠቁማል:: ወጣቱን ለማስተማርም ትምህርት ቤቶች÷ የሀይማኖት ድርጅቶችና ህዝብ በብዛት የሚሰበሰብባቸው ማህበራዊ ተቋማት ትልቅ ሚና መጫወት እንዳለባቸውና ግልጽ ውይይት እንደሚያስፈልግ ያሳስባል ብለዋል:: ይህ ሲባልም ኤድስን ለመከላከል ማንኛውም ሰው ዕድሜና ጾታ ሳይገድበው መንቀሳቀስ እንዳለበት ሊዘነጋ እንደማይገባም ይጠቁማል::

በማለት የመጀመሪያውን ምንባብ ሲገመግሙ ሁለተኛው ምንባብ ደግሞ

> ወጣቱ በስራ ክቡርነት አምኖ ራሱን ከጥገኝነት÷ ከአጉል ሱስና ከአልባሌ ስፍራዎች አርቆ እራሱንና አካባቢውን በሚገባ እንዲያውቅ ትምህርትና ስልጠና እንደሚጠቅም÷ ወላጆችና ልጆች ይበልጥ መቀራረብ እንደሚኖርባቸው ያስረዳል የሚል አስተያየት አቅርበዋል::

ከዚሁ የግምገማ ጥረታቸው ጋር በተዛመደ መልኩ ለውይይት ያህል አንድ ጥያቄ አቀረብኩላቸው:: ይኸውም የምንባቦቹ ጸሀፊዎች አስተያየት ወይም ስላቀረቡት መልዕክት ያላቸው ስሜት ምንድነው? የሚል ነበር:: ተማሪዎች ሲመልሱም "ጸሀፊዎቹ ያደረባቸውን ስጋትና ጭንቀት ለመግለጽ እንደሚሞክሩ ጠቁመዋል:: እነዚህን ነጥቦች በመዘርዘር ውይይት ከተደረገ በኋላ ደብተራቸውን ሰብስቤ ለቀጣዩ ጊዜ የጥንቱ የጋብቻና የአኗኗር ስርአት የሚለውንና የንግግር ችሎታ የሚለውን እንዲሁ አነጻጽረው ተጨማሪ አስተያየትም ይዘው እንዲመጡ የቤት ስራ ሰጥቻቸው ስአቱ በማለቁ ከክፍል ወጣሁ::

ረቡዕ 30/02/1992
የመግቢያ ሰአት 2:00
ክፍለ-ጊዜ 1ኛ

ተማሪዎች ባለፈው ጊዜ የተሰጣቸውን የቤት ስራ ሰርተው እንደሆነ ስጠይቃቸው ከአንድ ልጅ በስተቀር ሁሉም መስራታቸውን እጅ በማውጣት አረጋግጠዋል:: እኔም ያልሰራውን ተማሪ ለምን እንዳልሰራ ምክንያቱን ስጠይቅ የቤት ስራውን መሞከሩን ግን ደብተሩን ሳያመጣ በመምጣቱ መሆኑን ስለጠቆመኝ ሌላ ጊዜ አምጥቶ እንዲያሳይ ነግሬው የሌሎቹን ስራ ለማየት መዘዋወር

መጽሃፉ ውስጥ ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን ተናጋሪው ስለሚናገረው ርዕስ ጉዳይ ማወቅ፥ የንግግር ቋንቋውን ማወቅ፥ አድማጭን ማወቅ፥ አስፈላጊ ያልሆነ የአካል እንቅስቃሴን ማስወገድ የሚሉትን መመሪያዎች እናገኛለን:: ታዲያ ትክክለኛው የትኛው ነው? የሚል ጥያቄ ሰንዝረው ነበር:: ከአላማና ከግባቸው አኳያ ሲታዩ ሁለቱም ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን የሚቻልበትን መንገድ ያመለክታሉ:: ተመሳሳይነታቸውን ብንመለከት የዴሞስቴን እቅድ በወቅቱ ባላንጣዎቹን ተከራክሮ ለመርታት የሚጠበቅበትን ነገር ሲያስብ ጥሩ ተናጋሪ፥ አሳማኝ ሃሳብ አቅራቢ መሆን እንዳለበት በመረዳቱ የመረጠው የልምምድ መንገድ ከሰው ተለይቶ ራሱን በራሱ ማለማመድ ነው:: የምንባቡ ጸሀፊ እንደሚሉትም ዴሞስቴን በመለማመዱ በመጨረሻው ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን በቅቷል:: ታዲያ ይህ የልምምድ መንገድ መደበኛ ባልሆነ መንገድ በግል የሚደረግን ጥረትና ተስፋ አለመቁረጥን የሚያስተምር ነው:: መጽሃፉ ውስጥ ያለው መመሪያ የሚለውም ተቀባይነት ያለው መንገድ መሆኑን ማጤን አለብን:: ምክንያቱም ዴሞስቴን የሰዎችን ጫጫታ ለመቋቋም፥ እነሱንም ለማሳመን ሲል እኮ የተናጋሪዎቹን ማንነት ማወቁን ሊጠቁመን ይችላል:: በመሆኑም ሁለቱም ጸሀፊዎች ሳቀዱት የማስተማር አላማ የሚበቃ ጽሁፍ ማቅረባቸውን ገለጽኩላቸው:: በዚሁ ውይይትም የዕለቱ ምድብ ሰአት አበቃ::

ሰኞ 05/03/1992
**የመግቢያ ሰዓት** 3:20
**ክፍለ-ጊዜ 3ኛ**

አጠቃላይ አስተያየት:- በዚህ እለት ከመጀመሪያው የልምምድ ቀን ጀምሮ በተከታታይ የተወያየባቸውንና የሰሯቸውን መልመጃዎች እንዲሁም ልምምዶች የሚመለከት ውይይት ተካሄዷል:: ተማሪዎቹ የቀረቡላቸውን ምንባቦች ካነበቡና ከተወያዩባቸው በኋላ ከያንዳንዳቸው ጋር ተዛማጅ ይዘት ያላቸውን ጽሁፎች ከጋዜጦችና መጽሄቶች ፈልገው አቀራረብና አገላለጻቸውን አወዳድረዋል:: በነዚህ ተጨማሪ ጽሁፎች አማካይነት የተደረጉትን ልምምዶች ከራሳቸው እውቀትና ጽሁፎቹ አያይዘው በማንበብ፥ የየግስ አስተያየታቸውን በማቅረብ የተማሩትን ትምህርት በተግባር ለማዋል ችለዋል:: ይህም የበለጠ ለማንበብና አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማሻሻል እንደረዳቸው በውይይቱ ወቅትም አመልክተዋል:: ከቀረቡላቸው ምንባቦች ውስጥም አስፈላጊ ቁም ነገሮችን መቅሰማቸውን ገልጸዋል::

ረቡዕ 07/03/1992
**የመግቢያ ሰዓት** 2:00
**ክፍለ-ጊዜ 1ኛ**

ተማሪዎች የተዘጋጀውን ልምምድ ማጠናቀቃቸውንና የመጨረሻው ፈተና ብቻ እንደሚቀራቸው ተገልጸላቸዋል:: በልምምዱ ወቅት ልምምዱን ሳያስተጓጉሉ በመከታተላቸው አመሰግኜ ፈተናውን ለመፈተን የተመረጠው ቀን 09/03/92 ማለትም አርብ መሆኑ ተነግሮአቸዋል:: በመሆኑም ሁሉም በሰአቱ መገኘት እንዳለባቸውም አሳስቤ ጥያቄ ወይም አስተያየት ይኖራቸው እንደሆነ ጠየኩ:: ተማሪዎችም የመጀመሪያው የፈተና ወረቀት ሊሰጣቸው እንደሚገባ፥ ውጤታቸውን ማየት እንዳለባቸው አበክረው በመጠየቃቸው ከፈተና በኋላ እንደምሰጣቸው ቃል ገብቼ ከክፍላቸው ወጣሁ::

አርብ 09/03/1992

በዛሬው እለት የሁለቱም ቡድን ተማሪዎች ድህረ-ልምምድ ፈተና ተፈትነዋል:: እንደ ቅድመ ልምምድ ፈተናው ሁሉ በመፈተን የሚረዱኝ መምህራን በሰአቱ በመገኘታቸው ተማሪዎችን ወደ ክፍል አስገባናቸው:: ከዚህ በኋላ የፈተናውን አሰራር ከገለጽኩላቸው በኋላ የፈተናውን

ወረቀትና መልስ መስጫ አደልናቸው:: ፈተናውን ከመስራታቸው በፊት ጥያቄዎቹን ማንበብና ከምንባቦቹ ማገናዘብ እንደሚገባቸው፥ የተሰጣቸው ጊዜ ሁለት ሰአት በመሆኑ በቂ ጊዜ ስላላቸው ተረጋግተው እንዲሰሩ ነግሬ ስራቸውን ቀጠሉ:: በመጨረሻም የተፈቀደው ሰአት ሲያልቅ ሰርተው መጨረሳቸውን ስላስታወቁ ወረቀቶቹን ሰብስቤ የቀዳሚውን የፈተና ወረቀት ለተማሪዎቹ በየምድባቸው ሰጥቼ ሁሉንም አመስግኜ ተለያየን::

## ምንባብ አንድ

## የቋንቋ ተግባራት

የሰውን ልጅ ከሌሎች እንስሳት ከለዩትና ዝርያውም እንዳይጠፉ ካደረጉት ዋነኛው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሲሆን በዚሁ ሂደት የተገኙት የቋንቋ ችሎታ በውጤቱ ሂደት ምክንያት ያገኛቸው አዕምሮአዊና አካላዊ እድገቶችና ለውጦች ከፍተኛ ሚና አላቸው።

ቋንቋ ግለሰቡን ከህብረተሰቡ ጋር ያወሳስባል። ይህም ተግባር ውስበት ወይም ውስበታዊ ሊባል ይችላል። አንድ ህጻን ያደገበትን ህብረተሰብ ቋንቋ መናገር ሲችል የህብረተሰቡ ሙሉ አባል ይሆናል። በቋንቋ ችሎታውም አማካይነት ከህብረተሰቡ ጋር ይዋሃዳል። የረጅም ዘመን የእውቀት ክምችት ተካፋይ ይሆናል። በበኩሉም በቋንቋ አማካይነት ድርሻውን ያበረክታል።

የአንድ ሰው የቋንቋ ችሎታ የሚለካው በአራቱ የቋንቋ ክህሎት ማለት በማዳመጥ፥ በመናገር፥ በማንበብና በመጻፍ እንዲሁም የቋንቋውን ስነልሳንና ስነጽሁፍ በማወቅና በተግባር ላይ በማዋል በሚያሳየው ቅልጥፍና ነው። በጥራት አዳምጦ የተነገረውን ከጨበጠ ሀሳቡን በጥሩ ሁኔታ ከገለጸ፥ አስተካክሎ ካነበበና ከጻፈ የቋንቋ ችሎታው ከፍተኛ ነው ይባላል። ይሁን እንጂ ከዚህ ያነሰ ችሎታ ያለውም ሰው ቢሆን ከቋንቋ የበለጠ ለሀሳቡ መግለጫና ማስተላለፊያ ሊሆነው የሚችል ቀላል መንገድ አይኖርም። ለዚህም ነው የሰው ልጅ ሀሳቡን በቀለጠፈ፥ በጠራና በቀላል መንገድ መግለጽ የሚችለው በቋንቋ ብቻ ነው የሚባለው።

ቋንቋ የግለሰብን ማንነት ማሳወቂያ ነው። ሰአሊዎች ከተወሰኑ ቀለማት የተለያዩ የፈጠራ ስዕሎችን እንደሚሰሩ ሁሉ ግለሰቡ የራሱን ብቸኛ መለያ ባህርይ ውስጣዊ ስሜቱን፥ አስተሳሰቡን፡ ወዘተ የሚገልጸው በእዚሁ መሳሪያ ነው። የህብረተሰቡ አባል እንደመሆኑ መጠን ራሱን ለማሳወቅና ለመግለጽ የሚገለገልበት መሳሪያ ህብረተሰቡ ከሚገለገልበት ከተለየ ግን አለመግባባት ወይም አለመጣጣም ይፈጠራል።

ቋንቋ የግለሰቡን የአስተሳሰብ ሂደት መቃኛና መተንተኛ መሳሪያ ነው። ይህ መሳሪያ ግለሰቡ አስተሳሰቡን በቅደም ተከተልና በስርአት ለመደርደር ያስችለዋል። በተጨማሪም የህብረተሰቡን የአስተሳሰብ ሂደትና ልምድ የራሱ ለማድረግ ያስችለዋል።

ቋንቋ የመገናኛ ወይም የመግባቢያ መሳሪያ ነው። ይኸውም ግለሰቡን ከግለሰብ፥ ግለሰብን ከህብረተሰብ፥ ህብረተሰብን ከህብረተሰብ እንደ ድልድይ ሆኖ ያገለግላል። አንድ ግለሰብ ስለሌላው ግለሰብ፥ አንድ ህብረተሰብ ስለሌላው ህብረተሰብ የሚያውቀው፥ ከሌላው የሚማረው፥ ሌላውንም የሚያስተምረው፥ የሃሳብም ሆነ የሌላ አይነት እርዳታ የሚቀበለውና በበኩሉም የሚሰጠው በቋንቋ ነው።

ቋንቋ የሰው ልጅ ያካበተውን ልምድ፥ እውቀት፥ ወዘተ. ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚያስተላልፍ፥ አዳዲስ የሳይንስ ግኝቶችና የፈጠራ ስራዎችን መቅሰም የሚያስችል መሳሪያ ነው። በተለይ ትምህርትን ለመከታተል ተማሪው ከመምህሩ ወይም መምህሩ ከተማሪው እንዲሁም ተማሪዎች ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ለሚያደርጓቸው ግንኙነቶችና ለሚፈጥሩዋቸው ዝምድናዎች ከፍተኛ ድርሻ አለው።

/ከመማሪያ መጽሃፍ የተወሰደ/።

## መልመጃ አንድ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት መልስ::

ሀ. የሰው ልጅ ከሌሎች እንስሳት የለዩትና ዝርያውም እንዳይጠፋ ያደረጉት ምን ምን ናቸው?
ለ. አንድ ህጻን የህብረተሰቡ ሙሉ አባል የሚሆነው ምን ሲሆን ነው?
ሐ. አንድ ሰው ከህብረተሰቡ ጋር አለመግባባት የሚፈጥረው ምን ሲያደርግ ነው?
መ. እንደ ድልድይ ሆኖ ያገናኛል የተባለው ምንድነው?

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት <u>እውነት</u> ወይም <u>ሀሰት</u> በማለት መልስ::

ሀ. የሰው ልጅ ሃሳቡን በማያሻማ መንገድ ለመግለጽ የሚችለው በቋንቋ ብቻ አይደለም::
ለ. ከቋንቋ ተግባራት ውስጥ አንዱ ዕውቀትን ከአንዱ ወደ ሌላው ማስተላለፊያ ነው::
ሐ. ማንኛውም ሰው ህብረተሰቡን የሚጠበቅበትን ድርሻ ማበርከት የሚችለው በቋንቋ ችሎታው አማካይነት አይደለም::
መ. ማንኛውም ህብረተሰብ ማንኛውንም እንቅስቃሴ የሚያከናውነው በቋንቋ ነው::
ሠ. ማንኛውንም ትምህርት ለመከታተል የቋንቋ መኖር የግድ አይደለም::

3. ቀጥሎ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች ቀርበዋል:: ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጭ መልሶች መካከል የሚቀርበውን ምረጥ::

ሀ. "ይሁን እንጂ ከዚህ ያነሰ ችሎታ ያለውም ሰው ቢሆን ከቋንቋ የበለጠ ለሀሳቡ መግለጫና ማስተላለፊያ ሊሆነው የሚችል ቀላል መንገድ አይኖርም::" ሲል_______ ማለቱ ነው::
   1. ከቋንቋ የበለጠ ለሃሳቡ መግለጫ ማስተላለፊያ ሊሆነበው የሚችል ሌላ መንገድ አለው::
   2. ቋንቋ ቀላሉ የሃሳቡ መግለጫና ማስተላለፊያ መንገድ ነው::
   3. ቋንቋ አነስተኛ ችሎታ ያላቸው ሰዎች ብቻ ሐሳብ የሚገልጹበትና የሚያስተላልፉበት መንገድ ነው::
   4. ቋንቋ ከባዱ የሃሳብ መግለጫና ማስተላለፊያ መንገድ ነው::

ለ. ከሚከተሉት አንዱ ትክክል ነው::
   1. አእምሮአዊና አካላዊ ዕድገትና ለውጦች የተግባራዊ እንቅስቃሴ ውጤቶች ናቸው::
   2. አእምሮአዊና አካላዊ የዕድገት ለውጦች የቋንቋ ችሎታ ውጤቶች ናቸው::
   3. ተግባራዊ እንቅስቃሴ የቋንቋ ችሎታ ሂደታዊ ውጤት ነው::
   4. የቋንቋ ችሎታ÷ የአዕምሮአዊና አካላዊ ዕድገትና ለቀጦች የሰውን ልጅ ከሌሎች እንስሳት የለዩት ዋነኞቹ ነገሮች ናቸው::

ሐ. የሰው ልጅ ተግባራዊ እንቅስቃሴ_________ ::
   1. ሰብዕናውን አረጋገጠለት
   2. ከእንስሳት ለየው
   3. አእምሮአዊ ዕድገት ሰጠው
   4. መልሱ አልተሰጠም

መ. ከሚከተሉት ውስጥ የቋንቋ ተግባር ያልሆነው የቱ ነው?
   1. ቋንቋ ህብረተሰብን ከግለሰብ÷ ግለሰብን ከህብረተሰብ ያወሳስባል::
   2. ቋንቋ የግለሰብ ማንነት ማሳወቂያ ነው::
   3. ቋንቋ ቢኖርም ባይኖርም መግባባት የማይቀር ነው::
   4. ቋንቋ የመግባቢያ መሳሪያ ነው::

ሠ. የቋንቋ ከፍተኛ ድርሻ_________ ነው::
   1. ልምድን ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ
   2. አዳዲስ የሳይንስ ግኝቶችን ማስተላለፍ
   3. የፈጠራ ስራዎችን መቅሰሚያ መሳሪያ
   4. ሁሉም መልስ ናቸው

## መልመጃ ሁለት

1. ቀጥሎ ከቀረቡት ቃላት በተሰጠህ ምሳሌ መሰረት ስያሜ አውጣላቸው::
   ምሳሌ:- አከማቸ - ክምችት
   ቀለጠፈ - ቅልጥፍና

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. አዋሀደ | ለ. አወቀ | ሐ. ሄደ |
| መ. ቃኘ | ሠ. ለመደ | መ. ረዳ |

2. የሚከተሉት ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነገሩ የሚኖራቸውን የትርጉም ልዩነት በዐረፍተ ነገር አስገብተህ አሳይ::

| | |
|---|---|
| ሀ. የሚለካው | ሠ. መደርደር |
| ለ. ያለው | ረ. መተንተን |
| ሐ. እንደሚሰሩ | ሰ. የሚሰጠው |
| መ. መለያ | |

3. ቀጥሎ የተሰጡት ዐረፍተነገሮች ከምንባቡ ውስጥ እንዳሉ ወይም ተሻሽለው የወጡ ናቸው:: በዐረፍተ ነገሮቹ ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት በትክክል የሚተኳቸውን ቃላት ከተሰጡት አማራጭ መልሶች መካከል ምረጥ::

ሀ. የቋንቋ ችሎታ÷ አዕምሮአዊና አካላዊ ዕድገትና ለውጦች ከፍተና ሚና አላቸው::
   1. ድርሻ 2. ወገን 3. ተመሳሳይነት 4. ተልዕኮ

ለ. ቋንቋ ግለሰቡን ከህብረተሰቡ ህይወት ጋር ያወሳስባል::
   1. ያቆራኛል 2. ያገናኛል 3. ያያይዛል 4. ያደነጋግራል

ሐ. የአንድ ሰው የቋንቋ ክህሎት መለኪያ ዘዴዎች አሉ::
   1. ብቃት 2. ችሎታ 3. ጥራት 4. ክብደት

መ. በጥራት አዳምጦ የተነገረውን መጨበጥ በቋንቋ ትምህርት ይዳብራል::
   1. ማስቀረት 2. መረዳት 3. መያዝ 4. መንካት

ሠ. የሰው ልጅ ሀሳቡን በቀለጠፈ÷ በጠራና በቀላል መንገድ መግለጽ የሚችለው ብቋንቋ ብቻ ነው::
   1. በፍጥነት/በግልጽ 2. በአጭሩ/በግልጽ
   2. በተቻኮለ/በፍጥነት 3. በግልጽ/በአጭሩ

ረ. ግለሰቡ የራሱን ውስጣዊ ስሜት÷ አስተሳሰብ÷ ወዘተ የሚገልጸው በቃላት÷ ምርጫው÷ በዐረፍተ ነገር አሰካኩ ነው::
   1. አደራደሩ 2. አያያዙ 3. አገባቡ 4. 1 ና 3

ሰ. ቋንቋ የግለሰቡን የአስተሳሰብ ሂደት መቃኛና መተንተኛ መሳሪያ ነው::
   1. ማስተካከያ 2. መምሪያ 3. ማያ 4. መግሪያ

ሸ. ቋንቋ የሰው ልጅ ያካበተውን ልምድ÷ ዕውቀት÷ ወዘተ. ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚያስተላልፍበት መሳሪያ ነው::
   1. የሰበሰበውን 2. ያከማቸውን
   3. ያጠራቀመውን 4. ሁሉም

ቀ. ቋንቋ አዳዲስ የሳይንስ ግኝቶችና የፈጠራ ስራዎችን መቅሰም የሚያስችል ነው::
   1. መገብየት 2. ማዳበር
   3. መፍጠር 4. ማሰራጨት

## መልመጃ ሦስት

1. ስለ ቋንቋ ተግባር ከቀረበልህ ምንባብ የቀረ ነገር አለ? ሰው ጠይቀህ ወይንም መጽሀፍ አንብበህ ያገኘኸውን ለክፍል ጓደኞችህ አቅርብ::

## ምንባብ ሁለት

### ጥንታዊ የጋብቻና የአኑዋኑዋር ስርአት

መቼም ባንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ወደዱም ጠሉም የሚኖሩበትን ማህበር መንግስታሚ ህግ አክብረውና፥ ባህላዊ ያስተሳሰብ ያሰራርና ህግ የምንነት ስራቱን ተከትለው መኖር አለባቸው። የማህበሩን መንግስታወጸ ህግ የማያከብሩ "ህገ-ወጦች" ባህላዊ ስራቱን የማይከተሉ "ጋጠወጦች" ተብለው በማህበሩ ውስጥ ደንበኛ ያባልነት ቦታ አይኖራቸውም። ከማህበሩ ውጭእን ሆነው፥ ያካልና የመንፈስ ቅጣት ይደርስባቸዋል። ይሁን እንጂ የማህበራቸውን ጨቋኝ ወይም ግፈኛ ህግና ስራት ተሸክሞ የማህበሩ ደንበኛ አባል ሆኖ ከመኖር ከሱ ነጻ ሆኖ አይደርስ ቅጣት ወይም ችግር ቢደርስባቸው የሚመርጡ፥ አንዳንድ ግለሰቦች በየጊዜውና በየቦታው ጠፍተው አያውቁም። እንዲያ ያሉት ግለሰቦች ጋር ሲፈጠሩ ግፍንና ጭቆናን እንዳይችሉ በግፍና በጭቆና ላይ እንዲሸፍቱ ሆነው የሚፈጠሩ ናቸው።

በጥንቱ ልማድ፥ የልጆችን ጋብቻ የሚወስኑ ወላጆች እንጂ ልጆች እንኳዋንስ ለውሳኔው ተካፋዮች ሊሆኑ ከመሀከላቸው ሳይተዋወቁ እንዲያውም አንድ ቀን እንኳዋ ሳይተያዩ የሚጋቡ ነበሩ። በሀብት ይልቁንም በዘር "ያክሉናል፥ ይመስሉናል" ተባብለው ልጆቻቸውን የሚያጋቡ ወላጆች ነበሩ። አንዳንድ ጊዜ በሁለት ቤተሰቦች መሀከል የነፍስ ግድያ ቂም የኖረ እንደሆነ እንዲያ ያለውን ቂም የመበቀል ሃሳብ ከመሀከላቸው እንዲጠፋ፥ በመሀከላቸው "የፈሰሰው ደም እንዲደርቅ" እኒያ ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ማጋባት የተለመደ ነበር። የልጆች ጋብቻ በነፍስ ግድያ ለሚፈላለጉ ቤተሰቦች የሰላም ዋጋ ሆኖ የሚከፈል ነበር። እንዲሁም ከጥንት ልማዶች ሌላው ክፉ ነገር በተለይ ሴቶች ልጆች ላቅመ ሄዋን ሳይደርሱ የሚዳሩ መሆናቸው ነበር።

ለኔ እንደሚመስለኝ ከጥንታዊው ስርአተ ማህበር ያስተሳሰብ፥ ያስተያየትና ያሰራር ልማድ ከሁሉም ይልቅ ለእውቀትና ለዕድገት መሰናክል ሆኖ የኖረ፥ ሰው ሰርቶ ጥሮ ግሮ ሀብታም ከመሆን፥ ከሀብታም ወይም 'ከመሰረተ ጌታ' ተወልዶ 'ደሀ' መሆን ይመርጥ የነበረ መሆኑ ነው። የጅ ስራ ማወቅ "ይሀ እጀ ሰሪ" አሰኝቶ ያሰድብ ነበር። የጌታ ዘር ሆኖ በጥፍሩ ስራ የማይነካ ድሀ ግን ይታፈር ይከበር ነበር። ታዲያ እንዲያ ያለው አስተሳሰብ፥ ያስተያየትና ያሰራር ባህልና ልማድ ለጠቅላላው ህዝብ የውቀትና የድገት መሰናክል ከመሆን ሌላ በግለሰብ ደረጃም በባልና በምሽት፥ በወላጅና በልጅ፥ በጓደኞች መሀል ሊኖር ለሚገባው መልካም ግንኙነት ጠንቅ ነበር። በመሆኑም ሰርተው በጎ አዳሪዎች የሆኑ ሰዎች እንኳዋ ከትውልድ አገራቸው ወደ ማይታወቁበት ሩቅ አገር የሄዱ እንደሆነ በሄዱበት አገር አክብር ቦታ አግኝተው ለመኖር፥ አገራቸው ሰርተው ስለመሰረቱት መልካም ኑሮ ከማውራት ይልቅ ያልሆኑትን ዋሽተው 'የመሰረተ ጌታ' ልጆች ቢያንስ ቢያንስ ወገኖች መሆናቸውን ማውራት ይወዳሉ። ታዲያ ውሎ አድሮ ውሸታቸው ሲገለጽባቸው በነሱ ላይ እፍረትን፥ ከሌሎች ትዝብትን ያስከትልና በመጨረሻ የሚያሳዝን ሁኔታ ይደርሳል።

/ከየልምዣት ገጽ 6-8 የተወሰደ/።

### መልመጃ አንድ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት መልስ።

ሀ. ባህላዊ ስርዓቱን የማይከተሉ ጋጠ ወጦች ተብለው በማህበሩ የአባልነት ቦታ የሚያጡት እነማን ናቸው።

ለ. በግፍና በጭቆና ላይ ሸፍተው የሚኖሩት የማህበረሰቡ አባላት የትኞቹ ባቸው?

ሐ. በቤተሰቦች ጸብ የተነሳ በመካከላቸው የፈሰሰውን ደም የሚያደርቁበት አይነተኛ ዘዴ ምን ነበር?

መ. በአጉል ልማድ በተተበተበ ማህበረሰብ ውስጥ የበለጠ ክብር ያገኙ የነበሩት እነማን ናቸው?

ሠ. በማህበረሰቡ ውስጥ የሚያሳዝን ሁኔታ የሚያስከትለው ምንድነው?

2. የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልስ።

ሀ. ከትውልድ አገራቸው ርቀው የሚሄዱትና ክብር የሚያገኙትን በአገራቸው ተገቢ ማህበራዊ ስፍራ ያጡት ናቸው::

ለ. ለጠቅላላው ማህበረሰብ የእድገት መሰናክል የሚሆነው ከትውልድ ስፍራ መሰደድና ስራ መናቅ ነው::

ሐ. የአንድ ማህበረሰብ አባላት ሙሉ አባልነታቸውን ለማረጋገጥ ወግና ስርአቱን አክብረው መኖር አለባቸው::

መ. በምንባቡ አቅራቢ አመለካከት ለእድገት እንቅፋት የሚሆነው ወላጆች የልጆቻቸውን የጋብቻ ህይወት መወሰናቸው ነው::

ሠ. በምንባቡ ውስጥ የተገለጸውን ችግር ለማስወገድ የማህበረሰቡን አባላት ማስተማርና የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት ተገቢ ነው::

## መልመጃ ሁለት

1. ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት ትክክለኛ ፍች ፈልግላቸው::

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. | ጋጠ-ወጦች | ሠ. | እጀ ሰሪ |
| ለ. | ውጹአን | ረ. | በጎ አዳሪዎች |
| ሐ. | የሰላም ዋጋ | ሰ. | መሰናክል |
| መ. | መሰረታ ጌታ | ሸ. | ይታፈር |

## መልመጃ ሶስት

በምንባቡ ውስጥ የቀረበው ሀሳብ ስለ ጥንቱ የአኑዋኑዋር የጋብቻ ስርአት የሚያወሳ ነው:: በቡድን ተከፋፍላችሁ ሐሳቡን በመደገፍና በመቃረን ተከራከሩበት::

# ምንባብ ሶስት

## ኤድስና የመከላከል ዘመቻ

በየአመቱ "የኤድስ ቀን" እየተባለ በአለም ደረጃ የሚከበር አለም አቀፍ በአል አለ:: "የለውጥ ሀይል ከሆነው ወጣት ጋር አለም በኤድስ ላይ ይነሳ" በሚል መሪ መፈክር ስር ነው የዘንድሮው በሀገራችን የተከበረው:: ከዚህ ቀን በኋላ ህብረተሰቡ የባህሪይ ለውጥ እንዲያመጣ እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል፤ እየተደረጉም ነው:: የኤድስ መቅሰፍት በአለማችን ላይም ሆነ በሀገራችን እያደረሰ ካለው ጉዳት አንጻር እስከአሁን የተደረገው የማሳወቅ እና የመከላከል እንቅስቃሴ በጣም አነስተኛና ያልተቀናጀ ቢሆንም አሁን እየታየ ያለው ጅማሮ ተስፋ ሰጪ ነውና ሊበረታታ ይገባዋል::

ህብረተሰባችን በኤድስ ላይ ያለውን አመለካከት ለውጦ የባህርይ ለውጥ እንዲያመጣ የመገናኛ ብዙሀን ከማንም በላይ ወሳኝ ሚና ሊቱ ይችላሉ:: በዚህ በኩል ሬዲዮ ፋና ዲ.ኬ.ት ከተባለ ድርጅት ጋር በመተባበር ሰፊ የአየር ጊዜ በመስጠት በአራት ቋንቋዎች ያስተላለፋቸው ትምህርታዊ ቅስቀሳዎች ሊጠቀሱ የሚገባቸው ናቸው:: የኤድስ ደዌ በምድራችን ላይ ከተከሰተ ወዲህ ወረርሺኙ ከመቼውም ጊዜ በላቀ ሁኔታ እየተዛመተ በመምጣት ላይ ነው:: በአለማችን በበሽታው የተጠቁ ወገኖች ብዛት ከ4.7 ሚሊዮን በላይ የደረሰ ሲሆን ከነዚህ መካከል 1.4 ሚሊዮን የሚሆኑት ሞተዋል:: ባለፈው አንድ አመት ብቻ 5.8 ሚሊዮን ህዝብ በበሽታው የተለከፈ ሲሆን የማቾች ቁጥርም 2.5 ሚሊዮን ደርሷል::

የሀገራችንን ሁኔታ ስናይ ኤድስ ከተከሰተ በአጭር ጊዜ ውስጥ የህሙማኑና የቨይረሱ ተሸካሚዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚያስደነግጥ ፍጥነት እየጨመረ ነው:: በዚህም መሰረት እስከ መስከረም 30 ቀን 1991 ዓ.ም. ድረስ 69,931 የኤድስ ህሙማን መኖራቸው ከየጤና ድርጅቶች ከቀረቡት ሪፖርቶች የተረጋገጠ ሲሆን ወደ ጤና ድርጅቶች ለመምጣት ሳይችሉ የቀሩትን ህሙማን እግምት ውስጥ ሳናስገባ በሀገራችን የኤድስ ህሙማን ቁጥር ከ40,000 በላይ ሊደርስ እንደሚችል ይገመታል:: የቨይረሱ ተሸካሚዎች ቁጥርም አስራ ሶስት ሚሊዮን ይደርሳል:: በዚህ መሰረት በሀገራችን ለአቅመ አዳምና ሄዋን ከደረሱ ማለትም ከ15-49 የእድሜ ክልል ውስጥ ከሚገኙ ወጣቶችና ጎልማሶች መካከል 7.4 በመቶ የሚሆኑት በቨይረሱ ተለክፈዋል:: በአንዳንድ ከተሞችና አካባቢዎችም የተደረጉ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ከ12-18 በመቶ የሚሆኑ ነፍሰ ጡር ሴቶች የቨይረሱ ተሸካሚ ሆነው ተገኝተዋል::

በሀገራችን ለኤድስ እንደ ሰደድ እሳት መዛመት ባጠቃላይ ህብረተሰቡ የአመለካከትና የባህሪይ ለውጥ ሊያመጣ አለመቻሉ እንደ አቢይ ምክንያት የሚጠቀስ ሲሆን ለዚህም ባህላዊ÷ ሃይማኖታዊና ኤኮኖሚያዊ ተጽዕኖዎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉ መሆኑ ይታመናል:: ዛሬ በሀገራችን በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖቻችን ሲረግፉ በአይናችን እያየን በበሽታው ላይ የባህርይ ለውጥ አለማምጣትና በምስጢር ይዞ እንደሌላ ለመቁጠር መሞከሩ ለከፍተኛ እልቂት እየዳረገን መሆኑ በሁላችንም ዘንድ ግንዛቤው ሊኖረን ይገባል::

የለውጥ እንቅስቃሴ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ በቀላሉ የሚገመት አይደለም:: እየተስፋፋ የመጣውን የኤድስ ወረርሽኝ ለመቋቋም ደግሞ ጥረት ያስፈልጋል:: ጥናቱም የሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች መሆን አለበት:: በህብረተሰቡ ዘንድ የሚጠበቀው የባህርይ ለውጥ እንዲመጣ ደግሞ የመገናኛ ብዙሀን ግንባር ቀደም ሚና መጫወት ቢኖርባቸውም ከነሱ በተጨማሪ ወላጆች÷ ትምህርት ቤቶች÷ የሀይማኖት ተቋማት÷ በርካታ የህብረተሰብ ስራ ማህበራትና የሙያ ማህበራት ባንድነት ተቀናጅተው ተከታታይነት ያለው ቅስቀሳና ትምህርት መስጠት ይኖርባቸዋል::

/ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥር 6, 1991 የተወሰደ/::

# ምንባብ ሶስት

## ኤድስና የመከላከል ዘመቻ

በየአመቱ "የኤድስ ቀን" እየተባለ በአለም ደረጃ የሚከበር አለም አቀፍ በአል አለ:: "የለውጥ ሀይል ከሆነው ወጣት ጋር አለም በኤድስ ላይ ይነሳ" በሚል መሪ መፈክር ስር ነው የዘንድሮው በሀገራችን የተከበረው:: ከዚህ ቀን በኋላ ህብረተሰቡ የባህሪይ ለውጥ እንዲያመጣ እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል፤ እየተደረጉም ነው:: የኤድስ መቅሰፍት በአለማችን ላይም ሆነ በሀገራችን እያደረሰ ካለው ጉዳት አንጻር እስከአሁን የተደረገው የማሳወቅ እና የመከላከል እንቅስቃሴ በጣም አነስተኛና ያልተቀናጀ ቢሆንም አሁን እየታየ ያለው ጅማሮ ተስፋ ሰጪ ነውና ሊበረታታ ይገባዋል::

ህብረተሰባችን በኤድስ ላይ ያለውን አመለካከት ለውጦ የባህርይ ለውጥ እንዲያመጣ የመገናኛ ብዙሀን ከማንም በላይ ወሳኝ ሚና ሊቱ ይችላሉ:: በዚህ በኩል ሬዲዮ ፋና ዲ.ኬ.ት ከተባለ ድርጅት ጋር በመተባበር ሰፊ የአየር ጊዜ በመስጠት በአራት ቋንቋዎች ያስተላለፋቸው ትምህርታዊ ቅስቀሳዎች ሊጠቀሱ የሚገባቸው ናቸው:: የኤድስ ደዌ በምድራችን ላይ ከተከሰተ ወዲህ ወረርሺኙ ከመቼውም ጊዜ በላቀ ሁኔታ እየተዛመተ በመምጣት ላይ ነው:: በአለማችን በበሽታው የተጠቁ ወገኖች ብዛት ከ4.7 ሚሊዮን በላይ የደረሰ ሲሆን ከነዚህ መካከል 1.4 ሚሊዮን የሚሆኑት ሞተዋል:: ባለፈው አንድ አመት ብቻ 5.8 ሚሊዮን ህዝብ በበሽታው የተለከፈ ሲሆን የማቾች ቁጥርም 2.5 ሚሊዮን ደርሷል::

የሀገራችንን ሁኔታ ስናይ ኤድስ ከተከሰተ በአጭር ጊዜ ውስጥ የህሙማኑና የቫይረሱ ተሸካሚዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚያስደነግጥ ፍጥነት እየጨመረ ነው:: በዚህም መሰረት እስከ መስከረም 30 ቀን 1991 ዓ.ም. ድረስ 69,931 የኤድስ ህሙማን መኖራቸው ከየጤና ድርጅቶች ከቀረቡት ሪፖርቶች የተረጋገጠ ሲሆን ወደ ጤና ድርጅቶች ለመምጣት ሳይችሎ የቀሩትን ህሙማን እግምት ውስጥ ሳናስገባ በሀገራችን የኤድስ ህሙማን ቁጥር ከ40,000 በላይ ሊደርስ እንደሚችል ይገመታል:: የቫይረሱ ተሸካሚዎች ቁጥርም አስራ ሶስት ሚሊዮን ይደርሳል:: በዚህ መሰረት በሀገራችን ለአቅመ አዳምና ሄዋን ከደረሱ ማለትም ከ15-49 የእድሜ ክልል ውስጥ ከሚገኙ ወጣቶችና ጎልማሶች መካከል 7.4 በመቶ የሚሆኑት በቫይረሱ ተለክፈዋል:: በአንዳንድ ከተሞችና አካባቢዎችም የተደረጉ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ከ12-18 በመቶ የሚሆኑ ነፍሰ ጡር ሴቶች የቫይረሱ ተሸካሚ ሆነው ተገኝተዋል::

በሀገራችን ለኤድስ እንደ ሰደድ እሳት መዛመት ባጠቃላይ ህብረተሰቡ የአመለካከትና የባህሪይ ለውጥ ሊያመጣ አለመቻሉ እንደ አቢይ ምክንያት የሚጠቀስ ሲሆን ለዚህም ባህላዊ÷ ሃይማኖታዊና ኤኮኖሚያዊ ተጽዕኖዎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉ መሆኑ ይታመናል:: ዛሬ በሀገራችን በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖቻችን ሲረግፉ በአይናችን እያየን በበሽታው ላይ የባህርይ ለውጥ አለማምጣትና በምስጢር ይዞ እንደሌላ ለመቁጠር መሞከሩ ለከፍተኛ እልቂት እየዳረገን መሆኑ በሁላችንም ዘንድ ግንዛቤው ሊኖረን ይገባል::

ኤድስ በግለሰቦችም ሆነ በማህበረሰቡ ላይ ከፍተኛ ማህበራዊ÷ ኢኮኖሚያዊና ስነልቡናዊ ተጽዕኖ ያሳድራል:: በሽታው በግለሰቦች ላይ ከሚያስከትለው ስቃይና ሞት በተጨማሪ በቤተሰብ ላይ የሚያስከትላቸው ችግሮች እጥፍ ድርብ ናቸው:: ኤድስ በይበልጥ የሚያጠቃው በአፍላ የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ጎልማሶችንና አምራች ሀይሎችን በመሆኑ ሀገራችን በተያያዘችው መጠነ ሰፊ የልማት እንቅስቃሴ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ በቀላሉ የሚገመት አይደለም:: እየተስፋፋ የመጣውን የኤድስ ወረርሽኝ ለመቋቋም ደግሞ ጥረት ያስፈልጋል:: ጥናቱም የሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች መሆን አለበት:: በህብረተሰቡ ዘንድ የሚጠበቀው የባህርይ ለውጥ እንዲመጣ ደግሞ የመገናኛ ብዙሀን ግንባር ቀደም ሚና መጫወት ቢኖርባቸውም ከነሱ በተጨማሪ ወላጆች÷ ትምህርት ቤቶች÷ የሀይማኖት ተቋማት÷ በርካታ የህብረተሰብ ስራ ማህበራትና የሙያ ማህበራት ባንድነት ተቀናጅተው ተከታታይነት ያለው ቅስቀሳና ትምህርት መስጠት ይኖርባቸዋል::

/ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥር 6, 1991 የተወሰደ/::

## መልመጃ አንድ

1. የሚከተሉትን ዐ.ነገሮች እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልስ::

ሀ. ህብረተሰቡ ስለኤድስ ያለውን ግንዛቤ ለማዳበር በየአመቱ አለም አቀፍ በአል ማክበሩ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል::
ለ. የኤድስን በሽታ ስርጭት ለመግታት የህብረተሰቡን የአመለካከት መለወጥ ያስፈልጋል::
ሐ. ኤድስ የሚያጠቃው በወጣትነት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኘውን የህብረተሰብ ክፍል ብቻ ነው::
መ. ህብረተሰብ በኤድስ ላይ ያለውን አመለካከት እንዲለወጥ ማስተማርና መቀስቀስ የሁሉም ሰው ሀላፊነት ነው::
ሠ. በአለም ላይ ከተከሰቱት በሽታዎች ኤድስን የሚለየው በፍጥነት መዛመቱ እና ቀሳፊነቱ ነው::
ረ. የኤድስን በሽታ ስርጭት ለመቀነስ የሚቻለው የመከላከያውን ዘዴ በመጠቀም ብቻ ነው::

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት መልስ

ሀ. ከኤድስ በሽተኞችና ከቫይረሱ ተሸካሚዎች የበለጠ አደገኛ የሚሆኑት የትኞቹ ናቸው::
ለ. የኤድስ በሽታን ልዩ የሚያደርጉ ባህርያት የትኞቹ ናቸው?
ሐ. በሁለተኛው ምንባብ ጸሀፊ እምነት ለኤድስ በሽታ ስርጭት ትልቅ ድርሻ ያለው ምንድነው?
መ. ኤድስ ማህበራዊ ቀውስ የሚያስከትለው እንዴት ነው?
ሠ. ማህበረሰባችን ስለኤድስ ያለውን አመለካከት ለመለወጥ አስቸጋሪ ነው የተባለው ለምንድነው?

## መልመጃ ሁለት

ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት ትክክለኛ ፍች ፈልግላቸው::

ሀ. አስረሽ ምችው
ለ. አፍላ
ሐ. ሰደድ
መ. ቀሰፈ
ሠ. ጅማሮ
ረ. ወረርሽኝ
ሰ. መዛመት
ሸ. ቀውስ
ቀ. ታለመ
በ. ነባራዊ

## መልመጃ ሶስት

የምንባቡ መልዕክት የጥንቱን የአኑዋኑዋር ስርአት መቀየር እንደሚያስፈልግ ይገልጻል:: አንተ በደራሲው ትስማማለህ? ማስረጃ በማቅረብ ከክፍል ጓደኞችህ ጋር ተነጋገሩበት::

ከላይ የቀረበውን ምንባብ ቀጥሎ ካለው ጋር ለማነጻጸር ሞክር::

ኤድስ በአለም ላይ ከተከሰተ ገና ሀያ አመት ያላስቆጠረ ቢሆንም የሚያስከትላቸው ልዩ ልዩ ቀውሶችና የሚያደርሳቸው ጉዳቶች ግን ግንባር ቀደም ተጠቃሽ አድርገውታል:: እንደ አለም ጤና ድርጅት ዘገባ ከሆነ በየአመቱ በወጣ ምክንያት በአለም ላይ አንድ ሚሊዮን ህዝብ እንደሚሞት ሲገመት÷ በአንጻሩ ደግሞ በኤድስ ምክንያት በ1998 ብቻ 2.5 ሚሊዮን ህዝብ አልቋል:: ይህ ከፍተኛ ቀሳፊነቱ አንዱ ልዩ ባህሪው ነው:: ልዩ የሚያደርጉት የራሱ ተጨማሪ ባህርያትም አሉት:: እነርሱም የመስፋፋት ሀይሉ ከፍተኛ በመሆኑ ድንበር የለሽ በሽታ ነው:: ደረጃው ይለያይ እንጂ በደሀና በበለጸጉ ሀገሮች÷ በቆላም ሆነ በደጋ÷ በነጭም ሆነ በጥቁር ህብረተሰብ ውስጥ ይገኛል:: እስከ ዛሬ ድረስ ከሙከራ ውጭ ለመከላከያነት የሚያገለግል ክትባት አልተገኘለትም:: ኤድስ በአብዛኛው ከያንዳንዱ ግላዊና ምስጢራዊ የወሲብ ህይወት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ቁጥጥሩን ውስብስብ ያደርገዋል:: የኤች.አይ.ቪ መተላለፊያ መንገዶች የታወቁና የማያሻሙ ቢሆንም ከግንዛቤ ማነስ ምክንያት በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች በቫይረሱ የተጠቁትን

## መልመጃ አንድ

1. የሚከተሉትን ዐ.ነገሮች እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልስ::

ሀ. ህብረተሰቡ ስለኤድስ ያለውን ግንዛቤ ለማዳበር በየአመቱ አለም አቀፍ በአል ማክበሩ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል::

ለ. የኤድስን በሽታ ስርጭት ለመግታት የህብረተሰቡን የአመለካከት መለወጥ ያስፈልጋል::

ሐ. ኤድስ የሚያጠቃው በወጣትነት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኘውን የህብረተሰብ ክፍል ብቻ ነው::

መ. ህብረተሰብ በኤድስ ላይ ያለውን አመለካከት እንዲለወጥ ማስተማርና መቀስቀስ የሁሉም ሰው ሀላፊነት ነው::

ሠ. በአለም ላይ ከተከሰቱት በሽታዎች ኤድስን የሚለየው በፍጥነት መዛመቱ እና ቀሳፊነቱ ነው::

ረ. የኤድስን በሽታ ስርጭት ለመቀነስ የሚቻለው የመከላከያውን ዘዴ በመጠቀም ብቻ ነው::

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት መልስ

ሀ. ከኤድስ በሽተኞችና ከቫይረሱ ተሸካሚዎች የበለጠ አደገኛ የሚሆኑት የትኞቹ ናቸው::

ለ. የኤድስ በሽታን ልዩ የሚያደርጉ ባህርያት የትኞቹ ናቸው?

ሐ. በሁለተኛው ምንባብ ጸሀፊ እምነት ለኤድስ በሽታ ስርጭት ትልቅ ድርሻ ያለው ምንድነው?

መ. ኤድስ ማህበራዊ ቀውስ የሚያስከትለው እንዴት ነው?

ሠ. ማህበረሰባችን ስለኤድስ ያለውን አመለካከት ለመለወጥ አስቸጋሪ ነው የተባለው ለምንድነው?

## መልመጃ ሁለት

ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት ትክክለኛ ፍች ፈልግላቸው::

| | |
|---|---|
| ሀ. አስረሽ ምችው | ረ. ወረርሽኝ |
| ለ. አፍላ | ሰ. መዛመት |
| ሐ. ሰደድ | ሸ. ቀውስ |
| መ. ቀሰፈ | ቀ. ታለመ |
| ሠ. ጅማሮ | በ. ነባራዊ |

## መልመጃ ሶስት

የምንባቡ መልዕክት የጥንቱን የአኑዋኑዋር ስርአት መቀየር እንደሚያስፈልግ ይገልጻል:: አንተ በደራሲው ትስማማለህ? ማስረጃ በማቅረብ ከክፍል ጓደኞችህ ጋር ተነጋገሩበት::

ከላይ የቀረበውን ምንባብ ቀጥሎ ካለው ጋር ለማነጻጸር ሞክር::

ኤድስ በአለም ላይ ከተከሰተ ገና ሀያ አመት ያላስቆጠረ ቢሆንም የሚያስከትላቸው ልዩ ልዩ ቀውሶችና የሚያደርሳቸው ጉዳቶች ግን ግንባር ቀደም ተጠቃሽ አድርገውታል:: እንደ አለም ጤና ድርጅት ዘገባ ከሆነ በየአመቱ በወባ ምክንያት በአለም ላይ አንድ ሚሊዮን ህዝብ እንደሚሞት ሲገመት÷ በአንጻሩ ደግሞ በኤድስ ምክንያት በ1998 ብቻ 2.5 ሚሊዮን ህዝብ አልቋል:: ይህ ከፍተኛ ቀሳፊነቱ አንዱ ልዩ ባህሪው ነው:: ልዩ የሚያደርጉት የራሱ ተጨማሪ ባህርያትም አሉት:: እነርሱም የመስፋፋት ሀይሉ ከፍተኛ በመሆኑ ድንበር የለሽ በሽታ ነው:: ደረጃው ይለያይ እንጂ በደሀና በበለጸጉ ሀገሮች÷ በቆላም ሆነ በደጋ÷ በነጭም ሆነ በጥቁር ህብረተሰብ ውስጥ ይገኛል:: እስከ ዛሬ ድረስ ከሙከራ ውጭ ለመከላከያነት የሚያገለግል ክትባት አልተገኘለትም:: ኤድስ በአብዛኛው ከያንዳንዱ ግላዊና ምስጢራዊ የወሲብ ህይወት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ቁጥጥሩን ውስብስብ ያደርገዋል:: የኤች.አይ.ቪ. መተላለፊያ መንገዶች የታወቁና የማያሻሙ ቢሆንም ከግንዛቤ ማነስ ምክንያት በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች በቫይረሱ የተጠቁትን

ዜጎች እንደ ሀጢአተኛ የመመልከት ሁኔታ በብዙ ሀገሮች የታየ ጉዳይ ነው:: ይህም ለቫይረሱ ተጠቂዎች ከቤተሰብና ከመኖሪያ አካባቢ፥ ከመስሪያ ቤትና ከመሳሰሉት ቦታዎች መፈናቀልን እያስከተለ ነው:: ከፍተኛ ማህበራዊ ቀውስ::

በኢትዮጵያ የመጀመሪያዎቹ የኤድስ ተሸካሚዎች የተገኙት በሀገራችን አቆጣጠር በ1977 ዓ.ም. በተደረገ ጥናት ሲሆን ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የቫይረሱ ስርጭት በጣም ፈጣን በሆነ ሂደት በከተማም ሆነ በገጠር እየገሰገሰ ነው:: ከ1977 እስከ 1981 ዓ.ም. ድረስ የሴተኛ አዳሪዎችና የሾፌሮች በሽታ ተደርጎ ይታይ ነበር:: ከዚያ በኋላ ተከታታይ ጥናቶች እንዳመለከቱት በአጠቃላይ ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በቫይረሱ ተጠቂዎች መሆናቸው ተረጋግጦአል:: ስለዚህ የቫይረሱ መዛመቻ መንገዶች ውጤታማ በሆነ መንገድ ካልተገታ የሚያስከትለው ቀውስ እጅግ አስቃቂ እንደሚሆን አያጠራጥርም::

የኤድስን መስፋፋት መቀነስ የሚቻለው እያንዳንዱ ግለሰብ ስለበሽታው መተላለፊያ መንገዶችና መከላከያ ዘዴዎችን አውቆ የባህሪይ ለውጥ ማምጣት ሲችል ነው:: የባህርይ ለውጥ ማምጣት ደግሞ እንዲህ ቀላል ነገር አይደለም:: ብዙ በጣም ብዙ ጥረትን ይጠይቃል:: በ1988 ዓ.ም. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከአለም ጤና ድርጅት ጋር በመተባበር በኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ከተሞች ባደረገው ጥናት የኤድስ መተላለፊያ መንገዶችንና መከላከያ ዘዴዎችን በትክክል የሚያውቀው ህዝብ ብዛት ከ85% በላይ የነበረ ቢሆንም ግንዛቤውን አዳብሮ የባህሪ ለውጥ ማምጣት መቻሉን ያረጋገጠው ህዝብ ብዛት ግን 45% ያህሉ ብቻ ነበር::

እያንዳንዱ ግለሰብ ስለ በሽታው መከላከያ ዘዴዎች እንዲያውቅና የባህርት ለውጥ እንዲያመጣ የሚተላለፈው ትምህርት ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው ቢሆንም ብቻውን የታለመለትን ያህል ውጤት ሊያስገኝ አይችልም:: የግለሰብንና የማህበረሰቡን አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታዎች በተናጠልና በጥምር መመርመር ያስፈልጋል::

ዛሬ በሀገራችን ከጥንቱ በበለጠ ቡና ቤቶች፥ የምሽት ዳንስ ቤቶች፥ መናፈሻ ቤቶች፥ ድብቅ መዝናኛዎች፥ ቪዲዮ ስፍር ቁጥር በሌለው ሁኔታ በየቀበሌው ተስፋፍተው ከወጣት እስከ ጎልማሳው ከምሽት እስከ ንጋት በመጠጥ ሀይል አስረስ ምቸው ሲል ያድራል:: የወጣቱን ስነልቡና የሚሰልቡትን አስነዋሪ ተግባራት ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ ጥረት ሳናደርግ በሽታውን ስለመከላከል ብቻ ብንሰብክ ውጤታማ ሊሆን አይችልም:: የተቀነባበረና ሁሉን አቀፍ እንቅስቃሴ ማድረግ ያስፈልጋል::

/ከጦቢያ ጋዜጣ ሰኔ 3, 1991 የተወሰደ/::

## መልመጃ አንድ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት መልስ

ሀ. ኤድስን ከወባና ሌሎች በሽታዎች ልዩ የሚያደርጉትን ባህርያት ዘርዝር::
ለ. በሀገራችን በተደረገው ጥናት የባህሪይ ለውጥ ያመጣው ህዝብ ምን ያህሉ ፐርሰንት ነው?
ሐ. እንደ ደራሲው አባባል የኤድስን መስፋፋት ለመቀነስ ምን ማድረግ ያስፈልጋል?
መ. የህብረተሰቡን አስተሳሰብ ለመለወጥ ምን ማድረግ ይገባል?
ሠ. የኤድስ በሽታን ቁጥጥር አስቸጋሪ ከሚያደርጉት ምክንያቶች ዋነኛው የቱ ነው?

2. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልስ::
ሀ. ኤድስ ግለሰባዊ ባህርይ ስላለው በማስተማር ብቻ መከላከል ይቻላል::
ለ. ኤድስ የወጣቱን ክፍል ብቻ ለይቶ በይበልጥ የሚያጠቃ በሽታ ነው::
ሐ. ኤድስ በአጭር ጊዜ ውስጥ እየተስፋፋ የመጣ፥ ለመቆጣጠርም ሆነ ለማጥፋት አስቸጋሪ የሆነ ደዌ ነው::
መ. ኤድስን ለመቆጣጠር የሚደረገው ጥረት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ያገናዘበ መሆን አለበት::
ሠ. የጽሁፉ አጠቃላይ ይዘት የኤድስን አደገኛነት በማብራራት የሚያስጠነቅቅ ነው::

## መልመጃ ሁለት

1. ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት ተመሳሳይ ፈልግላቸው።

    ሀ. መዛመቻ
    ለ. ቀውስ
    ሐ. ቀሳፊነት
    መ. መንገዶችና ዘዴዎች
    ሠ. ቁጥር ስፍር
    ረ. መሰለብ

2. የምንባቡ አቅራቢ የኤድስን ስርጭት ለመከላከል ይረዳሉ በማለት የጠቀሳቸው የመፍትሄ ሃሳቦች አሉ። በገጠርም ሆነ በከተማ ያለውን ህዝብ በጋራ ወይም በተናጠል ከበሽታው ለመከላከል የሚያስችሉ ናቸውን? ምክንያት እያቀረባችሁ ተወያዩበት።

# ምንባብ አራት

## የንግግር ስርአትና ችሎታ

ዴሞስቴን በህጻንነቱ አባቱ ስለሞተበት ባለደራዎቹ ሆነው ያባቱን ገንዘብ የተረከቡት ሰዎች አባክነውት ነበርና÷ ለአቅመ አዳም ሲበቃ እነሱን ከሶ ያባቱን ሀብት ለማስመለስ ያስብ ነበር። ንግግር አዋቂ በመሆኑ ይመሰገን የነበረው ካሊስትራት የሚባለው ሰው ሲናገር ለመስማት÷ አስበው አንድ ቀን የዴሞስቴን አስተማሪዎች ወደ ሸንጎ ሲሄዱ ዴሞስቴን ከነሱ ጋር አብሮ እንዲሰማ ይዘውት ሄዱ።

ዴሞስቴን የዚህን ሰው ንግግር በመስማትና በሸንጎው ላይ በነበሩትም ሰዎች ዘንድ ምን ያህል እንደተደነቀ በማስተዋል ብርቱ ስሜት በመንፈሱ አድሮበት ልቡ ወደዚህ ጥበብ የተሳበው ከዚያን ቀን ጀምሮ ነው ብለው የሚናገሩ ሰዎች አሉ።

ዴሞስቴን በመጀመሪያ ከጉባኤ ላይ ቀርቦ በተናገረ ጊዜ ንግግር የማይችል ሆኖ ስለተገመተ ንግግሩን እያቋረጡበት ሁለት ጊዜ መለሱት። ይህም የሆነበት ምክንያት ድምጹ ደካማ÷ ምላሱ ኮልታፋ÷ ትንፋሹ አጭር ስለነበር ንግግሩ እየተሰባበረበት በሰሚዎቹ ዘንድ ሊደመጥ የማይገባው ሆኖ በመገኘቱ ነው።

የባለቅኔዎች÷ የፈላስፎችና የሊቃውንት÷ የደራሲያን አገር በመሆኗ ለማንኛውም ሰው ቢሆን በአቴና ህዝብ ዘንድ ቀርቦ ዴሞስቴን በነበረበት ዘመን በጉባኤ ፊት ለመናገር ተሰሚነትን ለማግኘት በዚሁም ደግሞ ለመመስገን በእውነቱ ቀላል ነገር እንዳልነበር መዘንጋት አይገባም።

ከዚህ በኋላ ዴሞስቴን ከሰው ተለይቶ እንደ ባህታዊ ብቻውን እየኖረ ንግግር የማሳመርን ጥበብ ይማር ጀመር። የሚንተባተበውን ምላሱን ለማፍታታት ሲል ባፉ ውስጥ ጠጠር እየጨመረ ብቻውን ሆኖ እንደ እብድ ሰው ከፍ ባለ ድምጽ በመናገር አንደበቱን ገራው። እንደዚሁም ደግሞ በጉባኤ ላይ ቀርቦ በሚናገርበት ሰአት ህዝብ ንግግሩን ለማቋረጥ የሚያደርግበትን የተቃዋሚነት ውካታ ለመልመድና ለማሸነፍ እንዲረዳው ሲል ከባህር ዳር ቆሞ ጮሆ በመናገር የባህሩን ውሃ ማዕበል ሲመታው ከሚያደርገው ጩኸት ጋር ንግግሩን ያወዳድር ነበር። በመሬት ውስጥ የሚኖርበትም ዋሻ አዘጋጅቶ ብዙ ወራት ሙሉ ከዚያ ሳይወጣ ሰው አሳቡን በመልካም ንግግር የሚገልጥበትን ዘዴ ሲሻ ቱሲዲድ የሚባለው ሊቅ የጻፈውን መጽሃፍ እየደጋገመ እስከ ስምንት ጊዜ ድረስ ይገለብጥ ነበር። ከተደበቀበትም ጉድጓድ ውስጥ ወጥቶ ህዝብ ወደሚገኝበት ቦታ የመሄድ አሳብ በመንፈሱ ውስጥ እንዳይገባ ለማድረግ ሲል የራሱን ጠጉር ግማሹን ተላጭቶ ግማሹን ትቶ ከሰው ዘንድ ሊቀርብ የማይችል አስቀያሚ መልክ ይዞ ኖረ።

ይህን በመሰለ አኳኋን ብቻውን እየኖረ ራሱን ለራሱ መምህር አድርጎ በማሰብ÷ በመመርመር÷ ቃሉን ከፍ አድርጎ ብቻውን በመናገር÷ በመጻፍ በመገልበጥም ስምንት አመት ሙሉ መንፈሱን እያበለጸገ አንደበቱን ካረመና ምላሱን ከሳለ በኋላ ዴሞስቴን እንደገና ጉባኤ ፊት ቀርቦ ተናገረ። በዚህ ጊዜ ግን የተሰበሰቡት ሰዎች ሁሉ ንግግሩን ሲሰሙ እጅግ አድርገው ተደነቁ። ዴሞስቴንም አስቦት ከነበረው አላማ ደረሰ።

/ከታላላቅ ሰዎች  የተወሰደ/።

### መልመጃ አንድ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት መልስ።

ሀ. ዴሞስቴን የተደነቀ ተናጋሪ ለመሆን የቻለበትን ስልቶች በቅደም ተከተል ዘርዝር።
ለ. ዴሞስቴን አስቦት የነበረውና በመጨረሻም የተሳካለትን ነገር ምንድነው?

ሐ. ዴሞስቴን ወደ ንግግር ጥበብ እንዲሳብ ተጽዕኖ ያሳደረበት የአቴና ፈላስፋና ተናጋሪ ማነው?
መ. ዴሞስቴን ግማሽ ጸጉሩን በመላጨትና ግማሹን በመተው እብድ የመሰለው ለምንድነው?
ሠ. ዴሞስቴን ከሰው ተለይቶ ራሱን በራሱ እንዲያስተምር ያነሳሳው ጊዜያዊ ችግር ምን ነበር?
ረ. የሌላ ሰው ጽሁፍን ደጋግሞ መገልበጥ ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን ይረዳልን? ለምን?

## መልመጃ ሁለት

1. ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት ተስማሚ ፍች ፈልግላቸው??

    ሀ. አባክነውት
    ለ. ሲያበቃ
    ሐ. ብለው የሚናገሩ
    መ. ማፍታታት
    ሠ. ሰአት
    ረ. በመንፈሱ ውስጥ እንዳይገባ
    ሰ. ባለደራዎች

2. ከሀ-ሰ ከተዘረዘሩት ቃላትና ሀረጋት መካከል ሁለት ፍች ያለውን ለይተህ አመልክት።

## መልመጃ ሦስት

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በራስህ አባባል አብራርተህ አቅርብ።

ሀ. አንቀጽ አራትና አምስት የሃሳብ ዝምድና አላቸውን?
ለ. አንተ አንዳንድ ነገሮችን በቅደም ተከተል ሰርተህ ያስመሰከርከው ችሎታ አለ? ዝርዝሩን ጽፈህ ለጓደኞችህ አንብብላቸው።
ሐ. የዚህ ምንባብ ጭብጥ አላማ ምን ይመስለሃል? ዘርዘር አድርገህ በጽሁፍ አቅርብ።

# ምንባብ አምስት

## ወጣትነት፥ ማህበራዊ ችግሮቹና የመፍትሄ ሃሳቦች

ከሀምሳ ሚሊዮን የኢትዮጵያ ህዝብ ሀምሳ በመቶው በወጣትነት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ነው:: ይህ ሁኔታ በአፍላ የወጣትነት እድሜ የሚገኘው የህብረተሰብ ክፍል ቁጥር እጅግ አሳሳቢ በሆነፍጥነት እየጨመረ በመሄድ ላይ መሆኑን ያመለክታል:: በሀገራችን ያለው የወጣቶች ብዛት ከማህበራዊ አገልግሎት አቅርቦት ጋር ሲነጻጸር በብዙ እጥፍ የሚበልጥ በመሆኑ ወጣቱ ህብረተሰብ ለበርካታ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ተጋልጦ ይገኛል:: ኋላ ቀር ባህል፥ የጾታና የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርትና አገልግሎት አለመስፋፋት ያሉትን ችግሮች በማባባስ በኩል የራሳቸውን አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ናቸው::

በተለይም በአሁኑ ወቅት የሚታየው ፈጣን ማህበራዊ ለውጥ፥ የከተሞች መስፋፋትና የቅርብ ቤተሰባዊ ትስስር መላላት አያሌ ወጣቶች የቤተሰባቸውን የቅርብ ቁጥጥር፥ ክትትልና ድጋፍ እንዲያጡ በማድረግ ለተለያዩ ማህበራዊና የጤና ችግሮች እንዲጋለጡ እያደረገ ይገኛል:: ምክንያተጠም ወጣቶች የህይወት ተሞክሮአቸውና ገጠመኞቻቸው አነስተኛ በመሆናቸው እድገትን ተከትለው የሚመጡ አያሌ ችግሮች ይገጥሟቸዋል:: ከእነዚህም ውስጥ በራሳቸው ጉዳይ ላይ በሳልና ተገቢ ውሳኔ መስጠት አለመቻልና ድርጊታቸው ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት አለመገንዘብ ይገኙበታል::

ስለሆነም ወጣቶች በሽግግር ዘመናቸው የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ተረድተው በቅድሚያ እንዲዘጋጁና ጤናማ ህይወት እንዲመሩ ተገቢውን እገዛና ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል:: ሊተኮርባቸው የሚገቡ ገንቢ መፍትሄዎች በጉርምስና ወቅት ስለሚታዩ አካላዊ፥ ስነባህርያዊና ማህበራዊ ለውጦች በማሳወቅ ወጣቶች ለቀጣዩ ህይወታቸው በቅድሚያ ዝግጅት እንዲያደርጉ መረጃ መስጠት፥ የቤተሰብ ምጣኔና የጾታ ትምህርት መሰረተ ሃሳቦችን ለወጣቶች በሰፊው ማሰራጨት እንዲሁም ወጣቶች ስሜታዊና ሃላፊነትን ያልተላበሰ የተቃራኒ ጾታዎች ግንኙነት ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ እንዲገነዘቡና ያልተፈለገ እርግዝናና የአባላዘር በሽታዎች እንዲከለከሉ ትምህርት መስጠት አስፈላጊ ነው::

በአጠቃላይ የምክር አገልግሎት ጠቃሚነት መታወቅ አለበት:: ምክክሩ ወጣቶች ይዘዋቸው በሚመጡት ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይት በማካሄድ ወጣቶች ስለራሳቸው በሚገባ እንዲገነዘቡ፥ የችግሮቻቸውን መንስኤ እንዲረዱና የራሳቸው መፍትሄና ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ ለማደፋፈር ያስችላል::

/ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥር 19, 1991 የተወሰደ/::

### መልመጃ አንድ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰለት መልስ::

ሀ. የቤተሰብ ቁጥርና ትስስር መላላት በወጣቶች ላይ ችግር የሚያመጣው በምን መንገድ ነው?
ለ. በምንባቡ መሰረት ከጤናና ማህበራዊ ችግሮች የበለጠ ወጣቶችን የሚጫነው የትኛው ነው?
ሐ. ወጣቶች በሽግግር ዘመናቸው በርካታ ችግሮች የሚያጋጥሟቸው ለምንድነው?
መ. በምንባቡ መሰረት የወጣቶችን ችግር ለመቅረፍ ምን ማድረግ ይገባል?
ሠ. የምክር አገልግሎትና መሰረታዊ ትምህርት ብቻ የወጣቱን የህብረተሰብ ክፍል ችግር ለማቃለል ይረዳል? እንዴት?

## መልመጃ ሁለት

2. የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች በምንባቡ መሰረት እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልስ::

ሀ. የወጣቱን የህብረተሰብ ክፍል ማህበራዊና የጤና ችግሮች ያበረከተው የትምህርት ማነስ ብቻ ነው::

ለ. የወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል በቁጥር እየጨመረ መሄድ ለስራ አጥነት መንስኤ ሊሆን ይችላል::

ሐ. ወጣቶችን ማስተማርና ተገቢ ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ ለሚጠብቃቸው ህይወት አስቀድመው እንዲዘጋጁ ይረዳል::

መ. ወጣቶችን የማስተማርና የማገዝ ሀላፊነት የሁሉም ህብረተሰብ ድርሻ መሆን ይኖርበታል::

ሠ. ለወጣቶች የሚደረገው እገዛና የሚሰጠው ትምህርት ስለራሳቸው የበለጠ እንዲያውቁና እንዲጠነቀቁ የሚያስችል መሆን ይኖርበታል::

## መልመጃ ሶስት

ስለወጣትነት የሚያብራራ ጽሁፍ ፈልገህ ካነበብህ በኋላ ያገኘኸውን ሃሳብ ጽፈህ ለጓደኞችህ አንብብላቸው::

## ለሙከራው ቡድን የተዘጋጁ መልመጃዎች

### ምንባብ አንድ

የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ቀጥሎ ካለው ምንባብ አንቀጾች የወጡ ናቸው:: አረፍተ ነገሮቹ የየአንቀጾቹ መግቢያ አረፍተ ነገሮች ናቸው:: አረፍተነገሮቹን በጥንቃቄ ካነበብህ በሁዋላ የየትኛው አንቀጽ አካል እንደሆኑ ለይተህ በተገቢው ቦታቸው አስገባ:: ምክንያትህን በማቅረብ ማብራሪያ ስጥ::

1. ለኔ እንደሚመስለኝ ከጥንታዊው ስርአተ ማህበር ያስተሳሰብ÷ ያስተያየትና ያሰራር ልማድ ከሁሉም ይልቅ ለዕውቀትና ለእድገት መሰናክል ሆኖ የኖረ÷ ሰው ሰርቶ÷ ጥሮ ግሮ ሀብታም ለመሆን ከሀብታም ወይም 'ከመሰረተ ጌታ' ተወልዶ 'ድሀ' መሆን ይመርጥ የነበረ መሆኑ ነው::

2. መቼመ ባንድ ማህበር ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ-ወደዱም ጠሉም የሚኖሩበትን ማህበር መንግስታዊ ህግ አክብረው÷ ባህላዊ ያስተሳሰብ÷ ያሰራርና የምነት ስራቱን ተከትለው መኖር አለባቸው::

3. በጥንቱ ልማድ÷ የልጆችን ጋብቻ የሚወስኑ ወላጆች እንጂ እንኳዋንስ ለውሳኔው ተካፋዮች ሊሆኑ ከመሀከላቸው ሳይተዋወቁ እንዲያውም አንድ ቀን እንኳ ሳይተያዩ የሚጋቡ ነበሩ::

### ጥንታዊ የጋብቻና የአኑዋኑዋር ስርአት

________________________________:: የማህበሩን መንግስታዊ ህግ የማያከብሩ "ህገ-ወጦች" ባህላዊ ስራቱን የማይከተሉ "ጋጠ-ወጦች" ተብለው በማህበሩ ውስጥ ደንበኛ ያባልነት ቦታ አይኖራቸውም:: ከማህበሩ ውጹአን ሆነው÷ ያካልና የመንፈስ ቅጣት ይደርስባቸዋል:: ይሁን እንጂ የማህበራቸውን ጨቋኝ ወይም ግፈኛ ስራት ተሸክሞ የማህበሩ ደንበኛ አባል ሆኖ ከመኖር ከሱ ነጻ ሆኖ አይደርስ ቅጣት ወይም ችግር ቢደርስባቸው የሚመርጡ÷ አንዳንድ ግለሰቦች በየጊዜውና በየቦታው ጠፍተው አያውቁም:: እንዲያ ያሉት ግለሰቦች ገና ሲፈጠሩ ግፍንና ጭቆናን እንዳይችሉ በግፍና በጭቆና ላይ እንዲሸፍቱ ሆነው የሚፈጠሩ ናቸው::

________________________________:: በሀብት ይልቁንም በዘር "ያክሉናል÷ ይመስሉናል" ታባብለው÷ ልጆቻቸውን የሚያጋቡ ወላጆች ነበሩ:: አንዳንድ ጊዜ በሁለት ቤተሰቦች መሀከል የነፍስ ግድያ ቂም የኖረ እንደሆነ እንዲያ ያለውን ቂም የመበቀል ሃሳብ ከመሀከላቸው እንዲጠፉ÷

በመሀከላቸው "የፈሰሰ ደም እንዲደርቅ" እኒያ ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ማጋባት የተለመደ ነበር:: የልጆች ጋብቻ በነፍስ ግድያ ለሚፈላለጉ ቤተሰቦች የሰላም ዋጋ ሆኖ የሚከፈል ነበር:: እንዲሁም ከጥንት ልማዶች ሌላው ክፉ ነገር በተለይ ሴቶች ልጆች ላቀመ ሄዋን ሳይደርሱ የሚዳሩ መሆናቸው ነበር::

______________________:: የጅ ሰራ ማወቅ "ይህ እጀ ሰሪ" አሰኝቶ ያሰድብ ነበር:: የጌታ ዘር ሆኖ በጥፍሩ ስራ የማይነካ ድሀ ግን ይታፈር ይከበር ነበር:: ታዲያ እንዲያ ያለው አስተሳሰብ÷ ያስተያየትና ያሰራር ባህልና ልማድ ለጠቅላላው ህዝብ የዕውቀትና የዕድገት መሰናክል ከሆኑ ሌላ በግለሰብ ደረጃም በባልና በምሽት÷ በወላጅና በልጅ÷ በጓደኞች መሀል ሊኖር ለሚገባው መልካም ግንኙነት ጠንቅ ነበር:: በመሆኑም ሰርተው በጎ አዳሪዎች የሆኑ ሰዎች እንኩዋ ከትውልድ አገራቸው ወደማይታወቁበት ሩቅ አገር የሄዱ እንደሆነ በሄዱበት አገር የክብር ቦታ አግኝተው ለመኖር÷ አገራቸው ሰርተው ስለመሰረቱት መልካም ኑሮ ከማውራት ይልቅ ያልሆኑትን ዋሽተው 'የሰመረተ ጌታ' ልጆች ቢያንስ ቢያንስ ወገኖች መሆናቸውን ማውራት ይወዳሉ:: ታዲያ ውሎ አድሮ ውሸታቸው ሲገለጽባቸው በነሱ ላይ እፍረትን÷ ከሌሎች ትዝብትን ያስከትልና በመጨረሻ የሚያሳዝን ሁኔታ ይደርሳል:: /ሀዲስ አለማየሁ÷ የልምዣት ከገጽ 6-8/::

## መልመጃዎች

1. የምንባቡ ይዘት ከጥንቱ የአኑዋኑዋር ልማድና ስርአት ጋር የተዛመደ ነው:: ታዲያ ከሚከተሉት አረፍተነገሮች መካከል የምንባቡን ፍሬ ሃሳብ ሊገልጽ የሚችለው የትኛው ይመስለሀል?

    ሀ. የጥንቱ የአኑዋኑዋር ልማድ÷ የአስተሳሰብና የአሰራር ስርአት ለማህበራዊ ግንኙነት÷ ለምርታማነትና ለባህል መዳበር ጉልህ አስተዋጽኦ ነበረው::
    ለ. የጥንቱ የጋብቻና የአኑዋኑዋር ዘዴ የሴቶችን የትዳር ጓደኛ የመምረጥና የመውደድ ነጻነት ይገድብ ነበር::
    ሐ. የዘር÷ የሀብትና የጋብቻ ስርአት በመፈቃቀድና በመዋደድ ላይ የተመሰረተ መሆን እንደሚገባው አይታመን ነበር::
    መ. በጥንቱ የጋብቻና የአኑዋኑዋር ዘይቤ መሰረት ከሴቶች ይልቅ ይጨቆኑ የነበሩት ወንዶችና መሰረተ ጌታ ያልሆኑት ብቻ ነበሩ::
    ሠ. ሀ ና መ    ረ. ሐ ና መ    ሰ. ለ ና ሐ

2. የጥንቱን የአስተሳሰብ÷ የአኑዋኑዋርና በአጠቃላይ የአሰራር ልማድ የሚቃረኑ ግለሰቦች የስርአቱ ተጻራሪዎች ናቸው:: እንደ ምንባቡ አቀራረብ እነዚህ ግለሰቦች ቁጥራቸው ውሱን ነው:: በመሆኑም ስርአቱን ለመለወጥ የሚያደርጉት ትግል በአጭር ጊዜ ውስጥ ውጤት አያመጣም:: ታዲያ ምን ማድረግ ይገባቸዋል? ተከታይ ለማብዛት መታገል ወይስ ራስን ከማህበረሰቡ ስርአት ማግለል?

3. የምንባቡ አቅራቢ ስራን መናቅ÷ በሰው ዘር መበላለጥ÷ አላቻ ጋብቻና ያለእድሜ ጋብቻ ለማህበረሰቡ አጠቃላይ እድገት እንቅፋት መሆናቸውን ይገልጻል:: እነዚህ ልማዶች በአሁኑ ጊዜ ሙሉ በሙሉ ተወግደዋል ለማለት ይቻላል? ማስረጃ በማቅረብ አብራራ::

4. በመጀመሪያውና በሁለተኛው አንቀጾች ውስጥ በተገለጹት የጋብቻ ሃሳቦች ትስማማለህ?

5. የምንባቡ ደራሲ የቀድሞውን ጋብቻ ልማድ አስከፊነት የገለጸበትን አረፍተ ነገር ለይተህ በጽሁፍ አቅርብ::

## II. ቃሎችና ሀረጎች

1. በምንባቡ ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃሎችና ሀረጎች አገባባዊ ፍች ከሰጠህ በሁዋላ በሌሎች ተመሳሳይ ቃሎች ተካቸው::
2. "ጋጠ-ወጦች" የሚለው አባባል ለገባበት ቦታ ትክክለኛ አገባብ ይመስልሀል? በጽሁፍ መልስ::

## III. ክፍል ሶስት

1. የምንባቡን አጠቃላይ ሃሳብ አብራርተህ በአንድ አንቀጽ ጻፍ።
2. አሁን ድረስ በአንዳንድ አካባቢዎች በምንባቡ የቀረበውን የጋብቻ ስርአት መቀጠል የሚደግፉ አሉ። እነዚህ ሰዎች አስተያየታቸውን እንዲለውጡ ምን ማድረግ እንደሚያስፈልግ ከጓደኞችህ ጋር ተወያዩበት።

### ምንባብ ሁለት

ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ከማንበብህ በፊት የሚቀጥሉትን ጥያቄዎች በፅሁፍ መልስ። መልስህን ከሌሎች ተማሪዎች መልሶች አነጻጽር።

1. ሰብአዊ እውቀትና የሌሎች እንስሳት እውቀት የሚለያይበት በምንድነው? የልዩነቱስ መንስኤ ምን ይመስልሀል?

2. ከእንስሳት ሁሉ ቋንቋን የሚጠቀሙት ሰዎች ብቻ ናቸውን? ሌሎቹስ እንስሳት እንዴት ሊግባቡ ይችላሉ?

3. ከሰው ልጆች በስተቀር ቋንቋን ለመማር ወይም ለመናገር የሚሞክሩ እንስሳት አጋጥመውህ/ሽ/ ያውቃሉ? አጋጥሞህ/ሽ/ ከሆነ እንዴት ይሞክራሉ?

4. ቋንቋን ማወቅና መጠቀም መቻል ምን ማለት ነው?
5. ሰውን ከሌሎች እንስሳት የሚለየው ቋንቋ ነውን?

### የቋንቋ ተግባራት

የሰውን ልጅ ከሌሎች እንስሳት ከሚለዩትና ዝርያውም እንዳይጠፉ ካደረጉት ዋነኛው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሲሆን፥ በዚሁ ሂደት የተገኙት የቋንቋ ችሎታ በውጤቱ ሂደት ምክንያት ያገኛቸው አእምሮአዊና አካላዊ ዕድገቶችና ለውጦች ከፍተኛ ሚና አላቸው።

ቋንቋ ግለሰቡን ከህብረተሰቡ ጋር ያወሳስባል። ይህም ተግባር ውስበት ወይም ውስበታዊ ሊባል ይችላል። አንድ ህፃን ያደገበትን ህብረተሰብ ቋንቋ መናገር ሲችል የህብረተሰቡ ሙሉ አባል ይሆናል። በቋንቋ ችሎታውም አማካይነት ከህብረተሰቡ ጋር ይዋሃዳል፣ የረጅም ዘመን የእውቀት ክምችት ተካፋይ ይሆናል። በበኩሉም በቋንቋ አማካይነት ድርሻውን ያበረክታል።

የአንድ ሰው የቋንቋ ችሎታ የሚለካው በአራቱ የቋንቋ ክህሎት ማለት በማዳመጥ፥ በመናገር፥ በማንበብና በመጻፍ እንዲሁም የቋንቋውን ስነልሳንና ስነጽሁፍ በማወቅና በተግባር ላይ በማዋል በሚያሳየው ቅልጥፍና ነው። በጥራት አዳምጦ የተነገረውን ከጨበጠ፥ ሀሳቡን በጥሩ ሁኔታ ከገለጸ፥ አስተካክሎ ካነበበና ከጻፈ የቋንቋ ችሎታው ከፍተኛ ነው ይባላል። ይሁን እንጂ ከዚህ ያነሰ ችሎታ ያለውም ሰው ቢሆን ከቋንቋ የበለጠ ለሀሳቡ መግለጫና ማስተላለፊያ ሊሆነው የሚችል ቀላል መንገድ አይኖርም። ለዚህም ነው የሰው ልጅ ሀሳቡን በቀለጠፈ፥ በጠራና በቀላል መንገድ መግለጽ የሚችለው በቋንቋ ብቻ ነው የሚባለው።

ቋንቋ የግለሰብን ማንነት ማሳወቂያ ነው። ስሊሎች ከተወሰኑ ቃሎች የተለያዩ የፈጠራ ስእሎችን እንደሚሰሩ ሁሉ ግለሰቡ የራሱን ብቸኛ መለያ ባህርይ ውስጣዊ ስሜቱን፥ አስተሳሰቡን ወዘተ. የሚገልጸው በእዚሁ መሳሪያ ነው። የህብረተሰቡ አባል እንደመሆኑ መጠን ራሱን ለማሳወቅና ለመግለጽ የሚገለገልበት መሳሪያ ህብረተሰቡ ከሚገለገልበት ከተለየ ግን አለመግባባት ወይም አለመጣጣም ይፈጠራል።

ቋንቋ የግለሰቡን የአስተሳሰብ ሂደት መቃኛና መተንተኛ መሳሪያ ነው። ይህ መሳሪያ ግለሰቡ አስተሳሰቡን በቅደም ተከተልና በስርአት ለመደርደር ያስችለዋል። በተጨማሪም የህብረተሰቡን የአስተሳሰብ ሂደትና ልምድ የራሱ ለማድረግ ያስችለዋል።

ቋንቋ የመገናኛ ወይም የመግባቢያ መሳርያ ነው:: ይኸውም ግለሰብን፥ ግለሰብን ከህብረተሰብ፥ ህብረተሰብን እንደ ድልድይ ሆኖ ያገለግላል:: አንድ ግለሰብ ስለሌላው ግለሰብ፥ አንድ ህብረተሰብ ስለሌላው ህብረተሰብ የሚያውቀው፥ ከሌላው የሚማረው፥ ሌላውንም የሚያስተምረው፥ የሃሳብም ሆነ ሌላ አይነት እርዳታ የሚቀበለውና በበኩሉም የሚሰጠው በቋንቋ ነው::

ቋንቋ የሰው ልጅ ያካበተውን ልምድ፥ እውቀት፥ ወዘተ. ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚያስተላልፍ፥ አዳዲስ የሳይንስ ግኝቶችንና የፈጠራ ስራዎችን መቅሰም የሚያስችል መሳሪያ ነው:: በተለይ ትምህርትን ለመከታተል ተማሪው ከመምህሩ ወይም መምህሩ ከተማሪው እንዲሁም ተማሪዎች ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ለሚያደርጉዋቸው ግንኙነትና ለሚፈጥሩዋቸው ዝምድናዎች ከፍተኛ ድርሻ አለው:: /ከመማርያ መጽሀፍ ተሻሽሎ የተወሰደ/::

## መልመጃዎች

I. የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንብበህ በጽሁፍ መልስ::

1. በአንደኛውና በመደምደሚያው አንቀጾች የተገለጸውን ሃሳብ አንድነትና ልዩነት ዘርዝር::

2ሀ. የምንባቡ ደራሲ የቋንቋንና የስእል ጥበብን ለማወዳደር የሞከረው እንዴት ነው?
 ለ. የአንድ ተናጋሪ የቃላት ምርጫ፥ የአረፍተነገር አመሰራረትና የአንድ ሰአሊ የቀለማት አጠቃቀም በምንባቡ ውስጥ መግለጽ ለደራሲው አላማ ያለው ጠቀሜታ ምን ያህል ነው? ለምን?

3. "አስተካክሎ ማንበብ" የሚለው አገላለጽ ለቋንቋ ችሎታ ትክክለኛ መግለጫ ይመስለሀል? ለምን?

4. ሶስተኛው አንቀጽ ከተቀሩት አንቀጾች ጋር ያለው ዝምድና ጠንካራ ነውን?

5. በምንባቡ መሰረት አንድ ሰው የማህበረሰቡ አባል የሚሆነው የማህበረሰቡን ቋንቋ በሚገባ ለመጠቀም ሲችል ነው:: ይህንን አባባል ምን ማለት እንደሆነ በአንድ አንቀጽ አብራራ::

6. "በተጨማሪም የህብረተሰቡን የአስተሳሰብ ሂደትና ልምድ የራሱ ለማድረግ ያስችለዋል" የሚለው አረፍተ ነገር ሃሳብ ምን ማለት እንደሆነ በራስህ አባባል በሶስት አረፍተ ነገሮች ግለጽ::

II. በምንባቡ ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃሎችና ሀረጎች በሌሎች ተመሳሳይ ቃሎች ተካቸው:: የምትተካቸው ቃሎች የምንባቡን ሃሳብ የሚለውጡ መሆን የለባቸውም::

II. የሚከተሉትን አረፍተነገሮች ትክክል ከሆነ ስለትክክለኛነታቸው፥ ስህተት ከሆኑ ደግሞ ስለስህተታቸው ከምንባቡ ምክንያት ስጥ::

1. ቋንቋ ማህበራዊ ክስተት ነው::
2. የቋንቋ ችሎታን ለማዳበር በማህበረሰቡ ውስጥ መወለድ ብቻ በቂ ነው::
3. አንድ ሰው ቋንቋን ይችላል የሚባለው በቋንቋው ሁለገብ የአጠቃቀም ችሎታ አዳብሮ ሲገኝ ነው::
4. ቋንቋ ራስን ማሳወቂያ ብቻ ሳይሆን ያለፈውን ለማስታወሻና የወደፊቱን ለመገመቻነት፥ ሊያገለግል ይችላል::

## IV. ክፍል አራት

1. በምንባቡ ውስጥ የቋንቋ ተግባራት ምን ምን እንደሆኑ ተዘርዝሮአል:: ነጥቦቹን በማጠቃለል ቋንቋ የመግባቢያ መሳርያ ነው ለማለት አይቻልም? ለምን?
2. የምንባቡን ፍሬ ሃሳብ አሳጥረህ በአንድ አንቀጽ ጻፍ::
3. በምንባቡ ውስጥ ተቃራኒ የሆኑ ሃሳቦች ቀርበዋል:: የትኞቹ እንደሆኑ ለይተህ አስቀምጥ::
4. ምንባቡን ከማንበብህ በፊት በግል ስለይዘቱ የገለጽከው ሃሳብና ከምንባቡ ያገኘኸውን አነጻጽር::

## ምንባብ ሦስት

የሚከተለውን ምንባብ ከማነበብህ በፊት የቀረቡትን ጥያቄዎች መልስ:: የምታቀርባቸውን መልሶች ከጓደኞችህ መልሶችና ከምንባቡ ይዘት ጋር ለማስተያየት ሞክር:: ከማንበብህ በፊት የመለስከው መልስና ካነበብህ በሁዋላ ያገኘኸውን የሃሳብ ልዩነት በአምስት አረፍተ ነገሮች በጽሁፍ አስረዳ::

1. የኤድስ በሽታን ስርጭት ለመግታትና ለመከላከል ምን መደረግ ይኖርበታል?
2. ህብረተሰቡ ስለኤድስ በሽታ ምንነትና የመተላለፍያ መንገዶቹን ተገንዝቦ እራሱን እንዲከላከል ማስተማር የማን ሃላፊነት ነው?
3. የኤድስ አደጋ የሚከፋው በየትኛው የእድሜ ክልል የሚገኘውን የህብረተሰብ ክፍል ነው?
4. ኤድስ ማህበራዊና ኢኮኖሚያሚ ቀውሶችን የሚያስከትለው እንዴት ነው?

## ኤድስና የመከላከል ዘመቻ

በየአመቱ "የኤድስ ቀን" እየተባለ በአለም ደረጃ የሚከበር አለም አቀፍ በአል አለ:: "የለውጥ ሃይል ከሆነው ወጣት ጋር አለም በኤድስ ላይ ይነሳ" በሚል መፈክር ስር ነው የዘንድሮው በሀገራችን የተከበረው:: ከዚህ ቀን በኋላ ህብረተሰቡ የባህርይ ለውጥ እንዲያመጣ እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል፤ እየተደረገም ነው:: የኤድስ መቅሰፍት በአለማችን ላይም ሆነ በሀገራችን እያደረሰ ካለው ጉዳት አንፃር እስከ አሁን የተደረገው የማሳወቅና የመከላከል እንቅስቃሴ በጣም አነስተኛና ያልተቀናጀ ቢሆንም አሁን እየታየ ያለው ጅማሮ ተስፋ ሰጪ ነውና ሊበረታታ ይገባዋል::

ህብረተሰባችን በኤድስ ላይ ያለውን አመለካከት ለውጦ የባህርይ ለውጥ እንዲያመጣ የመገናኛ ብዙሀን ከማንም በላይ ወሳኝ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ:: በዚህ በኩል ሬዲዮ ፋና ዲ.ኬ.ቲ ከተባለ ድርጅት ጋር በመተባበር ሰፊ የአየር ጊዜ በመስጠት በአራት ቋንቋዎች ያስተላለፋቸው ትምህርታዊ ቅስቀሳዎች በአርአያነት ሊጠቀሱ የሚገባቸው ናቸው::

የኤድስ ደዌ በምድራችን ላይ ከተከሰተ ወዲህ ወረርሺኙ ከመቼውም ጊዜ በላቀ ሁኔታ እየተዛመተ በመምጣት ላይ ነው:: በአለማችን በበሽታው የተጠቁ ወገኖች ብዛት ከ47 ሚሊዮን በላይ የደረሰ ሲሆን ከነዚህ መካከል 14 ሚሊዮን የሚሆኑት ሞተዋል:: ባለፈው አንድ አመት ብቻ 5.8 ሚሊዮን ህዝብ በበሽታው የተለከፈ ሲሆን የሟቾቹ ቁጥር 2.5 ሚሊዮን ደር ሷል::

የሀገራችን ሁኔታ ስናይ ኤድስ ከተከሰተ በአጭር ጊዜ ውስጥ የህሙማኑና የቫይረሱ ተሸካሚዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚያስደነግጥ ፍጥነት እየጨመረ ነው:: በዚህም መሰረት እስከ መስከረም 30 ቀን 1991 ዓ.ም. ድረስ 69,931 የኤድስ ህሙማን መኖራቸው ከየጤና ድርጅቶቹ ከቀረቡት ሪፖርቶች የተረጋገጠ ሲሆን ወደ ጤና ድርጅቶቹ ለመምጣት ሳይችሉ የቀሩትን ህሙማን እግምት ውስጥ ስናስገባ በሀገራችን የኤድስ ህሙማን ቁጥር ከ400,000 በላይ ሊደርስ እንደሚችል ይገመታል:: በዚህ መሰረት በሀገራችን አቅመ አዳምና ሄዋን ከደረሱ ማለትም ከ15-19 የእድሜ ክልል ውስጥ ከሚገኙ ወጣቶችና ጎልማሶች መካከል 7.4 በመቶ የሚሆኑት በቫይረሱ ተለክፈዋል:: በአንዳንድ ከተሞችና አካባቢዎችም የተደረጉ ጥናቶች እንደጠቁሙት ከ12-18 በመቶ የሚሆኑ ነፍሰ ጡር ሴቶች የቫይረሱ ተሻካሚ ሆነው ተገኝተዋል::

በሀገራችን ለኤድስ እንደ ሰደድ እሳት መዛመት ባጠቃላይ ህበረተሰቡ የአመለካከትና የባህርይ ለውጥ ሊያመጣ አለመቻሉ እንደ አቢይ ምክንያት የሚጠቀስ ሲሆን ለዚህም ባህላዊ÷ ሃይማኖታዊና ኢኮኖሚያዊ ተጽእኖዎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉ መሆኑ ይታመናል:: ዛሬ በሀገራችን በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖቻችን ሲረግፉ በአይናችን እያየን በበሽታው ላይ የባህርይ ለውጥ አለማምጣትና በምስጢር ይዞ እንደሌለ ለመቁጠር መሞከሩ ለከፍተኛ ጥፋትና እልቂት እየዳረገን መሆኑ በሁላችንም ዘንድ ግንዛቤው ሊኖረን ይገባል::

ኤድስ በግለሰቦችም ሆነ በማህበረሰቡ ላይ ከፍተኛ ማህበራዊ÷ ኢኮኖሚያዊና ስነልቡናዊ ተጽእኖ ያሳድራል:: በቤተሰብ ላይ የሚያስከትላቸው ችግሮች እጥፍ ድርብ ናቸው:: ኤድስ በይበልጥ የሚያጠቃው በአፍላ እድሜ ውስጥ ያሉ ጎልማሶችንና አምራች ሃይሎችን በመሆኑ ሀገራችን በተያያዘችው መጠነ ሰፊ የልማት እንቅስቃሴ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ በቀላሉ የሚገመት አይደለም:: እየተስፋፋ የመጣውን የኤድስ ወረርሽኝ ለቋቋም ደግሞ ጥረት ያስፈልጋል::

ጥረቱም የሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች መሆን አለበት:: በህብረተሰቡ ዘንድ የሚጠበቀው የባህሪ ለውጥ እንዲመጣ ደግሞ የመገናኛ ብዙሀን ግንባር ቀደም ሚና መጫወት ቢኖርባቸውም ከነሱ በተጨማሪ ወላጆች÷ ትምህርት ቤቶች÷ የህይማኖት ተቋማት÷ በርካታ የህብረተሰብ የህብረት ስራ ማህበራትና የሙያ ማህበራት ባንድነት ተቀናጅተው ተከታታይነት ያለው ቅሰቀሳና ትምህርት መስጠት ይኖርባቸዋል::

/ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥር 6,1991 ርእሰ አንቀጽ ተሻሽሎ የተወሰደ/::

## መልመጃዎች

### I. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማስረጃዎች አስደግፈህ በጽሁፍ መልስ::

1. የዚህ ምንባብ አቅራቢ ጽሁፉን ሲያቀርብ አላማው ምን ይመስለሀል?
2. ኤድስን ለመከላከል በአመት አንድ ቀን በአል ማክበር ብቻ በቂ ነውን? አብራራ::
3. የመጀርያው አንቀጽ ውስጥ "የለውጥ ሀይል ከሆነው ወጣት ጋር አለም በኤድስ ላይ ይነሳ" ይልና በመጨረሻም ደግሞ ህበረተሰቡ በበለጠ መተባበር እንዳለበት ያሳስባል:: ሁለቱ አባባሎች አይቃረቡም? ምክንያትህን ከምንባቡና ከራስህ ሃሳብ አዛምደህ አስረዳ::
4. ኤድስን ለመከላከል ህበረተሰቡ በሙሉ ከወጣቱ ጋር የሚነሳው ለምንድነው? ለወጣቱ ክፍል ልዩ ትኩረት መስጠቱስ ለምን አስፈለገ?
5. ስለ ኤድስ÷ ከህብረተሰባችን አመለካከት መለወጥ ያለበት የቱ ነው? መለወጥ ካለበትስ በምን በምን ምክንያቶች እንደሆነ ጠቁም::
6. ለጸረ-ኤድስ ቅስቀሳና ትምህርት የብዙሀን መገናኛ÷ ትምህርት ቤቶች÷ የሃይማኖት ተቋማት÷ የማምረቻ ድርጅቶችና የሰራተኛ ማህበራት የተመረጡት ለምንድነው?
7. በአለም ላይ በኤድስ ከተጠቁተና የቫይረሱ ተሸካሚ ከሆኑት ሰዎች የትኞቹ የበለጠ አስጊ ይሆናሉ?

### II. ቃሎችና ሀረጎች

1. በምንባቡ ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃሎችና ሀረጎች አገባባዊ ፍች ተናገር::
2. የምንባቡ ደራሲ የኤድስን አስከፊነት ለመግለጽ የተጠቀመባቸውን ሶስት ቃሎች ፈልግና ይዘታቸውን አስረዳ::
3. በሁለተኛው አንቀጽ ውስጥ "... ለውጦ የባህርይ ለውጥ እንዲያመጣ" ስለሚለው ሀረግ ትክክለኛነት ምን አስተያየት አለህ?

### III. ክፍል ሶስት

ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መካከል ትክክል ያልሆኑትን በማስተካከል ትክክል የሆኑትን ደግሞ ስለትክክለኛነታቸው በማስረጃ አረጋግጥ::

1. የኤድስን ስርጭትና ወረርሽኝ ለመግታት የሚያስፈልገው ህብረተሰቡን ማስተማርና ስለበሽታው ተረድቶ አመለካከቱን እንዲለውጥ ማድረግ ነው::
2. ኤድስ ማህበራዊ÷ ኢኮኖሚዊና ስነልቡናዊ ችግሮችን ቢያስከትልም መከላከል ስለሚቻል ብዙም አያሰጋም::
3. በሀገራችን ለኤድስ መስፋፋት በዋነኛነት የሚጠቀሰው የህብረተሰቡ የንቃተ ህሊና በሚፈለገው መጠን ከፍ ብሎ አለመገኘት ነው::
4. በአሁኑ ጊዜ በኤድስ ወረርሽኝ እየተጠቃ ያለው የሀገራችን የህብረተሰብ ክፍል ሙሉ በሙሉ በከተማው አካባቢ ያለው ብቻ ነው::

### IV. ክፍል አራት

1. የምንባቡን ሃሳብ አሳጥረህ በአንድ አንቀጽ ጻፍ::
2. ደራሲው በኢትዮጵያ ለኤድስ መዛመት የአመለካከት ለውጥ አለመኖር ዋነኛው እንደሆነ ያቀርባል:: በምክንያቱ ትክክለኛነት ትስማማለህ?

## V. ክፍል አምስት

ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተለውን ሰንጠረዥ አሟላ::

| ስለ ኤድስ ሲነገር ወይ ተጽፎ ያነበብኸው | ስለ ኤድስ የማታውቀውና ከምንባቡ ውስጥ የተገለጸው ዋና ሃሳብ |
|---|---|
| 1<br>2<br>3<br>4<br>5 | 1<br>2<br>3<br>4<br>5 |

### ምንባብ አራት

### የንግግር ስርአትና ችሎታ

የሚከተለውን ምንባብ ከማንበብህ በፊት ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልስ:: መልስህን ከምንባቡ ፍሬ ሃሳብ ጋር አስተያይተህ ከጓደኞችህ ጋር ተወያዩበት:: ምን ያህሉ መልስህ ከሌሎቹ ጓደኞችህና ከምንባቡ ፍሬ ሃሳብ ይመሳሰላል? ምን ያህሉስ አይመሳሰልም?

1. አንድ ሰው ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን ምን ምን ነገሮች ያስፈልጉታል?
2. አንድ ተናጋሪ እንደበተ ርቱእ ተናጋሪ ነው የሚባለው ምን ማድረግ ሲችል ይመስልሀል?
3. ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን የሚያስፈልገውን ችሎታ ለመካን መታደል እንጂ መማር አያስፈልግም በሚለው አስተያየት ትስማማለህ?
4. የመጀመርያውን አንቀጽ አንብበህ ባለታሪኩ የፈጸመውን ተግባርና አስተያየትህን አቅርብ::

### ምንባብ

ዴሞስቴን በህጻንነቱ አበቱ ስለሞተበት ባለደራዎች ሆነው ያባቱን ገንዘብ የተረከቡት ሰዎች አባክነውት ነበርና÷ ለአቅመ አዳም ሲበቃ እነሱን ከሶ ያባቱን ሀብት ለማስመለስ ያስብ ነበር:: ንግግር አዋቂ በመሆኑ ይመሰገን የነበረው ካሊስትራት የሚባለው ሰው ሲናገር ለመስማት አስበው አንድ ቀን የዴሞስቴን አስተማሪዎች ወደ ሸንጎ ሲሄዱ ዴሞስቴን ከነሱ ጋር አብሮ እንዲሰማ ይዘውት ሄዱ:

ዴሞስቴን የዚህን ሰው ንግግር በመስማትና በሸንጎው ላይ በነበሩትም ሰዎች ዘንድ ምን ያህል እንደተደነቀ በማስተዋል ብርቱ ስሜት በመንፈሱ አድሮበት ልቡ ወደዚህ ጥበብ የተሳበው ከዚያን ቀን ጀምሮ ነው ብለው የሚናገሩ ሰዎች አሉ::

ዴሞስቴን በመጀመርያ ከጉባኤ ላይ ቀርቦ በተናገረ ጊዜ ንግግር የማይችል ሆኖ ስለተገመተ ንግግሩን እያቋረጡት ሁለት ጊዜ መለሱት:: ይህም የሆነበት ምክንያት ድምጹ ደካማ÷ ምላሱ ኮልታፋ÷ ትንፋሹ አጭር ስለነበረ ንግግሩ እየተሰባበረበት በሰሚዎቹ ዘንድ ሊደመጥ የማይገባው ሆኖ በመገኘቱ ነው::

የባለቅኔዎች÷ የፈላስፎችና የሊቃውንት÷ የደራሲያን÷ አገር በመሆኗ ለማንኛውም ሰው ቢሆን በአቴና ህዝብ ዘንድ ቀርቦ ዴሞስቴን በነበረበት ዘመን በጉባኤ ፊት ለመናገርና ተሰሚነትን ለማግኘት በዚሁም ደግሞ ለመመስገን በእውነቱ ቀላል ነገር እንዳልነበር መዘንጋት አይገባም::

ከዚህ በሁዋላ ዴሞስቴን ከሰው ተለይቶ እንደ ባህታዊ ብቻውን እየኖረ ንግግር የማሳመርን ጥበብ ይማር ጀመር:: የሚንተባተበውን ምላሱን ለማፍታታት ሲል ባፉ ውስጥ ጠጠር እየጨመረ ብቻውን ሆኖ እንደ እብድ ሰው ከፍ ባለ ድምጽ በመናገር አንደበቱን ገራው:: እንደዚሁም

ደግሞ በጉባኤ ላይ ቀርቦ በሚናገርበት ሰአት ህዝብ ንግግሩን ለማቋረጥ የሚያደርግበትን የተቃዋሚነት ውካታ ለመልመድና ለማሸነፍ እንዲረዳው ሲል ከባህር ዳር ቆሞ ጮሆ በመናገር የባህሩን ውሃ ማዕበል ሲመታው ከሚያደርገው ጩኸት ጋር ንግግሩን ያወዳድር ነበር። በመሬት ውስጥ የሚኖርበት ዋሻ አዘጋጅቶ ብዙ ወራት ሙሉ ከዚያ ሳይወጣ ሰው አሳቡን በመልካም ንግግር የሚገልጥበትን ዘዴ ሲሻ ቱሲዲድ የሚባለው ሊቅ የጻፈውን እየደጋገመ እስከ ስምንት ጊዜ ድረስ ይገለብጥ ነበር። ከተደበቀበትም ጉድጓድ ውስጥ ወጥቶ ህዝብ ወደሚገኝበት ቦታ የመሄዱ አሳብ በመንፈሱ ውስጥ እንዳይገባ ለማድረግ ሲል የራሱን ጠጉር ግማሹን ተላጭቶ ግማሹን ትቶ ከሰው ዘንድ ሊቀርብ የማይችል አስቀያሚ መልክ ይዞ ኖረ።

ይህን በመሰለ አኳኋን ብቻውን እየኖረ ራሱን ለራሱ መምህር አድርጎ በማሰብ÷ በመመርመር÷ ቃሉን ከፍ አድርጎ ብቻውን በመናገር÷ በመጻፍና በመገልበጥም ስምንት አመት ሙሉ መንፈሱን እያበለጸገ አንደበቱን ካረመና ምላሱን ከሳለ በኋላ ዴሞስቴን እንደገና ጉባኤ ፊት ቀርቦ ተናገረ። በዚህ ጊዜ ግን የተሰበሰቡት ሰዎች ሁሉ ንግግሩን ሲሰሙ እጅግ አድርገው ተደነቁ÷ ዴሞስቴን አስቦት ከነበረው አላማ ደረሰ።

/ከበደ ሚካኤል ታላላቅ ሰዎች። 1956 ከገጽ 45-46 ለማስተማርያ እንዲሆን ተሻሽሎ የተወሰደ/።

## መልመጃዎች

### I. ቃሎችና ሀረጎች

1. በምንባቡ ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃሎችና ሀረጎች አውጥተህ በተመሳሳይ ቃሎችና ሀረጎች ተካቸው።
2. የዴሞስቴንን ጥሩ ተናጋሪነት ለመግለጽ ደራሲው የተጠቀመባቸው አባባሎች የትኞቹ ናቸው? ከአገባባቸው አንጻር ሲታዩ የደራሲው አላማ አሳክተዋል? ለምን?

### II. የምንባቡን ፍሬ ሃሳብ መለየት

1. ዴሞስቴን የተደነቀ ተናጋሪ ለመሆን የቻለበት ስልት በቅደም ተከተል ዘርዝር። የትኞቹ ጥሩ ስልቶች ናቸው ብለህ ታምናለህ? የትኞቹስ አይደሉም? ለምን?
2. ከሚከተሉት ስለዴሞስቴን ትክክለኛ ያልሆነውን አረፍተ ነገር ለይተህ ለምን ትክክል እንዳልሆነ በጽሁፍ አመልክት።

ሀ. ዴሞስቴን አንደበቱን በማስላት ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን የፈለገው በካሊስትራት ችሎታ ስለሚቀና ነው።

ለ. ዴሞስቴን የንግግር ጥበብ በራሱ ለራሱ ያስተማረው ሌሎችን በመስማት እና መጻህፍት በማንበብ ነው።

ሐ. ዴሞስቴን የንግግር ጥበብን ለመማር የፈለገው የአባቱን ሀብት ያባከኑትን ሰዎች ለመበቀል ሲል ብቻ ነው።

መ. በአገሩ በነበሩት ሊቃውንትና ፈላስፎች እኩል በጉባኤ ፊት ለመናገር የንግግር ችሎታ አስፈላጊ ስለነበር ዴሞስቴን ይህንኑ ጥበብ ለመካን ወሰነ።

3. ዴሞስቴን አስቦት የነበረውና በጨረሻም የተሳካለት ህልሙ÷
   - ሀ. በሸንጎ ፊት ቀርቦ በክርክር የመርታት÷
   - ለ. ጥሩ ተናጋሪና ተደማጭ የመሆን÷
   - ሐ. የውርስ ንብረቱን የቀሙትን ባላደራዎች የመርታት÷
   - መ. ካሊስታርትን የመሆን።
4. ዴሞስቴን የቱሲዲድን መጽሀፍ ካነበበና ደጋግሞ ካጠናው በሁዋላ ችሎታውን ማሻሻሉ በምንባቡ ተጠቁሞአል። በሌላ በኩል ደግሞ ራሱ ለራሱ መምህር ሆኖ አላማውን አሳካ ይላል። ሁለቱ አስተያየቶች÷
   - ሀ. ፍጹም ተመሳሳይና የሚጣጣሙ ናቸው÷
   - ለ. ፍጹም ተቃራኒና የማይቀራረቡ ናቸው÷
   - ሐ. ግልጽ ፍንጭ የላቸውም።

5. እንደምንባቡ አቀራረብ ማንኛውም ሰው ንግግርን ለመማር በተከታታይ ልምምድ ማድረግ ያስፈልገዋል:: ልምድ አስፈላጊ ከሆነ ደግሞ በምንባቡ ውስጥ የቀረቡት የመለማመጃ መንገዶች ትክክለኛ ናቸው::

ሀ. እውነት ለ. ሀሰት ሐ. ለመወሰን ያስቸግራል::

ክፍል ሶስት የሃሳብ አደረጃጀት የሚመለከቱ ጥያቄዎች

የሚከተሉት ጥያቄዎች ከምንባቡ አጻጻፍና መልእክት ቅደም ተከተል ጋር የተዛመዱ ናቸው:: ምንባቡን በጥንቃቄ ካነበብህ በሁዋላ ጥያቄዎቹን በጽሁፍ መልስ::

1. በአንደኛው አንቀጽ ውስጥ የሚገኙት አረፍተ ነገሮች የሃሳብ ዝምድና አላቸው?
2. አንቀጽ ሶስትና አምስት በሃሳብ እንዲዛመዱ ለማድረግ ይቻላል:: ለማዛመድ የተሻለው ዘዴ ምንድነው?
3. አንቀጽ ሁለት፥ ሶስትና አራት የምንባቡን ዋና ሃሳብ እንዲያጎሉ ቢፈለግ እንዴት መዋቀር አለባቸው?
4. የምንባቡን አጠቃላይ ሃሳብ አሳጥረህ ከጻፍህ በሁዋላ አንተ በተመሳሳይ የፈጸምከው ነገር ካለ በማወዳደር የሁለቱን ልዩነትና አንድነት አስረዳ::

IV. በሚከተሉት ሀሳቦች <u>እስማማለሁ</u> ወይም <u>አልስማማም</u> በማለት መልስ ከሰጠህ በሁዋላ ምክንያትህን ግለጽ::

1. እንደ ምንባቡ ደራሲ እምነት ዴሞስቴን የንግግር ጥበብን ለመማር የወሰነው የአባቱን ሀብት ያባከኑበትን ባላደራዎች ለመፋረድና የካሊስታራትን የንግግር ጥበብ ለመካን ነው::

2. ዴሞስቴን በጉባኤ ላይ ንግግር ሲያደርግ በመሀል እንዲያቋርጥ የተደረገው በራሱ ድክመት ብቻ ሳይሆን እሱ በነበረበት ዘመን በአቴና ፈላስፉዎችና ሊቆች ፊት ለፊት አባት የሌለው ልጅ መናገር ስለማይገባው ጭምር ነው::

3. በምንባቡ መሰረት ዴሞስቴን ምኞቱን እንዲያሳካ የረዳው ሊቅ ቱሲዲድ ሳይሆን ካሊስትራት ነው::

ክፍል V

1. የምንባቡን አጠቃላይ ይዘት ሳትለውጥ በሶስት አንቀጾች አሳጥር::
2. የምንባቡ አጠቃላይ አላማ ምንድነው? አገላለጹ ለአላማው ስኬት ያለው አስተዋጽኦ የተሳካ ነው ብለህ ታምናለህ?

## ምንባብ አምስት

### ወጣትነት፥ ማህበራዊ ችግሮቹና የመፍትሄ አቅጣጫዎች

የሚከተለውን ምንባብ በጥንቃቄ አስተውለህ አንብብ:: የምንባቡ የሃሳብ አደረጃጀት /የአንቀጾች አቀማመጥ/ የተዛባ ነው:: የመጀርያውና የመጨረሻው የሃሳብ አደረጃጀት ትክክለኛ ቦታዎችን እንደያዙ ናቸው:: የተዛባ አቀማመጥ ያላቸው በመሀል ያሉት ናቸው:: ስለዚህ ቅደም ተከተሉን አስተካክለህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልስ::

ከሃምሳ አምስት ሚሊዮን የኢትዮጵያ ህዝብ ሀምሳ በመቶው በወጣትነት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ነው:: ይህ ሁኔታ በአፍላ የወጣትነት እድሜ የሚገኘው የህብረተሰብ ክፍል ቁጥር እጅግ አሳሳቢ በሆነ ፍጥነት እየጨመረ በመሄድ ላይ መሆኑን ያመለክታል:: በሀገራችን ያለው የወጣት ብዛት ከማህበራዊ አገልግሎት አቅርቦት ጋር ሲነጻጸር በብዙ እጥፍ የሚበልጥ በመሆኑ ወጣቱ ህብረተሰብ ለበርካታ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ተጋልጦ ይገኛል:: ኋላ ቀር ባህል፥ የጾታና የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርትና አገልግሎት አለመስፋፋት እንዲሁም ወጣቱ ህይወቱን

በአግባቡ እንዲመራ የሚያግዘው የምክር አገልግሎት አለመስፋፋት ያሉትን ችግሮች በማባባስ በኩል የራሳቸውን አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ናቸው::

ስለሆነም ወጣቶች በሽግግር ዘመናቸው የሚያጋጥሙዋቸውን ችግሮች ተረድተው በቅድሚያ እንዲዘጋጁና ጤናማ ህይወት እንዲመሩ ተገቢውን እገዛና ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል:: ሊተኮርባቸው የሚገቡ ገንቢ መፍትሄዎች በጉርምስና ወቅት ስለሚታዩ አካላዊ፥ ስነባህርያዊና ማህበራዊ ለውጦች በማሳወቅ ወጣቶች ለቀጣዩ ህይወታቸው በቅድሚያ ዝግጅት እንዲያደርጉ መረጃ መስጠት፥ የቤተሰብ ምጣኔና የጾታ ትምህርት መሰረተ ሃሳቦችን ለወጣቶች በሰፊው ማሰራጨት እንዲሁም ወጣቶች ስሜታዊና ሃላፊነትን ያልተላበሰ የተቃራኒ ጾታዎች ግንኙነት ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ እንዲገነዘቡ ያልተፈለገ እርግዝናና የአባላዘር በሽታዎችን እንዲከላከሉ ትምህርት መስጠት አስፈላጊ ነው::

በተለይም በአሁኑ ወቅት የሚታየው ፈጣን ማህበራዊ ለውጥ፥ የከተሞችን መስፋፋትና የቅርብ ቤተሰባዊ ትስስር መላላት አያሌ ወጣቶች የቤተሰባቸውን የቅርብ ቁጥጥር፥ ክትትልና ድጋፍ እንዲያጡ በማድረግ ለተለያዩ ማህበራዊና የጤና ችግሮች እንዲጋለጡ እያደረገ ይገኛል:: ምክንያቱም ወጣቶች የህይወት ተሞክሮአቸውና ገጠመኞቻቸው አነስተኛ በመሆናቸው እድገትን ተከትለው የሚመጡ አያሌ ችግሮች ይገጥሙዋቸዋል:: ከእነዚህም ውስጥ በራሳቸው ጉዳይ ላይ በሳልና ተገቢ ውሳኔ መስጠት አለመቻልና ድርጊታቸው ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት አለመገንዘብ ይገኙበታል::

በአጠቃላይ የምክር አገልግሎት ጠቃሚነት ታወቅ አለበት:: ምክክሩ ወጣቶች ይዘዋቸው በሚመጡት ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይት፥ በማካሄድ ወጣቶች ስለራሳቸው በሚገባ እንዲገነዘቡ፥ የችግሮቻቸውን መንስኤ እንዲረዱና የራሳቸው መፍትሄና ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ ለማደፋፈር ያስችላል::

/ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥር 19,1991 ለማስተሪያነት እንዲውል ተሻሽሎ የተወሰደ/::

### መልመጃዎች

I. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማስረጃዎች በማስደገፍ የተብራራ መልስ ስጥ::

1. "የምንባቡ አቅራቢ የምክር አገልግሎት አለመኖር ወይም በስፋት አለመልመድ፥ ወጣቱ ህይወቱን በአግባቡ እንዳይመራ እንቅፋት ፈጥሮበታል ይለል:: ይህንን በሚልበት ጊዜ ወጣቱ ራሱን በራሱ መምራት እንደማይችል ለማመልከት አስቦ ነውን? በደራሲው አስተያየት ትስማማለህ?
2. የምንባቡ ደራሲ ካቀረባቸውና ከዘረዘራቸው የወጣቱ ችግሮች ማለትም ከጤና፥ ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች የትኛው የበለጠ አሳሳቢ ይሆናል?
3. የቤተሰብ ቁጥጥርና ክትትል ማነስ ለወጣቱ ችግር የሚፈጥረው በምን በምን መንገድ እንደሆነ ተወያዩበት::

II. የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች አንብበህ የያዙት ሃሳብ ትክክል ከሆነ እውነት፤ ትክክል ካልሆነ ሃሰት በማለት ከመለስህ በሁዋላ ምክንያትህን አቅርብ::

1. የህዝብ ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ ሲመጣ የሚያስከትለው ችግር በወጣቱ የህብረሰብ ክፍል ላይ የበለጠ ይጎላል::
2. የወጣቱን ማህበራዊ ችግሮች ለማስወገድ ወጣቱን በአስተሳሰብ መለወጥና ተከታታይ ትምህርት መስጠት አስፈላጊ ነው::
3. በምንባቡ መጨረሻ አንቀጽ እንደተገለጸው ወጣቱን በመምከርና በማስተማር ውሳኔውን እራሱ እንዲወስን የሚተው ከሆነ የሚደረገው ጥረት ሁሉ ፍሬ አልባ ይሆናል::
4. "ወጣቶች በሽሽግር ዘመናቸው የሚያጋጥሙዋቸውን ችግሮች ተረድተው" እንዲዘጋጁ ሲል ሽግግሩ የሚያለክተው ከቤተሰብ እርዳታ ማጣታቸውንና መቸገራቸውን ነው::

## ክፍል ሶስት

1. የምንባቡ ጸሀፊ ጎልተው የሚታዩትን የወጣቱን የህብረተሰብ ክፍል ማህበራዊ ችግሮችና መፍትሂዎቻቸውን ጠቁሞአል። ችግሮቹ የተጠቀሱት ብቻ ናቸውን?
2. የዚህን ምንባብ ሃሳብ እና የምንባብ ሁለትን ሃሳብ
   - ሀ. አንድነትና ልዩነታቸውን ለይተህ በጽሁፍ አቅርብ።
   - ለ. የአጻጻፍ ድክመትና ጥንካሬያቸውን አነጻጽር።
   - ሐ. በአጻጻፍ ስልቱ የተሻለ የሚሆነው የትኛው ነው?

አባሪ - ሠ-

የአመለካከት (attitude) መለኪያ ቀመር

$$t = \frac{\bar{x} - \mu}{\frac{SD}{\sqrt{N}}}$$

$\bar{x}$ : አማካይ
$\mu$ : የሚጠበቅ አማካይ
SD : መደበኛ ልይይት
N : ለመጠይቅ የሞሉ ተሳታፊዎች ቁጥር

የሚጠበቅ አማካይ (expected mean) ቀመር

$$Or(E(\bar{x})) = \frac{(Mq \times Map) + (Mq \times Mep)}{2}$$

$Or(E(\bar{x}))$ = የሚጠበቅ አማካይ
Mq = ከፍተኛው የመጠይቅ ቁጥር
Map = ለመጠይቅ ጥያቄዎች የሚሰጥ ከፍተኛው ነጥብ (4)
Mep = ለመጠይቅ ጥያቄዎች የሚሰጥ ዝቅተኛው ነጥብ (1)

1- ከ1-5 ላሉት ጥያቄዎች የተገኘ አስተያየት

$\bar{x}$ = 17.38
$\mu$ = 12.5
SD = 1.66
N = 80

$$t = \frac{\bar{x} - \mu}{\frac{SD}{\sqrt{N}}} = \frac{17.38 - 12.5}{\frac{1.66}{\sqrt{80}}}$$

$$= \frac{\frac{4.88}{1.66}}{8.94} = \frac{4.88}{1.66} \times 8.94$$

$$= 2.93 \times 8.94$$

$$= 26.28$$

የተሰላው የt- ዋጋ በ80 - 1 = 79 የነጻነት ደረጃ በ0.05 የጉልህነት ደረጃ 26.28 ነው። የt- ሰንጠረዥ ዋጋ ደግሞ 1.98 ነው። ይህ ውጤት ከተሳታፊዎች የተገኘው መልስ አስተያየት መሆኑን የሚያመለክት ነው

2- ከ6-21 ለቀረቡት የመጠይቅ ጥያቄዎች አስተያየቶች

$\mu$ = 40
$\bar{x}$ = 56.86
SD = 3.06
$SD^2$ = 9.39

$$t = \frac{\bar{x} - \mu}{\frac{SD}{\sqrt{N}}} = \frac{56.86 - 40}{\frac{3.06}{\sqrt{80}}}$$

$$\frac{\frac{16.86}{3.06}}{8.94} = \frac{16.86}{3.06} \times 8.94 = 5.50 \times 8.94$$

$$= 49.2$$

ስለዚህ፡ ይህ፡ የስሌት የt-ዋጋ ከt-ሰንጠረዥ ዋጋ 1.98 የበለጠ ስለሆነ የተገኘው ውጤት አስተማማኝ፡ ነው።

ለተማሪዎች የቀረበው መጠይቅ አስተማማኝነት፡ በCornbach Alpha ቀመር ሲሰላ.

$$\frac{N}{N-1}\left(1 - \frac{\sum si^2}{\sum SDi^2}\right)$$

N = የመጠይቅ፡ ጥያቄዎች ብዛት ።

$\sum si^2$ = የእያንዳንዱ መለስ ሰጪ የልዩነት ድምር ድምር ብዛት = 9.405

$\sum SDi^2$ = የአጠቃላይ መልስ ሰጪዎች የልዩነት ድምር ድምር ብዛት፡ 186.86

$$= \frac{21}{21-1}\left(1 - \frac{9.405}{186.86}\right)$$

$$= \frac{21}{20}\left(\frac{186.86 - 9.405}{186.86}\right)$$

$$= \frac{21}{20}\left(\frac{177.45}{186.86}\right)$$

$$= \frac{21}{20}(0.94)$$

$$1.05(0.94)$$

$$= 0.98$$

ይህ ስሌት እንደሚያሳየው ለተማሪዎች በተሰራጨው የጽሁፍ መጠይቅ ላይ የቀረቡት ጥያቄዎች አቀራረብ ወጥነት፡ ያለው ነው።

# ማረጋገጫ

ይህ ጥናት የእኔ መሆኑንና በጥናቱም የተጠቀምኩባቸውን ድርሳናት ዋቢነታቸውን በትክክል ማመልከቴንና መስነዴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ::

ስም:- እንግዳ ዘውዴ

ፊርማ:-

ቦታ:- አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ: ቋንቋዎች ጥናት ተቋም

ቀን:- 16/5/92 ዓ.ም